# ማ ው ጫ ።

## የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፤
## የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ።


መጀመሪያ ፡ አንቀጽ ።

| ቍጥር ፡ | ሕግ ። | ገጽ |
|---|---|---|
| ቍ. ፩ ፡ | የአፈጻጸሙ ፡ ወሰን | ፩ |
| ቍ. ፪ ፡ | ተፈጻሚ ፡ የሚሆንበት ፡ ጊዜ | ፩ |
| ቍ. ፫ ፡ | ስለ ፡ ቃል ፡ አተረጓጐም | ፩ |

አንደኛ ፡ መጽሐፍ ።

የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሥልጣን ፤ የዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤትና ፡ ፖሊስ ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሥልጣን ።

| | | |
|---|---|---|
| ቍ. ፬ ፡ | ወንጀልን ፡ ስለሚመለከት ፡ ሥልጣን | ፪ |
| ቍ. ፭ ፡ | ስለሚከሰሱ ፡ ሰዎች | ፪ |
| ቍ. ፮ ፡ | የሥልጣኑ ፡ ክበብ | ፪ |
| ቍ. ፯ ፡ | የይግባኝ ፡ ሥልጣን | ፪ |

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

ስለ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ጽ. ቤትና ፡ ስለ ፡ ፖሊስ ።

| | | |
|---|---|---|
| ቍ. ፰ ፡ | ስለ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ጽ/ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን | ፪ |
| ቍ. ፱ ፡ | ስለ ፡ ፖሊስ ፡ ተግባር | ፫ |
| ቍ. ፲ ፡ | የፖሊስ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ | ፫ |

ሁለተኛ ፡ መጽሐፍ ።

የመክሰስና ፡ የምርመራ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ።

አንቀጽ ፡ ፩ ።

የመክሰስና ፡ የምርመራ ፡ ሥራ ፡ አጀማመር ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

የሥነ ፡ ሥርዐቱ ፡ አጀማመር ።

ክፍል ፡ ፩ ።

ክስና ፡ አቤቱታ ፡ ስለማቅረብ ።

| | | |
|---|---|---|
| ቍ. ፲፩ ፡ | ስለ ፡ ወንጀል ፡ ክስ ፡ በጠቅላላው | ፫ |
| ቍ. ፲፪ ፡ | ጠቃሚው ፡ ሳይታወቅ ፡ የሚቀርብ ፡ የወንጀል ፡ ክስ | ፬ |

| ቍጥር ፡ | ሕግ ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ቍ· ፲፫ ፡ | በክስ ፡ አቤቱታ ፡ አቅራቢነት ፡ ብቻ ፡ የሚያስቀጣ ፡ ወንጀል ፡ .... | ፬ |
| ቍ· ፲፬ ፡ | የወንጀል ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ የማቅረብ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት . | ፭ |
| ቍ· ፲፭ ፡ | ባልታወቀ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የሚቀርብ ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ .... .... .... .... .... .... . | ፭ |
| ቍ ፡ ፲፮ ፡ | ክስን ፡ ወይም ፡ የክስ ፡ አቤቱታን ፡ ለመቀበል ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ባለሥልጣን ፡ .... .... .... .... .... .... .... | ፭ |
| ቍ ፡ ፲፯ ፡ | የወንጀል ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ መብት ፡ ለሌለው ፡ ባለሥልጣን ፡ ስለ ፡ መቅረብ ፡ .... .... .... .... .... | ፭ |
| ቍ ፡ ፲፰ ፡ | ሐሰተኛ ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ ሐሰተኛ ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ .. .... .... | ፮ |


ክፍል ፡ ፪ ።

<u>የእጅ ፡ ተፍንጅ ፡ ወንጀል ፡ ክስ ፡ አጀማመር ።</u>


| | | |
|---|---|---|
| ቍ ፡ ፲፱ ፡ | እጅ ፡ ተፍንጅ ፡ የሚባሉ ፡ ወንጀሎች ፡ .... .... .... .... | ፮ |
| ቍ ፡ ፳ ፡ | ተመሳሳይ ፡ ሁኔታዎች ፡ .... .... .... .... .... .... | ፮ |
| ቍ ፡ ፳፩ ፡ | የክስንና ፡ የመያዝን ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ አጀማመር ፡ ስለ ፡ ሚመለከቱ ፡ ውጤቶች ፡ .... .... .... ........ .... .... .... | ፮ |


ምዕራፍ ፡ ፪ ።

<u>የፖሊስ ፡ ምርመራ ።</u>


| | | |
|---|---|---|
| ቍ ፡ ፳፪ ፡ | መሠረቱ ። .... .... .... .... .... .... .... .... | ፯ |
| ቍ ፡ ፳፫ ፡ | የፖሊስ ፡ የምርመራ ፡ ተግባር ፡ .... .... .... .... .... | ፯ |
| ቍ ፡ ፳፬ ፡ | ስለ ፡ መረጃዎች ፡ አመዘጋገብ ፡ .... .... .... .... .... | ፯ |
| ቍ ፡ ፳፭ ፡ | የተከሰሰውን ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የተጠረጠረውን ፡ ሰው ፡ ስለመጥራት ፡ | ፯ |
| ቍ ፡ ፳፮ ፡ | ስለ ፡ መያዝ ፡ .... .... .... .... .... .... .... | ፯ |
| ቍ ፡ ፳፯ ፡ | ቃልን ፡ ስለ ፡ መቀበል ፡ .... .... .... .... .... .... .... | ፯ |
| ቍ ፡ ፳፰ ፡ | የዋስትና ፡ ወረቀት ፡ በማስፈረም ፡ ስለ ፡ መልቀቅ ፡ .... .... | ፯ |
| ቍ ፡ ፳፱ ፡ | ተከሳሹ ፡ ከተያዘ ፡ በኋላ ፡ የሚፈጸም ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ .... .... | ፯ |
| ቍ ፡ ፴ ፡ | በፖሊስ ፡ የሚደረገው ፡ የምስክሮች ፡ ምርመራ ፡ .... .... | ፰ |
| ቍ ፡ ፴፩ ፡ | የምስክርነት ፡ ቃል ፡ እንዲሰጥ ፡ ስላለመደለል ፡ .... .... | ፰ |
| ቍ ፡ ፴፪ ፡ | ስለ ፡ መበርበርና ፡ ስለ ፡ መያዝ ፡ .... .... .... .... .... | ፰ |
| ቍ ፡ ፴፫ ፡ | የብርበራ ፡ ማዘዣ ፡ ስለ ፡ መስጠት ፡ .... .... .... .... | ፱ |
| ቍ ፡ ፴፬ ፡ | የሐኪም ፡ ምርመራ ፡ .... .... .... .... .... .... .... | ፱ |
| ቍ ፡ ፴፭ ፡ | ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚነገሩትን ፡ ቃላትና ፡ የሚሰጡትን ፡ የእምነት ፡ ቃላት ፡ የመመዝገብ ፡ ሥልጣን ፡ .... .... .... .... | ፲ |

| ቍጥር | ሕግ ፡ | ገጽ ፣ |
|---|---|---|
| ቍ ፡ ፳፮ ፡ | የዕለት ፡ ምርመራ ፡ መዝገብ ፡ .... .... .... .... .... | ፲ |
| ቍ ፡ ፳፯ ፡ | ፖሊስ ፡ ስለሚያቀርበው ፡ ራፖር ፡ .. .... .... .... .... | ፲፩ |
| ቍ ፡ ፳፰ ፡ | ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ራፖር ፡ ሲደርሰው ፡ ማድረግ ፡ ስለሚገባው ፡ | ፲፩ |
| ቍ ፡ ፳፱ ፡ | የፖሊስ ፡ የምርመራ ፡ መዝገብን ፡ ስለ ፡ መዝጋት ፡ .... .... | ፲፩ |

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

<u>ስለ ፡ ክስ ፡ አቀራረብ ።</u>

| | | |
|---|---|---|
| ቍ ፡ ፴ ፡ | ስለ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ ግዴታ ፡ .... .... .... .... .... | ፲፪ |
| ቍ ፡ ፴፩ ፡ | አጠራጣሪ ፡ ሁኔታ ፡ .... .... .... .... .... .... .... | ፲፪ |
| ቍ ፡ ፴፪ ፡ | ክስ ፡ የማይቀርብባቸው ፡ ሁኔታዎች ፡ ................... | ፲፪ |
| ቍ ፡ ፴፫ ፡ | ክስ ፡ አይቀርብም ፡ የማለት ፡ ሥርዐት ፡ ( ፎርም ) .... .... | ፲፪ |
| ቍ ፡ ፴፬ ፡ | ክስ ፡ አይቀርብም ፡ የማለት ፡ ውጤት ፡ .... .... .... ... | ፲፫ |
| ቍ ፡ ፴፭ ፡ | ስለሚቀርበው ፡ ማመልከቻ ፡ ፎርምና ፡ ስለሚሰጥበት ፡ ውሳኔ ፡ | ፲፫ |
| ቍ ፡ ፴፮ ፡ | የግል ፡ ከሳሽ ፡ ስላለበት ፡ ኀላፊነት ። ........... | ፲፫ |
| ቍ ፡ ፴፯ ፡ | የግል ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ መብት ፡ ስለተሰጣቸው ፡ ሰዎች ፡ | ፲፫ |
| ቍ ፡ ፴፰ ፡ | ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ክስ ፡ እስኪያቀርብበት ፡ ድረስ ፡ በግል ፡ የቀረበው ፡ ክስ ፡ እንዲቆም ፡ ስለ ፡ ማድረግ ፡ .... .... .... .... .... | ፲፬ |

አንቀጽ ፡ ፪ ።

<u>ምርመራው ፡ እስኪደረግ ፡ ድረስ ፡ ስለሚደረገው ፡ ጥንቃቄ ።</u>

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

ስለ ፡ መያዝ ።

ክፍል ፡ ፩ ።

<u>ያለ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ ስላለመያዝ ።</u>

| | | |
|---|---|---|
| ቍ ፡ ፴፱ ፡ | መሠረቱ ፡ .... .... .... .... .... .... | ፲፬ |
| ቍ ፡ ፵ ፡ | የእጅ ፡ ከፍንጅ ፡ ወንጀል ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ያለፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ ስለ ፡ መያዝ ፡ .... .... .... .... | ፲፬ |
| ቍ ፡ ፵፩ ፡ | ያለ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ ፖሊስ ፡ ስለ ፡ ተሰጠው ፡ የመያዝ ፡ መብት ፡ .... .... .... .... .... .... .... | ፲፬ |

| ቍጥር ፡ | ሕግ ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| | **ክፍል ፡ ፪ ።** | |
| | **በፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ ስለ ፡ መያዝ ።** | |
| ቍ ፡ ፺፪ ፡ | መሠረቱ ፡ .... .... .... .... .... .... .... | ፲፭ |
| ቍ ፡ ፺፫ ፡ | የመያዝ ፡ ትእዛዝ ፡ ስለ ፡ መስጠት ፡ ........................ | ፲፭ |
| ቍ ፡ ፺፬ ፡ | የመያዝ ፡ ትእዛዝ ፡ መቼ ፡ እንደሚሰጥ ፡ .... .... .... .... | ፲፮ |
| ቍ ፡ ፺፭ ፡ | አስቸካይ ፡ ሁኔታ ፡ ሲገጥም ፡ የመያዝ ፡ ትእዛዝ ፡ ለማግኘት ፡ የሚ ደረግ ፡ ጥያቄ ፡ .... .... .... .... .... .... | ፲፮ |
| | **ክፍል ፡ ፫ ።** | |
| | **ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።** | |
| ቍ ፡ ፺፮ ፡ | የአያያዙ ፡ ሁኔታ ፡ .... .... .... .... .... .... | ፲፯ |
| ቍ ፡ ፺፯ ፡ | ለመያዝ ፡ ርዳታ ፡ አስፈላጊ ፡ ስለሚሆንበት ፡ .... .... .... | ፲፯ |
| ቍ ፡ ፺፰ ፡ | የተያዘውን ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ማስረከብ ፡ .... .... .... .... | ፲፯ |
| ቍ ፡ ፺፱ ፡ | በማረፊያ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ መቈየት ፡ .... .... .... .... | ፲፯ |
| | **ምዕራፍ ፡ ፪ ።** | |
| | **ለምርመራ ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ ለማቈየት ፡ የሚፈቀድ ፡** | |
| | **የተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ ሁኔታ ።** | |
| ቍ ፡ ፻ ፡ | ለምርመራ ፡ የሚፈቀድ ፡ የተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ ሁኔታ ፡ .......... | ፲፯ |
| ቍ ፡ ፻፩ ፡ | በማረፊያ ፡ ቤት ፡ የተያዘው ፡ ሰው ፡ ከጠበቃው ፡ ጋራ ፡ ለመገናኘት ፡ ስላለው ፡ መብት ፡ ........................ | ፲፯ |
| ቍ ፡ ፻፪ ፡ | ዋስ ፡ የሚሆን ፡ ስለ ፡ መፈለግ ፡ . . . ................ | ፲፯ |
| | **ምዕራፍ ፡ ፫ ።** | |
| | **የዋስትና ፡ ወረቀት ፡ አስፈርሞ ፡ ስለ ፡ መልቀቅ ።** | |
| | **ክፍል ፡ ፩ ።** | |
| | **የዋስትና ፡ ወረቀት ።** | |
| ቍ ፡ ፻፫ ፡ | መሠረቱ ፡ ........................................ | ፲፰ |
| ቍ ፡ ፻፬ ፡ | በዋስትና ፡ ወረቀት ፡ እንዲለቀቅ ፡ የሚቀርብ ፡ ማመልከቻ ፡ | ፲፰ |
| ቍ ፡ ፻፭ ፡ | ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሚሰጠው ፡ የመያዝ ፡ ትእዛዝ ፡ ላይ ፡ የሚሰጠውን ፡ ዋስትና ፡ ስለ ፡ ማመልከት ፡ . . . ................ | ፲፰ |

| ቍጥር ፡ | ሕግ ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ቍ ፡ ፷፮ ፡ | በዋስትና ፡ ወረቀት ፡ የመልቀቅ ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ ስለሚሰጠው ፡ ውሳኔ ? | ፲፱ |
| ቍ ፡ ፷፯ ፡ | የዋስትና ፡ ወረቀት ፡ በመፈረም ፡ ስላለመልቀቅ ፡ | ፲፱ |
| ቍ ፡ ፷፰ ፡ | የዋስትና ፡ ወረቀት ፡ በመፈረም ፡ ስለመልቀቅ ፡ | ፲፱ |
| ቍ ፡ ፷፱ ፡ | የሚሰጠውን ፡ የዋስትና ፡ ልክ ፡ ስለ ፡ መወሰን ፡ | ፲፱ |
| ቍ ፡ ፸ ፡ | የዋስቹ ፡ ግዴታዎች ፡ | ፳ |
| ቍ ፡ ፸፩ ፡ | የዋስትናው ፡ ወረቀት ፡ የሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ | ፳ |
| ቍ ፡ ፸፪ ፡ | ስለ ፡ መልቀቅ ፡ | ፳ |
| ቍ ፡ ፸፫ ፡ | ስሕተት ፡ ወይም ፡ ማታለል ፡ | ፳ |
| ቍ ፡ ፸፬ ፡ | አዲስ ፡ ነገር ፡ | ፳፩ |
| ቍ ፡ ፸፭ ፡ | በዋስትና ፡ ወረቀት ፡ እንዲለቀቅ ፡ ያልተፈቀደ ፡ ሲሆን ፡ ለይግባኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማመልከቻ ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ፡ | ፳፩ |


## ክፍል ፡ ፪ ።

## የዋስትናው ፡ ወረቀት ፡ ውጤት ።


| | | |
|---|---|---|
| ቍ ፡ ፸፮ ፡ | ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስላለመቅረብ ፡ | ፳፩ |
| ቍ ፡ ፸፯ ፡ | በዋስትና ፡ ወረቀት ፡ የተለቀቀው ፡ ተከሳሽ ፡ ይጠፋል ፡ ተብሎ ፡ የሚጠረጠር ፡ ሲሆን ። | ፳፪ |
| ቍ ፡ ፸፰ ፡ | የዋስትና ፡ መውረድ ። | ፳፪ |
| ቍ ፡ ፸፱ ፡ | በዋስትና ፡ የተያዘውን ፡ ስለ ፡ መውረስ ፡ | ፳፪ |


# ሦስተኛ ፡ መጽሐፍ ።

## ቀዳሚ ፡ ምርመራ ፡ አድራጊ ፡ ፍርድ ፡ ቤትና ፡ ክሱ ፡

## ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲሰማ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።


| | | |
|---|---|---|
| ቍ ፡ ፹ ፡ | መሠረቱ ፡ | ፳፫ |
| ቍ ፡ ፹፩ ፡ | ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ፡ | ፳፫ |
| ቍ ፡ ፹፪ ፡ | ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ | ፳፫ |
| ቍ ፡ ፹፫ ፡ | የቀዳሚ ፡ ምርመራ ፡ አጀማመር ፡ | ፳፫ |
| ቍ ፡ ፹፬ ፡ | የዐቃቤ ፡ ሕግን ፡ ማስረጃ ፡ ስለ ፡ መቀበል ፡ | ፳፬ |
| ቍ ፡ ፹፭ ፡ | ተከሳሹ ፡ ቃሉን ፡ ለመስጠት ፡ ፈቃደኛ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ መጠየቅ ፡ | ፳፬ |

| ቍጥር ፡ | ሕግ ፡ | ገጽ ፡ |
| --- | --- | --- |
| ቍ ፡ ፹፮ ፡ | ተከሳሹ ፡ ስለሚሰጠው ፡ ቃል ፡ .... .... .... .... | ፳፬ |
| ቍ ፡ ፹፯ ፡ | ተጨማሪ ፡ ምስክሮች ፡ ... .... .... .... .... .... | ፳፬ |
| ቍ ፡ ፹፰ ፡ | ማስረጃን ፡ ስለ ፡ መመዝገብ ፡ .... .... .... .... .... | ፳፭ |
| ቍ ፡ ፹፱ ፡ | ነገሩ ፡ እንዲሰማ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ፡ .... ... | ፳፭ |
| ቍ ፡ ፺ ፡ | ምስክሮች ፡ የሚፈርሙት ፡ የራስ ፡ ዋስትና ፡ ወረቀት ፡ .... .... | ፳፭ |
| ቍ ፡ ፺፩ ፡ | ለመዝገብ ፡ ቤቶች ፡ ሹም ፡ የሚላክ ፡ መዝገብ ፡ .. .... .... | ፳፭ |
| ቍ ፡ ፺፪ ፡ | በመዝገቡ ፡ ውስጥ ፡ ስለሚገኘው ፡ ዝርዝር ፡ .... .... | ፳፮ |
| ቍ ፡ ፺፫ ፡ | ተከሳሹ ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እንዲቈይ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ፡ ... .... | ፳፮ |


## አራተኛ ፡ መጽሐፍ ።

## ክሱ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ መሰማት ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።


| | | |
| --- | --- | --- |
| ቍ ፡ ፺፬ ፡ | የቀጠሮ ፡ ቀን ፡ የሚሰጡበት ፡ ምክንያቶች ፡ .... .... .... | ፳፯ |
| ቍ ፡ ፺፭ ፡ | አዲስ ፡ ቀጠሮና ፡ መጥሪያዎች ፡ .... .... .... .... | ፳፰ |
| ቍ ፡ ፺፮ ፡ | የቀጠሮ ፡ ውጤት ፡ .... .... .... .... .... | ፳፰ |
| ቍ ፡ ፺፯ ፡ | መረጃዎች ፡ ኤግዚቢቶች ፡ .... .... .... .... | ፳፰ |
| ቍ ፡ ፺፰ ፡ | በመዝገቡ ፡ ውስጥ ፡ መኖር ፡ ስለሚገባው ፡ ነገር ፡ .... .... | ፳፱ |


### ምዕራፍ ፡ ፪ ።

### ነገሩ ፡ የሚሰማበት ፡ ስፍራ ።


| | | |
| --- | --- | --- |
| ቍ ፡ ፺፱ ፡ | ነገሩ ፡ የሚሰማበት ፡ ደንበኛ ፡ ስፍራ ፡ ... .... .... .... | ፴ |
| ቍ ፡ ፻ ፡ | ተከሳሹ ፡ ወንጀሉን ፡ በፈጸመበት ፡ ስፍራ ፡ ወይም ፡ የወንጀሉ ፡ ውጤት ፡ በታወቀበት ፡ ስፍራ ፡ ስለ ፡ መክሰስ ፡ .. .... | ፴ |
| ቍ ፡ ፻፩ ፡ | ከአንድ ፡ ወንጀል ፡ ጋራ ፡ ነክነት ፡ ስላለው ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ወንጀል ፡ የሚቈጠር ፡ ተግባር ፡ ክሱ ፡ የሚይታይበት ፡ ስፍራ ፡ | ፴ |
| ቍ ፡ ፻፪ ፡ | ወንጀል ፡ የተሠራበት ፡ ቦታ ፡ ያልታወቀ ፡ ሲሆን ፡ ክሱ ፡ የሚታይ በት ፡ ስፍራ ፡ .. .... .... .... .... .... | ፴ |

| ቁጥር ፡ | ሕግ ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ቁ ፡ ፻፫ ፡ | በጉዞ ፡ ላይ ፡ የተፈጸመ ፡ ወንጀል ፡ .... .... .... .... | ፴፩ |
| ቁ ፡ ፻፬ ፡ | በኢትዮጵያ ፡ መርከብ ፡ ወይም ፡ አይሮፕላን ፡ ላይ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ውጭ ፡ የተፈጸመ ፡ ወንጀል ፡ የሚታይበት ፡ ስፍራ ፡ | ፴፩ |
| ቁ ፡ ፻፭ ፡ | የመሰየም ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ .... .... | ፴፩ |
| ቁ ፡ ፻፮ ፡ | ክሱን ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ስፍራ ፡ ስለ ፡ ማዛወር ፡ .. .... .... | ፴፩ |
| ቁ ፡ ፻፯ ፡ | ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ነገሩ ፡ የሚታይበትን ፡ ስፍራ ፡ ስለ ፡ መምራቱ ፡ | ፴፪ |


## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ክስ ፡ ማመልከቻ ።


| ቁጥር ፡ | ሕግ ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ቁ ፡ ፻፰ ፡ | መሠረቱ ፡ .... .... .... .... .... .... | ፴፪ |
| ቁ ፡ ፻፱ ፡ | የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ ስለ ፡ ማዘጋጀት ፡ ስለ ፡ ማቅረብና ፡ ለተከሳሹ ፡ መስጠት ፡ .... .... .... .... .... .... | ፴፪ |
| ቁ ፡ ፻፲ ፡ | የክሱን ፡ ማመልከቻ ፡ ሥልጣኑ ፡ ላልሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በስሕተት ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ፡ .... .... .... .... .... | ፴፫ |
| ቁ ፡ ፻፲፩ ፡ | የክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ ዐይነትና ፡ የሚጻፍበት ፡ .... .... | ፴፫ |
| ቁ ፡ ፻፲፪ ፡ | የወንጀሉ ፡ ዝርዝር ፡ ሁኔታ ፡ .... .... .... .... | ፴፫ |
| ቁ ፡ ፻፲፫ ፡ | የተፈጸመው ፡ ወንጀል ፡ ዐይነት ፡ የሚያጠራጥር ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ | ፴፬ |
| ቁ ፡ ፻፲፬ ፡ | ቅጣትን ፡ የሚያከብዱ ፡ ወንጀሎች ፡ ክስ ፡ አቀራረብና ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ .... .... .... .... .... .... | ፴፬ |
| ቁ ፡ ፻፲፭ ፡ | በወንጀል ፡ የተከሰሰን ፡ ሰው ፡ ሙከራ ፡ በማድረግ ፡ ወይም ፡ በረዳትነት ፡ ወይም ፡ በአነሣሽነት ፡ ጥፋተኛ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ፡ | ፴፬ |
| ቁ ፡ ፻፲፮ ፡ | ክሱ ፡ ከአንድ ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ .... .... .... | ፴፭ |
| ቁ ፡ ፻፲፯ ፡ | በአንድ ፡ ላይ ፡ የሚቀርብ ፡ ክስ ፡ .. .... .... .... | ፴፭ |
| ቁ ፡ ፻፲፰ ፡ | የመሳሳት ፡ ውጤት ፡ .... .... .... .... .... | ፴፭ |
| ቁ ፡ ፻፲፱ ፡ | ክሱን ፡ ስለ ፡ መለወጥ ፡ ወይም ፡ በክሱ ፡ ላይ ፡ መጨመር ፡ | ፴፭ |
| ቁ ፡ ፻፳ ፡ | የክስ ፡ መለወጥ ፡ ወይም ፡ የመጨመር ፡ ውጤት ፡ .... .... | ፴፮ |
| ቁ ፡ ፻፳፩ ፡ | ስለ ፡ ምስክሮች ፡ እንደ ፡ ገና ፡ መጠራት ፡ .... .... .... | ፴፮ |
| ቁ ፡ ፻፳፪ ፡ | ስለ ፡ ክስ ፡ ማንሣት ፡ .... .... .... .... .... | ፴፮ |

ቍጥር ሕግ ፡ ገጽ ፡

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

<u>የክሱ ፡ መሰማት ፡ ስለ ፡ መጀመር ።</u>

ክፍል ፡ ፩ ።

<u>ስለ ፡ ክሱ ፡ ክርክር ።</u>

ቍ ፡ ፻፹፫ ፡ ክሱ ፡ የሚሰማበትን ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ መወሰን ፡ .... .... .... ፴፯
ቍ ፡ ፻፹፬ ፡ ስለ ፡ ምስክሮች ፡ መጠራት ፡ .... .... .... .... .... ፴፯
ቍ ፡ ፻፹፭ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚሰጠው ፡ የመያዝ ፡ ትእዛዝ ፡ .... .... ... ፴፯
ቍ ፡ ፻፹፮ ፡ ስለ ፡ ክሱ ፡ መሰማት ፡ አጀማመር ፡ .... .... .... .... ፴፰
ቍ ፡ ፻፹፯ ፡ የተከሳሹ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መቅረብ ፡ .... .... .... .... ፴፰
ቍ ፡ ፻፹፰ ፡ ማንነቱን ፡ ስለ ፡ ማረጋገጥ ፡... .... .... .... .... ... ፴፰
ቍ ፡ ፻፹፱ ፡ የክሱን ፡ ማመልከቻ ፡ ስለ ፡ ማንበብ ፡ .... .... .... ፴፰
ቍ ፡ ፻፺ ፡ የክሱን ፡ ማመልከቻ ፡ ስለ ፡ መቃወም ፡ .... .... .... ፴፰
ቍ ፡ ፻፺፩ ፡ መቃወምን ፡ ስለ ፡ መወሰን ፡ .... .... .... .... .... ፴፱
ቍ ፡ ፻፺፪ ፡ ስለ ፡ ተከሳሹ ፡ እምነት ፡ ክህደት ፡ መጠየቅ ፡ .... .... .... ፴፱
ቍ ፡ ፻፺፫ ፡ ጥፋተኛ ፡ አይደለሁም ፡ ስለ ፡ ማለት ፡ ክህደት ፡ .... .... ፵
ቍ ፡ ፻፺፬ ፡ ስለ ፡ እምነት ፡ የሚሰጥ ፡ ቃል ፡.... .... .... .... .... ፵
ቍ ፡ ፻፺፭ ፡ የተከሳሹ ፡ እምነት ፡ ክህደት ፡ ማሻሻል ፡. .... .... .... ፵

ክልፍ ፡ ፪ ።

ማስረጃና ፡ ፍርድ ።

ቍ ፡ ፻፺፮ ፡ የክሱ ፡ መከፈትና ፡ የዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ምስክሮች ፡ መጠራት ፡ ፵
ቍ ፡ ፻፺፯ ፡ የዋናው ፡ ጥያቄ ፡ ዐይነት ፡ .... .... .... .... .... ፵፩
ቍ ፡ ፻፺፰ ፡ የተከሳሹ ፡ የቀድሞ ፡ ጥፋተኛነት ፡ .... .... .... .... ፵፩
ቍ ፡ ፻፺፱ ፡ ድጋሚ ፡ ጥያቄ ፡ .... .... .... .... .... .... .... ፵፩
ቍ ፡ ፪፻ ፡ መስቀልያ ፡ ጥያቄ ፡ ስላለመጠየቅ ፡ .... .... .... .... ፵፩
ቍ ፡ ፪፻፩ ፡ ዐቃቤ፡ ሕጉ ፡ ክሱን ፡ ባላስረዳ፡ ጊዜ ፡ ስለ፡ተከሳሹ ፡ ነጻ ፡ መለቀቅ ፡ ፵፩
ቍ ፡ ፪፻፪ ፡ የመከላከያ ፡ ማስረጃን ፡ ስለ ፡ መጀመር ፡ .. .... .... .... ፵፪
ቍ ፡ ፪፻፫ ፡ ተጨማሪ ፡ ምስክሮች ፡ .... .... .... .... .... .... ፵፪
ቍ ፡ ፪፻፬ ፡ በቀዳሚ ፡ ምርመራ ፡ አድራጊ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ምስክሮች ፡ የሰጡት ፡ ቃል ፡ በማስረጃነት ፡ ሊቀርብ ፡ ስለ ፡ መቻሉ ፡ ፵፪
ቍ ፡ ፪፻፭ ፡ በፖሊስ ፡ ምርመራ ፡ የተሰጠ ፡ ቃል ፡ በማስረጃነት ፡ ሊቀርብ ፡ ስለመቻሉ ፡ ፵፫

| ቍጥር ፡ | ሕግ ። | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ቍ ፡ ፻፺፮ ፡ | ማስረጃን ፡ ስለ፡መቃወም ፡ .... .... .... .... .... .. | ፺፫ |
| ቍ ፡ ፻፺፯ ፡ | ማስረጃውን ፡ በመዝገብ ፡ ስለ ፡ መጻፍ ፡ | ፺፫ |
| ቍ ፡ ፻፺፰ ፡ | የክርክሩ ፡ ማቆምያ ፡ ንግግር ፡ .... .... .... .... | ፺፫ |
| ቍ ፡ ፻፺፱ ፡ | ስለ ፡ ፍርድና ፡ ቅጣት ፡ .... .... .... .... .... | ፺፬ |

ምዕራፍ ፡ ፭ ።

የግል ፡ ከሳሽ ፡ የሚያቀርበው ፡ ክስ ።

| ቍጥር ፡ | ሕግ ። | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ቍ ፡ ፪፻ ፡ | አቤቱታና ፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ፡ .... .... | ፺፭ |
| ቍ ፡ ፪፻፩ ፡ | ባለጕዳዮቹን ፡ ለማስታረቅ ፡ ስለሚደረግ ፡ ሙከራ ፡ .. .... | ፺፭ |
| ቍ ፡ ፪፻፪ ፡ | ስለ ፡ ኪሣራ ፡ የሚደረግ ፡ መተማመኛ ፡ .... .... .... | ፺፭ |
| ቍ ፡ ፪፻፫ ፡ | ክርክሩን ፡ ስለ ፡ መስማትና ፡ ፍርድ ፡ ስለ ፡ መስጠት ፡ .... | ፺፭ |

ምዕራፍ ፡ ፮ ።

ወንጀል ፡ በመሥራቱ ፡ ጉዳት ፡ ስለ ፡ ደረሰበት ፡ ሰው ።

| ቍጥር ፡ | ሕግ ። | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ቍ ፡ ፪፻፬ ፡ | መሠረቱ ፡ ... .... .... .... .... .... .... | ፺፭ |
| ቍ ፡ ፪፻፭ ፡ | ማመልከቻውን ፡ ስላለመቀበል ፡ .... .... .... .... | ፺፮ |
| ቍ ፡ ፪፻፮ ፡ | ማመልከቻውን ፡ ፈቅዶ ፡ ስለ ፡ መቀበል ፡ .... .... .... | ፺፯ |
| ቍ ፡ ፪፻፯ ፡ | የተበደለው ፡ ሰው ፡ ከክሱ ፡ ስለ፡ መውጣት ፡ . .... .... | ፺፯ |
| ቍ ፡ ፪፻፰ ፡ | ተከሳሹን ፡ ነጻ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ መልቀቅ ፡ .... | ፺፯ |
| ቍ ፡ ፪፻፱ ፡ | ስለ ፡ ካሣ ፡ አወሳሰን ፡ የሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ፡ ... .... .... | ፺፯ |

አንቀጽ ፡ ፪ ።

ልዩ ፡ ሥን ፡ ሥርዐት ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

ተከሳሹ ፡ በሌለ ፡ ጊዜ ፡ የሚፈጸም ፡ ሥን ፡ ሥርዐት ።

| ቍጥር ፡ | ሕግ ። | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ቍ ፡ ፪፻፲ ፡ | መሠረቱ ፡ .. .... .... .... .... .... .... | ፺፰ |

ክፍል ፡ ፩ ።

ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ባቀረበው ፡ ክስ ፡ ተከሳሹ ፡ እፍርድ ፡ ቤት ፡ (ዐ/ሕግ?)
ስላለመቅረቡ ።

| ቍጥር ፡ | ሕግ ። | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ቍ ፡ ፪፻፲፩ ፡ | ተከሳሹ ፡ በሌለበት ፡ ነገሩ ፡ የሚሰማበት ፡ ሁኔታ ፡ .... .... | ፺፰ |
| ቍ ፡ ፪፻፲፪ ፡ | መጥሪያ ፡ .... .... .... .... .... .... .... | ፺፱ |
| ቍ ፡ ፪፻፲፫ ፡ | ነገሩን ፡ ስለ ፡ መስማትና ፡ ፍርድ ፡ ስለ ፡ መስጠት ፡ .... .... | ፺፱ |
| ቍ ፡ ፪፻፲፬ ፡ | ፍርዱን ፡ ውድቅ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ፡ ... .... .... .... | ፺፱ |

| ቍጥር ፡ | ሕግ ፡ | ገጽ ፤ |
|---|---|---|
| | **ክፍል ፡ ፪ ።** | |
| | **በግል ፡ ክስ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አለ ፡ መቅረብ ።** | |
| ቍ ፡ ፻፷፭ ፡ | የግል ፡ ከሳሽ ፡ አለመቅረብ ፡ .. .... .... .... .... | ፺፱ |
| ቍ ፡ ፻፷፮ ፡ | ተከሳሹ ፡ ስላለመቅረቡ ፡ .... .... .... .... .... | ፻ |
| | **ምዕራፍ ፡ ፪ ።** | |
| | **የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ወንጀል ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ።** | |
| ቍ ፡ ፻፷፯ ፡ | ለተከሳሹ ፡ መጥሪያ ፡ ስለመላክ ፡.... .... .... .... .. | ፻ |
| ቍ ፡ ፻፷፰ ፡ | በደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ወንጀል ፡ የተከሰሰው ፡ ሰው ፡ ጥፋተኛነቱን ፡ በጽሕፈት ፡ ሊያምን ፡ ይችላል ። .. .... .... .... | ፻ |
| ቍ ፡ ፻፷፱ ፡ | ሥነ ፡ ሥርዓትና ፡ ፍርድ ፡ .... .... .... .... .... | ፻ |
| ቍ ፡ ፻፸ ፡ | ተከሳሹ ፡ ደንብ ፡ በመተላለፍ ፡ ወንጀል ፡ ተከሶ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የመቅረብ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ .... .... .... .... .... | ፻፩ |
| | **ምዕራፍ ፡ ፫ ፤** | |
| | **አካለመጠን ፡ ያላደረሱ ፡ ወጣቶች ፡ ስለፈጸሙት ፡ ወንጀል ፡** | |
| | **ክስ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡** | |
| ቍ ፡ ፻፸፩ ፡ | መሠረቱ ፡.... .... .... .... .... .... .... | ፻፩ |
| ቍ ፡ ፻፸፪ ፡ | የወንጀሉን ፡ ክስ ፡ የማቅረብ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ .... .... | ፻፩ |
| ቍ ፡ ፻፸፫ ፡ | አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ወጣት ፡ ሞግዚት ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለመቅረት ፡ .... .... .... .... .... | ፻፪ |
| ቍ ፡ ፻፸፬ ፡ | አካለመጠን ፡ ያላደረሱ ፡ ወጣቶች ፡ ጠበቃ ፡ እንዲኖራቸው ፡ ማድረግ ።.... .... .... .... .... .... .. | ፻፪ |
| ቍ ፡ ፻፸፭ ፡ | አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ወጣት ፡ ከችሎቱ ፡ ክፍል ፡ እንዲወጣ ፡ ስለማድረግ ፡.... .... .... .... .... .... | ፻፪ |
| ቍ ፡ ፻፸፮ ፡ | የነገሩ ፡ መሰማት ፡ .... .... .... .... | ፻፫ |
| ቍ ፡ ፻፸፯ ፡ | ፍርድ ፡ .... .... .... .... .... .... .... | ፻፫ |
| ቍ ፡ ፻፸፰ ፡ | በወላጆችና ፡ በሞግዚት ፡ ላይ ፡ የሚሰጥ ፡ ትእዛዝ፡ .... .... | ፻፬ |
| ቍ ፡ ፻፸፱ ፡ | በአንዳንድ ፡ ሁኔታ ፡ አካለመጠን ፡ ላላደረሰው ፡ ወጣት ፡ ስለሚከፈለው ፡ አበል ፡ .... .... ........ .... .... | ፻፬ |
| ቍ ፡ ፻፹ ፡ | አካለመጠን ፡ ባላደረሰ ፡ ወጣት ፡ ላይ ፡ የሚሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ መለወጥ ፡ ወይም ፡ ማሻሻል ፡ .... .... .... .... | ፻፬ |

ቍጥር ፡ ሕግ ፡ ገጽ ፡

## አምስተኛ ፡ መጽሐፍ ።

## ስለ ፡ ይግባኝና ፡ ተከሳሹ ፡ በሌለበት ፡ የተሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ ለመሻር ፡ ስለሚቀርበው ፡ ማመልከቻ ።

### ፩ኛ ፡ አንቀጽ ።

### ይግባኝ ።


ቍ ፲፻፹፩ ፡ መሠረቱ ፡ .... .... .... .... .... .... .... ፶፭
ቍ ፡ ፲፻፹፪ ፡ ይግባኝ ፡ ለማየት ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ፶፭
ቍ ፡ ፲፻፹፫ ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ችሎት ፡ ስለሚቀርቡ ፡ ማመልከቻ ዎች ፡ .... .... ...... .... .... .... .... .... ፶፭
ቍ ፡ ፲፻፹፬ ፡ የትእዛዝ ፡ ይግባኝ ፡ ስላለመኖሩ ፡ ... .... .... .... .... ፶፮
ቍ ፡ ፲፻፹፭ ፡ የጥፋተኛነት ፡ ውሳኔ ፡ በተሰጠበት ፡ ወይም ፡ በቅጣቱ ፡ ይግባኝ ፡ ስለ ፡ ማለት ፡ .... .... .... .... .... .... .... ፶፮
ቍ ፡ ፲፻፹፮ ፡ የተበደለው ፡ ሰው ፡ ካሣ ፡ በሚጠይቅበት ፡ ነገር ፡ ይግባኝ ፡ ስለ ፡ ማለት ፡ ... .... .... .... .... .... .... .... ፶፮
ቍ ፡ ፲፻፹፯ ፡ ይግባኝ ፡ ማለትን ፡ ስለ ፡ ማስታወቅና ፡ የይግባኝ ፡ ማመልከቻ ፡ ፶፯
ቍ ፡ ፲፻፹፰ ፡ ፍርድ ፡ እንዳይፈጸም ፡ ስለ ፡ ማገድ ፡ .... .... .... ፶፯
ቍ ፡ ፲፻፹፱ ፡ በይግባኝ ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ ስለሚጻፈው ፡ .... .... ፶፰
ቍ ፡ ፲፻፺ ፡ ለይግባኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለሚላኩ ፡ የይግባኝ ፡ ማመልከቻዎች ፡ መረጃዎች ፡ እና ፡ ( ኤግዚቢቶች ፡ ) መዝገብ ፡ .... .... ፶፰
ቍ ፡ ፲፻፺፩ ፡ የይግባኝ ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ይግባኝ ፡ ለማቅረብ ፡ ፈቃድ ፡ ለማግ ኘት ፡ የሚቀርብ ፡ ማመልከቻ ፡ .... .... .... .... ፶፰
ቍ ፡ ፲፻፺፪ ፡ የነገሩ ፡ መሰማት ፡ .... .... .... .... .... .... .... ፶፱
ቍ ፡ ፲፻፺፫ ፡ ከነገረተኞች ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ ይግባኙ ፡ በሚሰማበት ፡ ቀን ፡ ስላለመቅረቡ ፡ .... .... .... .... .... .... .... ፶፱
ቍ ፡ ፲፻፺፬ ፡ ተጨማሪ ፡ ማስረጃ ፡ .... .... .... .... .... .... ፶፱
ቍ ፡ ፲፻፺፭ ፡ የይግባኝ ፡ ሰሚ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ .... .... .... ፶፱
ቍ ፡ ፲፻፺፮ ፡ የተፈረደባቸው ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሆነው ፡ አንዱ ፡ ብቻ ፡ ይግባኝ ፡ ሲያቀርብ ፡ .... .... .... .... .... ........ .... ፷

| ቍጥር | ሕግ ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| | **አንቀጽ ፡ ፱ ።** | |
| | **ተከሳሹ ፡ በሌለበት ፡ የተፈረደውን ፡ ፍርድ ፡ ውድቅ ፡ ለማድረግ ፡ ስለሚቀርብ ፡ ማመልከቻ ።** | |
| ቍ ፡ ፻፺፯ ፡ | ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ... .... .... .... .... | ፷፩ |
| ቍ ፡ ፻፺፰ ፡ | ማመልከቻው ፡ የሚቀርብበት ፡ ጊዜና ፡ ዐይነት ፡ .... .... | ፷፩ |
| ቍ ፡ ፻፺፱ ፡ | ማመልከቻውን ፡ ለመቀበል ፡ የሚፈቀድባቸው ፡ ምክንያቶች ፡ | ፷፩ |
| ቍ ፡ ፪፻ ፡ | ማመልከቻው ፡ ሲቀርብ ፡ ስለሚፈጸመው ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ | ፷፩ |
| ቍ ፡ ፪፻፩ ፡ | የነገሩ ፡ መሰማት ፡ .... .... .... .... .... .... .... | ፷፩ |
| ቍ ፡ ፪፻፪ ፡ | ፍርድ ፡ .... .... .... .... .... .... .... .... | ፷፩ |
| | **ስድስተኛ ፡ መጽሐፍ ።** | |
| | **<u>የቅጣት ፡ አፈጻጸም ።</u>** | |
| | **ምዕራፍ ፡ ፩ ።** | |
| | **<u>ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።</u>** | |
| ቍ ፡ ፪፻፫ ፡ | መሠረቱ ፡ .... .... .... .... .... .... .... | ፷፪ |
| ቍ ፡ ፪፻፬ ፡ | የሞት ፡ ፍርድ ፡ ስለ ፡ ተፈረደበት ፡ ሰው ፡ የሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ፡ | ፷፪ |
| ቍ ፡ ፪፻፭ ፡ | የግል ፡ ነጻነቱን ፡ እንዲያጣ ፡ ስለ፡ተፈረደበት፡ ሰው ፡ የሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ፡ .... .... .... .... .... .... .... | ፷፪ |
| ቍ ፡ ፪፻፮ ፡ | በአንዳንድ ፡ ነገሮች ፡ የቅጣቱ ፡ ጊዜ ፡ እንዲተላለፍ ፡ ለማድረግ ፡ የሚቻል ፡ ስለመሆኑ ፡ .... .... .... .... | ፷፪ |
| ቍ ፡ ፪፻፯ ፡ | ግርፋት ፡ ስለ ፡ ተፈረደበት ፡ ሰው ፡ የሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ፡ | ፷፫ |
| ቍ ፡ ፪፻፰ ፡ | ለወንጀሉ ፡ አላፊ ፡ ስላልሆኑ ፡ ሰዎች ፡ የሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ፡ | ፷፫ |
| ቍ ፡ ፪፻፱ ፡ | የቅጣት ፡ ገንዘብን ፡ ስለ ፡ ማስገባት ፡ .... .... .... | ፷፫ |
| ቍ ፡ ፪፻፲ ፡ | ስለ ፡ ኪሣራ ፡ ወጪ ፡ እና ፡ ስለ ፡ ካሣ ፡ አከፋፈል ፡ . . | ፷፬ |
| ቍ ፡ ፪፻፲፩ ፡ | ንብረት ፡ ስለ ፡ መውረስ ፡ .... .... .... .... .... | ፷፬ |
| ቍ ፡ ፪፻፲፪ ፡ | ንብረትን ፡ ስለማስያዝ ፡ .... .... .... .... .... | ፷፬ |
| ቍ ፡ ፪፻፲፫ ፡ | አካለመጠን ፡ ስላላደረሱ ፡ ወጣቶች ፡ የሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ፡ | ፷፭ |
| ቍ ፡ ፪፻፲፬ ፡ | ስለ ፡ ግዴታ ፡ ሥራ፡ ስለ፡ተጨማሪ፡ቅጣትና፡ ስለሚወሰደው ፡ ጥንቃቄ ፡ .... .... .... .... .... .... .... | ፷፭ |
| ቍ ፡ ፪፻፲፭ ፡ | የፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ትእዛዝ ፡ በመዝገብ ፡ ስለ ፡ መጻፍ ፡ | ፷፮ |

ቍጥር ፡ ሕግ ገጽ ፡

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

ስለ ፡ ቅጣት ፡ የሚሰጡትን ፡ ትእዛዞች ፡ ስለ ፡ መለወጥ ።

ቍ ፡ ፪፻፲፯ ፡ መሠረቱ ፡ .... .... .... .... .... .... .... ፳፯
ቍ ፡ ፪፻፲፰ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐትና ፡ ውሳኔ ፡ .... .... .... .... .... ፳፯

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

ስለ ፡ መሰየም ።

ቍ ፡ ፪፻፲፱ ፡ ስለ ፡ መሰየም ፡ የሚቀርብ ፡ ማመልከቻ ፡ .... .... .... ፳፯
ቍ ፡ ፪፻፳ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐትና ፡ ውሳኔ ፡ .... .... .... .... .... ፳፯

ሰባተኛ ፡ መጽሐፍ ።

በወንጀል ፡ ነገር ፡ የሚከፈል ፡ የኪሣራ ፡ ወጪ ።

ቍ ፡ ፪፻፳ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ለሚያቀርበው ፡ ክስ ፡ የኪሣራ ፡ ወጪ ፡ . . . ፳፰
ቍ ፡ ፪፻፳፩ ፡ የግል ፡ ክስ ፡ የኪሣራ ፡ ወጪ ፡ ... .... .... .... .. ፳፰
ቍ ፡ ፪፻፳፪ ፡ የተበደለው ፡ ወገን ፡ .... .... .... .... .... .... ፳፰

ስምንተኛ ፡ መጽሐፍ ።

የአጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ በአጭር ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ የሚያዩት ፡ ዳኝነት ።

ቍ ፡ ፪፻፳፫ ፡ ዳኝነቱ ፡ .... .... .... .... .... .... .... ፳፱
ቍ ፡ ፪፻፳፬ ፡ ይግባኝ ፡ .... .... .... .... .... .... .... ፳፱

የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡

# የወንጀለኛ፡መቅጫ፡ሕግ፡ሥነ፡ሥርዐት ።

፲፱፻፶፬፡ዓ. ም.

ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ቍ፡፩/፲፱፻፶፬፡ዓ. ም. በተለይ ፡ የወጣ ፡
አዲስ ፡ አበባ ።

በግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡
በ፴፩ኛው ፡ ዓመተ ፡ መንግሥት ፡ ፲፱፻፶፬ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡
ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ታተመ ።

በብርሃንና ፡ ሰላም ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።

ቍጥር ፡ ፩/፲፱፻፶፩ ፡ ዓ. ም.

የ፲፱፻፶፩ ፡ ዓ. ም. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡

# አ ዋ ጅ ።

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፤

ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

ይህ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ በኛ ፡ መሪነት ፡ እንዲዘጋጅ ፡ አድርገን ፡ የሕግ ፡ መወሰኛና ፡ የግሕ ፡ መምሪያ ፡ ምክር ፡ ቤቶቻችን ፡ ስለተቀበሉት ።

በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥታችን ፡ ቍ. ፴፬እና ፡ ፹፰ ፡ መሠረት ፡ የሕግ ፡ መወሰኛና ፡ የሕግ ፡ መምሪያ ፡ ምክር ፡ ቤቶቻችን ፡ የመከሩበትን ፡ አይተን ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ አውጀናል ።

(፩) ይህ ፡ አዋጅ ፡ የ፲፱፻፶፩ ፡ ዓ ም የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ አዋጅ ፡ ተብሎ ፡ ሊጠቀስ ፡ ይችላል ።

(፪) ይህ ፡ የ፲፱፻፶፩ ፡ ዓ. ም. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት፡ አዋጅ ፡ በተለይ ፡ በቍጥር ፡ ፩/፲፱፻፶፩ ፡ ዓ. ም. ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ውስጥ፡ ታትሞ ፡ በወጣ ፡ በሦስተኛው ፡ ወር ፡ የጸና ፡ ይሆናል ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ ጥትምት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፩ ፡ ዓ. ም.

ጸሐፌ ፡ ትእዛዝ ፡ አክሊሉ ፡ ሀብተ ፡ ወልድ ፤

ጠቅላይ ፡ ሚኒስትርና ፡ የጽሕፈት ፡ ሚኒስትር ።

BACK

የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡

# የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ።

## መጀመሪያ ፡ አንቀጽ ።

### ቍ ፡ ፩ ። የአፈጻጸሙ ፡ ወሰን ።

(፩) ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ሌላ ፡ ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በማንም ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ እኩል ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

(፪) ግልጽ፡ የሆነ ፡ ሌላ፡ ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ሥልጣን ፡ ላለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ለዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ ለፖሊስ ፡ ለሚቀርቡ ፡ ጕዳዮች፡ ሁሉ ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

### ቍ ፡ ፪ ። ተፈጻሚ ፡ የሚሆንበት ፡ ጊዜ ።

(፩) የዚህ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች፡ በሥራ፡ ላይ ፡ ከሚውሉበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ለሚጀመሩ ፡ ጕዳዮችና ፡ በክርክር ፡ ላይ ፡ ላሉ ፡ ክሶች ፡ ሁሉ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

(፪) ማንኛውንም ፡ ክስ ፡ መስማት ፡ ጀምሮ ፡ የነበረው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ያልተጠቀሰ ፡ ከሆነ ፡ በዚህ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ክሱን ፡ ለማየት ፡ ሥልጣን፡ ያለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተጀመረውን ፡ ክስ ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

### ቍ ፡ ፫ ። ስለ ፡ ቃል ፡ አተረጓጐም ።

በዚህ፡ ሕግ፡ የሚከተሉት፡ ቃላት፡ ከዚህ፡ የሚከተለው፡ ፍቺ፡ ተሰጥቷቸዋል ፤

« ፍርድ ፡ ቤት » ፡ ማለት ፡ በሕግ ፡ የተቋቋመ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማለት ፡ ነው ።

«ሕግ» ፡ ማለት ፡ ዐዋጅ ፤ ድንጋጌ ፤ ትእዛዝና ፡ ማናቸውም ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ በሕግ ፡ የሚወጣ ፡ ጭምር ፡ ነው ።

«ሚኒስትር» ፡ ማለት ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስትር ፡ ማለት ፡ ነው ።

«ጠቅላይ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግና፡ ምክትል፡ ጠቅላይ፡ ዐቃቤ፡ ሕግ፡ ማለት» ፡ በ፲፱፻፵፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በቍጥር ፡ ፻፹፫፡ ስለ ፡ ዐቃብያነ ፡ ሕጎች ፡ በወጣው ፡ ዐዋጅ ፡ መሠረት፡ የተሾሙ ፡ ናቸው ።

«ዐቃቤ ፡ ሕግ» ፡ ማለት ፡ በ፲፱፻፵፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በቍጥር ፡ ፻፹፫ ፡ ስለ ፡ ዐቃብያነ ፡ ሕጎች ፡ በወጣው ፡ ዐዋጅ ፡ መሠረት ፡ የተሾመ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ነው ።

«የተደነገገ» ፡ ማለት ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ የተደነገጉ ፡ ወይም ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ በሚወጡት ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያዎች ፡ ማለት ፡ ነው ።

«የፍርድ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ሹም» ፡ ማለት ፡ ምክትሉን ፡ የፍርድ ፡ መዝገብ፡ ቤት፡ ሹም፤ ረዳቱን ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ሹምና ፡ የፍርድ ፡ ጸሐፊውንም ፡ ጭምር ፡ ነው ።

« አካለመጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ወጣት » ፡ ማለት ፡ ዕድሜው ፡ ከ፱ ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ፲፭ ፡ ዓመት ፡ የሆነ ፡ ማለት ፡ ነው ።

# አንደኛ ፡ መጽሐፍ ።

## የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሥልጣን ፡ የዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤትና ፡ ፖሊስ ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሥልጣን ።

**ቍ ፡ ፬ ። ወንጀልን ፡ ስለሚመለከት ፡ ሥልጣን ።**

(፩) በአንደኛው ፡ ሠንጠረዥ ፡ በሦስተኛው ፡ ዐምድ ፡ ሠንጠረዥ ፡ የተገለጹት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በመጀመሪያውና ፡ በሁለተኛው ፡ ዐምዶች ፡ የተገለጹትን ፡ ወንጀሎች ፡ ለማየትና ፡ ሕጉ ፡ የሚያዘውን ፡ ቅጣት ፡ ለመፍረድ ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ።

(፪) የፍርድ ፡ ሚኒስትር ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ በሚወጣ ፡ ትእዛዝ ፡ በአንደኛው ፡ ሠንጠረዥ ፡ ለመለወጥ ፡ ወይም ፡ ለማሻሻል ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፭ ። ስለሚከሰሱ ፡ ሰዎች ።**

(፩) በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ቍጥር ፡ ፶፫ ፡ እንደተመለከተው ፡ ዕድሜው ፡ ከ፱ ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ፲፭ ፡ ዓመት ፡ የሆነ ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ልጅ ፡ ዕድሜው ፡ አካለመጠን ፡ ከደረሰ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ በተከሰሱበት ፡ የወንጀል ፡ ነገር ፡ አብሮ ፡ ሊታይ ፡ አይቻልም ።

(፪) በወታደር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ የሚታይ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ አባልና ፡ የሲቪል ፡ ሰው ፡ አብረው ፡ ሊሞገቱ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፮ ። የሥልጣኑ ፡ ክበብ ።**

ከቍጥር ፡ ፺፱ ፡ እስከ ፡ ፻፯ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በተወሰነላቸው ፡ ቦታዎች ፡ (አጥቢያዎች) ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ።

**ቍ ፡ ፯ ። የይግባኝ ፡ ሥልጣን ።**

በቍጥር ፡ ፻፹፪ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ይግባኝ ፡ የማየት ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ።

### ምዕራፍ ፡ ፪ ።

### ስለ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤትና ፡ ስለ ፡ ፖሊስ ።

**ቍ ፡ ፰ ። ስለ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ።**

(፩) ጠቅላይ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ምክትል ፡ ጠቅላይ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግና ፡ ዐቃብያነ ፡ ሕጎች ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ የተሰጣቸውን ፡ ተግባር ፡ ለመፈጸም ፡ ኀላፊዎች ፡ ናቸው ።

(፪) የዐቃቤ፡ ሕግ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ተግባሩን ፡ በሚፈጽምበት ፡ ጊዜ ፡ አስፈላጊ፡ የሆነውን ፡ ትእዛዝና ፡ መምሪያ ፡ ለፖሊስ ፡ እንዲተላለፍ ፡ ማድረግና ፡ ፖሊሶቹም ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ግዴታቸውን ፡ መፈጸማቸውን ፡ ማረጋገጥ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፱ ። ስለ ፡ ፖሊስ ፡ ተግባር ።**

በዚህ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ፖሊስ ፤

(ሀ) ሰላምን ፡ በመጠበቅና ፡ ወንጀል ፡ እንዳይሠራ ፡ መከላከል ፤

(ለ) የሚፈጸመውን ፡ ወንጀል ፡ ማውጣት ፤

(ሐ) ወንጀለኞችን ፡ መያዝ ፤

(መ) የፖሊስ፡ ሠራዊት፡ ብልደረብ ፡ እንደ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ሲሾም ፡ በወንጀል ፡ ነገር ፡ ሕግን ፡ በማስከበር ፤ የዐቃቤ ፡ ሕግን ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ መርዳት ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፲ ። የፖሊስ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ።**

የፖሊስ ፡ ሠራዊት ፡ ብልደረብ ፡ እንደ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ሆኖ ፡ ሲሾም ፡ የዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤትን ፡ መሪ ፡ ትእዛዝ ፡ ይቀበላል ።

# ሁለተኛ ፡ መጽሐፍ ።

## የመከሰስና ፡ የምርመራ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ።

## አንቀጽ ፡ ፩ ።

## የመከሰስና ፡ የምርመራ ፡ ሥራ ፡ አጀማመር ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### የሥነ ፡ ሥርዐት ፡ አጀማመር ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### ክስና ፡ አቤቱታ ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ።

**ቍ ፡ ፲፩ ። ስለ ፡ ወንጀል ፡ ክስ ፡ በጠቅላላው ።**

(፩) ማንም፡ ሰው፡ ማንኛውንም፡ ወንጀል፡ ሲሠራ ፡ ያየ ፡ ወይም ፡ ያላየም ፡ ቢሆን፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ እንዲቀርብ ፡ ወንጀሉን ፡ ለማስታወቅ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) ማንም፡ ሰው፡ በወንጀለኛ፡ መቅጫ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፳፯ ፤ ፫፻፵፩ ፡ እና ፡ ፬፻፴፰ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ የተሠራውን፡ ወንጀል ፡ የማስታወቅ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፲፪ ። ጠቋሚው ፡ ሳይታወቅ ፡ የሚቀርብ ፡ የወንጀል ፡ ክስ ።**

ካልታወቀ ፡ ጠቋሚ፡ የቀረበ፡ የወንጀል፡ ማስታወቅ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የሕግ ፡ መጣስን ፡ የሚገልጽ ፡ ሆኖ ፡ ወንጀሉ ፡ ለመሠራቱ ፡ በአካባቢ ፡ ሁኔታ ፡ የተደገፈና ፡ የሚታመን፡ መስሎ ፡ የተገኘ፡ እንደ፡ ሆነ፡ በቍጥር ፡ ፳፪ ፡ እና ፡ በተከታዩ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ እውነትን ፡ ለማግኘት ፡ ያለዚያም ፡ የቀረበውን ፡ ክስ ፡ ለማረጋገጥ ፡ ሥልጣን ፡ ባለው ፡ ፖሊስ ፡ ይመረመራል ።

**ቍ ፡ ፲፫ ። በክስ ፡ አቤቱታ ፡ አቅራቢነት ፡ ብቻ ፡ የሚያስቀጣ ፡ ወንጀል ።**

በተበዳዩ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ተበዳዩ ፡ ባለመብት፡ በሆኑ ፡ ሰዎች፡ ክስ፡ አቅራቢነት ፡ ብቻ ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ የሚያስከስሱና ፡ የሚያስቀጡ ፡ ወንጀሎች ፡ ከሆኑ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፲፯ ፡ እስከ ፡ ፪፻፳፪ ፡ እና ፡ ፯፻፳፩ ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፲፬ ። የወንጀል ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ የማቅረብ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ።**

(፩) ማናቸውም ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ ( ቍጥር ፡ ፲፩ ) ፡ ወይም ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ (ቍጥር ፡ ፲፫ )፡ የቀረበለት ፡ ሰው ፡ በጽሑፍ ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ የክሱን ፡ አቤቱታ ፡ ላቀረበው ፡ ሰው ፡ ተነቦለት ፡ ቀኑን ፡ ጽፎ ፡ ይፈርምበታል ።

(፪) በወንጀለኛ፡ መቅጫ፡ በቍጥር፡ ፪፻፲፬ ፡ እንደተመለከተው ፡ የወንጀል ፡ ክስ፡ ወይም ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ አቅራቢዎች ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሁሉም፡ በወንጀሉ፡ክስ፡ ወይም፡ በክስ፡ አቤቱታው፡ ላይ፡ መፈረም፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ፲፭ ። ባልታወቀ፡ ሰው፡ ላይ፡ የሚቀርብ፡ የወንጀል፡ ክስ ፡ ወይም ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ።**

የወንጀል ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ የክስ ፡ አቤቱታ፡ ያቀረበው፡ ሰው ፡ ወንጀለኛውን፡ ለይቶ፡ ለማወቅ ፡ ያልተቻለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወንጀለኛውን ፡ ለይተው ፡ የሚያሳውቁትን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ምልክቶች ፡ ሁሉ ፡ በዝርዝር ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፲፮ ። ክስን፡ ወይም ፡ የክስ፡ አቤቱታን፡ ለመቀበል ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ባለሥልጣን ።**

(፩) ማናቸውንም፡ የወንጀል፡ ክስ፡ (ቍጥር፡ ፲፩ ) ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ (ቍ ፡ ፲፫) ፡ ለፖሊስ ፡ ወይም ፡ ለዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ማቅረብ ፡ ይቻላል ። አካለመጠን ፡ ባላደረሰ ፡ ወጣት ፡ ላይ ፡ የሚቀርብ ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፹፪ ፡ መሠረት ፡ መቅረብ ፡ አለበት ።

(፪) የወንጀሉ፡ ክስ፡ ወይም፡ የክሱ ፡ አቤቱታ፡ ለዐቃቤ፡ ሕጉ ፡ ሲቀርብለት ፡ በቍጥር ፡ ፳፪ ፡ እና ፡ በተከታዮቹ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የተባለው ፡ ወንጀል ፡ እንዲመረመር ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ሥልጣን ፡ ላለው ፡ ፖሊስ ፡ ማስተላለፍ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፲፯ ። የወንጀል ፡ ክስ፡ ወይም ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ መብት ፡ ለሌለው ፡ ባለሥልጣን ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ።**

የወንጀሉ፡ ክስ፡ ወይም፡ የክሱ ፡ አቤቱታ ፡ ለፖሊስ ፡ ወይም ፡ ለዐቃቤ ፡ ሕግ፡ መቅረቡ ፡ ቀርቶ ፡ ለአንድ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ባለሥልጣን ፡ ወይም ፡ ይህንኑ፡

BACK



ጉዳይ ፡ ለመቀበል ፡ መብት ፡ ለሌለው ፡ ለፖሊስ ፡ ባለሥልጣን ፡ ወይም ፡ ለዐቃቤ፡ ሕግ ፡ የቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይኸው ፡ ሰው ፤ ባለሥልጣን ፡ ወይም ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ሳይዘገይ ፡ በቶሎ ፡ ጉዳዩ ፡ ለሚመለከተው ፡ ሥልጣን ፡ ላለው ፡ ፖሊስ ፡ ወይም ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ይህንኑ ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ መላክ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፲፰ ። ሐሰተኛ ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ ሐሰተኛ ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ።

ሐሰተኛ ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ ሐሰተኛ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ያቀረበ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ በወንጀለኛው ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፬፻፵፩ ፡ እና ፡ ፭፻፹ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ይቀጣል ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## የእጅ ፡ ተፍንጅ ፡ ወንጀል ፡ ክስ ፡ አጀማመር ።

ቍ ፡ ፲፱ ። እጅ ፡ ተፍንጅ ፡ የሚባሉ ፡ ወንጀሎች ።

(፩) አንድ ፡ ወንጀል ፡ እጅ ፡ ተፍንጅ ፡ ነው ፡ የሚባለው ፤ ወንጀል ፡ አድራጊው፡ ወንጀሉን ፡ ሲሠራ ፡ የተያዘ ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ ለመሥራት ፡ ሲሞክር ፡ ወይም፡ የወንጀሉን ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ፈጸመ ፡ ወዲያውኑ ፡ የተያዘ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

(፪) ወንጀል ፡ አድራጊው፡ የወንጀሉን፡ ሥራ ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ፡ ወዲያውኑ ፡ ሲሸሽ፡ ምስክሮቹ ፡ ወይም ፡ ሕዝቡ ፡ የተከታተሉት ፡ ወይም ፡ የሕዝቡ ፡ ጩኸትና ፡ እሪታ ፡ የተሰማ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወንጀሉ ፡ የእጅ ፡ ተፍንጅ ፡ መሰል ፡ እንደ ፡ ሆነ፡ ይቈጠራል ።

ቍ ፡ ፳ ። ተመሳሳይ ፡ ሁኔታዎች ።

አንድ፡ ወንጀል፡ የእጅ፡ ተፍንጅ፡ ነው ፡ ተብሎ፡ በቍ፡ ፲፱፡ ሊጠቀስ፡ የሚቻለው፤

(ሀ) ወንጀሉ ፡ በተሠራበት፡ ቦታ፡ ወዲያውኑ ፡ ፖሊስ ፡ የተጠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡

(ለ) ወንጀሉ ፡ ሲሠራ ፡ ወይም፡ እንደ፡ ተፈጸመ ፡ ወንጀሉ ፡ ከተሠራበት ፡ ቦታ፡ ላይ ፡ የይድረሱልኝ ፡ እሪታ ፡ የተሰማ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፳፩ ። የክስንና ፡ የመያዣን፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ አጀማመር፡ ስለሚመለከቱ ፡ ውጤቶች።

(፩) በቍጥር ፡ ፲፱ ፡ እና ፡ ፳ ፡ በተዘረዘሩት ፡ ወንጀሎች ፡ መሠረት ፡ ወንጀሉ ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ሳይቀርብ ፡ ክስ ፡ ሊቀርብበት ፡ የማይችል ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ እንዲቀርብበት ፡ አስፈላጊ ፡ ሳይሆን ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ይቻላል ።

(፪) እንደዚህ፡ ያለው ፡ ሁኔታ፡ በሚያጋጥምበት፡ ጊዜ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚሰጠው፡ የመያዣ፡ ትእዛዝ፡ ሳይኖር፡ በቍጥር ፡ ፶፱ ፡ እና ፡ በተከታዮቹ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት፡ ወንጀለኛውን ፡ ለመያዝ ፡ ይቻላል ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## የፖሊስ ፡ ምርመራ ።

### ቍ ፡ ፳፪ ። መሠረቱ ።

(፩) ፖሊስ ፡ የተሠራውን፡ ወንጀል፡ በሚያውቅበት ፡ ወይም ፡ በጥርጣሬ ፡ በሚረዳበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ በዚሁ ፡ ምዕራፍ ፡ በተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ምርመራ ፡ ያደርጋል ።

(፪) አካለመጠን፡ ያላደረሱ፡ ወጣቶች፡ ስለ፡ ፈጸሙት፡ ወንጀል፡ ምርመራ፡ በፍርድ፡ ቤቱ ፡ ትእዛዝ ፡ በቍጥር ፡ ፻፸፪፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

### ቍ ፡ ፳፫ ። የፖሊስ ፡ የምርመራ ፡ ተግባር ።

ለፖሊስ፡ መርማሪ፡ የቀረበው ፡ ክስ፡ወይም፡ የክስ፡ አቤቱታ፡ ወይም፡ መረጃዎች፡ የሚያጠራጥር ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ቢያስብም ፡ መርማሪው ፡ ፖሊስ ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ የምርመራ ፡ ተግባሩን ፡ መፈጸም ፡ ይገደዳል ።

### ቍ ፡ ፳፬ ። ስለ ፡ መረጃዎች ፡ አመዘጋገብ ።

የቀረበለትን ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ በቍጥር ፡ ፲፬ ፡ በተመለከተው ፡ ዐይነት ፡ ከመዘገበ ፡ በኋላ ፡ መርማሪው ፡ ፖሊስ ፡ ወንጀሉን ፡ የሚመለከቱትን ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፤ ቀኑንና ፡ ዘመኑን ፤ የወንጀል ፡ አድራጊውን ፡ ስም ፡ ወይም ፡ መታወቂያውን ፤ የዋናዎቹን፡ ምስክሮች፡ ስምና፡ አድራሻቸውን፤ እንዲሁም፡ የሚገኘውን፡ ሌላ ፡ ማስረጃ ፡ ሁሉ ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ካቀረበው ፡ ሰው ፡ ጠይቆ፡ መመዝገብ ፡ አለበት ።

### ቍ ፡ ፳፭ ። የተከሰሰውን ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የተጠረጠረውን ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ መጥራት ።

አንድ ፡ ሰው ፡ የወንጀል ፡ ሥራ ፡ መፈጸሙን ፡ ለማመን ፡ መርማሪው ፡ ፖሊስ ፡ ምክንያት ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ በሚገኝባቸው ፡ ሁኔታዎች ፡ ሁሉ ፡ የተባለው ፡ ሰው ፡ ቀርቦ ፡ እንዲጠየቅ ፡ ፖሊሱ ፡ እንድትቀርብ ፡ በሚል ፡ በጽሑፍ ፡ ትእዛዝ ፡ ሊጠራው ፡ ይችላል ።

### ቍ ፡ ፳፮ ። ስለ ፡ መያዝ ።

(፩) የተከሰሰው ፡ ወይም፡ የተጠረጠረው፡ ሰው ፡ ያልተያዘ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ወንጀሉ፡ በሕጉ፡ መሠረት፡ የሚያሲዘው፡ ሆኖ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በቍጥር፡፳፭፡ በተመለከተው፡ መሠረት፡ የተጠራው ፡ ሰው ፡ ያልቀረበ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እንዲያዝ ፡ መርማሪው ፡ ፖሊስ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ጥንቃቄዎች ፡ ሁሉ ፡ ማድረግ ፡ አለበት ።

(፪) ከፍርድ ፡ ቤት ፡ የመያዝ ፡ ትእዛዝ፡ ሳይሰጥ፡ ሰውዬውን፡ ለመያዝ ፡ የማይቻል፡ ሲሆን ፤ መርማሪው ፡ ፖሊስ፡ በቍጥር ፡ ፶፫ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ የመ

BACK



ያዝ ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፳፯ ። ቃልን ፡ ስለ ፡ መቀበል ።

(፩) በቍጥር፡ ፳፭፡ በተመለከተው፡ መሠረት፡ እንዲቀርብ ፡ የተጠራው ፡ ወይም ፡ በቍጥር፡ ፳፯ ፤ ፶ ፤ ወይም፡ ፶፩ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ተይዞ ፡ የቀረበው ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ማንነቱና ፡ አድራሻው ፡ ከተረጋገጠ ፡ በኋላ ፡ ለቀረበበት ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ቃሉን ፡ እንዲሰጥ ፡ ይጠየቃል ።

(፪) ሰውዬው፡ ምላሽ፡ እንዲሰጥ፡ ለማስገደድ ፡ አይቻልም ። ነገር ፡ ግን ፡ ምላሽ ፡ ለመስጠት ፡ ነጻ ፡ እንደ፡ ሆነና፡ ፈቅዶ፡ የሚሰጠው ፡ ማናቸውም፡ ቃል፡ በማስረጃነት፡ የሚቀርብ፡ መሆኑን፡ ጠያቂው፡ ፖሊስ፡ ለተጠያቂው፡ መንገር፡ይገባዋል ።

(፫) ማንኛውም ፡ የተሰጠ ፡ ቃል ፡ መመዝገብ ፡ አለበት ።

(፬) የተያዘውም ፡ ሰው ፡ የሚሰጠው ፡ ቃል ፡ የሚመዘገብበት ፡ ቋንቋ ፡ በትክክል፡ የማይገባው፡ የሆነ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ችሎታ፡ ያለው ፡ አስተርጓሚ ፡ ይሰጠዋል ። አስተርጓሚውም ፡ የተጠየቀውንና ፡ የሰጠውን ፡ ምላሽ ፡ ትክክል ፡ መሆኑን ፡ ያረጋግጥለታል ።

ቍ፡ ፳፰ ። የዋስትና ፡ ወረቀት ፡ በማስፈረም ፡ ስለ ፡ መልቀቅ ።

(፩) የተሠራው፡ ወይም፡ አቤት ፡ የተባለበት፡ ወንጀል ፡ በጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ይህንኑ ፡ በመሰል ፡ ተለዋጭ ፡ ቅጣት ፡ የማያስቀጣ ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ ወንጀል፡ የተሠራ ፡ ለመሆኑ ፡ ወይም ፡ እንዲቀርብ ፡ የተጠራው ፡ ወይም ፡ የተያዘው ፡ ተከሳሽ ፡ አቤት ፡ የተባለበትን ፡ ወንጀል ፡ መሥራቱ ፡ የሚያጠራጥር ፡ ሲሆን ፡ ተከሳሹ ፡ የገንዘብ ፡ መቀጫ ፡ እንዲከፍል ፡ የራስ ፡ የዋስትና ፡ ወረቀት ፡ ወይም ፡ በተጨማሪ ፡ ለዚሁ ፡ ገንዘብ ፡ ዋስ ፡ የሆነውን ፡ የዋስትና ፡ ወረቀት ፡ በማስፈረም ፡ መርማሪው ፡ ፖሊስ ፡ በሚወስነው ፡ ቦታ ፡ ቀንና ፡ ሰዓት ፡ እንዲቀርብ ፡ በመወሰን ፡ ተከሳሹን ፡ ሊለቀው ፡ ይችላል ።

(፪) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፡ በዋስትና ፡ ወረቀት ፡ ያልተለቀቀ ፡ ተከሳሽ ፡ በቍጥር ፡ ፷፬ ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ በዋስትና ፡ ወረቀት ፡ እንዲለቀቅ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፳፱ ። ተከሳሹ ፡ ከተያዘ ፡ በኋላ ፡ የሚፈጸም ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ።

(፩) ተከሳሹ ፡ በፖሊስ ፡ የተያዘ ፡ ወይም ፡ በቍጥር ፡ ፶፰ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው፡ በሌላ፡ ሰው ፡ ተይዞ፡ ለፖሊስ ፡ የተሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከተያዘበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ፡ ከአርባ፡ ስምንት፡ ሰዓት ፡ በማይበልጥ፡ ጊዜ፡ ውስጥ፡ ወይም፡ የሚገኝበት፡ ቦታ ፡ ሁኔታዎችና ፡ መገናኛዎች ፡ በሚያመቹበት ፡ (በሚፈቅዱለት) ፡ መጠን ፡ በተቻለ፡ ፍጥነት ፡ ፖሊሱ ፡ የተያዘውን ፡ ሰው ፡ በጣም ፡ አቅራቢያው ፡ ወደሆነው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ። የተያዘውን ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለማድረስ ፡ የሚፈጀው ፡ ጊዜ ፡ አይታሰብም ።

BACK



(፪) ተከሳሹ ፡ የቀረበለት ፡ ፍርድ፡ ቤት፡ በቍጥር ፡ ፺፱ ፡ በተመለከተው፡ መሠረት፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ማንኛውንም ፡ ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል።

**ቍ ፡ ፴ ። በፖሊስ ፡ የሚደረገው ፡ የምስክሮች ፡ ምርመራ ።**

(፩) አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ መርማሪው ፡ ፖሊስ ፡ ስለ ፡ ተፈጸመው ፡ ወንጀል ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ወንጀል ፡ ሥሪጡ ፡ ማንኛውንም ፡ ተገቢነት ፡ ያለውን ፡ ማስረጃ ፡ መስጠት ፡ የሚችለውን ፡ ማንኛውንም ፡ ሰው ፡ ጠርቶ፡ መመርመር ፡ ይችላል ።

(፪) የሚጠየቀው ፡ ሰው ፡ ለቀረበለት ፡ ጥያቄ፡ ሁሉ ፡ እውነተኛውን ፡ መልስ ፡ መስጠት ፡ አለበት ። ለቀረበለት ፡ ጥያቄ ፡ የሚሰጠው ፡ ምላሽ ፡ በወንጀል ፡ ሊያስከስሰው፡ የሚችል፡ የሆነ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ምላሽ፡ አልሰጥም፡ ለማለት ፡ ይችላል ።

(፫) ሰውዬው ፡ የሚሰጠው ፡ ማንኛውም ፡ ቃል ፡ መመዝገብ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፴፩ ። የምስክርነትን ፡ ቃል ፡ እንዲሰጥ ፡ ስላለመደለል ።**

(፩) ፖሊሱ ፡ ወይም፡ ሥልጣን፡ ያለው ፡ ሰው ፡ የምስክርነትን ፡ ቃል ፡ ሲቀበል ፡ ተጠያቂውን ፡ መደለል ፡ ወይም ፡ እንዲደለል ፡ ማድረግ ፤ የተሰፋ ፡ ቃል ፡ መስጠት ፤ የማስፈራራት ፤ የኀይል፡ ሥራ ፡ ወይም፡ ሌሎች ፡ ከሕግ ፡ ውጭ ፡ የሆኑ ፡ ዘዴዎች ፡ መፈጸም ፡ ወይም ፡ ማድረግ ፡ ወይም ፡ መጥቀም ፡ አይችልም ።

(፪) ተጠያቂው ፡ ሰው ፡ የምርመራውን ፡ ጉዳይ ፡ ስለሚመለከት ፡ ነገር ፡ ፈቅዶ ፡ ለመናገር ፡ ዝግጁ ፡ በመሆን ፡ ቃሉን ፡ እንዲሰጥ ፡ ወይም ፡ ቃሉም ፡ እንዲመዘገብ ፡ ሲጠይቅ ፤ ፖሊሱ ፡ ወይም ፡ ማንኛውም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ በማናቸውም ፡ አደራረግ ፡ ዘዴ ፡ ሊከለክለው ፡ ወይም ፡ ሊያግደው ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፴፪ ። ስለ ፡ መበርበርና ፡ ስለ ፡ መያዝ ።**

ማንኛውም ፡ መርማሪ ፡ ፖሊስ ፡ ወይም ፡ የፖሊስ ፡ ሠራዊት፡ ባልደረባ ፡ ከዚህ፡ በታች፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ የሰውን ፡ ቤት ፡ መበርበር ፡ ወይም፡ ዕቃን ፡ መያዝ ፡ ይችላል ።

(፩) በተከሰሰበት ፡ ወንጀል ፡ ወይም ፡ ወንጀል ፡ ሠርቷል ፡ ተብሎ ፡ በተጠረጠረበት ፡ ነገር ፡ ማስረጃ ፡ የሚሆን ፡ በሰውነቱ ፡ ደብቋል ፡ የሚያሰኝ ፡ በቂ ፡ ምክንያት፡ ከሌለ፡ በቀር ፡ የተያዘውን፡ ሰው ፡ ለመበርበር ፡ አይቻልም ። ብርበራውም፡ የሚደረገው ፡ ከተያዘው ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ የተመሳሰለ ፡ ጾታ ፡ ባለው ፡ ሰው ፡ ነው ።

(፪) ማንኛውም፡ መርማሪ፡ ፖሊስ፡ ወይም፡ የፖሊስ፡ ሠራዊት፡ ባልደረባ፡ በፍርድ፡ ቤት፡ የተሰጠ፡ የሥስተኛው፡ ሠንጠረዥ፡ ዐይነት ፡ የሆነ፡ የብርበራ፡ ማዘዣ፡ ካልያዘ ፡ በቀር ፡ ቤትን ፡ መበርበር ፡ አይችልም ። ስለሆነም ፡ ያለ፡ ብርበራ ፡ ማዘዣ ፡ መበርበር ፡ የሚፈቀድለት ፡—

(ሀ) ወንጀለኛውን ፡ እጅ ፡ ከፍንጅ ፡ ሲከታተሉትና ፡ እቤት ፡ ውስጥ ፡ ሲገባ፡ ወይም ፡ ወንጀል፡የሠራበትን፡ነገር ፡ እቤት፡ውስጥ ፡ ያስቀመጠ፡ሲሆን ፤ ወይም ፡

(ለ) ከሦስት ፡ ዓመት፡ በላይ ፡ ሊያስቀጣ፡ የሚችል፡ በቍጥር ፡ ፲፩ ፡ መሠረት ፡

ክስ ፡ ወይም ፡ አቤቱታ ፡ የቀረበበት ፡ ወንጀል ፡ ለማስረጃ ፡ የሚሆን ፡ ወንጀሉ ፡ የተፈጸመበት ፡ ነገር ፡ በአንድ ፡ ቦታ ፡ የተደበቀ ፡ ወይም ፡ የተቀመጠ፡ መሆኑ፡ ለመርማሪው ፡ ፖሊስ ፡ ወይም ፡ ለፖሊስ ፡ ሠራዊት፡ባልደረባ ፡ በተነገረው፡ መሠረት ፡ ተገቢ ፡ ጥርጣሬ ፡ የሚያሳድር ፡ ሲሆንና ፡ የብርበራውን፡ ማዘዣ ፡ እስቲቀበል ፡ ድረስ ፡ ወንጀል ፡ ተሠራበት ፡ የተባለው ፡ ነገር ፡ ካለበት ፡ ቦታ፡ይወሰዳል ፡ ተብሎ ፡ በበቂ ፡ ምክንያት ፡ የታመነ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፴፫ ። የብርበራ ፡ ማዘዣ ፡ ስለ ፡ መስጠት ።

(፩) የብርበራ ፡ ማዘዣ ፡ ማንኛቸውም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊሰጥ፡ ይችላል ። ፍርድ፡ ቤቱ ፡ ለፍትሕ ፡ ዓለማ ፡ ወይም ፡ ለማናቸውም ፡ ምርመራ ፤ ለክሱ፡ መስማት፡ ወይም፡ በሕጉ፡ መሠረት ፡ ለሌላው ፡ የክስ ፡ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ የማዘዣው፡ መስጠት ፡ የሚጠቅም ፡ መሆኑን ፡ ካልተረዳው ፡ በቀር ፡ የብርበራ ፡ ማዘዣ ፡ መስጠት ፡ አይችልም ።

(፪) ማናቸውም፡ የብርበራ፡ ማዘዣ፡ የሚበረበረውንና ፡ የሚያዘውን ፡ ዕቃ ፡ ማመልከት ፡ አለበት ። በማዘዣው ፡ ውስጥ ፡ ከተመለከተው ፡ በቀር ፡ መርማሪው ፡ ፖሊስ፡ወይም፡የፖሊስ፡ሠራዊት ፡ ባልደረባ ፡ ሌላውን ፡ ዕቃ፡መያዝ፡ አይችልም ።

(፫) መርማሪው ፡ ፖሊስ ፡ ወይም ፡ የፖሊስ ፡ ሠራዊት ፡ ባልደረባ ፡ ዕቃውን ፡ በሚይዝበት ፡ ጊዜ ፡ የተያዘውን ፡ ዕቃ ፡ ዝርዝር ፡ መጻፍ ፡ አለበት ። ቢቻል ፡ በጉዳዩ ፡ ነጻ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ የዕቃው ፡ ዝርዝር ፡ ሊስት ፡ ትክክል ፡ መሆኑን ፡ እንዲያረጋግጥና ፡ እንዲፈርምበት፡ ያስፈልጋል ። ለክሱ ፡ መስማት ፡ አስፈላጊ፡ የሆነው ፡ የተያዘው ፡ ዕቃ ፡ መረጃ ፡ (ኤግዚቢት) ፡ ሆኖ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እስቲሰጥ፡ ድረስ፡ ጠንቃቃ፡ ቦታ፡ መቀመጥ ፡ አለበት ። የማያስፈልገው ፡ ማንኛውም፡ ዕቃ ፡ ግን ፡ ደረሰኝ ፡ በመቀበል ፡ ለተወሰደበት ፡ ሰው ፡ ተመላሽ ፡ ይሆናል ።

(፬) መርማሪው ፡ ፖሊስ ፡ ወይም ፡ የፖሊስ ፡ ሠራዊት ፡ ባልደረባ ፡ ብርበራ ፡ በሚያደርግበት ፡ ጊዜ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ኀይል ፡ ብቻ ፡ ለመፈጸም ፡ ይችላል ። እንዲሁም ፡ ከቤቱ፡ ውስጥ ፡ ለመግባት ፡ የተከለከለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተገቢ ፡ በሆነ ፡ ኀይል ፡ ለመግባት ፡ ይችላል ።

(፭) ከፍርድ ፡ ቤት ፡ በተለይ፡ ካልታዘዘ ፡ በቀር ፡ ብርበራ ፡ የሚደረገው ፤ ከጠዋቱ፤አሥራ ፡ ሁለት፡ሰዓት፡ጀምሮ፡እስከ ፡ ማታው፡አሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፴፬ ። የሐኪም ፡ ምርመራ ።

(፩) በፍትሐ፡ ብሔር፡ ሕግ፡ በቍጥር፡ ፳፡ የተመለከተው፡ ቢኖርም፡ መርማሪው፡ ፖሊስ፡ ወይም፡ የፖሊስ፡ ሠራዊት ፡ ባልደረባ፡ ተከሳሹ፡ የተከሰሰበትን፡ ወንጀል፡ ተመልክቶ፡ ተከሳሹ፡በሐኪም፡ መመርመር፡ የሚያስፈልገው፡ መሆኑን፡ ከተረዳ ፡ የማከም ፡ ፈቃድ ፡ ያለው ፡ ሐኪም ፡ ምርመራውን ፡ እንዲያደርግና ፡ የምርመራውንም ፡ ውጤት ፡ ሐኪሙ ፡ በጽሑፍ ፡ እንዲያስታውቅ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

BACK



በዚህ ፡ ቍጥር ፡ መሠረት፡ የሚደረገው፡ ምርመራ፡ የደም ፡ ምርመራንም ፡ ይጨ ምራል ።

(፪) መርማሪው፡ ፖሊስ፡ ወንጀል፡ በተፈጸመበት፡ ሰው፡ ፈቃድ፡ ወይም፡ ችሎታ፡ የሌለው፡ እንደ፡ ሆነ፤ ከወላጁ፡ ወይም ፡ ከሞግዚቱ ፡ ጋራ ፡ በመስማማት ፡ የወን ጀሉ ፡ ምርመራ ፡ በሚደረግበት ፡ ጊዜ ፡ የሐኪም ፡ ምርመራ ፡ የሚያስፈልገው ፡ መስሎ ፡ የታየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለማከም ፡ የፈቃድ ፡ ወረቀት ፡ ያለው ፡ ሐኪም ፡ ምርመራ ፡ እንዲያደርግ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ። የምርመራውንም ፡ ውጤት ፡ ሐኪሙ ፡ በጽሑፍ ፡ እንዲሰጥ ፡ ማድረግ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፴፭ ። ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚነገሩትን ፡ ቃላትና ፡ የሚሰጡትን ፡ የእምነት ፡ ቃላት ፡ የመመዝገብ ፡ ሥልጣን ።**

(፩) የቀዳሚ ፡ ምርመራ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥነ፡ ሥርዐት፤ ወይም ፡ የወንጀሉ ፡ ክስ፡ መሰማት ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ ማናቸውም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማንኛውንም ፡ የተሰጠውን ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ የእምነት ፡ ቃላት ፡ ለመመዝገብ ፡ ይችላል ።

(፪) ፍርድ፡ ቤቱ፡ ቃል፡ ወይም ፡ የእምነት፡ ቃል ፡ የሰጠውን ፡ ሰው ፡ ሳይጠይቅና፡ በነጻ፡ ፈቃዱ፡ ቃሉን፡ መስጠቱን፡ ሳያረጋግጥ፡ የተሰጠውን፡ ቃል፡ ወይም፡ የእም ነት፡ ቃል ፡ መመዝገብ፡ አይችልም ። ይኸውም፡ በመዝገቡ፡ ላይ፡ መጻፍ፡አለበት።

(፫) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተሰጠውን ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ የእምነት ፡ ቃል ፡ ሳያጓድል ፡ በሙሉ፡ በጽሑፍ ፡ ይመዘግባል ፤ ጽሑፉም ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ የእምነት ፡ ቃል ፡ ለሰጠው ፡ ሰው ፡ ከተነበበለት ፡ በኋላ ፡ ይፈርምበታል ፤ ቀኑንም ፡ ይጽፍበታል፤ በተሰጠውም ፡ ቃል ፡ ላይ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ይፈርምበታል ።

(፬) ክሱን ፡ የሚመረምረው ፡ ወይም ፡ ክሱን ፡ የሚሰማው ፡ ሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ለዚሁ ፡ ፍርድ ፡ ቤትና ፡ ለዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ የመዝገቡን ፡ ግልባጭ ፡ መላክ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፴፮ ። የዕለት ፡ ምርመራ ፡ መዝገብ ።**

(፩) በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ምርመራ፡ የሚያደርግ፡ ማናቸ ውም ፡ ፖሊስ ፡ በየቀኑ ፡ የተደረገውን ፡ የምርመራ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ከዚህ ፡ በሚከተለው ፡ ዐይነት ፡ በዕለት ፡ ምርመራው ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፤

(ሀ) ምርመራው ፡ የተጀመረበትንና ፡ የተፈጸመበትን ፡ ቀን ፤

(ለ) ምርመራ ፡ ሲደረግ ፡ የተወሰደውን ፡ ማናቸውንም ፡ እርምጃ ፤

(ሐ) ምርመራው ፡ ያስገኛቸውን ፡ ሁኔታዎች ፤

(መ) የተሰበሰቡትን ፡ የማስረጃ ፡ ዐይነቶች ፡ ሁሉ፤ መግለጽ፡ አለበት ።

(፪) እንደዚሁም ፡ በምርመራው ፡ ጊዜ ፡ የተላከለትን ፡ ማናቸውንም ፡ የአንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ የዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ትእዛዝ ፡ በዚሁ ፡ የዕለት ፡ ምርመራ ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ መጻፍ ፡ አለበት ።

BACK



**ቍ ፡ ፴፯ ። ፖሊስ ፡ ስለሚያቀርበው ፡ ራፖር ።**

(፩) በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት፡ ማናቸውም፡ የፖሊስ፡ ምርመራ፡ ከሚያስፈልገው ፡ ጊዜ ፡ በላይ ፡ ሳይዘገይ ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

(፪) ምርመራው ፡ እንደ፡ ተፈጸመ፡ ወዲያው፡ ምርመራውን ፡ ያደረገው ፡ ፖሊስ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ፡ የተዘረዘሩትን፡ የሚያመለክት ፡ አንድ ፡ ራፖር ፡ ለዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ይልካል ።

(ሀ) የተከራካሪዎቹን ፡ ስም ፤

(ለ) ስለ፡ ቀረበው፡ አቤቱታ፡ ዐይነትና፡ የነገሩን፡ ሁኔታ፡ ያውቃሉ፡ የተባሉትን፡ ሰዎች ፡ ስም ፤

(ሐ) የተሰበሰቡትን ፡ ማስረጃዎች ፡ ዐይነት ።

(፫) እንዲሁም፡ ራፖሩ፡ የአጠባበቅ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ የተለየ ፡ ነገር ፡ የተደረገውን፡ ሁሉ ፡ ማመልከት ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፴፰ ። ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ራፖሩ ፡ ሲደርሰው ፡ ማድረግ ፡ ስለሚገባው ።**

በቍጥር ፡ ፴፯ ፡ መሠረት ፡ የፖሊስ ፡ ራፖር ፡ ሲደርሰው ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፤

(ሀ) በቍጥር፡ ፺፱፡ እስከ፡ ፻፳፪፡ በተመለከተው፡ መሠረት ፡ ክሱን ፡ አዘጋጅቶ ፡ በተከሳሹ ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፤ ወይም ፡

(ለ) ከቍጥር ፡ ፹ ፡ እስከ ፡ ፺፫ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት፡ ነገሩ ፡ ለቀዳሚ ፡ ምርመራ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲቀርብ ፡ ማዘዝ ፤ ወይም ፡

(ሐ) ተጨማሪ፡ ምርመራ ፡ እንዲደረግ፡ ማዘዝ ፤ ወይም ፡

(መ) በቍጥር ፡ ፴፱፡ በተመለከተው፡ መሠረት ፡ አልከስም፡ ለማለት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፴፱ ። የፖሊስ ፡ የምርመራ ፡ መዝገብን ፡ ስለ ፡ መዝጋት ።**

(፩) ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ የፖሊስ ፡ የምርመራ ፡ መዝገብን፡ የሚዘጋው ፤

(ሀ) ተከሳሹ ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡

(ለ) ተከሳሹ ፡ ዕድሜው፡ ከዘጠኝ፡ ዓመት፡ በታች ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም፡

(ሐ) በኢንተርናሲዮናል፡ ሕግ፡ (ዲፕሎማቲክ ፡ ኢሙኒቲ)፡ መሠረት፡ ተከሳሹ ፡ የማይከሰስ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ መብቱ ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ።

(፪) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ መሠረት፡ ክሱ፡ የተዘጋ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከቍጥር ፡ ፵፫ ፡ እስከ ፡ ፵፰ ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ አይሆኑም ።

(፫) ክሱን ፡ ሲዘጋ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ የዘጋበትን ፡ ውሳኔ ፡ ግልባጭ ፡ ለጠቅላይ ፡ ዐቃቤ፡ ሕግ፤ ለግል ፡ አቤት፡ ባይ፡ ያለ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ምርመራውን ፡ ላደረገው፡ ፖሊስ ፡ መላክ ፡ አለበት ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ክስ ፡ አቀራረብ ።

### ቍ ፡ ፵ ። ስለ፡ ክስ፡ ማቅረብ፡ ግዴታ ።

(፩) ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ በተከሳሹ ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ መኖሩን፡ የተረዳው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በቍጥር ፡ ፵፪ ፡ የተመለከተው ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ፡ ሆኖ፡ በዚህ፡ ክፍል፡ ድንጋጌ፡ በተመለከተው፡ መሠረት፡ ክስ፡ ማቅረብ፡ አለበት ።

(፪) በቍጥር፡ ፲፰፪፡ በተመለከተው፡ መሠረት፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ካልታዘዘ ፡ በቀር፡ አካለመጠን ፡ ባላደረሱ ፡ ወጣቶች ፡ ላይ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ አይችልም ።

### ቍ ፡ ፵፩ ። አጠራጣሪ ፡ ሁኔታ ።

ክስ፡ ለማቅረብ ፡ አጠራጣሪ ፡ ሁኔታ ፡ በሚያጋጥምበት ፡ ጊዜ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ፡ መሪ፡ ትእዛዝ፡ እንዲሰጠው፡ ነገሩን ፡ ለጠቅላይ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ያስተላልፋል ።

### ቍ ፡ ፵፪ ። ክስ ፡ የማይቀርብባቸው ፡ ሁኔታዎች ።

(፩) ክስ ፡ ማቅረብ ፡ የማይቻለው ፤

(ሀ) ጥፋተኛ ፡ ለማድረግ፡ በቂ፡ የሆነ፡ መረጃ ፡ የሌለ ፡ መሆኑን ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ የተረዳው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡

(ለ) የተከሰሰውን ፡ ሰው ፡ ለማግኘት ፡ የማይቻል ፡ ወይም ፡ በሌለበት ፡ ክሱ ፡ ሊታይ ፡ የማይቻል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡

(ሐ) ክሱን ፡ ለማቅረብ ፡ በይርጋ ፡ የታገደ ፡ ወይም ፡ ለተፈጸመው ፡ ወንጀል ፡ ምሕረት፡ ወይም፡ የዐዋጅ፡ ምሕረት፡ (ይቅርታ)፡ ተደርጎ ፡ እንደ፡ ሆነ፤ ወይም፡

(መ) የፍርድ፡ ሚኒስትሩ፡ በፈረመበት ፡ ማዘዣ፡ ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ ሲል ፡ ክስ፡ እንዳይቀርብ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉን ፡ ያዘዘው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከተመለከቱት ፡ በቀር ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ በማንኛውም ፡ ሌላ ፡ ሁኔታ ፡ ክስ ፡ አላቀርብም ፡ ለማለት ፡ አይችልም ።

(፫) ዓቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ስለ ፡ መንግሥት ፡ ጉዳይ ፡ ክስ ፡ እንዲያቀርብ ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስትር ፡ ሲያዘው ፡ ክስ ፡ ያቀርባል ።

### ቍ ፡ ፵፫ ። ክስ ፡ አይቀርብም ፡ የማለት ፡ ሥርዐት ፡ (ፎርም) ።

(፩) በቍጥር፡ ፵፪፡ መሠረት፡ ክስ ፡ አይቀርብም ፡ የማለት፡ውሳኔ ፡ በጽሑፍ፡ መሆንና ፡ ክስ ፡ አይቀርብም ፡ የተባለበትን ፡ ምክንያት ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።

(፪) የዚሁ፡ ውሳኔ ፡ ግልባጭ ፡ በቍጥር ፡ ፵፯ ፡ ለተጠቀሰው፡ ተገቢ ፡ ሰውና፡ ምርመራ ፡ ላደረገው ፡ ፖሊስ ፡ መላክ ፡ አለበት ።

BACK



ቍ ፡ ፵፩ ። ክስ ፡ አይቀርብም ፡ የማለት ፡ ውጤት ።

(፩) የክስ፡ አቤቱታ፡በማቅረብ፡ብቻ፡በሚያስቀጣ፡የወንጀል፡ነገር፡በቍጥር፡ ፵፪፡ ንኡስ፡ ቍጥር፡ ፩፡ (ሀ) መሠረት ፡ ክስ ፡ አይቀርብም ፡ የማለት ፡ ውሳኔ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ፡ የሰጠ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ በቍጥር ፡ ፵፯ ፡ ለተጠቀሰው ፡ ተገቢ ፡ የሆነው ፡ ሰው፡ የግል ፡ ክስ ፡ እንዲያቀርብ ፡ በጽሑፍ ፡ ይፈቅድለታል ። የዚሁም ፡ ውሳኔ ፡ ግል ባጭ ፡ ክሱን ፡ ለማየት ፡ መብት ፡ ላለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መላክ ፡ አለበት ።

(፪) የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ማቅረብ ፡ ሳያስፈልግ፡ የሚያስቀጣ ፡ ወንጀል ፡ በቍጥር ፡ ፵፪፡ ንኡስ ፡ ቍጥር፡ ፩፡ (ሀ)መሠረት፡ ክስ፡ አይቀርብም፡የማለት፡ ውሳኔ፡ ዐቃቤ፡ ሕጉ፡ የሰጠ ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ በቍጥር፡ ፵፯፡ የተጠቀሰው ፡ ተገቢ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ የዐቃቤ ፡ ሕጉን፡ ውሳኔ፡ ከተቀበለበት፡ ጊዜ፡ አንሥቶ ፡ በሠላሳ ፡ ቀን፡ ውስጥ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ክስን ፡ እንዲያቀርብ ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲሰጠው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፵፰ ። ስለሚቀርበው ፡ ማመልከቻ ፡ ፎርምና ፡ ስለሚሰጥበት ፡ ውሳኔ ።

(፩) ክሱ ፡ ቢቀርብ ፡ ኖሮ ፡ ለማየት ፡ መብት ፡ ይኖረው ፡ የነበረው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሚሰጠው ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ይግባኙ ፡ ይቀርብለት ፡ ለነበረው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በቍጥር ፡ ፵፩ ፡ ንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፪) የተገለጸው፡ ማመልከቻ፡ መቅረብ ፡ አለበት ።

(፪) ፍርድ፡ ቤቱም፡ በቍጥር ፡ ፵፪ ፡ ንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) (ሀ)መሠረት ፡ ክስ ፡ እን ዳይቀርብ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ የሰጠውን ፡ ውሳኔና ፡ ምክንያት ፡ ካመዛዘነ ፡ በኋላ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ የሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ ማጽደቅ፡ ወይም ፡ ክሱ ፡ እንዲቀርብ ፡ ለማ ዘዝ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፵፮ ። የግል ፡ ከሳሽ ፡ ስላለበት ፡ ኀላፊነት ።

በቍጥር ፡ ፵፩፡ በንኡስ ፡ ቍጥር፡ (፪) መሠረት፡ የግል ፡ ክስ ፡ እንዲያቀርብ ፡ የተ ፈቀደለት ፡ የግል ፡ ከሳሽ ፡ የሚከራከረው ፡ በራሱ ፡ ኀላፊነትና ፡ ኪሣራ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፵፯ ። የግል ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ መብት ፡ ስለ ፡ ተሰጣቸው ፡ ሰዎች ።

ከዚህ ፡ በታች ፡ ከተዘረዘሩት ፡ ሰዎች ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ የግል ፡ ክስ ፡ ለማ ቅረብ ፡ አይችልም ።

(ሀ) የተበደለው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ እንደራሴው ፤ ወይም ፡

(ለ) ባል ፡ ስለሚስቱ ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ ስለባሏ ፤ ወይም ፡

(ሐ) ችሎታ ፡ ስለሌለው ፡ ሰው ፡ እንደራሴው ፤ ወይም ፡

(መ) በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ ስለ ፡ ተሰጠው ፡ ማኅበር ፡ ወኪሉ ።

**ቊ ፡ ፵፰ ። ዐቃቤ ፡ ሕጉ፡ ክስ ፡ እስኪያቀርብበት ፡ ድረስ ፡ በግል ፡ የቀረበው ፡ ክስ ፡ እንዲቆም ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።**

በግል ፡ ክስ ፡ ከቀረበው ፡ ወንጀል ፡ የበለጠ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ወንጀል ፡ ለመሠራቱ ፡ ለግል ፡ ክሱ ፡ በቀረበው ፡ ማስረጃ ፡ የተገለጸ ፡ ሲሆን ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ አዲስ ፡ ክሱን፡ እስኪያቀርብ፡ ድረስ፡ የግል ፡ ክስ ፡ እንዲቆም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ። ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ ክሱን ፡ ማቆም ፡ አለበት ።

## አንቀጽ ፡ ፪ ።

## ምርመራው ፡ እስኪደረግ ፡ ድረስ ፡ ስለሚደረገው ፡ ጥንቃቄ ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ስለ ፡ መያዝ ።

#### ክፍል ፡ ፩ ።

#### ያለ ፡ ፍርድ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ፡ ስላለመያዝ ።

**ቊ ፡ ፵፱ ። መሠረቱ ።**

ግልጽ ፡ የሆነ፡ ሌላ፡ ተቃራኒ፡ ድንጋጌ፡ ከሌለ፡ በቀር፡ ማንም፡ ሰው፡ ቢሆን ፡ ያለ፡ ፍርድ ፡ ቤት፡ ትእዛዝ፡ ሊያዝ ፡ ወይም ፡ ያለ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እንዲቈይ ፡ ለማድረግ ፡ አይቻልም። ያለ ፡ ፍርድ ፡ ቤት፡ ትእዛዝ ፡ የሚደረገው ፡ የሰው ፡ መያዝ ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ በተመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት፡ ብቻ ፡ ነው ።

**ቊ፡ ፶ ። የእጅ፡ ከፍንጅ፡ ወንጀል፡ በተፈጸመ፡ጊዜ፡ ያለ፡ፍርድ፡ ቤት፡ ትእዛዝ፡ ስለ፡መያዝ።**

ማንኛውም፡ ሰው፡ ወይም ፡ የፖሊስ፡ ሠራዊት፡ ባልደረባ ፡ በቊጥር ፡ ፲፱ ፡ እና ፡ ፳ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ከሦስት፡ ወር ፡ በማያንስ፡ በቀላል ፡ ቅጣት ፡ የሚያስቀጣ ፡ የእጅ ፡ ከፍንጅ ፡ ወንጀል ፡ የተፈጸመ ፡ እንደ፡ሆነ ፤ ያለ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ ወንጀል ፡ ሠሪውን ፡ ለመያዝ ፡ ይችላል ።

**ቊ ፡ ፶፩ ። ያለ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ ፖሊስ ፡ ስለ ፡ ተሰጠው ፡ የመያዝ ፡ መብት ።**

(፩) ያለ፡ፍርድ፡ ቤት፡ትእዛዝ፡ የፖሊስ፡ ሠራዊት፡ ባልደረባ፡መያዝ፡ የሚችለው፡—

(ሀ) ከአንድ፡ ዓመት ፡ በማያንስ ፡ እስራት ፡ የሚያስቀጣ ፡ ወንጀል ፡ ለመሥራት ፡ ዝግጁ ፡ የሆነውን ፡ ወይም ፡ ሠርቷል ፡ ተብሎ ፡ በሚገባ ፡ የተጠረጠረውን ፡ ሰው ፤

(ለ) የሕዝብን ፡ ጸጥታ ፡ በማበላሸት ፡ ላይ ፡ የሚገኘውን ፡ ሰው ፤

BACK



(ሐ) የፖሊስ፡ ሠራዊት ፡ ባልደረባ፡ ሥራውን፡ በሚፈጽምበት ፡ ጊዜ ፡ ተቃዋሚነትን ፡ በማሳየት፡ የሚከላከለውን ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ ከታሰረበት ፡ የሚያመልጠውን ፡ ወይም ፡ ለማምለጥ ፡ የሚሞክረውን ፡ ሰው ፤

(መ) ከፖሊስ ፡ ተጠባባቂነት ፡ የሚያመልጥ ፡ ወይም፡ አምልጦ ፡ የሄደ ፡ ለመሆኑ ፡ በሚገባ ፡ የሚጠረጠረውን ፡ ሰው ፤

(ሠ) ከወታደርነት ፡ ወይም ፡ ከፖሊስ ፡ ሠራዊት፡ ከድቶ ፡ የሄደ ፡ ለመሆኑ ፡ በሚገባ ፡ የሚጠረጠረውን ፡ ሰው ፤

(ረ) ሕግ ፡ የማይፈቅድለትን ፡ የቤት ፡ መሠርሠሪያ ፡ ወይም ፡ ቤትን ፡ ሰብሮ ፡ መግቢያ ፡ መዛሪያ ፡ የተገኘበት ፡ ሰው ፤

(ሰ) ሕግ ፡ የማይፈቅድለትን ፡ የተሰረቀ፡ ዕቃ ፡ የያዘ ፡ ለመሆኑ ፡ በሚገባ ፡ የሚያስጠረጥር ፡ ሆኖ ፡ ወይም ፡ ወንጀል ፡ በመፈጸም ፡ ረገድ ፡ ያገኘው ፡ ዕቃ ፡ በይዞታው ፡ የተገኘበት ፡ ሰው ፤

(ሸ) በወንጀለኛ፡ መቅጫ፡ ሕግ፡በቍጥር፡ ፬፻፸፩፡ እንደተመለከተው፡ አደገኛ፡ ሥራ ፡ ፈት ፡ መሆኑ ፡ በሚገባ ፡ የሚጠረጠረውን ፡ ሰው ፡ ነው ።

(፪) የመንግሥት፡ ባለሥልጣን፡ ሠራተኞች፡ ያለ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ ሰውን ፡ ለመያዝ ፡ በሌላ ፡ በልዩ ፡ ሕግ ፡ የሚሰጣቸው ፡ ሥልጣን ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## በፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ ስለ ፡ መያዝ ።

### ቍ ፡ ፶፪ ። መሠረቱ ።

(፩) ሰውዬው ፡ ከመያዙ፡ በፊት፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የመያዝ ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲሰጥ ፡ ሕጉ ፡ የሚያዝ ፡ ሲሆን ፤ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያሉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

(፪) ፍርድ፡ ቤት ፡ የሚሰጠው ፡ የመያዝ ፡ ትእዛዝ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በሦስተኛው ፡ ሠንጠረዥ ፡ ዐይነት ፡ የተዘጋጀ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(፫) የፍርድ፡ ቤቱ፡ የመያዝ፡ ትእዛዝ ፡ እስኪፈጸም ፡ ወይም ፡ ትእዛዝ ፡ በሰጠው፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እስኪሻር ፡ ድረስ ፡ ትእዛዙን ፡ የሰጠው ፡ ዳኛ ፡ ቢሞትም ፤ ከሥራው ፡ ቢወጣም ፡ ወይም ፡ ቢዛወርም ፤ የተባለው ፡ ትእዛዝ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ ይቈያል ።

### ቍ ፡ ፶፫ ። የመያዝ ፡ ትእዛዝ ፡ ስለ፡ መስጠት ።

(፩) ማናቸውም ፡ መርማሪ ፡ ፖሊስ ፡ በሚያቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ ማናቸውም ፡ ፍርድ፡ ቤት፡ ቢሆን ፡ የመያዝ፡ ትእዛዝ፡ ይሰጣል ። የመያዝ ፡ ትእዛዙም ፡ የሚሰጠው፡ ትእዛዙ፡ በተሰጠበት፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት፡ ላለው፡ የፖሊስ ፡ አዛዥ ፡ ነው ።

(፪) የመያዝ፡ ትእዛዝ፡ በማናቸውም፡ ቀንና፡ ሰዓት ፡ ቢሆን ፡ ሊሰጥ ፡ ይቻላል ።

BACK



(፫) ሰው ፡ እንዲያዝ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ በማናቸውም ፡ ቦታ ፡ ማናቸውም ፡ የፖሊስ ፡ ሠራዊት ፡ ባልደረባ ፡ እንዲፈጸም ፡ ማድረግ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፶፬ ። የመያዝ ፡ ትእዛዝ ፡ መቼ ፡ እንደሚሰጥ ።

ሰውን ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለማቅረብ ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ የማይቻል ፡ በሚሆንበት፡ ጊዜና፡ መቅረቡም፡ ፍጹም፡ አስፈላጊ፡ ሲሆን፡ የመያዝ፡ ትእዛዝ፡ ይሰጣል ።

ቍ ፡ ፶፭ ። አስቸኳይ፡ ሁኔታ፡ ሲገጥም፡ የመያዝ፡ ትእዛዝ፡ ለማግኘት፡ የሚደረግ ፡ጥያቄ።

(፩) አስቸኳይ ፡ ሁኔታ፡ ሲያጋጥም ፡ መርማሪው ፡ ፖሊስ ፡ በቴሌፎን ፡ ወይም ፡ በቴሌግራም ፡ የመያዝ ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲሰጥ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) እንደዚህ፡ ያለው ፡ ሁኔታ ፡ በሚያጋጥምበት ፡ ጊዜ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጥያቄውን ፡ በኻያ፡ አራት ፡ ሰዓት ፡ ውስጥ ፡ በጽሑፍ ፡ ማረጋገጥ ፡ አለበት ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

ቍ ፡ ፶፮ ። የአያያዙ ፡ ሁኔታ ።

(፩) ፖሊስ ፡ የሚይዘውን ፡ ሰው፡ ማንነቱን ፡ (የሚያዘው ፡ ሰው ፡ እሱ ፡ መሆኑን ) ፡ አስቀድሞ ፡ ማረጋገጥ ፡ አለበት ።

(፪) በፍርድ ፡ ቤት ፡ የመያዝ ፡ ትእዛዝ፡ የተሰጠው፡ የሆነ ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ ፖሊሱ ፡ እንዲይዝ ፡ የታዘዘበትን ፡ ለሚያዘው ፡ ሰው ፡ ማንበብ ፡ አለበት ። ትእዛዙንም ፡ የሚያዘው ፡ ሰው ፡ የጠየቀው፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማሳየት ፡ አለበት ።

(፫) የሚያዘው ፡ ሰው ፡ በቃል ፡ ወይም ፡ እጁን ፡ በመስጠት ፡ እንዲያዝ ፡ ያልተስማማ ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ ፖሊሱ ፡ ሰውዬውን፡ በመንካት፡ ወይም ፡ በመጨበጥ ፡ ለመያዝ ፡ ይችላል ።

(፬) የሚያዘውም ፡ ሰው ፡ አልያዝም ፡ ብሎ ፡ በኀይል ፡ የተከላከለ ፡ ወይም ፡ ለማምለጥ፡ የሞከረ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ሁኔታው፡ በሚፈቅደው፡ ተመዛዛኝ፡ ዘዴ ፡ ፖሊሱ፡ ሰውዬውን ፡ ለመያዝ ፡ ይችላል ።

(፭) የዚህ ፡ ቍጥር ፡ ድንጋጌ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በራሱ ፡ አስተያየት ፡ በሚሰጠው ፡ የመያዝ ፡ ትእዛዝ ፡ ላይም ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፶፯ ። ለመያዝ ፡ ርዳታ ፡ አስፈላጊ ፡ ስለሚሆንበት ።

ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ ወይም ፡ ያለ ፡ ትእዛዝ ፡ በሚደረገው ፡ የሰው ፡ መያዝ ፡ ለመርዳት፡ በፖሊስ ፡ የተጠየቀ ፡ እንደ፡ ሆነና፡ በራሱ ፡ ላይ፡ አደጋ፡ የማይደርስበት፡ የሆነ፡ እንደ፡ ሆነ፡ (በቍ፡ ፯፻፳፩፡ የወንጀለኛ፡ መቅጫ፡ ሕግ ፡ መሠረት ) ፡ ርዳታ ፡ ለመስጠት ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

BACK



ቍ ፡ ፶፰ ። የተያዘውን ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ማስረከብ ።

(፩) የተያዘውን ፡ ሰው ፡ ከሚያስፈልገው ፡ በላይ ፡ ሳያዘገይ ፡ የያዘው ፡ ሰው ፡ አቅራቢያ ፡ ለሆነው ፡ ለፖሊስ ፡ ጣቢያ ፡ ወዲያውኑ ፡ ማስረከብ ፡ አለበት ።

(፪) ሰውዬውን፡ የያዘው፡ ሰው ፡ ወንጀሉ፡ ሲሠራ ፡ ያየ ፡ ከሆነ፡ በቍጥር ፡ ፴ ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ ቃሉንም ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፶፱ ። በማረፊያ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ማቈየት ።

(፩) በቍጥር ፡ ፳፱ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ የተያዘው ፡ ሰው ፡ የቀረበለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ ይቈይ ፡ ወይም ፡ በዋስትና ፡ ወረቀት ፡ ይለቀቅ ፡ ብሎ ፡ መወሰን፡ አለበት ።

(፪) የፖሊሱም ፡ ምርመራ፡ ያልተፈጸመ ፡ እንደ፡ ሆነ፤ መርማሪው ፡ ፖሊስ ፡ ምርመራውን ፡ የሚፈጽምበት ፡ በቂ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሰጠው ፡ ተከሳሹ ፡ ማረፊያ ፡ ቤት ፡ እንዲቈይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፫) በማረፊያ ፡ ቤት ፡ ለማቈየት ፡ የሚሰጠውም ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ በጽሑፍ ፡ መሆን ፡ አለበት ፤ ለያንዳንዱ ፡ በማረፊያ ፡ ቤት፡ ለማቈየት፡ የሚጠየቀው ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ ከ፲፬ ፡ አራት ፡ ቀን ፡ ሊበልጥ ፡ አይችልም ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## ለምርመራ፡ በማረፊያ፡ ቤት፡ ለማቈየት፡ የሚፈቀድ፡ የተጨማሪ፡ ጊዜ፡ ሁኔታ ።

ቍ ፡ ፷ ። ለምርመራ ፡ የሚፈቀድ ፡ የተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ ሁኔታ ።

ማንኛውም ፡ የተያዘ ፡ ሰው ፡ የወህኒ ፡ ቤት ፡ ሕግ ፡ በሚያዘው ፡ ሁኔታ ፡ መሠረት ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ ይቈያል ።

ቍ ፡ ፷፩ ። በማረፊያ ፡ ቤት ፡ የተያዘው ፡ ሰው ፡ ከጠበቃው ፡ ጋራ ፡ ለመገናኘት ፡ ስላለው ፡ መብት ።

ተይዞ ፡ ወይም ፡ ለምርመራ ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ የሚቈይ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ጠበቃ ፡ አስጠርቶ ፡ ለመነጋገር ፡ ይፈቀድለታል ። እንዲሁም ፡ ለመጻፍ ፡ የሚያገለግለውን ፡ መሣሪያ ፡ የጠየቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይሰጠዋል ።

ቍ ፡ ፷፪ ። ዋስ፡ የሚሆን ፡ ስለ፡ መፈለግ ።

በማረፊያ ፡ ቤት ፡ ተይዞ ፡ የቈየ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በዋስ ፡ የሚለቀቅ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዋስ ፡ ፈልጎ ፡ እንዲያገኝ ፡ ርዳታ ፡ ይደረግለታል ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## የዋስትና ፡ ወረቀት ፡ አስፈርሞ ፡ ስለ ፡ መልቀቅ ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### የዋስትና ፡ ወረቀት ።

**ቍ ፡ ፷፫ ። መሠረቱ ።**

(፩) ማንኛውም ፡ የተያዘ ፡ ሰው ፡ የተከሰሰበት ፡ ወንጀል ፡ የሞት ፡ ቅጣትን ፡ ወይም ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ወይም ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ የማያስቀጣው ፡ ከሆነና ፡ ወንጀል ፡ የተፈጸመበት ፡ ሰው ፡ በደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ የማይሞት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የዋስትና ፡ ወረቀት ፡ አስፈርሞ ፡ ለመልቀቅ ፡ ይችላል ።

(፪) የዋስትና ፡ ወረቀት ፡ በዋስ ፡ ወይም ፡ ያለ ፡ ዋስ ፡ በማስፈረም ፡ የሚለቀቀው ፡ ሰው ፡ በሚፈለግበት ፡ ጊዜ ፡ እንዲያቀርብ ፡ የሚያደርገው ፡ በቂ ፡ ዋስትና ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ካልተረዳው ፡ በቀር ፡ የተያዘውን ፡ ሰው ፡ የዋስትና ፡ ወረቀት ፡ በማስፈረም ፡ መፈቀቅ ፡ አይችልም ።

(፫) የዚህ ፡ ቍጥር ፡ ድንጋጌ ፡ ቢኖርም ፡ በቍ ፡ ፷፯ ፡ የተነገረው፡የተጠበቀ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፷፬ ። በዋስትና ፡ ወረቀት ፡ እንዲለቀቅ ፡ የሚቀርብ ፡ ማመልከቻ ።**

(፩) በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ የተያዘው ፡ ሰው ፡ በዋስትና ፡ ወረቀት ፡ እንዲለቀቅ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ማመልከቻውን ፡ በጽሑፍ ፡ አድርጎ ፡ አመልካቹ ፡ መፈረም ፡ አለበት ። ማመልከቻ ፡ ያቀረበበትን ፡ ምክንያት ፡ በአጭሩ ፡ መግለጽና ፡ ማቅረብ ፡ የሚችለውን ፡ የዋስትና ፡ ወረቀት ፡ ሁኔታ ፡ ማመልከት ፡ አለበት ።

(፫) በዋስትና ፡ ወረቀት ፡ እንዲለቀቅ ፡ የሚቀርበውን ፡ ማመልከቻ ፡ ማናቸውም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለመፍቀድ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፷፭ ። ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሚሰጠው ፡ የመያዝ ፡ ትእዛዝ ፡ ላይ ፡ የሚሰጠውን ፡ ዋስትና፡ ስለ፡ማመልከት ።**

(፩) ማናቸውም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሰውን ፡ የመያዝ ፡ ትእዛዝ፡ሲሰጥ ፤ በትእዛዙ ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ የተገለጸውን ፡ የዋስትና ፡ ወረቀት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ባዘዘው ፡ መሠረት ፡ የሚያዘው ፡ ሰው ፡ የፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የመያዝ ፡ ትእዛዙን ፡ እንዲያስፈጽም ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የታዘዘውን ፡ ፖሊስ ፡ የዋስትናውን ፡ ወረቀት ፡ ካስፈረመው ፡ በኋላ ፡ የተያዘውን ፡ ሰው ፡ ከማረፊያ ፡ ቤት ፡ መልቀቅ ፡ አለበት ፡ ብሎ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

BACK



(፪) በትእዛዙ ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ የሚጻፈው ፤

(ሀ) የዋስትናው ፡ ገንዘብ ፡ ልክና ፡ ዋሶቹ ፡ ያሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) እፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መቅረብ ፡ ያለበትን ፡ ቀን ፤ ማመልከት ፡ አለበት ።

(፫) የመያዝ፡ ትእዛዙ ፡ እንደሚያመለክተው ፡ በዚህ ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፡ የዋስትናው ፡ ወረቀት ፡ ግዴታ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ የመያዝ ፡ ትእዛዝን ፡ እንዲያስፈጽም፡ የታዘዘው፡ ፖሊስ፡ የተያዘውን፡ ሰው ፡ መልቀቅና ፡ የዋስትናውን ፡ ወረቀት ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

## ቍ ፡ ፷፯ ። በዋስትና ፡ ወረቀት ፡ የመለቀቅ ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ ስለሚሰጠው ፡ ውሳኔ ።

ማናቸውም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በዋስትና ፡ ወረቀት ፡ የመልቀቅ ፡ ማመልከቻ ፡ ሲደርሰው ፡ ማመልከቻው ፡ ያለ ፡ መዘግየት ፡ መታየት ፡ አለበት ። በዚሁ ፡ ጕዳይ፡ ዐቃቤ፡ ሕጉ፡ ወይም፡ እሱ፡ የሌለ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ መርማሪው ፡ ፖሊስ ፡ ትችትና ፡ አሳብ ፡ እንዲሰጥ ፡ ይጠይቀዋል ። ውሳኔውንም፡ በአርባ ፡ ስምንት ፡ ሰዓት ፡ ውስጥ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

## ቍ ፡ ፷፯ ። የዋስትና ፡ ወረቀት ፡ በመፈረም ፡ ስላለመልቀቅ ።

በዋስትና ፡ ወረቀት ፡ የመለቀቅ ፡ ማመልከቻን ፡ መቀበል ፡ የማይቻለው ፤

(ሀ) በዋስትናው ፡ ወረቀት ፡ የተመለከቱትን ፡ ግዴታዎች ፡ አመልካቹ ፡ የሚፈጽም ፡ የማይመስል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) አመልካቹ ፡ ቢለቀቅ ፡ ሌላ ፡ ወንጀል ፡ ይፈጽም ፡ ይሆናል ፡ ተብሎ ፡ የሚገመት ፡ ሲሆን ፤

(ሐ) ምስክሮችን ፡ በመግዛት ፡ (በማባበል) ፡ ወይም ፡ አስረጂ ፡ የሚሆኑበትን ፡ ያጠፉ ፡ ይሆናል ፡ ተብሎ ፡ የሚገመት ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

## ቍ ፡ ፷፰ ። የዋስትና ፡ ወረቀት ፡ በማስፈረም ፡ ስለ ፡ መልቀቅ ።

የዋስትና ፡ ወረቀት ፡ በማስፈረም ፡ ለመለቀቅ ፡ የቀረበውን ፡ ማመልከቻ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተቀበለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የተያዘው ፡ ሰው ፡ በዋስትናው ፡ ወረቀት ፡ ውስጥ ፡ የሚለቀቅባቸውን ፡ ግዴታዎች ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይወስናል ።

## ቍ ፡ ፷፱ ። የሚሰጠውን ፡ የዋስትና ፡ ልክ ፡ ስለ ፡ መወሰን ።

(፩) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚጠሩትን ፡ ዋሶች ፡ አመራረጥና ፡ የዋስትናውን ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ በመሰለው ፡ ይወስናል ።

(፪) ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ይህንኑ ፡ ጕዳይ ፡ ሲወስን ፤

(ሀ) የወንጀሉን ፡ ክስ ፡ ከባድነትና ፤

(ለ) ተከሳሹ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከመቅረብ ፡ የማይቀር ፡ መሆኑንና ፤

BACK



(ሐ) የተከሳሹ ፡ መለቀቅ ፡ ለሕዝብ ፡ ጸጥታ ፡ የሚያስከትለውን ፡ አደጋና ፤
(መ) ተከሳሹና ፡ ዋሶቹ ፡ ያላቸውን ፡ ሀብት ፤ ማመዛዘን ፡ አለበት ።

(፫) ማመልከቻውን፡ ፈቅዶ፡ መቀበል፡ ወይም ፡ ያለመቀበል ፡ ውሳኔ ፡ በጽሑፍ፡ ሆኖ ፡ የውሳኔውንም ፡ ምክንያት ፡ ጭምር ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፷ ። የዋሶቹ ፡ ግዴታዎች ።

(፩) በዋስትናው ፡ ወረቀት ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር፡ የክሱ ፡ መታየት ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ተጀምሮ ፡ የክሱ ፡ መሰማት ፡ ከጊዜ ፡ ወደ ፡ ጊዜ ፡ የሚቀጠርም ፡ ቢሆን ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜና ፡ ቦታ ፡ በቀጠሮው ፡ ቀን ፡ ዋሱ ፡ በዋስትና ፡ ወረቀት ፡ የተለቀቀውን ፡ ተከሳሽ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የማቅረብ ፡ ኀላፊነት ፡ አለበት ።

(፪) በቍ ፡ ፷፯ ፡ እና ፡ ፷፰ ፡ የተመለከቱት ፡ ውሳኔዎች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

(፫) የዋስትናውን፡ ወረቀት ፡ የፈረመው ፡ ዋሱ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዋስትናው፡ ውድቅ ፡ ይሆናል ። የተሰጡትም ፡ መያዣዎች ፡ የዋሱ ፡ ወራሾች ፡ ለሆኑ ፡ የግል ፡ ባለመብቶች ፡ ተመላሽ ፡ ይሆናሉ ። በዋስትና ፡ ወረቀት ፡ የተለቀቀውም ፡ ተከሳሽ ፡ ሌላ ፡አዲስ ፡ ዋስ ፡ እንዲጠራ ፡ ይታዘዛል ።

ቍ ፡ ፷፩ ። የዋስትናው ፡ ወረቀት ፡ የሚቈይበት ፡ ጊዜ ።

(፩) የዋስትናው ፡ ወረቀት ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ በሦስተኛው ፡ ሠንጠረዥ ፡ በተመለከተው ፡ ፎርም ፡ ዐይነት ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(፪) የዋስትናው ፡ ወረቀት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ሆኖ፡ ይቈያል ፤ ግን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከጊዜ ፡ ወደ ፡ ጊዜ ፡ ለማራዘም ፡ ይችላል ።

(፫) በዋስትና፡ ወረቀት፡ በተለቀቀው ፡ ተከሳሽ ፡ ላይ ፡ የቀረበው ፡ ክስ ፡ የተተወ፡ እንደ፡ ሆነ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የዋስትናው፡ ወረቀት ፡ እንዲቀር፡ ያደርጋል ።

ቍ ፡ ፷፪ ። ስለ ፡ መልቀቅ ።

የዋስትናው ፡ ወረቀት ፡ እንደ ፡ ተፈረመ ፡ ሌሎችም ፡ ሥርዐቶች ፡ (ፎርማሊቲዎች) ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ተፈጸሙ ፡ ተከሳሹ ፡ ከማረፊያ ፡ ቤት ፡ መለቀቅ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፷፫ ። ስሕተት ፡ ወይም ፡ ማታለል ።

(፩) በስሕተት ፡ ወይም ፡ በማታለል ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ አደራረግ ፡ ምክንያት ፡ የዋሶቹ ፡ ዋስትና ፡ በቂ ፡ ሳይሆን ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ፍርድ፡ ቤቱ ፡ በዋስትና ፡ ወረቀት ፡ የተለቀቀው ፡ ተከሳሽ ፡ እንዲያዝ ፡ ትእዛዝ፡ ለመስጠት፡ ይችላል ። የተባለው ፡ ተከሳሽ ፡ ሲቀርብ ፡ በቂ ፡ ዋሶች ፡ እንዲሰጥ ፡ ፍርድ፡ ቤቱ፡ ያዘዋል ።

BACK



(፪) ተከሳሹም ፡ የታዘዘውን ፡ እንቢ ፡ ያለ ፡ ወይም ፡ ለማድረግ ፡ ያልቻለ ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ እንደ ፡ ገና ፡ እማረፊያ ፡ ቤት ፡ እንዲቈይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

ቍ ፡ ፷፬ ። አዲስ ፡ ነገር ።

በዋስትና ፡ ወረቀት፡ እንዲለቀቅ፡ ውሳኔ፡ በተሰጠ፡ ጊዜ ፡ ያልተገለጸ ፡ አዲስ ፡ ነገር፡ የተገኘ፡ እንደ፡ ሆነ፤ ፍርድ፡ ቤቱ፡ በማናቸውም፡ ጊዜ፡ ቢሆን፡ በሥልጣኑ፡ ወይም፡ በማናቸውም ፡ ባለጕዳይ ፡ አመልካችነት ፡ ተከሳሹ፡ በዋስትና ፡ ወረቀት፡ የተለቀቀበትን፡ ሁኔታዎች፡ (ግዴታዎች) ፡ እንደ፡ገና፡ ተመልክቶ፡ የተለቀቀው ፡ ተከሳሽ ፡ አዲስ ፡ ዋሶች ፡ እንዲያመጣ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እንዲቈይ ፡ ለማዘዝ ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፷፭ ። በዋስትና ፡ ወረቀት ፡ እንዲለቀቅ ፡ ያልተፈቀደ ፡ ሲሆን ፡ ለይግባኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማመልከቻ ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ።

(፩) በዋስትና ፡ ወረቀት ፡ ለመለቀቅ ፡ የቀረበውን ፡ ማመልከቻ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያልተቀበለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በቍ ፡ ፻፹፪ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ ለተመለከተው ፡ የይግባኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሻያ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ማመልከቻውን ፡ ሊያቀ ርብ፡ ይችላል ። ማመልከቻውም ፡ በዋስትና፡ ወረቀት ፡ ሊለቀቅ ፡ የሚገባበትን ፡ ምክንያት ፡ በግልጽ ፡ ማመልከት ፡ አለበት ።

(፪) የይግባኙ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማመልከቻውን ፡ ከመረመረ ፡ በኋላ ፡ ማመልከቻ ውን ፡ አልቀበልም ፡ ለማለት ፡ ወይም ፡ በሚወስነው ፡ ግዴታ ፡ መሠረት ፡ በዋስትና ፡ ወረቀት ፡ ለመልቀቅ ፡ ይችላል ። በዚህ ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፡ ይህ ፡ የይግባኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ይግባኝ ፡ የለውም ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## የዋስትናው ፡ ወረቀት ፡ ውጤት ።

ቍ ፡ ፷፮ ። ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስላለመቅረብ ።

(፩) በዋስትና፡ ወረቀት ፡ የተለቀቀው ፡ ተከሳሽ ፡ በቀጠሮው ፡ ቀን ፡ ሳይቀርብ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ተከሳሹ ፡ እንዲያዝ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የመያዝ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

(፪) ዋሶቹም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተጠርተው ፡ ቀርበው ፡ ሊከፍሉ ፡ የገቡትን፡ግዴታ፡ ለመንግሥት ፡ ገቢ ፡ የማይሆንበት ፡ ምክንያት ፡ ቢኖራቸው ፡ ማስረዳት ፡ አለ ባቸው ።

(፫) በዋስትናው ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ የነገሩን ፡ ሁኔታ ፡ በሚፈቅደው ፡ ረገድ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

BACK



ቍ ፡ ፸፺ ። በዋስትና ፡ ወረቀት ፡ የተለቀቀው ፡ ተከሳሽ ፡ ይጠፋል ፡ ተብሎ ፡ የሚጠረጠር ፡ ሲሆን ።

(፩) ዋሶቹ ፡ ተከሳሹ ፡ ይጠፋል ፡ ብለው ፡ ሲጠረጥሩ ፡ ይህንኑ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አመልክተው ፡ ዋስትናቸው ፡ እንዲወርድላቸው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላሉ ።

(፪) ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ተከሳሹ ፡ እንዲያዝ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጥቶ ፡ ተከሳሹ ፡ ከተያዘ ፡ በኋላ ፡ ከዋሶቹ ፡ ላይ ፡ ዋስትናቸውን ፡ ያወርድላቸዋል ።

ቍ ፡ ፸፰ ። የዋስትና ፡ መውረድ ።

(፩) ዋሶች ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ የተለቀቀውን ፡ ተከሳሽ ፡ በዋስትና ፡ ወረቀት፡ ለለቀቀው፡ ፍርድ፡ ቤት ፡ ሲያቀርቡ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ዋስትናቸውን ፡ ያወርድላቸዋል ።

(፪) በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ዋሶቹ ፡ በሙሉ ፡ የዋስትናው ፡ ወረቀት ፡ እንዲወርድላቸው ፡ ወይም ፡ ከዋሶቹ ፡ አንዱ ፡ የገባው ፡ ዋስትና ፡ እንዲወርድለት ፡ የዋስትናውን ፡ ወረቀት ፡ የተቀበለውን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መጠየቅ ፡ ይችላሉ ። በዚህም ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተለቆ ፡ የነበረውን ፡ ተከሳሽ ፡ እንዲያዝ፡ ትእዛዝ፡ መስጠት ፡ አለበት ። ተከሳሹም ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ የዋስትናውን ፡ ወረቀት ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ ዋስትናው ፡ እንዲወርድለት ፡ የጠየቀው ፡ አመልካች ፡ የሰጠው ፡ ዋስትና ፡ ብቻ ፡ እንዲወርድ ፡ ያደርጋል ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ እና ፡ ፪ ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ ተከሳሹ፡ ሌሎች፡ በቂ፡ ዋሶች፡ እንዲሰጥ፡ ይደረጋል ። ይህን፡ ለማድረግ ፡ ያልቻለ ፡ ወይም ፡ ፈቃደኛ ፡ ያልሆነ፡ እንደ፡ሆነ፤ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እንዲቈይ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

ቍ ፡ ፸፱ ። በዋስትና ፡ የተያዘውን ፡ ስለ ፡ መውረስ ።

ተከሳሹ፡ የዋስትናው፡ ወረቀት ፡ የሚያስገድደውን ፡ ያልፈጸመ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ተከሳሹ ፡ ወይም ፡ ዋሶቹ ፡ ዋስትና ፡ የተገባበት ፡ ገንዘብ ፡ ሊወረስ ፡ የማይገባበትን ፡ ምክንያት ፡ ካላስረዱ ፡ በቀር ፡ ዋስትና ፡ የተገባበት ፡ ገንዘብ ፡ ለመንግሥት ፡ ገቢ ፡ ይሆናል ።

BACK



# ሦስተኛ ፡ መጽሐፍ ።

## ቀዳሚ ፡ ምርመራ ፡ አድራጊ ፡ ፍርድ ፡ ቤትና ፡ ክሱ ፡

## ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲሰማ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።

**ቍ ፡ ፹ ። መሠረቱ ።**

(፩) በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፳፪ ፡ (ከባድ ፡ የግፍ ፡ አገዳደል )፡ ወይም ፡ በቍጥር ፡ ፯፻፴፯ ፡ (ከባድ ፡ የሆነ ፡ የወንበዴነት ፡ ሥራ) ፡ በመሥራት፡ የተከሰሰ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ለቀዳሚ ፡ ምርመራ ፡ አድራጊ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነገሩ ፡ እንዲጣራ ፡ መቅረብ ፡ አለበት ።

ስለ ፡ ሆነም ፡ ወዲያውኑ ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነገሩ ፡ መታየት ፡ አለበት ፡ ብሎ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ያቀረበውን ፡ አሳብ ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት፡ ከተረዳ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ነገሩ ፡ ለቀዳሚ ፡ ምርመራ ፡ አድራጊ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መቅረብ ፡ የለበትም ፡ ብሎ ፡ ለመወሰን ፡ የዚህ ፡ ቍጥር ፡ ድንጋጌ ፡ አያግደውም ።

(፪) በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ብቻ ፡ መታየት ፡ በሚገባው ፡ በሌላ ፡ ወንጀል ፡ የተከሰሰ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ በቍጥር ፡ ፴፰ ፡ (ለ) መሠረት ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ካላዘዘ ፡ በቀር ፡ ቀዳሚ ፡ ምርመራ ፡ አድራጊ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነገሩ ፡ እንዲጣራ ፡ መቅረብ ፡ የለበትም ።

**ቍ ፡ ፹፩ ። ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ።**

ከቍጥር ፡ ፺፱ ፡ እስከ ፡ ፻፯ ፡ የተመለከተው ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ ወንጀሉ ፡ በተፈጸመበት ፡ ስፍራ ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ የወረዳ ፡ ግዛት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የቀዳሚ ፡ ምርመራ ፡ ያደርጋል ።

**ቍ ፡ ፹፪ ። ሥነ ፡ ሥርዐት ።**

(፩) የቀዳሚ ፡ ምርመራ ፡ ሁሉ ፡ ከዚህ ፡ በሚከተሉት ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማል ።

(፪) በቍጥር ፡ ፺፬ ፡ በተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ መሠረት ፡ ቀጠሮ ፡ ሊሰጥ፡ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፹፫ ። የቀዳሚ ፡ ምርመራ፡ አጀማመር ።**

(፩) ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፹ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ መሠረት ፡ በቀዳሚ ፡ ርምመራ ፡ አድራጊ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነገሩ ፡ እንዲቀርብ ፡ የሚያስፈልግ ፡ መሆኑን ፡ ሲወስን ፡ የውሳኔውን ፡ ግልባጭ ፡ ሥልጣኑ ፡ ለሚፈቅድለት ፡ የወረዳ ፡ ግዛት ፡

ፍርድ ፡ ቤትና ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነ ፡ ጊዜም ፡ ለዚሁ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ይልካል ።

(፪) ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ምርመራው ፡ የሚደረግበትን ፡ ቀን ፡ ወስኖ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ለክሱ፡ ማስረጃ፡ የሚሆኑት ፡ ምስክሮች ፡ እንዲቀርቡለት ፡ መጥሪያ ፡ ያዝለታል ።

(፫) ቀዳሚ፡ ምርመራ፡ በሚደረግበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያለው ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ስለ፡ ክሱ ፡ ክርክሩን ፡ ያመለክታል ።

ቍ ፡ ፹፬ ። የዐቃቤ ፡ ሕግን ፡ ማስረጃ ፡ ስለ ፡ መቀበል ።

የተከሰሰው ፡ ሰው ፡ ራሱ ፡ ሲቀርብ ፡ ወይም ፡ እንዲቀርብ ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ነገሩን ፡ እንዲጀምርና ፡ ምስክሮቹን ፡ እንዲጠራ ፡ ያደርጋል ።

ቍ ፡ ፹፭ ። ተከሳሹ ፡ ቃሉን ፡ ለመስጠት ፡ ፈቃደኛ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ መጠየቅ ።

(፩) የዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ምስክሮች ፡ ከተሰሙና ፡ ቃላቸውም ፡ ከተመዘገበ ፡ በኋላ ፡ ለክሱ ፡ መልስ ፡ ተከሳሹ ፡ ቃሉን ፡ ለመስጠት ፡ ፈቃደኛ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይጠይቀዋል ።

(፪) ቀዳሚ ፡ ምርመራ ፡ የሚያደርገው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ክሱ ፡ የሚያሟግት ፡ ያለመሆኑንና ፡ የተከሳሹን ፡ ጥፋተኛነት ፡ ወይም ፡ ነጻ ፡ መሆን ፡ በዚሁ ፡ በቀዳሚ ፡ ምርመራ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሳይሆን ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚወሰን ፡ መሆኑን ፡ ለተከሳሹ ፡ ይነግረዋል ።

(፫) ቃሉን ፡ እንዲሰጥ ፡ የማይገደድ ፡ መሆኑንና ፡ በፈቃዱ ፡ የሰጠው ፡ ቃል ፡ ግን ፡ በጽሑፍ ፡ ሆኖ ፡ በማስረጃነት ፡ ነገሩ ፡ ሲሰማ ፡ የሚቀርብ ፡ መሆኑን ፡ ለተ ከሳሹ ፡ ይነግረዋል ።

ቍ ፡ ፹፮ ። ተከሳሹ ፡ ስለሚሰጠው ፡ ቃል ።

(፩) ተከሳሹ፡ ቃሉን፡ መስጠት፡ ያልመረጠ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ነገሩ ፡ እንዲሰማ ፡ ለከ ፍተኛው ፡ ፍርድ፡ ቤት፡ ያቀርባል ።

(፪) ተከሳሹ ፡ ቃሉን ፡ መስጠት ፡ የመረጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ቃሉ፡ተጽፎ፡ለተከሳሹ ፡ ተነቦለት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከፈረመበት ፡ በኋላ ፡ በመዝገቡ ፡ ውስጥ ፡ ይቀመጣል።

ቍ ፡ ፹፯ ። ተጨማሪ ፡ ምስክሮች ።

ምስክርነታቸው ፡ ትክክለኛ ፡ ፍርድ ፡ ለመስጠት ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ፡ከታየው ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ያልቈጠራቸውን ፡ ምስክሮች ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ መጥራትና ፡ ማስመስከር ፡ ይችላል ።

BACK



ቊ ፡ ፹፰ ። ማስረጃን ፡ ስለ ፡ መመዝገብ ።

በቊጥር ፡ ፻፵፯ ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ ማስረጃው ፡ መመዝገብ ፡ አለበት ። እንዲሁም ፡ የየአንዳንዱ ፡ ምስክር ፡ ቃል ፡ ለየብቻው ፡ በወረቀት ፡ ላይ ፡ መጻፍ ፡ አለበት ።

ቊ ፡ ፹፱ ። ነገሩ ፡ እንዲሰማ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ።

(፩) ተከሳሹ ፡ ቃሉን ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የሰጠውን ፡ ቃል ፡ በመዝገብ ፡ ከጻፈ፡ በኋላ ፡ የቀዳሚ ፡ ምርመራ ፡ አድራጊ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነገሩን ፡ አጣርቶ ፡ ክሱን፡ ወይም ፡ ክሶቹን ፡ ሳይለይ ፡ ከሳሹ ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲቀርብና ፡ ነገሩ ፡ እንዲሰማ ፡ ያደርጋል ።

(፪) ክሱን፡ ወይም፡ ክሶቹን፡ በዚህ፡ ሕግ፡ ከቊ፡ ፻፱፡ እስከ ፡ ፻፳፪ ፡ በተመለከተው፡ መሠረት ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ በሚያዘጋጀው ፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ ውስጥ ፡ መዘርዘር ፡ አለበት ።

(፫) ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ተከሳሹ ፡ መጥራት ፡ የሚፈልጋቸውን ፡ ምስክሮች ፡ ዝርዝር፡ እስከነአድራሻቸው ፡ እንዲያቀርብ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

ቊ ፡ ፺ ። ምስክሮች ፡ የሚፈርሙት ፡ የራስ ፡ ዋስትና ፡ ወረቀት ።

(፩) ቀዳሚ ፡ ምርመራ ፡ በሚያደርገው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የመሰከሩ ፡ ምስክሮች ፡ ሁሉ ፡ በሚጠሩበት ፡ ቀን ፡ ከዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲቀርቡ ፡ ቀዳሚ ፡ ምርመራ ፡ አድራጊው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የራስ ፡ ዋስትና ፡ ወረቀት ፡ ያስፈርማቸዋል ።

(፪) ማንኛውም ፡ ምስክር ፡ የራስ ፡ ዋስትና ፡ ወረቀት ፡ አልፈርምም ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ፡ ቤት፡ ክሱ፡ እስከሚታይበት፡ ድረስ ፡ ወይም ፡ እቀርባለሁ ፡ ብሎ ፡ የራስ ፡ ዋስትና ፡ ወረቀት ፡ እስኪፈርም ፡ ድረስ ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እንዲቈይ ፡ ማድረግ ፡ ይችላል ።

ቊ ፡ ፺፩ ። ለመዝገብ ፡ ቤቶች ፡ ሹም ፡ የሚላክ ፡ መዝገብ ።

(፩) ተከሳሹ ፡ ወደ፡ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነገሩ ፡ እንዲታይ ፡ ሲላክ፡ዋናው ፡ መዝገብና ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚቀርብ ፡ ማንኛውም ፡ መረጃ ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ቤቶች ፡ ሹም ፡ ይላካሉ ፤ በብዛቱ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ምክንያት ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ ለመላክ፡አስቸጋሪ ፡ የሆነ ፡ ማንኛውም ፡ መረጃ ፡ በፖሊስ ፡ እጅ ፡ ሊቈይ ፡ ይችላል ።

(፪) በፖሊስ ፡ እጅ ፡ የቈዩትንና ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ የተላኩትን ፡ መረጃዎች ፡ የሚገልጽ ፡ ዝርዝር ፡ ከመዝገቡ ፡ ጋራ ፡ ይላካል ።

BACK



(፫) የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የመዝገብ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ ከቀዳሚ፡ መርማሪው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የመጣውን ፡ መዝገብ ፡ ግልባጭ ፡ ማድረግና ፡ ለዐቃቤ ፡ ሕግና ፡ ለተከሳሹ ፡ የመስጠት ፡ አላፊነት ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፺፱ ። በመዝገቡ ፡ ውስጥ ፡ ስለሚገኘው ፡ ዝርዝር ።

(፩) መዝገቡ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የተመለከቱት ፡ ዝርዝሮች ፡ ይገኙበታል ፤

(ሀ) የክሱ ፡ መዝገብ ፡ ቍጥር ፤

(ለ) ወንጀሉ ፡ የተፈጸመበት ፡ ቀን ፤

(ሐ) የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ቀርቦ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የቀረበበት ፡ ቀን ፤

(መ) የክስ ፡ አቤት ፡ ባዩ ፡ እንዳለ ፤ ስምና ፡ አድራሻው ፤

(ሠ) የታወቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የተከሳሹ ፡ ስም ፤ አድራሻ ፡ ሥራውና ፡ ዕድሜው ፤ ዜግነቱ ፤

(ረ) በክስ ፡ ማመልከቻው ፡ የተገለጸው ፡ ወንጀልና ፡ ተገቢነት ፡ ያለው ፡ ሲሆን ፡ ወንጀሉ ፡ የተፈጸመበት ፡ ንብረት ፡ ዋጋና ፡ ወንጀሉ ፡ የተፈጸመበት ፡ ሰው ፡ ልዩ ፡ ሁኔታ ፤

(ሰ) ተከሳሹ ፡ እንዲያዝ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ የተሰጠበት ፡ ቀን ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ መጀመሪያ ፡ ተከሳሹ ፡ የተያዘበት ፡ ቀን ፤

(ሸ) ተከሳሹ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የቀረበበት ፡ ቀን ፤

(ቀ) የዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ስምና ፡ አስፈላጊ ፡ ሲሆን ፡ የተከሳሽ ፡ ጠበቃ ፡ ስም ፤

(በ) ቀጠሮ ፡ የተሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ቀጠሮው ፡ የተሰጠበት ፡ ቀንና ፡ ምክንያት ፤

(ተ) ቀዳሚው ፡ ምርመራ ፡ የተፈጸመበት ፡ ቀን ፤

(ቸ) በቀዳሚው ፡ ምርመራ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተሰጠ ፡ ማንኛውም ፤ ቃል ፤ ተከሳሹ ፡ የሰጠው ፡ ቃል ፡ ጭምር ፤

(ነ) የመከላከያ ፡ ምስክሮች ፡ ዝርዝር ፡ ሊስት ።

(፪) ለዐቃቤ ፡ ሕጉና ፡ ለተከሳሹ ፡ በሚላኩት ፡ የመዝገብ ፡ ግልባጮች ፤ ላይ ፤ እነ ዚሀ ፡ ዝርዝሮች ፡ መገኘት ፡ አለባቸው ።

ቍ ፡ ፻ ። ተከሳሹ ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እንዲቈይ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።

በዋስትና ፡ ወረቀት፡ መልቀቅን፡ የሚመለከት፡ የዚሀ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌ ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ ቀዳሚ ፡ ምርመራ ፡ ያደረገው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ክሱ ፡ እከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እስኪታይ ፡ ድረስ ፡ ተከሳሹ ፡ ማረፊያ ፡ ቤት ፡ እንዲቈይ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

BACK



# አራተኛ ፡ መጽሐፍ ።

## ክሱ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ መሰማት ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

**ቍ ፺፬ ። የቀጠሮ ፡ ቀን ፡ የሚሰጡበት ፡ ምክንያቶች ።**

(፩) ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ወይም ፡ ተከሳሹ ፡ ሲያመለክት ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ፡በራሱ፡ አስተያየት ፡ ትክክለኛ ፡ ፍርድ ፡ ለመስጠት ፡ የሚረዳ ፡ ከሆነ ፡ ክሱ ፡ በሚሰማ በት ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ቀጠሮ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

(፪) በተለይም ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በተዘረዘሩት ፡ ምክንያቶች ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ቀጠሮ ፡ ሊሰጥ ፡ አይቻልም ።

(ሀ) ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፤ የግል ፡ ከሳሹ ፡ ወይም ፡ ተከሳሹ ፡ በበቂ ፡ ምክንያት ፡ ሳይቀ ርቡ ፡ የቀሩ ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡

(ለ) የዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ወይም ፡ የተከሳሹ ፡ ምስክሮች ፡ ሳይቀርቡ ፡ የቀሩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡

(ሐ) በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሚፈረድ ፡ ነገር ፡ ቀዳሚ ፡ ምርመራ ፡ ያልተ ደረገበት፡ሆኖ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ለምርመራ ፡ ጊዜ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ሲሆን ፤ ወይም ።

(መ) ተጨማሪ ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ አስፈላጊ ፡ ሲሆን ፤ ወይም ፡

(ሠ) ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ወይም ፡ ተከሳሹ ፡ እንደሚቀርብ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ሊገምት ፡ የማይችለው ፡ ወይም ፡ እንደሚቀርብ ፡ ያላሰበው ፡ አዲስ ፡ ማስረጃ ፡ በድን ገት ፡ የቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡

(ረ) የክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ በተለወጠ ፡ ወይም ፡ በተጨመረ ፡ ጊዜ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ፡ ወይም ፡ ተከሳሹ ፡ ክሱን ፡ ወይም ፡ መከላከያውን ፡ እንደ፡ገና ፡ ለማመዛዘን ፡ ጊዜ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ሲሆን ፤ ወይም ፡

(ሰ) ተከሳሹ ፡ የክሱ ፡ ወይም ፡ የቀዳሚው ፡ ምርመራ ፡ መዝገብ ፡ ግልባጭ፡ያልደ ረሰው፡ወይም ፡ የደረሰው ፡ ክሱ ፡ የሚሰማበት ፡ ቀን ፡ አቅራቢያ ፡ በመሆኑ ፡ የሚገባውን ፡ መከላከያ ፡ ለማቅረብ ፡ ጊዜ ፡ ያጠረው ፡ ሲሆን ፤ ወይም ፡

(ሸ) የነገሩ ፡ መሰማት ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ክሱን፡እንዲጀምር ፡ ፈቃድ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ሲሆን ፤ ወይም ፡

(ቀ) በሌላው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የቀረቡ ፡ ክሶች ፡ በመጀመሪያ ፡ ውሳኔ ፡ ካላገኙ ፡ በቀር ፤ በተሰማው ፡ ነገር ፡ ውሳኔ ፡ የማይሰጥ ፡ ሲሆን ፤ ወይም ፡

(በ) የተከሳሽን ፡ አእምሮ ፡ ትክክለኛነት ፡ በልዩ ፡ ዐዋቂ ፡ መወሰን ፡ የሚያስፈልገው ፡ ሲሆን ፤ ወይም ፡

(ተ) ተከሳሹ ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በጥበቃ ፡ ሥር ፡ እንዲቈይ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ሆኖ ፡ ሲያገኘው ፤ ወይም ፡

(ቸ) የነገሩ ፡ መሰማት ፡ በአንድ ፡ ቀን ፡ ለመፈጸም ፡ የማይቻል ፡ በመሆኑ ፡ ለሚቀጥለው ፡ ቀን ፡ የሚቀጠር ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

(፫) በ (ሀ) እና ፡ ከ (ረ) እስከ ፡ (ሸ) ድረስ ፡ ባሉት ፡ ምክንያቶች ፡ ከአንድ ፡ ሳምንት ፡ የበለጠ ፡ ቀጠሮ ፡ አይሰጥም ።

## ቍ ፡ ፺፭ ። አዲስ ፡ ቀጠሮና ፡ መጥሪያዎች ።

(፩) በቍ ፡ ፺፬ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፫ ፡ የተመለከተው ፡ እንደ፡ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ የነገሩ፡ መሰማት ፡ የሚቀጠረው ፡ ለቀጠሮ ፡ ምክንያት ፡ የሆነውን ፡ ጕዳይ ፡ ለመፈጸም ፡ በቂ ፡ እስከሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) በዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ወይም ፡ በተከሳሹ ፡ ጥፋት ፡ ሳይሆን ፡ ቀጠሮ ፡ የተሰጠበት፡ ምክንያት ፡ ሳይፈጸም ፡ የቀረ ፡ እንደሆን ፡ ያንኑ ፡ ያህል ፡ ወይም ፡ አጭር ፡ ቀጠሮ ፡ ይሰጣል ።

(፫) በቍ ፡ ፺፬ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፪ ፡ (ሐ) እና ፡ ከ (ቀ) እስከ ፡ (ተ) በተጻፈው ፡ መሠረት ፡ የነገሩ ፡ መሰማት ፡ ከተቀጠረ ፡ በኋላ ፡ ቀጠሮ ፡ የተሰጠበት ፡ ምክንያት ፡ ሲፈጸም ፡ ባለጕዳዮቹና ፡ ምስክሮቹ ፡ እንዲቀርቡ ፡ አዲስ ፡ መጥሪያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይሰጣል ።

## ቍ ፡ ፺፮ ። የቀጠሮ ፡ ውጤት ።

(፩) ቀጠሮ ፡ በተሰጠ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቀጠሮ ፡ የተሰጠበት ፡ ምክንያት ፡ እንዲፈጸም ፡ አስፈላጊውን ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ። ይኸውም ፡ በቍ ፡ ፴፫ ፤ ፶፫ ፡ እና፡ ፻፳፭ ፡ በተመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፡ ከሚሰጠው ፡ የመያዝ ፡ ትእዛዝ ፡ ጭምር ፡ ነው ።

(፪) በቍጥር ፡ ፺፬ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፪ ፡ (በ) ወይም ፡ (ተ) መሠረት ፡ ቀጠሮ፡ሲሰጥ፤ ተከሳሹ ፡ አእምሮውን ፡ ልዩ ፡ ዐዋቂ ፡ ሊመረምረው ፡ በሚቻልበት ፡ ስፍራ ፡ ተይዞ ፡ እንዲቈይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

## ቍ ፡ ፺፯ ። መረጃዎች ፡ (ኤግዚቢቶች) ።

መረጃዎች ፡ (ኤግዚቢቶች) ፡ ሁሉ ፡ ላይና ፡ በቍ ፡ ፴ ፡ መሠረት ፡ ምስክር ፡ በሰጠው፡ ቃልና፡ በቍጥር፡ ፳፯፡ መሠረት፡ ተከሳሹ ፡ የሰጠው ፡ ቃል ፡ ጭምር፡ ላይ፡

BACK



የፍርድ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ቊጥርና ፡ ምልክት ፡ ያደርግባቸዋል ። እነዚህን ፡ መረጃዎች ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ በተጠበቀ ፡ ስፍራ ፡ ያስቀምጣቸዋል ፤ ያለ ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ ትእዛዝ ፡ አይወጡም ።

ቍ ፡ ፺፰ ። በመዝገቡ ፡ ውስጥ ፡ መኖር ፡ ስለሚገባው ፡ ነገር ።

(፩) በፍርድ ፡ ቤት ፡ ነገሩ ፡ የሚመረመርበትን ፡ መዝገብ ፡ ዳኞች ፡ ይፈርሙበታል ። በመዝገቡም ፡ ላይ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱት ፡ ሊኖሩበት ፡ ያስፈልጋል ።

(ሀ) የክሱ ፡ ወይም ፡ የአቤቱታው ፡ ግልባጭ ፤

(ለ) የቀዳሚው ፡ ምርመራ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፤ ያለ ፡ እንደ፡ ሆነ ፤

(ሐ) የመያዝ ፡ ትእዛዝ ፡ የተሰጠበት ፡ ቀን ፡ ( ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ) ፤ ወይም ፡ ተከሳሹ ፡ መጀመሪያ ፡ የተያዘበት ፡ ቀን ፤

(መ) ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ተከሳሹ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የቀረበበት ፡ ቀን ፤

(ሠ) ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ወይም ፡ የግል ፡ ከሳሹ ፡ ያቀረበው ፡ የክስ ፡ ማመልከቻና ፡ በክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ የተለወጠው ፡ ወይም ፡ የተጨመረው ፡ ነገር ፡ እንዲሁም ፡ የግል ፡ ከሳሽ ፡ ያቀረበው ፡ ክስ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፤ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ የፈቀደበት ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ አብሮ ፡ ይያያዛል ፤

(ረ) ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ወይም ፡ የግል ፡ ከሳሹ ፡ የሰጠው ፡ የክስ ፡ መክፈቻ ፡ ንግግር ፡ ግልባጭ ፤

(ሰ) የተከሳሹ ፡ እምነት ፡ ክደት ፤

(ሸ) ምስክሮች ፡ የሰጡት ፡ ቃል ፡ በሙሉ ፤ መስቀልያና ፡ ዳግመኛ ፡ ጥያቄ ፡ ጭምር ፤

(ቀ) ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ወይም ፡ ተከሳሹ ፡ የተቃወመው ፡ ማንኛውም ፡ ነገር ፡ እና ፡ ለተቃወመው ፡ ጉዳይ ፡ የተሰጠው ፡ ውሳኔ ፤ ወዲያውኑ ፡ በመዝገብ ፡ ይጻፋል ። ምስክር ፡ ቃሉን ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ ሲሆን ፡ የምስክሩን ፡ ቃል ፡ መስጠት ፡ አቁሞ ፡ እዚሁ ፡ ቦታ ፡ መቃወሚያው ፡ መጻፍ ፡ አለበት ፤

(በ) የቀረበው ፡ መረጃ ፡ የተሰጠው ፡ ቊጥርና ፡ ያቀረበው ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ወይም ፡ ተከሳሹ ፡ መሆኑ ፡ ተለይቶ ፡ ይጻፋል ፤

(ተ) ስለ ፡ ሕግ፡ የቀረበ ፡ ክርክር ፡ እና ፡ የተሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ይኸውም ፡ በመዝገቡ ፡ የሚጻፈው ፡ ክርክሩ ፡ በተነሣበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ፤

(ቸ) የተሰጠውን ፡ ቀጠሮ ፡ ሁሉና ፡ የክሱ ፡ መሰማት ፡ እንዲቀጠር ፡ የተደረገበት ፡ ቀንና ፡ ለቀጠሮው ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ጉዳይ ፡ ጭምር ፤

(ነ) ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ወይም ፡ ተከሳሹ ፡ ይግባኝ ፡ ለማለት ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ለመሆኑ ፡ መነገራቸውን ፡ ነው ።

(፪) ነገሩ፡ በሚሰማበት ፡ በማንኛውም ፡ ቀን ፡ መዝገቡ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በተመለከተው ፡ ዐይነት ፡ ይጀመራል ፤

BACK



(ሀ) የነገሩ ፡ ስምና ፡ ቍጥር ፤
(ለ) ቀኑና ፡ ሰዓቱ ፤
(ሐ) የዐቃቤ ፡ ሕጉና ፡ የተከሳሹ ፡ ጠበቃ ፡ ስም ፤
(መ) የዳኞቹ ፡ ስም ፤

(፫) ነገሩ፡ በሚሰማበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ነገሩ ፡ ምን፡ ሰዓት ፡ እንደ፡ተቋረጠና ፡ የተቀጠረበት ፡ ቀንና ፡ ሰዓት ፡ መጻፍ ፡ አለበት ።

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

ነገሩ ፡ የሚሰማበት ፡ ስፍራ ።

ቍ ፡ ፺፱ ። ነገሩ ፡ የሚሰማበት ፡ ደንበኛ ፡ ስፍራ ።

ማንኛውም ፡ ወንጀል ፡ በተፈጸመበት ፡ ስፍራ ፡ሥልጣኑ ፡ በሚፈቅድለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይታያል ።

ቍ ፡ ፻ ። ተከሳሹን ፡ ወንጀሉን ፡ በፈጸመበት ፡ ስፍራ ፡ ወይም ፡ የወንጀሉ ፡ ውጤት ፡ በታወቀበት ፡ ስፍራ ፡ ስለ ፡ መክሰስ ።

አንድ ፡ ሰው ፡ በማንኛውም ፡ ምክንያት ፡ የፈጸመው ፡ ማንኛውም ፡ ወንጀልና ፡ የወንጀሉ ፡ ውጤት ፡ ሲገኝ ፡ ይህ ፡ ወንጀል ፡ በተፈጸመበት ፡ ስፍራ ፡ ሥልጣን ፡ ባለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ የወንጀሉ ፡ ውጤት ፡ በታወቀበት ፡ ስፍራ ፡ በሚገኘው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይከሰሳል ።

ቍ ፡ ፻፩ ። ከአንድ፡ ወንጀል ፡ ጋራ ፡ ነክነት ፡ ስላለው ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ወንጀል ፡ የሚቈጠር፡ ተግባር፡ ክሱ፡ የሚታይበት፡ ስፍራ ።

ከሌላው፡ወንጀል፡ ጋራ፡ ግንኙነት፡ በመደረጉ፡ እንደ፡ አንድ፡ ወንጀል፡ የሚቈጠር ፡ ተግባር ፤ በክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ የሚጠቀሰው ፡ የመጀመሪያው ፡ የወንጀል ፡ ተግባር ፡ ክስ ፡ የሚታየው ፡ ከሁለቱ ፡ አንዱ ፡ ወንጀል ፡ በተፈጸመበት ፡ ቦታ ፡ ለማየት ፡ ሥልጣን ፡ ባለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፻፪ ። ወንጀል፡ የተሠራበት ፡ ቦታ ፡ ያልታወቀ ፡ ሲሆን ፤ ክሱ ፡ የሚታይበት ፡ ስፍራ።

(ሀ) ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ስፍራዎች ፡ ውስጥ ፡ በየትኛው ፡ ስፍራ ፡ ወንጀሉ ፡ እንደ፡ ተፈጸመ ፡ ያልተረጋገጠ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፤ ወይም ፡

(ለ) ወንጀሉ ፡ በከፊል፡ አንድ ፡ ስፍራ ፡ በከፊል ፡ ደግሞ ፡ በሌላ ፡ ስፍራ ፡ የተፈጸመ ፡ ሲሆን ፤ ወይም ፡

(ሐ) ወንጀሉ ፡ ከአንድ ፡ በበለጡ ፡ ስፍራዎች ፡ መፈጸሙ ፡ ሲቀጥል ፤ ወይም ፡

BACK



(መ) በልዩ፡ ልዩ ፡ ስፍራዎች ፡ የተፈጸሙ ፡ አያሌ ፡ የወንጀል ፡ ተግባሮች ፡ የተሠሩ ፡ ሲሆን ፤ ሥልጣን ፡ ባለው ፡ በአንዱ ፡ ስፍራ ፡ በሚገኘው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነገሩ ፡ ሊሰማ ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፻፫ ። በጕዞ ፡ ላይ ፡ የተፈጸመ ፡ ወንጀል ።

ወንጀለኛው፡ በጕዞው ፡ ላይ ፡ ሳለ ፡ ወንጀል፡ የፈጸመ ፡ እንደ፡ሆነ ፤ ወንጀለኛው ፡ ወይም ፡ የተበደለው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ወንጀል ፡ የተፈጸመበት ፡ ነገር ፡ በጕዞው ፡ በሚያልፍበት ፡ ስፍራ ፡ ውስጥ ፡ ወንጀሉን ፡ ለማየት ፡ ሥልጣን ፡ ባለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወንጀለኛው ፡ ይከሰሳል ።

ቍ ፡ ፻፬ ። በኢትዮጵያ ፡ መርከብ፡ ወይም፡ አይሮፕላን፡ ላይ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ውጭ ፡ የተፈጸመ ፡ ወንጀል ፡ የሚታይበት ፡ ስፍራ ።

በኢትዮጵያ ፡ መርከብ፡ ወይም፡ አይሮፕላን ፡ ላይ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ውጭ፡ የተፈጸመ ፡ ወንጀል፡ በኢትዮጵያ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ እንደ፡ ተፈጸመ ፡ ይቈጠራል ።

ቍ ፡ ፻፭ ። የመሰየም ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ።

ስለ ፡ መሰየም ፡ የሚቀርበው ፡ ጥያቄ ፤ እንዲሰረዝ ፡ የተጠየቀውን ፡ የቅጣት ፡ ፍርድ ፡ ለሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይቀርባል ።

ቍ ፡ ፻፮ ። ክሱን ፡ ወደሌላ ፡ ስፍራ ፡ ስለ ፡ ማዛወር ።

ነገሩ ፡ ከመሰማቱ፡ በፊት፡ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ወይም ፡ ተከሳሹ ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ፡ ቤት ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለውን ፡ በማመልከት ፤

(ሀ) የበታች ፡ የወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይህንን ፡ ነገር ፡ ያለ ፡ አድሎ ፡ በትክክል ፡ ለመስማት ፡ የማይችል ፡ መሆኑን ፡ ወይም ፡

(ለ) ያልተለመደ፡አስቸጋሪ፡የሕግ፡ክርክር፡የሚነሣ፡ መስሎ፡ በታየ፡ ጊዜ፤ወይም፡

(ሐ) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፡ የሚሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ለሁለቱ ፡ ተከራካሪ ፡ ወገኖች ፡ ወይም ፡ ለምስክሮች ፡ ምቹ ፡ መሆኑን ፤ ወይም ፡

(መ) ይህ፡ ትእዛዝ፡ ቢሰጥ፡ ባጭር፡ ጊዜ፡ ውስጥ፡ ትክክለኛ፡ ፍርድ፡ ለመስጠት፡ የሚያስችል ፡ መሆኑን ፤ ወይም ፡ በዚህ፡ ሕግ፡ ድንጋጌ፡ መሠረት፡ አስፈላጊ ፡ ከሆነ ፤ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ ሲታየው ፤

(፩) ማንኛውም ፡ ወንጀል ፡ በዚህ፡ ምዕራፍ፡ ከቍጥር፡ ፺፱፡ እስከ፡ ፻፬፡ በተጻፈው፡መሠረት፡ ሥልጣን፡ ያልተሰጠው፡ ቢሆንም፡ በሌላው፡ ረገድ፡ ግን፡ ይህንኑ ፡ ዐይነት ፡ ወንጀል ፡ ለማየት ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ማናቸውም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነገሩን ፡ እንዲያይ ፤

(፪) ተከሳሹ ፡ በዚሁ ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ፡ ቤት፡ ቀርቦ፡ ነገሩ ፡ እንዲሰማ ፤ ትእዛዝ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ። የሚሰጠውም ፡ ትእዛዝ ፡ ይግባኝ ፡ የሌለው ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፻፯ ። ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ነገሩ ፡ የሚታይበትን ፡ ስፍራ ፡ ስለ ፡ መምረጡ ።

ከቍ ፡ ፻ ፡ እስከ ፡ ፻፭ ፤ በቍጥር ፡ ፻፲፯ ፡ ወይም ፡ ፻፲፯ ፡ በተጻፈው ፡ መሠረት ፡ በሚቀርቡ፡ ነገሮች ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ክሱ፡ የሚቀርብበትን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይወስናል ። በዚህም ፡ ውሳኔ ፡ መሠረት ፡ ክሱ ፡ የቀረበለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነገሩን ፡ ለመስማት ፡ ሥልጣን ፡ ይኖረዋል ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ክስ ፡ ማመልከቻ ።

ቍ ፡ ፻፰ ። መሠረቱ ።

(፩) የደንብ ፡ መተላለፍ፡ ከሆነ ፡ ክስ፡ በቀር፤ ማንም፡ ሰው፡ በዚሁ፡ ምዕራፍ ፡ መሠረት ፡ ክስ ፡ ሳይቀርብበት ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ነገሩ ፡ እንዲሰማ ፡ አይደረግም ።

(፪) የሚቀርበው ፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፤

(ሀ) በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤትም፡ ሆነ፡ ወይም ፡ በዝቅተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ የቀረበ ፡ ሲሆንና ፤

(ለ) በግል ፡ ከሳሽነት፡ ክስ፡ እንዲያቀርብ ፡ በተፈቀደለት ፡ የግል ፡ ከሳሽ ፡ የቀረበ፡ ሲሆን ፤ የክሱ ፡ ማመልከቻ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት፡ መዘጋጀት ፡ አለበት ።

(፫) አካለመጠን ፡ ባላደረሱ ፡ ወጣቶች ፡ ላይ ፡ የሚቀርብ፡ ክስ፡ በዚህ፡ ሕግ፡ በቍ፡ ፻፸፪ ፡ መሠረት፡ ሌላ ፡ ትእዛዝ፡ ካልተሰጠ ፡ በቀር ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ መሠረት ፡ አይፈጸምም ።

ቍ ፡ ፻፱ ። የክስ፡ ማመልከቻ፡ ስለ፡ ማዘጋጀት፤ ስለ፡ ማቅረብና፡ ለተከሳሹ፡ ስለ፡ መስጠት።

(፩) ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ የፖሊስ፡ ምርመራ፡ መዝገብ፡ (ቍ ፡ ፴፯) ፡ ወይም ፡ የቀዳሚ ፡ ምርመራ፡ ፍርድ፡ ቤት፡ መዝገብ፡(ቍ፡ ፺፩)፡ በደረሰው፡ በዐሥራ፡ አምስት፡ ቀን፡ ጊዜ፡ ውስጥ፡ በፖሊስ ፡ የምርመራ ፡ መዝገብ ፡ ወይም ፡ በቀዳሚ ፡ ምርመራው ፡ መዝገብ ፡ መሠረት ፡ የሚገባ ፡ የመሰለውን፡ ክስ ፡ አዘጋጅቶ፡ ሥልጣን፡ ላለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያቀርባል ።

(፪) ነገሩ ፡ በከፍተኛው፡ ፍርድ፡ ቤት ፡ መሰማቱ ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ የቀዳሚ ፡ ምርመራ፡ ፍርድ፡ ቤት፡ መዝገብን፡ ዐቃቤ፡ ሕጉ፡ ተመልክቶ፡ ነገሩ፡ ሊሰማ፡ የሚገባው፡ በዝቅተኛ፡ ፍርድ፡ ቤት፡ መስሎ፡ የታየው፡ እንደሆን፡ ቀዳሚ፡ ምርመራ፡ አድራጊው ፡ ፍርድ፡ ቤት፡ የሰጠው፡ ውሳኔ ፡ ቢኖርም ፡ እንኳን ፡ ተገቢ ፡ የመሰለውን፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ አዘጋጅቶ ፡ ሥልጣን ፡ ላለው ፡ ዝቅተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያቀርባል ።

(፫) ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ የቀዳሚ፡ ምርመራ፡ፍርድ፡ቤት፡መዝገብ፡ሲመረምር፡የተፈጸሙት፡

ወንጀሎች ፡ በከፊል ፡ የፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፤ በከፊል ፡ ደግሞ ፡ የዝቅተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ ሆኖ ፡ ሲያገኝ ፡ ተገቢ ፡ የመሰለውን ፡ ክስ ፡ አዘጋጅቶ ፡ ሁሉንም ፡ ወንጀሎች ፡ የማየት ፡ ሥልጣን ፡ ላለው ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያቀርባል ።

(፬) የክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ ግልባጭ ፡ ለተከሳሹ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ በነጻ ፡ ይሰጠዋል ።

ቍ፡ ፻፲። የክሱን፡ ማመልከቻ፡ ሥልጣኑ፡ ላልሆነ፡ ፍርድ፡ ቤት፡ በስሕተት፡ ስለ፡ማቅረብ።

ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ የክሱን ፡ ማመልከቻ ፡ ሥልጣን ፡ ለሌለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ፍርድ፡ ቤቱ፡ የክሱን ፡ ማመልከቻ ፡ አልቀበልም ፡ ማለት ፡ አለበት ። ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ የክሱን ፡ ማመልከቻ ፡ ሥልጣን ፡ ላለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲያቀርብ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉን ፡ ያዘዋል ። ይህነኑም ፡ በክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።

ስለ፡ ሆነም ፡ የዝቅተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ብቻ ፡ በወንጀለኛው ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቍ ፡ ፯፻፴ ፡ መሠረት ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ክስ ፡ ሲያቀርብ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ክሱን ፡ አልቀበልም ፡ ማለት ፡ የለበትም ። እንደዚህ፡ ያለውም፡ ክስ፡ ሲቀርብለት፡ ፍርድ፡ ቤቱ፡ ክሱን ፡ ለማየት ፡ ሥልጣን፡ አለው ።

ቍ ፡ ፻፲፩ ። የክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ ዐይነትና ፡ የሚጻፍበት ።

(፩) ማንኛውም፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ ቀንና ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ የተጻፈበትና፡ የተፈረመበት ፡ እንዲሁም ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የተዘረዘሩት፡ እንዲገለጹበት ፡ ያስፈልጋል ።

(ሀ) የተከሳሹ ፡ ስም ፤

(ለ) ተከሳሹ ፡ የተከሰሰበትን ፡ ወንጀል፡ እንዲሁም ፡ የወንጀሉ ፡ መሠረታዊ ፡ ነገርና ፡ ሁኔታዎች ፤

(ሐ) ወንጀሉ ፡ የተፈጸመበት ፡ ጊዜና ፡ ስፍራ ፡ ተገቢ ፡ በሆነ ፡ ጊዜም ፡ የተበደለው ፡ ሰው ፡ ስም ፡ ወይም ፡ ወንጀሉ ፡ የተፈጸመበት ፡ ንብረት ፤

(መ) ተከሳሽ ፡ ወንጀሉን ፡ በመፈጸም ፡ ተላልፏል ፡ የተባለበት ፡ ሕግና ፡ የሕጉን ፡ ቍጥር ፤

(፪) ማንኛውም፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ ከዚህ ፡ ሕግ ፡ ተያይዞ ፡ በሚገኘው ፡ በሁለተኛው ፡ ሠንጠረዥ፡ ዐይነት ፡ ወይም ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ከዚሁ ፡ ጋራ፡ ተመሳሳይ ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፡ መዘጋጀት ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፻፲፪ ። የወንጀሉ ፡ ዝርዝር ፡ ሁኔታ ።

ተከሳሹ ፡ የተከሰሰበትን ፡ ወንጀል ፡ ለይቶ ፡ ዐውቆ ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ እንዲችል ፡ እያንዳንዱ ፡ ክስ ፡ ወንጀሉንና ፡ ሁኔታውን ፡ በዝርዝር ፡ መግለጽ ፡ አለበት ። ስለ ፡ ወንጀሉና ፡ ስለ ፡ ሁኔታው ፡ የሚሰጠው ፡ ዝርዝር ፡ መግለጫ ፡ ወንጀ

ለኛው ፡ የፈጸመው ፡ ተግባር ፡ ወንጀል ፡ ከሚያደርገው ፡ ሕግ ፡ አነጋገር ፡ ጋራ፡ በጣም ፡ የተቀራረበ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፻፲፫ ። የተፈጸመው ፡ ወንጀል ፡ ዐይነት ፡ የሚያጠራጥር ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ።

(፩) ለተፈጸመው፡ ተግባር፡ ወይም ፡ ተግባሮች፡ የሚቀርበው፡ ማስረጃ፡ ከአያሌ ፡ ወንጀሎች ፡ ውስጥ ፡ የትኛውን ፡ እንደሚያረጋግጥ ፡ ለማወቅ ፡ ባጠራጠረ ፡ ጊዜ ፡ ተከሳሹ ፡ ለመፈጸሙ ፡ ይበልጥ ፡ ማስረጃ ፡ ያለ ፡ በሚመስለው ፡ ወንጀልና ፡ እንዲሁም ፡ በተጨማሪ ፡ በማስረጃው ፡ ሊረጋገጥ ፡ ይቻላል ፡ በሚባሉት ፡ ወንጀሎች ፡ ሁሉ ፡ ይከሰሳል ።

(፪) የቀረበው፡ ማስረጃ ፡ ተከሳሹ ፡ በተጨማሪ ፡ የሚያስከስሰው ፡ ወንጀል ፡ ከሆነና፡ ፍርድ፡ ቤቱም ፡ ወንጀሉን ፡ ለማየት ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ከሆነ ፡ ክስ ፡ ባይቀርብበትም ፡ በዚሁ ፡ ወንጀል ፡ በተከሳሹ ፡ ላይ ፡ ለመፍረድ ፡ ይቻላል ። ይኸውም ፡ ተጨማሪው ፡ ከክሱ ፡ ውስጥ ፡ ካለው ፡ ወንጀል ፡ አነስተኛ ፡ ወንጀል ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ነው ።

(፫) ፍርድ፡ ቤቱ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ፡ በቍ ፡ ፺ ፡ እና ፡ ፱ ፡ መሠረት ፡ ከመፈጸም ፡ በዚህ ፡ ቍጥር ፡ ድንጋጌ ፡ አይታገድም ።

ቍ ፡ ፻፲፬ ። ቅጣትን ፡ የሚያከብዱ ፡ ወንጀሎች፡ ክስ ፡ አቀራረብና ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ።

(፩) ተከሳሹ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ በፈጸማቸው ፡ ወንጀሎች ፡ ምክንያት ፡ ቅጣትን ፡ በሚያከብድ፡ ወንጀል ፡ የሚከሰስ ፡ ሲሆን ፤ የሚከሰሰው ፡ ቅጣቱ ፡በማይከብድበት ፡ ወንጀል፡ ሆኖ ፡ ክሱ ፡ የሚታየው ፡ ቅጣትን ፡ የሚያከብዱ ፡ ወንጀሎችን ፡ ለማየት ፡ ሥልጣን ፡ ባለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ።

(፪) ተከሳሹ፡ ቅጣቱ፡ በማይከብድበት፡ ወንጀል ፡ ጥፋተኛ፡ ሆኖ ፡ ከተገኘ ፡ በተከሳሹ፡ ላይ፡ ያስቀጣዋል፡ተብሎ፡ የጥፋተኛነት፡ ውሳኔ፡ ከተሰጠ፡ በኋላና፡ ከቅጣቱ፡ ውሳኔ፡ በፊት፡ ተከሳሹ፡ ከዚህ፡ ቀደም፡ ጥፋተኛ፡ የሆነበት፡ ክሱ ፡ በሚሰማበት ፡ ጊዜ ፡ የቀረበ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ቅጣቱ ፡ በሚከብድበት ፡ ወንጀል ፡ ያስቀጣው ፡ ነበር ፡ የሚያሰኘው ፡ ከሆነ ፤ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በወንጀል ፡ የተቀጣበትን ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፤ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ማስረዳት ፡ አለበት ። ቅጣቱ ፡ በሚከብድበት ፡ ወንጀል ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ እንደ፡ተገኘ ፡ ተቈጥሮ ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጣል ። በዚሁም ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የጥፋተኛነትን ፡ ውሳኔ ፡ ይለውጣል ።

ቍ ፡ ፻፲፭ ። በወንጀል ፡ የተከሰሰን ፡ ሰው ፡ ሙከራ ፡ በማድረግ ፡ ወይም ፡ በረዳትነት ፡ ወይም ፡ በአነሣሽነት ፡ ጥፋተኛ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ በወንጀል፡ የተከሰሰ ፡ ሲሆን ፡ በተጨማሪ ፡ በሙከራ ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ የቀረበበት ፡ ባይሆንም ፡ በሙከራ ፡ ወንጀል ፡ ለመፍረድ ፡ ይቻላል ።

BACK



(፪) አንድ ፡ ሰው ፡ ወንጀል ፡ ሠርተሃል ፡ ተብሎ ፡ በዋና ፡ ወንጀለኛነት ፡ ቢከሰ ሰም፡ በአነሣሽነት፡ ወይም፡ በአባሪነት፡ ክስ፡ የቀረበበት፡ ባይሆንም፡ በወንጀሉ ፡ አነሣሽነት ፡ ወይም ፡ በአባሪነት ፡ ለመፍረድ ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፻፲፮ ። ክሱ ፡ ከአንድ ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ።

(፩) በአንድ፡ ተከሳሽ ፡ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ በክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ ብዙ ፡ ክሶች ፡ ሊቀ ርቡበት ፡ ይችላሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እየአንዳንዱ ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ ለየብቻው ፡ መገለጽ ፡ አለበት ።

(፪) የቀረቡበት ፡ ክሶች፡ በአንድነት ፡ መታየት ፡ አለባቸው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የክሶቹ ፡ በአንድነት ፡ መታየት፡ በተከሳሹ ፡ መከላከያ ፡ ችግር ፡ የሚያመጣበት ፡ የመሰለ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ክሶቹ ፡ ተነጣጥለው፡ለት ፡ ለየብቻ ፡ እንዲሰሙ ፡ ማዘዝ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፻፲፯ ። በአንድ ፡ ላይ ፡ የሚቀርብ ፡ ክስ ።

(፩) በምንም ፡ ዐይነት ፡ ደረጃ ፡ ወይም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ጊዜ ፡ ለአንድ ፡ ወንጀል ፡ ወይም ፡ ወንጀሎች ፡ ተካፋይ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ በአንድነት ፡ ተከሰው ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ነገራቸው ፡ ይሰማል ።

(፪) ትክክለኛ፡ ፍርድ ፡ ለመስጠት ፡ ጠቃሚ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ነገሩ ፡ ተለያይቶ ፡ እን ዲሰማ ፡ ከማድረግ ፡ ፍርድ፡ ቤቱን ፡ የዚህ ፡ ቍጥር ፡ ድንጋጌ ፡ አይከለክለውም ።

(፫) አያሌ ፡ ሰዎች ፡ በአንድ፡ የወንጀል ፡ ሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ የፈጸሙት ፡ የወንጀል ፡ ተግባር ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቢሆንም ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በአንድ ፡ ላይ ፡ ሊከ ሰሱ ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፻፲፰ ። የመሳሳት ፡ ውጤት ።

ስለ ፡ ወንጀሉ፡ ወይም፡ ስለ፡ወንጀሉ፡ አስፈላጊ፡ ዝርዝር ፡ በክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ስሕተት ፡ ሲደረግ ፡ ወይም ፡ ወንጀሉ ፡ ወይም ፡ ስለ፡ወንጀሉ ፡ አስፈላጊ ፡ ዝርዝር፡ ሳይጠቀስ፡ የቀረ፡ ሆኖ፡ ሲገኝ፡ የወንጀሉ፡ መሠረታዊ፡ ነገር፡ ሆኖ፡መቈ ጠር ፡ የለበትም ። ነገር፡ ግን፡ ስሕተቱ፡ ወይም፡ ሳይጠቀስ፡ የቀረው ፡ አስፈላጊ ፡ ነገር ፡ ካልሆነ ፡ ወይም ፡ ስሕተቱ ፡ ወይም ፡ ሳይጠቀስ ፡ የቀረው ፡ ተከሳሹን ፡ ያሳሳተው፡ ካልሆነ፡ ወይም፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ትክክለኛ ፡ ፍርድ ፡ መስጠት ፡ የማይቻል ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ስሕተት ፡ ወይም ፡ ሳይጠቀስ ፡ የቀረው ፡ ነገር ፡ ክሱን ፡ ዋጋ ፡ አያሳጣውም ።

ቍ ፡ ፻፲፱ ። ክሱን ፡ ስለ ፡ መለወጥ ፡ ወይም ፡ በክሱ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ መጨመር ።

(፩) በተከሳሹ ፡ ላይ ፡ በቀረበው ፡ ክስ ፡ ዋና፡ ስሕተት ፡ የተገኘ ፡ ሲሆን፡ ወይም ፡ ያልተጠቀሰ፡ ነገር ፡ ሲገኝና፡ ይኸውም ፡ ተከሳሹን ፡ የሚያሳስት ፡ ወይም ፡ ያሳ ሳት፡ በመሰለ ፡ ጊዜ ፡ ፍርዱ ፡ ከመስጠቱ፡ በፊት ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ በራሱ፡

BACK



አስተያየት ፡ ወይም ፡ ማመልከቻ ፡ በቀረበለት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ ክሱ ፡ እንዲለወጥ ፡ ወይም ፡ እንዲጨመር ፡ ወይም ፡ አዲስ ፡ ክስ ፡ እንዲዘጋጅ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፪) ክሱ ፡ በተለወጠ ፡ ጊዜ ፤ በተጨመረ ፡ ወይም ፡ አዲስ ፡ ክስ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ለተከሳሹ ፡ ይነበብለትና ፡ እንዲረዳው ፡ ይደረጋል ።

(፫) በቍጥር፡ ፻፲፰፡ መሠረት ፡ እንደ፡ ተመለከተው፡ በተደረገ፡ ስሕተት ፡ ወይም ፡ ሳይጠቀስ ፡ የቀረ ፡ ነገር ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ በዚህ ፡ ቍጥር ፡ መሠረት፡ ይፈጸማል ።

## ቍ ፡ ፻፳ ። የክስ ፡ መለወጥ ፡ ወይም ፡ የመጨመር ፡ ውጤት ።

(፩) ክሱ፡ በተለወጠ ፤ በተጨመረ ፡ ወይም ፡ አዲስ ፡ ክስ ፡ በተዘጋጀ ፡ ጊዜ ፡ ተከሳሹ ፡ በዚሁ ፡ ክስ ፡ ነገሩ ፡ እንዲሰማ ፡ ዝግጁ ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይጠይቀዋል ።

(፪) ተከሳሹ ፡ ዝግጁ ፡ አይደለሁም ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተከሳሹ ፡ የሰጠውን ፡ ምክንያት ፡ ይመረምራል ። ክሱ ፡ ወዲያውኑ ፡ ቢቀጥል ፡ የተከሳሹ ፡ የመከላከል፡ መብት፡ የማይነካ፡ መስሎ፡ ለፍርድ፡ ቤቱ ፡ በታየው ፡ ጊዜ ፡ ክሱ ፡ እንዳልተለወጠ ፡ ወይም ፡ እንዳልተጨመረ ፡ ቈጥሮ ፡ ነገሩን ፡ መስማት ፡ ይቀጥላል ።

(፫) በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አስተያየት ፡ ነገሩን ፡ ወዲያው፡ መቀጠል ፡ የተከሳሹን ፡ የመከላከል፡ መብት፡ ወይም ፡ የዐቃቤ ፡ ሕጉን ፡ ክስ ፡ ሁኔታ ፡ የሚለውጥ ፡ ሆኖ፡ ባገኘው ፡ ጊዜ ፡ ቀጠሮ ፡ እንዲደረግ ፡ ያዛል ፡ (ቍ ፡ ፺፬ )።

## ቍ ፡ ፻፳፩ ። ስለ ፡ ምስክሮች ፡ እንደ ፡ ገና ፡ መጠራት ።

የነገሩ ፡ መሰማት ፡ ከተጀመረ፡ በኋላ ፡ ክሱ ፡ የተለወጠ ፡ ወይም ፡ የተጨመረ፡ ወይም ፡ አዲስ ፡ ክስ ፡ የተዘጋጀ ፡ ከሆነ ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ወይም፡ ተከሳሹ፡ ከተሰሙት፡ ምስክሮች ፡ ውስጥ ፡ ማንኛውንም ፡ እንደ፡ገና ፡ አስጠርቶ ፡ በክሱ ፡ ላይ ፡ ስለ፡ ተለወጠው ፡ ወይም፡ ስለ፡ተጨመረው ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ አዲሱ፡ ክስ ፡ የመጠየቅ፡ መብትና ፡ ለፍሬ ፡ ነገሩ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ ማስረጃ ፡ የማቅረብ ፡ መብት ፡ አለው ።

## ቍ ፡ ፻፳፪ ። ስለ ፡ ክስ ፡ ማንሣት ።

(፩) በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፳፪ ፡ ( ከባድ ፡ የግፍ ፡ አገዳደል ) ፡ ወይም፡ በቍጥር ፡ ፪፻፴፯ ፡ (ከባድ ፡ የወንበዴነት ፡ ተግባር )፡ መሠረት፡ ከቀረበው፡ ክስ ፡ በቀር ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ በተከሳሹ ፡ ላይ ፡ ያቀረበውን ፡ ማንኛውንም፡ ክስ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፈቃድ ፡ ከፍርድ ፡ በፊት ፡ ክሱ ፡ በሚሰማበት ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ክሱን ፡ ለማንሣት ፡ ይችላል ።

(፪) ክሱን ፡ እንዳነሣ ፡ በመንግሥት ፡ ታዝዣለሁ ፡ ብሎ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ለፍርድ፡ ቤቱ ፡ ሲያመለክት ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ክሱን ፡ እንዲያነሣ ፡ ከመንግሥት ፡ የታዘዘ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከተረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መፍቀድ ፡ አለበት ።

(፫) በቍጥር ፡ ፻፲፱ ፡ መሠረት፡ አዲስ ፡ ክስ ፡ ያልተዘጋጀ ፡ እንደ፡ሆነ ፤ ተከሳሹ ፡ ለጊዜው ፡ ይለቀቃል ።

(፬) ፍርድ፡ ቤቱ ፡ ክሱን ፡ ለማንሣት ፡ ወይም፡ ላለማንሣት ፡ ለሚሰጠው ፡ ውሳኔ፡ ምክንያቱን ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

(፭) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፡ ክሱ ፡ የተነሣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ክሱን ፡ ለወደፊት ፡ ለመቀጠል ፡ የሚከለክል ፡ አይሆንም ።

## ምዕራፍ ፡ ፩ ።

## የክሱ ፡ መሰማት ፡ ስለ፡ መጀመር ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### ስለ ፡ ክሱ ፡ ክርክር ።

**ቍ ፡ ፻፳፫ ። ክሱ ፡ የሚሰማበትን ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ መወሰን ።**

በቍጥር ፡ ፻፱ ፡ መሠረት፡ ክሱ፡ ለፍርድ፡ ቤት፡ ሲቀርብ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ነገሩ ፡ የሚሰማበትን ፡ ቀን ፡ ወስኖ ፡ በተወሰነው፡ ቀንና፡ ሰዓት፡ ተከሳሹና፡ ዐቃቤ፡ ሕጉ ፡ እንዲቀርቡ ፡ ፍርድ፡ ቤቱ ፡ መጥሪያ ፡ ይሰጣል ፤ ተከሳሹ ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ ያለ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ እንዲቀርብ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አስፈላጊውን ፡ ያደርጋል ።

**ቍ ፡ ፻፳፬ ። ስለ ፡ ምስክሮች ፡ መጠራት ።**

(፩) ነገሩ ፡ የሚሰማበት ፡ ቀን፡ እንደ፡ ተወሰነ ፡ ወድያውኑ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉና፡ ተከሳሹ ፡ እንዲቀርቡ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ የምስክሮቻቸውንና ፡ ያሉም ፡ እንደ፡ ሆነ፡ በምስክርነት ፡ የሚቀርቡትን ፡ ልዩ፡ ዕውቀት ፡ ያላቸው፡ ሰዎች ፡ ( ኤክስፔርቶች ) ፡ ስም፡ ዝርዝር ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ ይሰጣሉ ፤ የመዝገብ ፡ ቤቱም፡ ሹም፡ በዚህ፡ ሕግ ፡ መጨረሻ ፡ በተመለከተው ፡ በሦስተኛው ፡ ሰንጠረዥ ፡ ዐይነት ፡ መጥሪያውን ፡ ይሰጣል ።

(፪) ዐቃቤ ፡ ሕጉና ፡ ተከሳሹ ፡ ነገሩ ፡ በሚሰማበት ፡ ቀን ፡ መረጃዎች ፡ ( ኤግዚቢቶች ፡ ) ሁሉ ፡ እፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዲቀርቡ ፡ የማድረግ ፡ ግዴታ ፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ፻፳፭ ። ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚሰጠው ፡ የመያዝ ፡ ትእዛዝ ።**

አንድ ፡ ተከሳሽ፡ ወይም ፡ ምስክር፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ መጥሪያ ፡ ደርሶት ፡ መጥሪያው ፡ ለመድረሱ፡ ማስረጃ ፡ እያለ ፡ በታዘዘበት ፡ ቀን ፡ ሳይቀርብ ፡ የቀረ ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ ተከሳሹ ፡ ወይም ፡ ምስክሩ ፡ በፖሊስ ፡ ተይዞ ፡ እንዲቀርብ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

BACK



**ቍ ፡ ፻፳፮ ። ስለ ፡ ክሱ ፡ መሰማት ፡ አጀማመር ።**

(፩) ክሱ ፡ ሊሰማ ፡ በተቀጠረበት ፡ ቀንና ፡ ሰዓት፡ ክሱን ፡ ለመስማት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያስችላል ።

(፪) ለክሱ፡ ክርክር ፡ አስተርጓሚ፡ አስፈላጊ፡ በሆነ ፡ ጊዜ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ችሎታ፡ ያለውን ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ አስተርጓሚ፡ ይመርጣል ። ይህ ፡ ባልተገኘ፡ ጊዜ ፡ ለተከሳሹ ፡ ወይም ፡ ለዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ዘመድ ፡ ያልሆነ ፡ ወይም ፡ ለክሱ ፡ ምስክር ፡ ያልሆነ ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይመርጣል ።

(፫) በክሱ፡ ፋይል ፡ የተጠቀሱት ፡ ተከራካሪዎች ፡ ይጠራሉ ፤ ተከሳሹም ፡ መቅረብ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፻፳፯ ። የተከሳሹ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መቅረብ ።**

(፩) ክሱን ፡ እንዲሰማና ፡ መከላከል ፡ እንዲችል ፡ ተከሳሹ፡ ራሱ ፡ በችሎት ፡ መገኘት ፡ አለበት ፤ ጠበቃ ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከጠበቃው ፡ ጋራ ፡ ይቀርባል ።

(፪) ተከሳሹ፡ በበቂ፡ ዘብ፡ ተጠብቆ ፡ ይቀርባል ፤ አደገኛ ፡ ለመሆኑ ፡ ወይም ፡ የኀይል፡ ተግባር ፡ የሚፈጽም ፡ ለመሆኑ ፡ ወይም ፡ ለማምለጥ ፡ የሚሞክር ፡ መሆኑን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ከሌለ ፡ በስተቀር ፡ በሰንሰለት ፡ ታስሮ ፡ አይቀርብም ።

**ቍ ፡ ፻፳፰ ። ማንነቱን ፡ ስለ ፡ ማረጋገጥ ።**

ተከሳሹ ፡ በሣጥን ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ከቆመ ፡ በኋላ ፡ ማንነቱ ፤ ዕድሜውና ፡ ሥራው ፡ መረጋገጥ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፻፳፱ ። የክሱን ፡ ማመልከቻ ፡ ስለ ፡ ማንበብ ።**

የችሎቱ ፡ ፕሬዚዳን ፡ ክሱን ፡ ለተከሳሹ ፡ ካነበበለት ፡ በኋላ ፡ ተከሳሹ ፡ የክሱን ፡ ማመልከቻ ፡ የሚቃወም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይጠይቀዋል ።

**ቍ ፡ ፻፴ ። የክሱን፡ ማመልከቻ ፡ ስለ ፡ መቃወም ።**

(፩) ተከሳሹ ፡ ስለ ፡ ክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ ፎርም ፡ ወይም ፡ በክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ የተገለጸውን ፡ የሚቃወም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ከቍ ፡ ፻፲፱፡ አንሥቶ፡ በተከታዮቹ ፡ ቍጥሮች ፡ የተመለከቱት ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

(፪) ተከሳሹ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የተዘረዘሩትን ፤

(ሀ) በዚሁ ፡ ነገር ፡ ክስ ፡ በሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተጀምሮ ፡ በቀጠሮ ፡ ያለ ፡ መሆኑን ፤ ወይም ፡

(ለ) በዚሁ ፡ ክስ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ተከሶ ፡ ነጻ ፡ የወጣ ፡ ወይም ፡ የጥፋተኛነት ፡ ውሳኔ ፡ የተሰጠበት ፡ መሆኑን ፤ ወይም ፡

(ሐ) ክስ ፡ የቀረበበት ፡ ወንጀል ፡ በይርጋ ፡ ሕግ ፡ የታገደ ፡ ወይም ፡ ምሕረት ፡ ወይም ፡ የዐዋጅ ፡ ምሕረት፡ (ይቅርታ)፡ የተደረገለት ፡ መሆኑን ፤ ወይም ፡

BACK



(መ) ከሌሎች ፡ ወንጀለኞች ፡ ጋራ ፡ በተከሰሰ ፡ ጊዜና ፡ ለብቻው፡ ከሌሎቹ ፡ ተን ጥሎ ፡ ክሱ ፡ ባይታይለት ፡ የሚጐዳው ፡ መሆኑን ፤ ወይም ፡

(ሠ) ክሱን ፡ ለማቅረብ ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ፈቃድ ፡ ያልተሰጠ ፡ መሆኑን ፤ ወይም ፡

(ረ) በሌላው ፡ ችሎት ፡ የቀረበው ፡ ክስ ፡ ሳይፈጸም፡ በዚህ ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ ውሳኔ ፡ ሊሰጥ ፡ የማይገባ ፡ መሆኑን ፤ ወይም ፡

(ሰ) ለፈጸማቸው ፡ ተግባሮች ፡ ኀላፊ ፡ ያለመሆኑን ፤

ባመለከተ ፡ ጊዜ ፡ በቍ ፡ ፻፴፮ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማል ።

(፫) በዚህ፡ ቍጥር፡ መሠረት፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሲጠይቀው፡ ተከሳሹ ፡ የክሱን፡ ማመ ልከቻ፡ ወድያውኑ፡ ካልተቃወመ፡ በቀር፡ ቈይቶ፡ እንዲህ፡ ያለውን ፡ መቃወሚያ፡ ነገሩ፡ በሚሰማበት፡ በሌላ፡ ጊዜ፡ ሊያነሣ፡ አይችልም ። ስለ ፡ ሆነም፡ መቃወም ፡ የሚችለው ፡ መቃወሚያው ፡ የሚጸና ፡ ፍርድ ፡ ከመሰጠት ፡ የሚያግድ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

## ቍ ፡ ፻፴፩ ። መቃወምን ፡ ስለ ፡ መወሰን ።

(፩) በቍጥር ፡ ፻፴ ፡ ንኡስ፡ ቍ ፡ (፪) ፡ መሠረት፡ የሚደረገውን ፡ ማንኛውንም ፡ መቃወሚያ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ፡ በመዝገቡ ፡ ከጻፈ፡ በኋላ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ለቀረበው ፡ መቃወሚያ ፡ የሚሰጠው ፡ መልስ ፡ እንዳለው ፡ ይጠየቃል ።

(፪) ሕግን ፡ በመጥቀስ ፡ የቀረበውን ፡ መቃወሚያ ፡ ለመወሰን ፡ የሚችል ፡ ሲሆን ፤ ወይም ፡ በነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ የቀረበውን ፡ መቃወሚያ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ያልተቃ ወመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ፍርድ፡ ቤቱ፡ አንድ ፡ ውሳኔ ፡ ወዲያውኑ ፡ ይሰጣል ።

(፫) ማስረጃው ፡ ባለመሟላቱ ፡ ምክንያት ፡ ወድያውኑ ፡ ውሳኔ ፡ መስጠት ፡ ያል ተቻለ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ያለ፡ መዘግየት ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነው ፡ ማስረጃ ፡ እንዲቀ ርብ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

(፬) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አስፈላጊው ፡ ማስረጃ ፡ ሲቀርብለት ፡ ወዲያውኑ ፡ ውሳኔ ፡ ይሰ ጣል ።

## ቍ ፡ ፻፴፪ ። ስለ ፡ ተከሳሹ ፡ እምነት ፤ ክሕደት ፡ መጠየቅ ።

(፩) ክሱ ፡ ለተከሳሹ ፡ ተነቦለት ፡ እንዲረዳው፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ የችሎቱ ፡ ፕሬ ዚዳን ፡ የተከሳሹን ፡ እምነት ፡ ክሕደት ፡ ይጠይቀዋል ።

(፪) ክሱ ፡ ከአንድ ፡ በላይ፡ በሆነ ፡ ጊዜ፡ የችሎቱ ፡ ፕሬዚዳን ፡ እያንዳንዱን ፡ ክስ ፡ በተለይ ፡ ለተከሳሹ ፡ እንብቦለት ፡ ካስረዳው ፡ በኋላ ፡ ለየአንዳንዱ ፡ ክስ ፡ እም ነት ፡ ክሕደቱን ፡ ተቀብሎ ፡ በመዝገብ ፡ ይጽፋል ።

(፫) እምነት ፡ ክሕደቱ ፡ ተከሳሹ ፡ በሚሰጠው፡ ቃል ፡ አነጋገር ፡ ዐይነት ፡ መመ ዝገብ ፡ አለበት ።

BACK



**ቍ ፡ ፻፴፫ ። ጥፋተኛ ፡ አይደለሁም ፡ ስለ፡ ማለት ፡ (ክሕደት) ።**

(፩) ተከሳሹ፡ ለክሱ፡ መልስ፡ ያልሰጠ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ወይም ፡ ክሱን ፡ የካደ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ጥፋተኛ ፡ አይደለሁም ፡ ብሏል ፡ ተብሎ ፡ በመዝገብ ፡ ይጻፋል ።

(፪) ተከሳሹ ፡ ወንጀሉን ፡ አምኖ ፡ በአፈጻጸሙ ፡ ረገድ ፡ ለይቶ ፡ መብቱን ፡ የጠበቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጥፋተኛ ፡ አይደለሁም ፡ ብሏል ፡ ሲል፡ በመዝገብ ፡ ይጽፋል ።

**ቍ ፡ ፻፴፬ ። ስለ ፡ እምነት ፡ የሚሰጥ ፡ ቃል ።**

(፩) ተከሳሹ ፡ በክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ የተዘረዘረውን ፡ ወንጀል ፡ ለመሥራቱ ፡ በሙሉ፡ ያመነ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ፍርድ፡ ቤቱ፡ ተከሳሹ ፡ ጥፋተኛ፡ ነኝ፡ ብሏል ፡ ሲል ፡ በመዝገብ ፡ ከጻፈ ፡ በኋላ ፡ በተከሳሹ ፡ ላይ ፡ የጥፋተኝነት ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጣል ።

(፪) ጥፋተኛ ፡ ነኝ ፡ ብሏል ፡ ተብሎ ፡ በመዝገብ ፡ በተጻፈ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ሲያገኘው ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ለክሱ ፡ የሚደግፈውን ፡ ማስረጃ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ለማዘዝና ፡ ተከሳሹም ፡ የመከላከያ ፡ ማስረጃውን ፡ እንዲያቀርብ፡ ለመፍቀድ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፻፴፭ ። የተከሳሹ ፡ እምነት ፡ ክሕደት ፡ ማሻሻል ።**

(፩) የተሰጠው ፡ ቃል ፡ የእምነት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ እና ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ክሱን ፡ መስማት ፡ በሚቀጥልበት ፡ ጊዜ ፡ ጥፋተኛ ፡ አይደለሁም ፡ የማለት ፡ ቃል ፡ መመዝገብ ፡ የሚገባው፡ ሆኖ ፡ ያገኘ ፡ እንደ፡ሆነ ፡ ጥፋተኛ ፡ አይደለሁም ፡ የሚለውን፡ ቃል ፡ ይመዘግባል ።

(፪) በተከሳሹ ፡ ላይ ፡ የተሰጠው ፡ የጥፋተኝነት ፡ ውሳኔ ፡ ውድቅ ፡ ይሆናል ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## ማስረጃና ፡ ፍርድ ።

**ቍ ፡ ፻፴፮ ። የክሱ ፡ መክፈትና ፡ የዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ምስክሮች ፡ መጠራት ።**

(፩) የተከሳሹ፡ እምነት፡ ክሕደት፡ በመዝገብ፡ ከገባ፡ በኋላ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ክሱን፡ ሲከፍት ፡ ሊያስረዳ ፡ ያቀረበውን ፡ ክስና ፡ የሚያቀርበውን ፡ ማስረጃ ፡ ዐይነት ፡ ባጭሩ ፡ ይገልጻል ፤ ይህንንም ፡ በትክክል ፡ ያለ ፡ አድልዎ ፡ ማመልከት ፡ አለበት ።

(፪) ከዚህ ፡ በኋላ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ምስክሮቹንና ፡ በምስክርነት ፡ የሚቀርቡ ፡ ልዩ ፡ ዕውቀት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ( ኤክስፐርቶቹ ) ፡ እንዲሉ ፡ መጥራት ፡ አለበት ። የምስክርነት ፡ ቃላቸውን ፡ ከመስጠታቸው ፡ በፊት ፡ ምስክሮቹና ፡ በምስክርነት ፡ የሚቀርቡ ፡ ልዩ ፡ ዕውቀት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ መማል ፡ ወይም ፡ እውነትን ፡ ለመናገር ፡ ማረጋገጥ ፡ አለባቸው ።

(፫) ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ዋናውን ፡ ጥያቄ ፡ ጠይቋቸው ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ተከሳሹ ፡ ወይም ፡ ጠበቃው ፡ መስቀልያ ፡ ጥያቄ ፡ ይጠይቃቸዋል ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉም ፡ ድጋሚ ፡ ጥያቄ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፬) ትክክለኛ ፡ ፍርድ ፡ ለመስጠት ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ ሲታየው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ምስክሩን ፡ ማናቸውንም ፡ ጥያቄ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

<u>ቍ ፡ ፻፴፯ ። የዋናው ፡ ጥያቄ ፡ ዐይነት ።</u>

(፩) በዋናው ፡ ጥያቄ ፤ የሚቀርቡ ፡ ጥያቄዎች ፡ ውሳኔ ፡ ስለሚሰጥበት ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ተገቢ ፡ የሆኑትንና ፡ በቀጥታም ፡ ሆነ ፡ ቀጥታ ፡ ባልሆነ ፡ መንገድ ፡ ምስክሩ ፡ ስለሚያውቃቸው ፡ ፍሬ ፡ ነገሮች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

(፪) እንደ ፡ ነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ ተከሳሹ ፡ ወይም ፡ ጠበቃው ፡ ወይም ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ሳይፈቅዱ ፡ የመምራት ፡ ጥያቄ ፡ ምስክሩ ፡ አይጠየቅም ።

(፫) መስቀልያ ፡ ጥያቄ ፤ በዋናው ፡ ጥያቄ ፡ በተሰጠው ፡ መልስ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ የስሕተት ፡ ቃል ፤ የሚያጠራጥር ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ እውነት ፡ ያልሆነውን ፡ ቃል ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለመግለጽና ፡ ለማስተባበል ፡ የሚደረግ ፡ ጥያቄ ፡ ነው ። የመምራት ፡ ጥያቄዎች ፡ በመስቀልያ ፡ ጥያቄ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይቻላል ።

<u>ቍ ፡ ፻፴፰ ። የተከሳሹ ፡ የቀድሞ ፡ ጥፋተኛነት ።</u>

(፩) ሕጉ ፡ በተለይ ፡ በግልጽ ፡ ካልፈቀደ ፡ በቀር ፡ በፍርድ ፡ ጥፋተኛነቱ ፡ ከመታወቁ ፡ በፊት ፡ ተከሳሹ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ተከሶ ፡ የጥፋተኛነት ፡ ውሳኔ ፡ የተሰጠበት ፡ መሆኑ ፡ አይገለጽም ።

(፪) በማንኛውም ፡ ቀዳሚ ፡ ምርመራ ፡ በሚያደርገው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ተከሳሹ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ የተወሰነበት ፡ መሆኑ ፡ አይገለጽም ።

<u>ቍ ፡ ፻፴፱ ። ድጋሚ ፡ ጥያቄ ።</u>

ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፤ ተከሳሹ ፡ ወይም ፡ ጠበቃው ፡ በመስቀልያ ፡ ጥያቄ ፡ የተነሣውን ፡ ነገር ፡ ለማጣራት ፡ ብቻ ፡ ድጋሚ ፡ ጥያቄ ፡ ይጠይቃል ።

<u>ቍ ፡ ፻፵ መስቀልያ ፡ ጥያቄ ፡ ስላለመጠየቅ ።</u>

በአንድ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ መስቀልያ ፡ ጥያቄ ፡ አለመጠየቅ ፡ ተቃዋሚውን ፡ ወገን ፡ የነገሩን ፡ እውነተኛነት ፡ እንደ ፡ አመነ ፡ አይቈጠርም ።

<u>ቍ ፡ ፻፵፩ ። ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ክሱን ፡ ባላስረዳ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ተከሳሹ ፡ ነጻ ፡ መለቀቅ ።</u>

ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ማስረጃውን ፡ አሰምቶ ፡ ከጨረሰ ፡ በኋላ ፡ ማፍረሻ ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ አስፈላጊ ፡ ሳይሆን ፡ ተከሳሹን ፡ ጥፋተኛ ፡ የሚያደርገው ፡ ሆኖ ፡ ባልተ

BACK



ገኘ ፡ ጊዜ ፡ እና ፡ ማስረጃው ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ ሳያገኘው ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተከሳሹ ፡ በነጻ ፡ እንዲለቀቅ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያዛል ።

**ቍ ፡ ፻፵፪ ። የመከላከያ ፡ ማስረጃን ፡ ስለ ፡ መጀመር ።**

(፩) ተከሳሹ ፡ በቀረበበት ፡ ማስረጃ ፡ መሠረት ፡ የተመሰከረበት ፡ ከሆነና ፡ የተበደለው ፡ ወገን ፡ ያቀረባቸው ፡ ምስክሮች ፡ ከተሰሙ ፡ በኋላ ፡ መከላከያውን ፡ እንዲጀምርና ፡ ለክሱ ፡ መልስ ፡ ቃሉን ፡ መስጠትና ፡ የመከላከያ ፡ ምስክሮቹን ፡ ማቅረብ ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለተከሳሹ ፡ ይነግረዋል ።

(፪) ተከሳሹ ፡ ወይም ፡ ጠበቃው ፡ መከላከያውን ፡ መክፈትና ፡ በመከላከያ ፡ ሊያስረዳ ፡ ያቀረበውን ፡ ማስረጃውን ፡ በመግለጽ ፡ አጭር ፡ መግለጫ ፡ ይሰጣል ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ምስክሮቹን ፡ ወይም ፡ በምስክርነት ፡ ቃላቸውን ፡ የሚሰጡት ፡ ልዩ ፡ ዐዋቂዎች ፡ እንዳሉ ፡ ጠርቶ ፡ ቃላቸውን ፡ ከመስጠታቸው ፡ በፊት ፡ እንዲምሉ ፡ ወይም ፡ እውነትን ፡ ለመናገር ፡ እንዲያረጋግጡ ፡ ይደረጋል ።

(፫) የመከላከያ ፡ ምስክሮቹ ፡ በማንኛውም ፡ ተራ ፡ ሊጠሩ ፡ ይቻላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ተከሳሹ ፡ ቃሉን ፡ መስጠት ፡ የፈቀደ ፡ እንደሆነ ፡ በመጀመሪያ ፡ ቃሉን ፡ ይሰጣል ። ተከሳሹም ፡ በሚሰጠው ፡ ቃል ፡ መስቀልያ ፡ ጥያቄ ፡ ሊጠየቅ ፡ አይችልም ፤ ግን ፡ ተከሳሹ ፡ ስለ ፡ ሰጠው ፡ ቃል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ነገሩን ፡ ለማብራራት ፡ መጠየቅ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፻፵፫ ። ተጨማሪ ፡ ምስክሮች ።**

(፩) ትክክለኛ ፡ ፍርድ ፡ ለመስጠት ፡ ምስክርነቱ ፡ አስፈላጊ ፡ ከመሰለው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፍርድ ፡ ከመስጠቱ ፡ በፊት ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ማንኛውንም ፡ ምስክር ፡ መጥራት ፡ ይችላል ።

(፪) ዐቃቤ ፡ ሕጉና ፡ ተከሳሹ ፡ ባቀረቡት ፡ የምስክር ፡ ስም ፡ ዝርዝር ፡ ላይ ፡ ያልተጠቀሱ ፡ ቢሆኑም ፡ ማንኛውንም ፡ ምስክር ፡ መቍጠር ፡ ይችላሉ ፤ እነዚህ ፡ ምስክሮች ፡ ነገሩን ፡ ለማዘግየት ፡ ሳይሆን ፡ ለፍሬ ፡ ነገሩ ፡ ምስክርነታቸው ፡ አስፈላጊ ፡ ሲመስለው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዲጠሩ ፡ መጥሪያ ፡ እንዲደርሳቸው ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

(፫) ክሱ ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲታይ ፡ የቀረበ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በቀዳሚ ፡ ምርመራ ፡ አድራጊው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያልተሰሙ ፡ ምስክሮችንም ፡ ቢሆን ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ የፈለገውን ፡ ምስክር ፡ ስምና ፡ የሚሰጠውን ፡ ምስክርነት ፡ ዐይነት ፡ ለተከሳሹ ፡ በጽሑፍ ፡ ገልጾ ፡ ለመጥራት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፻፵፬ ። በቀዳሚ ፡ ምርመራ ፡ አድራጊ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ምስክሮች ፡ የሰጡት ፡ ቃል ፡ በማስረጃነት ፡ ሊቀርብ ፡ ስለ ፡ መቻሉ ።**

(፩) ምስክሩ ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የአእምሮ ፡ ጕድለት ፡ ያገኘው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ማግኘት ፡ ያልተቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በሕመም ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ በኢ

ትዮጵያ፡ ግዛት፡ ውስጥ፡ ባለመኖሩ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መቅረብ ፡ ያልቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በቀዳሚ ፡ ምርመራ ፡ አድራጊ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሰጠው ፡ ቃል ፡ ተነቦ ፡ በማስረጃነት ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይቀርባል ።

(፪) በምስክርነት ፡ ቃሉን ፡ የሚሰጥ፡ ልዩ ፡ ዐዋቂ ፡ በምስክርነት ፡ ባይጠራም ፡ በቀዳሚ ፡ ምርመራ ፡ አድራጊ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሰጠው ፡ ቃል ፡ ተነቦ ፡ በማስረጃ ነት ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊቀርብ ፡ ይችላል ።

<u>ቍ ፡ ፻፵፭ ። በፖሊስ፡ ምርመራ ፡ የተሰጠ ፡ ቃል ፡ በማስረጃነት፡ ሊቀርብ ፡ ስለ፡መቻሉ ።</u>

(፩) ዐቃቤ ፡ ሕጉ፡ ወይም ፡ ተከሳሹ ፡ ሲያመለክት ፡ በፖሊስ ፡ ምርመራ ፡ ጊዜ ፡ የተሰጠውን ፡ የምስክርነት ፡ ቃል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊመለከተው ፡ ይችላል ።

(፪) ከዚህ ፡ በኋላ፡ ለትክክለኛው ፡ ፍርድ ፡ አሰጣጥ ፡ የሚጠቅም ፡ መስሎ ፡ ከታየው ፡ የዚህ ፡ ቃል ፡ ግልባጭ ፡ ለተከሳሹ ፡ እንዲደርሰው፡ አድርጎ ፡ በዚህ ፡ መሠረት ፡ ምስክሩ ፡ የሰጠውን ፡ ቃል ፡ ለማስተባበል ፡ ይቻላል ።

<u>ቍ ፡ ፻፵፮ ። ማስረጃን ፡ ስለ ፡ መቃወም ።</u>

ዐቃቤ፡ ሕጉ ፡ ወይም ፡ ተከሳሹ፡ አንድ፡ ማስረጃ፡ ሊቀርብ ፡ አይገባም ፡ ወይም ፡ ምስክሩ ፡ ጥያቄ ፡ ሊጠየቅ ፡ አይገባም ፡ ብሎ ፡ ሲቃወም ፡ ጥያቄው ፡ ወይም ፡ ማስረጃው፡ የሚገባ፡ መሆን ፡ አለመሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ወዲያውኑ፡ ይወስናል ።

<u>ቍ ፡ ፻፵፯ ። ማስረጃውን ፡ በመዝገብ ፡ ስለ ፡ መጻፍ ።</u>

(፩) የያንዳንዱን፡ ምስክር ፡ ቃል ፡ ሲቀበል ፡ በመጀመሪያ ፡ የምስክሩን ፡ ስም ፤ አድራሻውን ፤ ሥራውንና ፡ ዕድሜውን፡ እንዲሁም፡ መሐላ፡ ማድረጉን፡ ወይም፡ እውነት ፡ ለመናገር ፡ ማረጋገጡን ፡ መጥቀስ ፡ አለበት ።

(፪) የያንዳንዱን፡ ምስክር፡ ቃል፡ የችሎቱ፡ ሰብሳቢ፡ ዳኛ ፡ ራሱ፡ በመዝገብ ፡ ይጽፋል፤ ነገር፡ ግን ፡ በአንድ ፡ ምክንያት ፡ መጻፍ ፡ ያልቻለ ፡ እንደሆን ፡ በሱ ፡ መሪነትና ፡ ተቈጣጣሪነት ፡ ሌላው ፡ ዳኛ ፡ ወይም ፡ የፍርድ ፡ ጸሐፊው ፡ እንዲጽፍ ፡ ያደርጋል ።

(፫) ማስረጃው ፡ ሲመዘገብ ፡ ዋና ፡ ጥያቄ ፤ መስቀልያ ፡ ጥያቄ ፤ ድጋሚ ፡ ጥያቄ ፡ ተብሎ፡ይከፈላል ፤ መስቀልያ ፡ ጥያቄውና ፡ ድጋሚ፡ ጥያቄው፡ የሚጀመርበትና፡ የሚያልቅበት ፡ ስፍራ ፡ በመዝገቡ ፡ ውስጥ ፡ እንደሚለይ ፡ ተደርጎ ፡ ይጻፋል ።

(፬) ሰብሳቢው ፡ ዳኛ ፡ አንዳንድ ፡ ጥያቄን፡ ወይም ፡ መልስን ፡ በተለይ ፡ ለመጻፍ ፡ ካልፈቀደ፡ በቀር፡ የሚሰጠውን ፡ የምስክርነት ፡ ቃል ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ እንደ ፡ ተነገረው ፡ በሐተታ ፡ ዐይነት ፡ መመዝገብ ፡ አለበት ።

<u>ቍ ፡ ፻፵፰ ። የክርክሩ ፡ ማቆሚያ ፡ ንግግር ።</u>

(፩) የመከላከያ ፡ ማስረጃ ፡ መስማት፡ ከተፈጸመ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ ሕጉና ፡ ስለ፡ነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ይናገራል ።

BACK



(፪) ከዚህ፡ በኋላ ፡ ተከሳሹ ፡ ወይም፡ ጠበቃው፡ ስለ፡ሕጉና ፡ ስለ፡ ነገሩ ፡ ማስረጃ፡ ሁኔታ ፡ ይናገራል ። እሱም፡ ሁል፡ ጊዜ ፡ የመጨረሻውን ፡ ንግግር ፡ ያደርጋል።

(፫) ተከሳሾቹ ፡ ብዙ፡ እንደ፡ሆኑ ፡ ተከሳሹ ፡ ወይም ፡ ጠበቃው ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ፡ ንግግር ፡ የሚያደርግበትን ፡ ተራ ፡ ሰብሳቢው ፡ ዳኛ ፡ ይወስናል ።

ቍ ፡ ፻፵፱ ። ስለ ፡ ፍርድና ፡ ቅጣት ።

(፩) የመጨረሻው፡ ንግግርና፡ በቍጥር፡ ፻፵፰ ፡ መሠረት ፡ የሚደረገው ፡ ንግግር፡ ጭምር፡ ያለ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፍርዱን ፡ ይሰጣል። ፍርዱም፡ ቀን፡ ተጽፎበት ፡ በፍርድ ፡ ሰጪው ፡ ዳኛ ፡ መፈረም ፡ አለበት ። የማስረጃው ፡ አጭር ፡ መግለጫ ፤ ማስረጃውን ፡ የተቀበለበትና ፡ ያልተቀበለበትን፡ ምክንያቶች ፡ ፍርዱ ፡ የተመሠረተበትን ፡ ሕግ ፡ መጥቀስና ፡ ጥፋትም ፡ ሆኖ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ ያስገኘውን ፡ ሕግ ፡ በፍርዱ ፡ ውስጥ ፡ መጻፍ ፡ አለበት ።

(፪) ተከሳሹ ፡ ጥፋተኛ ፡ አይደለም፡ በተባለ ፡ ጊዜ ፡ ተከሳሹ ፡ ነጻ ፡ እንዲሆንና፡ አስፈላጊም ፡ ሲሆን ፡ ከማረፊያ ፡ ቤት ፡ እንዲለቀቅ ፡ የሚል ፡ ትእዛዝ ፡ በፍርዱ ፡ ውስጥ ፡ እንዲገለጽ ፡ ያስፈልጋል ።

(፫) ተከሳሹም ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው ፡ በተባለ ፡ ጊዜ፡ ስለ ፡ ቅጣት ፡ ማክበድ ፡ ወይም ፡ ማቅለል ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ያለውን ፡ አስተያየት ፡ እንዲሰጥ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይጠይቀዋል ። ዐቃቤ ፡ ሕጉም ፡ ስለ፡ ተከሳሹ ፡ ጠባይ ፡ ለማስረዳት ፡ ምስክሮች ፡ ለመጥራት ፡ ይችላል ።

(፬) ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ስለ፡ ቅጣቱ ፡ አስተያየቱን ፡ ከሰጠ ፡ በኋላ ፡ ተከሳሹ ፡ ወይም ፡ ጠበቃው፡ መልስ ፡ የመስጠት ፡ መብት ፡ አለው ፤ ስለ፡ ጠባዩም ፡ ለማስረዳት፡ ምስክሮች፡ ለመጥራት፡ ይችላል ። ተከሳሹ፡ ቀድሞ፡ በጥፋተኛነት ፡ አልተፈረደበትም ፡ ያለ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በጥፋተኛነት ፡ የተፈረደበት ፡ ለመሆኑ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማስረዳት ፡ አለበት ።

(፭) ከዚህ ፡ በኋላ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቅጣትን ፡ ይወስናል ፡ ቅጣቱም ፡ የተሰጠበትን ፡ የሕግ ፡ ቍጥሮች ፡ ጠቅሶ ፡ መጻፍ ፡ አለበት ።

(፮) በዚህ፡ ቍጥር ፡ የተነገረው ፡ ቢኖርም ፡ በወንጀለኛው ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፻፺፭ ፡ እና ፡ ፻፺፮ ፡ የተመለከተው ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ነው ።

(፯) ፍርድ፡ ከተሰጠ ፡ በኋላ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ወይም ፡ ተከሳሹ ፡ ስላለው ፡ የይግባኝ ፡ መብት ፡ ይነገረዋል ።

BACK



## ምዕራፍ ፡ ፩ ።

## የግል ፡ ከሳሽ ፡ የሚያቀርበው ፡ ክስ ።

ቍ ፡ ፪፻ ፣ አቤቱታና ፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ።

(፩) በቍጥር ፡ ፵፬ ፡ ንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ መሠረት ፡ የግል ፡ ክስ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ፈቃድ ፡ የተሰጠው ፡ የግል ፡ ከሳሽ ፡ በዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ አቤቱታውንና፡ የክሱን ማመልከቻ፡ሥልጣኑ ፡ ለሚፈቅድለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት፡ ያቀርባል ።

(፪) የክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ የቀረበው ፡ ለግል ፡ ከሳሹ ፡ በተሰጠው ፡ ፈቃድ ፡ መሠረት ፡ ያልሆነ ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ በተሰጠው ፡ ፈቃድ ፡ መሠረት ፡ ክሱን ፡ እንዲያሻሽል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያዛል ።

ቍ ፡ ፪፻፩ ፡ ባለጉዳዮቹን ፡ ለማስታረቅ ፡ ስለሚደረግ ፡ ሙከራ ።

(፩) አቤቱታውና ፡ ክሱ ፡ ሲቀርብ ፡ የግል ፡ ከሳሹና ፡ ተከሳሹ ፡ እንዲቀርቡ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መጥሪያ ፡ ይሰጣል ።

(፪) የክስ፡ ማመልከቻውን፡ ከማንበቡ፡ በፊት፡ ፍርድ፡ ቤቱ፡ ተከራካሪዎቹን ፡(የግል፡ ከሳሽንና፡ ተከሳሹን)፡ ለማስታረቅ፡ ይሞክራል ። ዕርቅ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ፡ ቤቱ፡ ዕርቁን ፡ በመዝገብ ፡ ይጽፋል ። ዕርቁም ፡ የፍርድ ፡ ውጤት ፡ ይኖረዋል።

ቍ ፡ ፪፻፪ ። ስለ ፡ ኪሣራ ፡ የሚደረግ ፡ መተማመኛ ።

በነገረተኞቹ፡ መካከል፡ ዕርቅ፡ እንዲሆን፡ ለማድረግ፡ ባልተቻለ፡ ጊዜ፡ ፍርድ፡ቤቱ፡ የግል፡ ከሳሹ፡ ስለ፡ኪሣራ፡ ዋስትና፡ እንዲሰጥ፡ ማድረግ፡ ያስፈልግ፡ እንደ፡ሆነ፡ይወስናል ። ስለ፡ ኪሣራ ፡ ዋስትና፡ እንዲሰጥ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ፡ ዋስትናውንና ፡ ዋስትና፡ የሚሰጥበትን ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ፡ በሚሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ውስጥ ፡ ይወስናል ።

ቍ ፡ ፪፻፫ ። ክርክሩን ፡ ስለ ፡ መስማትና ፡ ፍርድ ፡ ስለ ፡ መስጠት ።

የግል ፡ ከሳሹ ፡ በቍ ፡ ፪፻፪ ፡ መሠረት ፡ ትእዛዝ ፡ ተሰጥቶት ፡ ትእዛዙን ፡ የፈጸመ፡ እንደ፡ሆነ ፤ ከቍ፡ ፻፳፫ ፡ እስከ፡ ቍ፡ ፻፷፱ ፡ በተመለከተው፡ መሠረት ፡ የነገሩ፡ መሰማት ፡ ይቀጥላል ። ተከራካሪዎቹ፡ በዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ በኩል፡ በሚቀርበው ፡ ክስ፡ ዐይነት ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ ይኖራቸዋል ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## ወንጀል ፡ በመሠራቱ ፡ ጉዳት ፡ ስለ፡ደረሰበት ፡ ሰው ።

ቍ ፡ ፪፻፬ ። መሠረቱ ።

(፩) በወንጀሉ፡ የተበደለው፡ ሰው፡ ወይም፡ እንደራሴው ፡ የነገሩ ፡ መሰማት ፡ ሲጀመር ፡ ነገሩን ፡ የሚሰማው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ካሣ ፡ እንዲ

ያዝለት ፡ መጠየቅ ፡ ይችላል ። የሚፈለገውንም ፡ ካሣ ፡ ዐይነትና ፡ ልክ ፡ በጽሑፍ ፡ ወስኖ ፡ ያመለክታል ። ማመልከቻውን ፡ ሲያቀርብ ፡ በሕግ ፡ የተወሰነውን ፡ የዳኝነት ፡ እንደ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ነገር ፡ መክፈል ፡ የለበትም ።

(፪) ማመልከቻውን ፡ የሚያቀርበው ፡ ሰው ፡ የዐቃቤ ፡ ሕግንና ፡ የመከላከያን ፡ ምስክሮች ፡ ስም ፡ ዝርዝር ፡ እንዲያይና ፡ ተጨማሪ ፡ ምስክር ፡ መጥራት ፡ የሚፈልግ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ይጠየቃል። በፍትሐ፡ ብሔር፡ ነገር ፡ እንደሚደረገው ፡ ሁሉ፡ ለሚፈልጋቸው ፡ ተጨማሪ ፡ ምስክሮች ፡ መጥሪያ ፡ በሕግ ፡ የተወሰነውን ፡ ገንዘብ ፡ ይከፍላል ።

(፫) የዚሀ ፡ ምዕራፍ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ በኩል ፡ ለሚቀርበው ፡ ክስና፡ በግል ፡ ከሳሽ ፡ በኩል ፡ ለሚቀርበውም ፡ ክስ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

(፬) ማመልከቻውን ፡ የሚያቀርበው ፡ ሰው፡ በግል፡ ከሳሽነት ፡ የሆነ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ በወንጀሉ ፡ ክስ ፡ የሚያቀርባቸውን ፡ ምስክሮች ፡ ዝርዝርና ፡ ለካሣው ፡ መጠየቂያ ፡ ክስ ፡ የሚያቀርባቸውን ፡ ምስክሮች ፡ ይለያል ። የንኡስ ፡ ቊ ፡ (፩) እና ፡ (፪) ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

<u>ቊ ፡ ፻፶፰ ። ማመልከቻውን ፡ ስላለመቀበል ።</u>

(፩) ፍርድ፡ ቤቱ፡ የቀረበለትን ፡ ማመልከቻ ፡ ከተመለከተ ፡ በኋላ ፡ በራሱ ፡ አስተያየት ፡ ወይም ፡ በዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ወይም ፡ በተከሳሹ ፡ አመልካችነት ፡ ከዚሀ ፡ እንደሚቀጥለው ፡ ሆኖ ፡ ባገኘው ፡ ጊዜ ፤

(ሀ) ተከሳሹ ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡

(ለ) በተከሳሹ ፡ ላይ፡ የቀረበውን፡ ክስ ፡ ለመስማት ፡ ተከሳሽ ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡

(ሐ) ተበዳዩ ፡ ሥልጣኑ ፡ በሚፈቅድለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክስ ፡ አቅርቦ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡

(መ) ማመልከቻውን ፡ ያቀረበ ፡ ሰው ፡ ክሱን ፡ ለማቅረብ ፡ የማይገባው ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡

(ሠ) በዐቃቤ ፡ ሕጉና ፡ በመከላከያ ፡ ከሚቀርቡት ፡ ምስክሮች ፡ በላይ ፡ አያሌ ፡ ምስክሮች ፡ በተጨማሪነት ፡ ካልተጠሩ ፡ በቀር ፡ የካሣውን ፡ ልክ ፡ መወሰን ፡ የማይቻል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡

(ረ) ካሣ ፡ በመጠየቅ ፡ ተበዳዩ ፡ ያቀረበውን ፡ ክስ ፡ መስማት ፡ የወንጀሉን ፡ ነገር ፡ ለመስማት ፡ አስቸጋሪ ፡ የሚያደርግ ፤ የሚያዘበራርቅ ፡ ወይም ፡ የሚያዘገይ ፡ መስሎ ፡ የታየው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ማመልከቻውን ፡ የማይቀበለው ፡ መሆኑን ፡ ይወስናል ።

(፪) ክስ ፡ የቀረበበት ፡ የካሣ ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሥልጣን ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማመልከቻውን ፡ አልቀበልም ፡ ብሎ ፡ ይወስናል ።

(፫) ፍርድ፡ ቤቱ ፡ ማመልከቻውን ፡ ስላለመቀበሉ ፡ የሚሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ የመጨረሻና ፡ ይግባኝ ፡ የሌለው ፡ ነው ። በወንጀሉ ፡ የተበደለው ፡ ሰው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይነግረዋል ።

**፻፶፮ ። ማመልከቻውን ፡ ፈቅዶ ፡ ስለ ፡ መቀበል ።**

(፩) የተበደለውን፡ ሰው ፡ ማመልከቻ፡ ፍርድ፡ ቤቱ ፡ ፈቅዶ ፡ የተቀበለው ፡ እንደ ፡ ሆነ፤ የተበደለው፡ ሰው፡ በወንጀሉ፡ ክስ፡ ነገር፡ ለመግባትና፡ እንደ፡ ደንበኛ ፡ ተከራካሪ፡ ወገን ፡ በሚቀርበው ፡ ማስረጃ ፡ ሙሉ ፡ የተካፋይነት ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) የመከላከያው ፡ ማስረጃ፡ ሲፈጸም፡ የተበደለው፡ ሰው ፡ ወይም ፡ እንደራሴው ፡ የሚፈልገውን ፡ ካሣ ፡ መጠን ፡ ራሱ ፡ ወይም ፡ ጠበቃው ፡ እንዲያመለክት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይፈቅድለታል ። ተከሳሹ ፡ ወይም ፡ ጠበቃው ፡ መልስ ፡ የመስጠት ፡ መብት ፡ ይኖረዋል ።

**፻፶፯ ። የተበደለው ፡ ሰው ፡ ከክሱ ፡ ስለ ፡ መውጣት ።**

የተበደለው ፡ ሰው ፡ መከላከያው ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ የክስ ፡ ማመልከቻውን ፡ ትቶ ፡ ሥልጣኑ ፡ በሚፈቅድለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በተከሳሹ ፡ ላይ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

**፻፶፰ ። ተከሳሹን ፡ ነጻ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ፡ ወይም ፡ ስለ፡ መልቀቅ ።**

ተከሳሹ ፡ ነጻ ፡ በተለቀቀ ፡ ወይም ፡ ለጊዜው ፡ በተለቀቀ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ስለ ፡ ካሣ ፡ ፍርድ ፡ አይሰጥም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የተበደለው ፡ ሰው ፡ ሥልጣኑ ፡ በሚፈቅድለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተከሳሹን ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ መክሰስ ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ ይነግረዋል ።

**፻፶፱ ። ስለ ፡ ካሣ ፡ አወሳሰን ፡ የሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ።**

(፩) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጉዳት ፡ ለደረሰበት ፡ ወገን ፡ ካሣ ፡ ሲፈርድለት ፤

(ሀ) የተወሰነው ፡ ካሣ፡ መጠን ፡ ለተበደለው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ለእንደራሴው ፡ እንዲከፈል ፤

(ለ) በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ነገር ፡ እንደሚከፈለው ፡ ሁሉ ፡ የኪሣራ ፡ ወጪ ፡ ለተበደለው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ለእንደራሴው ፡ እንዲከፈል ፤

(ሐ) በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ነገር ፡ እንደሚደረገው ፡ ተከሳሹ ፡ ዳኝነት ፡ እንዲከፍል ፡ ብሎ ፤ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

(፪) ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ እንደማንኛውም ፡ ደንበኛ ፡ ክስ ፡ ፍርድ ፡ ይሰጣል ።

BACK



## አንቀጽ ፡ ፪ ።

## ልዩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ተከሳሹ ፡ በሌለ ፡ ጊዜ ፡ የሚፈጸም ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ።

**ቍ ፡ ፪፻፵ ። መሠረቱ ።**

(፩) አካለመጠን ፡ ባላደረሱ ፡ ወጣቶች ፡ ላይ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በዐቃቤ ፡ ሕግም ፡ ሆነ ፡ በግል ፡ ክስ ፡ የተከሰሰው ፡ ሰው ፡ ባልቀረበ ፡ ጊዜ ፡ የዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

(፪) ነገሩ፡ ሊሰማ፡ በተቀጠረበት፡ ቀን፡ ተከሳሹ ፡ ራሱ ፡ ሳይቀርብ፡ የቀረ ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ ለመቅረቱ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ የሚሰጥለት ፡ እንደራሴ ፡ ያል ቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ተከሳሹ ፡ እንዲያዝ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

(፫) እንዲያዝ፡ የተሰጠውን፡ ትእዛዝ፡ መፈጸም ፡ ያልተቻለ ፡ እንደ፡ሆነ ፤ ተከሳሹ ፡ በሌለበት ፡ ነገሩ ፡ እንዲሰማ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያስብበታል ። በዚህ ፡ መሠረት ፡ ትእዛዝ ፡ የተሰጠ ፡ ሲሆን ፡ ከዚህ ፡ የሚከተሉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ባቀረበው ፡ ክስ ፡ ተከሳሹ ፡ እፍርድ ፡ ቤት ፡ ስላለመቅረቡ ።

**ቍ ፡ ፪፻፵፩ ። ተከሳሹ ፡ በሌለበት ፡ ነገሩ ፡ የሚሰማበት ፡ ሁኔታ ።**

(፩) ተከሳሹ፡ ያለ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ነገሩ ፡ ሊሰማ ፡ በተቀጠረበት ፡ ቀን ፡ ሳይ ቀርብ ፡ የቀረ ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ አለመቅረቡን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በመዝገቡ ፡ ከጻፈ ፡ በኋላ ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ በተጻፈው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ነገሩ ፡ በሌለበት ፡ እንዲ ሰማ ፡ ያዛል ።

(፪) በዚህ ፡ ክፍል ፡ በተጻፈው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በተመለከቱት ፡ ወንጀሎች፡ ካልሆነ፡ በቀር፡ ተከሳሹ ፡ በሌለበት ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ አይሰማም ።

(ሀ) ከአሥራ ፡ ሁለት ፡ በታች ፡ በማያንስ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ የሚያሳስር ፡ ወንጀል ፡ የሠራ ፤ ወይም ፡

(ለ) በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከቍ ፡ ፫፻፶፬ ፡ እስከ ፡ ፫፻፷፭ ፡ ድረስ ፡ ያሉ ትን ፡ ወንጀሎች ፡ ፈጽሞ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ከአምስት ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ በላይ ፡ መቀጫ ፡ በሚያስቀጣ ፡ ወንጀል ፡ የተከሰሰ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

(፫) የተከሰሰው፡ ሰው፡ የውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ ጥገኛ ፡ በመሆኑና ፡ ጥገኛ ፡ ያደረገው ፡ አገር፡ አሳልፎ ፡ ያልሰጠው ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በሌለበት፡ ነገሩ፡ ሊሰማ ፡ የማይቻል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፤ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቍ ፡ ፲፱ ፡ በቀመለከተው ፡ መሠረት ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፩፻፷፪ ። መጥሪያ ።

ተከሳሹ ፡ በሌለበት ፡ ነገሩ ፡ እንዲሰማ ፡ ፍርድ፡ ቤቱ ፤ ትእዛዝ ፡ የሰጠ፡እንደሆነ ፤

(ሀ) ይህ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትዛዝ ፡ ተከሳሹ ፡ የተከሰሰበት ፡ ወንጀል ፡ ዝርዝር ፡ ነገሩ ፡ እንዲሰማ ፡ በተቀጠረበት ፡ ቀን ፡ ተከሳሹ ፡ ሳይቀርብ ፤ ቢቀር ፡ በሌለበት ፡ የሚፈረድ ፡ መሆኑን ፡ የሚገልጽ ፡ የመጥሪያ ፡ ማስታወቂያ ፡ በጋዜጣ ፡ እንዲወጣ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያዛል ።

(ለ) ለተከሳሹ ፡ የሚደርስ ፡ መስሎ ፡ ከታየው ፡ መጥሪያው ፡ የሚደርስበትን ፡ ሌላ ፡ መንገድ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊያዝ ፡ ይችላል ።

ቍጥር ፡ ፩፻፷፫ ። ነገሩ ፡ ስለ ፡ መስማትና ፡ ፍርድ ፡ ስለ ፡ መስጠት ።

(፩) በቍጥር ፡ ፻፷፪ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ተከሳሹ ፡ ያልቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ክሱ ፡ እንደማንኛውም ፡ ክስ ፡ ይቀጥላል ።

(፪) የዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ምስክር ፡ ከተሰማ ፡ በኋላ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ የመጨረሻ ፡ ንግግር ፡ ያደርጋል ።

(፫) ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ እንደማንኛውም ፡ ደንበኛ ፡ ክስ ፡ ፍርድ ፡ ይሰጣል ።

ቍ ፡ ፻፷፬ ። ፍርዱን ፡ ውድቅ ፡ ስለ፡ ማድረግ ።

ፍርዱ ፡ ውድቅ ፡ እንዲሆን ፡ ከቍ ፡ ፻፺፯ ፡ እስከ ፡ ፻፶፱ ፡ በተመለከቱት ፡ ምክንያቶች ፡ መሠረት ፡ ማመልከቻ ፡ ማቅረብ ፡ ይቻላል ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## በግል ፡ ክስ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አለመቅረብ ።

ቍ ፡ ፻፷፭ ። የግል ፡ ከሳሽ ፡ አለመቅረብ ።

(፩) የግል ፡ ከሳሽ ፡ ነገሩ ፡ ሊሰማ ፡ በተቀጠረበት ፡ ቀን ፡ ያለ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ሳይቀርብ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ክሱን ፡ ሰርዞ ፡ ተከሳሹ ፡ ከክሱ ፡ ውጭ ፡ እንዲሆን ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

(፪) በንኡስ ፡ ቍጥር፡ (፩) መሠረት ፡ ክሱ ፡ በተሰረዘ ፡ ጊዜ፡ የግል ፡ ከሳሽ ፡ ክሱ ፡ በተሰረዘበት ፡ በዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ክሱ ፡ እንደ፡ገና ፡ እንዲታይ ለት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ። የግል ፡ ከሳሹ ፡ ነገሩ ፡ ሊሰማ ፡

በተቀጠረበት ፡ ቀን ፡ ሳይቀርብ ፡ የቀረው ፡ ካቅሙ ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ኀይል ፡ መሆኑን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ካላስረዳ ፡ በቀር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማመልከቻውን ፡ አይቀበለውም ።

(፫) ማመልከቻውን፡ በዐሥራ፡ አምስት፡ ቀን፡ ውስጥ፡ ያላቀረበ፡ እንደ፡ሆነ፤ ወይም፡ ማመልከቻውን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያልተቀበለው ፡ እንደ፡ሆነ ፤ የግል ፡ ከሳሹን ፡ በሚመለከተው ፡ ረገድ ፡ የክሱ ፡ መሰረዝ ፡ የመጨረሻ ፡ ይሆናል ።

## ቍ ፡ ፻፷፮ ። ተከሳሹ ፡ ስላለመቅረቡ ።

ተከሳሹ ፡ በሌለ ፡ ጊዜ ፡ በቍ ፡ ፻፷፪ ፡ እና ፡ ፻፷፫ ፡ የተመለከተው ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ። ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ተከሳሹ ፡ እንዲያዝ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

# ምዕራፍ ፡ ፪ ።

# የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ወንጀል ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ።

## ቍ ፡ ፻፷፯ ። ለተከሳሹ ፡ መጥሪያ ፡ ስለ፡ መላክ ።

(፩) የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ወንጀል ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ወይም ፡ የግል ፡ ከሳሹ፡ ተከሳሹ ፡ እንዲጠራ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መጥሪያ ፡ እንዲሰጥ ፡ ያመለክታል ።

(፪) በማመልከቻውና፡ በመጥሪያው ፡ ላይ ፡ የተከሳሹ ፡ ስም ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ወንጀል ፡ የተፈጸመበት ፡ ሁኔታና ፡ ክሱ ፡ የቀረበበት ፡ ሕግና ፡ የሕጉ፡ ቍጥር ፡ መጻፍ ፡ አለበት ።

## ቍ ፡ ፻፷፰ ። በደንብ፡ መተላለፍ ፡ ወንጀል ፡ የተከሰሰ ፡ ሰው ፡ ጥፋተኛነቱን ፡ በጽሕፈት፡ ሊያምን ፡ ይችላል ።

ተከሳሹ ፡ በመጥሪያው ፡ ላይ ፡ ለተከሰሰበት ፡ ወንጀል ፡ ጥፋተኛነቱን ፡ የሚያምን፡ መሆኑን ፡ በጽሑፍ፡ ገልጾ ፡ ለፍርድ፡ ቤቱ፡ መላክ ፡ ይችላል ። በዚህም ፡ ጽሑፍ፡ ላይ ፡ ቀኑና ፡ የተከሳሹ ፡ ፊርማ ፡ መኖር ፡ አለበት ። በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ነገርና፡ በቍ፡ ፻፷፫ ፡ ንኡስ ፡ ቍጥር፡ (፫) የተመለከተው ፡ እንደ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ በመጥሪያው ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መቅረቡ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑ ፡ ሊቀር ፡ ይችላል ።

## ቍ ፡ ፻፷፱ ። ሥነ ፡ ሥርዐትና ፡ ፍርድ ።

(፩) መጥሪያው ፡ ጥፋትን ፡ በማመን ፡ ተጽፎበት ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ የተላከ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የክሱን ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ከዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ አረጋግጦ ፡ በተከሳሹ ፡ ላይ ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጣል ፤ የፍርዱንም ፡ ግልባጭ ፡ ለተከሳሹ ፡ ይልካል ።

BACK



(፪) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የገንዘብ ፡ መቀጫ ፡ ብቻ ፡ የሚፈርድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ወዲያውኑ ፡ ይወስናል ።

(፫) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተከሳሹ፡ እንዲታሰር ፤ የግዴታ ፡ ሥራ ፡ እንዲሠራ፡ ጧይም ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ እንዲሰጠው ፡ ወይም ፡ መውቀስ ፡ ሲፈልግ ፡ ተከሳሹ ፡ እንዲቀርብ ፡ መጥሪያ ፡ ይሰጣል ፤ ለተከሳሹም ፡ የቅጣቱ ፡ ውሳኔ ፡ ከመሰጠቱ ፡ በፊት ፡ የመከላከል ፡ መብት ፡ ይሰጠዋል ።

ቊ ፡ ፻፸ ። ተከሳሹ ፡ ደንብ ፡ በመተላለፍ ፡ ወንጀል ፡ ተከሶ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የመቅረብ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ።

(፩) ተከሳሹ ፡ በመጥሪያው፡ ላይ ፡ ጥፋተኛነቱን፡ በማመን ፡ ያልጻፈ ፡ እንደ፡ሆነ ፤ ነገሩ ፡ እንዲሰማ ፡ በተቀጠረው ፡ ቀንና ፡ ሰዓት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይቀርባል ።

(፪) ዐቃቤ ፡ ሕጉና፡ ተከሳሹ ፡ ምስክሮች ፡ እንዳላቸው ፡ ምስክሮቻቸው ፡ በቀጠሮው ፡ ቀን ፡ እንዲቀርቡ ፡ አስፈላጊውን ፡ ይፈጽማሉ ።

(፫) ሥነ ፡ ሥርዐቱ ፡ በቃል ፡ ይፈጸማል ። ምስክሩ፡ ከሚሰጠው ፡ ቃል ፡ ውስጥ ፡ ዋናውን ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በመዝገቡ ፡ ይጽፋል ። ለፍርዱ ፡ ምክንያት ፡ የሆነውን ፡ ነገርና ፡ ሕግ ፡ በመጥቀስ ፡ ባጭሩ ፡ ጽፎ ፡ በቃል ፡ ፍርድ ፡ ይሰጣል ።

(፬) ተከሳሹ ፡ በግል ፡ ክስ ፡ ያለ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ በቀጠሮው ፡ ቀን ፡ ሳይቀርብ ፡ የቀረ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ወዲያውኑ ፡ ፍርድ ፡ ይሰጣል ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## አካለመጠን፡ ያላደረሱ፡ ወጣቶች፡ ስለ፡ ፈጸሙት፡ ወንጀል፡ ክስ፡ ሥነ፡ ሥርዐት ።

ቊ ፡ ፻፸፩ ። መሠረቱ ።

አካለመጠን ፡ ባላደረሱ ፡ ወጣቶች ፡ ላይ ፡ የሚቀርብ ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ በዚህ፡ ምዕራፍ ፡ በተመለከተው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማል ።

ቊ ፡ ፻፸፪ ። የወንጀሉን ፡ ክስ ፡ የማቅረብ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ።

(፩) አካለመጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ወጣት ፡ በወንጀል ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ ፖሊሱ ፤ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፤ ወላጁ ፡ ወይም ፡ ሞግዚቱ ፡ ወይም ፡ በቅርብ ፡ ወደሚገኘው ፡ የወረዳ ፡ ግዛት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወድያውኑ ፡ ይዞት ፡ ይቀርባል ።

(፪) አካለመጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ወጣት ፡ ያመጣው፡ ሰው ፡ የወንጀሉንና ፡ የምስክሮቹን፡ ዝርዝር፡ እንዲገልጽና ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የአቤቱታ ፡ ማመልከቻ

BACK



ውን፡ እንደ፡ደንቡ፡ እንዲያቀርብ፡ ፍርድ፡ ቤቱ ፡ ይጠይቀዋል ። የሚሰጠውንም፡ ቃል ፡ እና ፡ አቤቱታ ፡ በመዝገብ ፡ ይጽፋል ፤ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ፖሊስ ፡ ምርመራውን ፡ የሚፈጽምበትን ፡ ሁኔታ ፡ የሚገልጽ ፡ መምሪያ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

(፫) የቀረበው ፡ ክስ ፡ ከዐሥር ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በሞት፡ የሚያስቀጣ፡ በሆነ ፡ ጊዜ፡ (ወንጀለኛ፡ መቅጫ፡ ሕግ ፡ ቍ ፡ ፻፸፫) ፡ ዐቃቤ፡ ሕጉ ፡ የክስ ፡ ማመልከቻውን ፡ አዘጋጅቶ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

(፬) ነገሩ ፡ መቀጠር ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ በላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መቅረብ ፡ የሚያስፈልገው ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ወጣት ፡ ነገሩ ፡ በሚሰማበት ፡ ቀን ፡ ለማቅረብ ፡ ለሚችሉ ፡ ለወላጆቹ ፤ ለሞግዚቱ ፡ ወይም ፡ ለዘመዶቹ ፤ እነሱም ፡ የሌሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለወህኒ ፡ ቤት ፡ ሳይሆን ፡ ለአንድ ፡ ድርጅት ፡ (ኢኒስቲቱሽን) ፡ ወይም ፡ እራሱን ፡ ለቻለ ፡ ጨዋ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ይሰጣል ። ምስክሮቹ ፡ነገሩ ፡ በሚሰማበት ፡ ቀን ፡ ሊቀርቡ ፡ ግዴታ ፡ ይገባሉ ።

ቍ፡ ፻፸፫። አካለመጠን፡ያላደረሰውን፡ወጣት፡ ሞግዚት፡ ወደ፡ ፍርድ፡ ቤት፡ ስለ፡መጥራት።

አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ወጣት ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ እና ፡ ወላጆቹ፤ ሞግዚቱ፡ ወይም፡ ሌላ፡ ሰው ፡ ከቤተ፡ ዘመዶቹ ፡ ባልቀረቡ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ፡ ቤቱ ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ እንዳሉ ፡ ጠይቆ ፤ እንዳሉ ፡ ወዲያው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲቀርቡ ፡ መጥሪያ ፡ እንዲደርሳቸው ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

ቍ ፡ ፻፸፬ ። አካለመጠን ፡ ያላደረሱ ፡ ወጣቶች ፡ ጠበቃ፡ እንዲኖራቸው ፡ ስለ፡ማድረግ ።

(ሀ) አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ወጣት ፡ ወላጆቹ ፤ ሞግዚቱ ፡ ወይም ፡ ቤተ ፡ ዘመዱ ፡ ባልቀረቡ ፡ ጊዜ ፤ ወይም ፡

(ለ) አካለመጠን፡ ያላደረሰው፡ ወጣት፡ ከዐሥር፡ ዓመት፡ በላይ፡ በጽኑ፡ እስራት፡ ወይም ፡ በሞት ፡ በሚያስቀጣ ፡ ወንጀል ፡ በተከሰሰ ፡ ጊዜ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ወጣት ፡ የሚረዳው ፡ ጠበቃ ፡ ያዘለታል ።

ቍ ፡ ፻፸፭ ። አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ወጣት ፡ ከችሎቱ ፡ ክፍል ፡ እንዲወጣ ፡ ስለ ማድረግ ።

አካለመጠን፡ ያላደረሰው ፡ ወጣት ፡ ሊሰማው ፡ የማይገባ ፡ ነገር ፡ በማስረጃነት የቀረበ፡ ወይም፡ ትችት ፡ የሚሰጥበት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፤ ሊሰማው ፡ የማይገባው ፡ ነገር በሚነገርበት ፡ ወይም ፡ በሚመሰከርበት ፡ ጊዜ ፡ ከችሎቱ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ እን[ዲ]ወጣ ፡ ይደረጋል ።

**ቍ ፡ ፻፸፯ ። የነገሩ ፡ መሰማት ።**

(፩) አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ወጣት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ነገሩ ፡ በሙሉ ፡ የሚሰማው ፡ በዝግ ፡ ችሎት ፡ ውስጥ ፡ ነው ፤ ነገሩ ፡ በሚሰማበት ፡ ጊዜ ፡ ከምስክሮች ፤ በምስክርነት ፡ ቃላቸውን ፡ ከሚሰጡት ፡ ከልዩ ፡ ዐዋቂዎችና፡ ከወላጆች፡ ወይም፡ ከሞግዚት፡ ወይም ፡ ከበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ አባሎች ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ሊገኝ ፡ አይገባም ። ማንኛውም ፡ ነገር ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሚሰማበት ፡ ጊዜ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ መገኘት ፡ አለበት።

(፪) አካለመጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ወጣት ፡ የተከሰሰበትን ፡ ነገር ፡ የሚሰማው ፡ ችሎት፡ በሌላ ፡ ነገር ፡ ተሰይሞ ፡ ከሚያነጋግረው ፡ አኳኋንና ፡ ሁኔታ ፡ የተለየ ፡ ይሆናል።

(፫) በቍ ፡ ፻፸፬፡ ንኡስ፡ ቍጥር ፡ ፩፡ መሠረት፡ የቀረበው ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ አቤቱታ፡ ወይም ፡ በቍ ፡ ፻፸፭ ፡ ንኡስ፡ ቍጥር ፡ ፫፡ መሠረት ፡ የቀረበው ፡ ክስ ፡ ማመልከቻ፡ አካለመጠን ፡ ላላደረሰው፡ ወጣት ፡ ከተነበበለት ፡ በኋላ ፡ ለክሱ ፡ ወይም፡ ለአቤቱታው ፡ የሚሰጠው ፡ መልስ ፡ እንዳለው ፡ ይጠየቃል ።

(፬) ተከሳሹ፡ በሚሰጠው፡ መልስ፡ የቀረበበትን፡ ክስ፡ ወይም፡ አቤቱታ ፡ በሙሉ፡ ዐውቆ ፡ ያመነ ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በታየው ፡ ጊዜ ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ወጣት፡ የሰጠውን፡ መልስ፡ በመዝገብ ፡ ጽፎ ፡ ወዲያውኑ፡ የጥፋተኛነት ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

(፭) ተከሳሹ ፡ የተከሰሰበትን ፡ ወንጀል ፡ በሙሉ ፡ ከተረዳው ፡ በኋላ ፡ ክሱን ፡ ወይም ፡ አቤቱታውን ፡ ያላመነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለቀረበው ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ አቤቱታ ፡ ለመመስከር ፡ የሚጠሩትን ፡ ምስክሮች ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይጠይቃል ። አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ወጣት ፡ ወይም ፡ እንደራሴው ፡ ወይም ፡ ጠበቃው፡ ማንኛውም ፡ ምስክር ፡ እንዲጠራለት ፡ ማድረግ ፡ ይችላል ።

(፮) ምስክሮቹን ፡ ሁሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ፡ በጥያቄ፡ ከመረመረ ፡ በኋላ ፡ የተከሳሹ ፤ ወገን ፡ መስቀልያ፡ ጥያቄ ፡ ሊጠይቅ፡ ይችላል። የሚሰጠው ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ በመዝገብ ፡ ይጻፋል ።

(፯) ማስረጃው ፡ ተሰምቶ ፡ ካለቀና ፡ የተከሳሹ ፡ ወገን ፡ ስለ ፡ ነገሩ ፡ ጠቅላላ ፡ ንግግር ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፤ ፍርድ ፡ ይሰጣል ።

**ቍ ፡ ፻፸፰ ። ፍርድ ።**

(፩) ፍርዱ ፡ በምን፡ ሕግ፡ መሠረት፡ እንደ፡ ተሰጠ፡ በፍርዱ ፡ ውስጥ ፡ ይጠቀሳል ። አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ወጣት ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ ያልተገኘ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ወዲያውኑ ፡ በነጻ፡ ይለቀቃል። ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ፡ በቍ ፡ ፻፸፩ ፡ እና፡ በሚቀጥሉት ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚገባውን ፡ ጥንቃቄ ፡ ወይም ፡ ቅጣት ፡ ይወስናል ።

(፪) አካለመጠን ፡ ላላደረሰው ፡ ወጣት ፡ የሚጠቅም ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ እንዲያስችለው፡ ስለ ፡ ወጣቱ፡ ጠባይና፡ ስለ፡ ቀድሞው ፡ ጥፋቱ ፡ ለመጠየቅ ፡ ከማ

BACK



ንኛውም ፡ ድርጅት ፡ ማንኛውንም ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ እንደራሴ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ፡ መጥራት ፡ ይችላል ።

(፫) እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ የሚሰጡት ፡ ቃል ፡ ከተሰማ ፡ በኋላ ፡ የተከሳሹ ፡ ወገን መልስ ፡ መስጠትና፡ ስለ፡ ጠባዩ፡ ምስክሮች ፡ መጥራት ፡ ይችላል። እነዚህንም ምስክሮች ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከጠየቀ ፡ በኋላ ፡ የተከሳሹ ፡ ወገን ፡ ስለ ፡ ቅጣቱ፡ በቃል ፡ ሊያመለክት ፡ ይችላል ።

(፬) ፍርድ ፡ የሚሰጠው፡ እንደ ፡ ማንኛውም ፡ ደንበኛ ፡ ክስ ፡ ነው ። ፍርድ ፡ ቤቱ ውሳኔውን ፡ አካለመጠን ፡ ላላደረሰው ፡ ወጣት ፡ ካስረዳው ፡ በኋላ ፡ ለወ ፊቱ ፡ ጠባዩን ፡ እንዲያርም ፡ ያስጠነቅቀዋል ።

ቍ ፡ ፻፸፫ ። በወላጆችና ፡ በሞግዚት ፡ ላይ ፡ የሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ።

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አካለመጠን፡ ያላደረሰው ፡ ወጣት ፡ ወላጆች ፡ ወይም ፡ በሕ ኀላፊ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ተግባራቸውን ፡ በሚገባ ፡ ያልፈጸሙ ፡ ሲመስለው ፡ ጠንቀቂያና ፡ ምክር ፡ ሊሰጣቸው ፡ ወይም ፡ ሊወቅሳቸው ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፻፸፬ ። በአንዳንድ ፡ ሁኔታ ፡ አካለመጠን ፡ ላላደረሰው ፡ ወጣት ፡ ስለሚከፈለ አበል ።

(፩) ቤት ፡ ሰቦቹ ፡ ወይም፡ በሕግ ፡ ኀላፊ ፡ የሆኑት ፡ ሰዎች ፡ አካለመጠን ፡ ያ ረሰውን ፡ ወጣት ፡ በሚገባ ፡ ባለመጠበቃቸውና ፡ ባለመያዛቸው ፡ ምክንያ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ወጣቱን ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ እንዲያድግ ፡ ወይም ፡ ወደሚ ምበት ፡ ወይም ፡ ወደሚሻሻልበት ፡ ድርጅት ፡ ሲልከው ፤ ለእድገቱና ፡ ለኑሮ የሚደረገውን ፡ ወጪ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ወላጆቹ ፡ ወይም ፡ በሕ ኀላፊ ፡ የሆኑት ፡ ሰዎች ፡ እንዲከፍሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፪) የዚህ ፡ ግዴታ ፡ ልክና ፡ ጊዜ ፡ በፍርዱ ፡ ውስጥ ፡ መወሰን ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፻፸፭ ። አካለመጠን ፡ ባላደረሰ ፡ ወጣት ፡ ላይ ፡ የሚሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ መለ ወይም ፡ ማሻሻል ።

አካለመጠን፡ ባላደረሰው፡ ወጣት ፡ ላይ ፡ ትእዛዝ ፡ የሰጠ ፡ ማንኛውም ፡ ፍ ቤት ፡ በራሱ ፡ አስተያየት ፡ ወይም ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ወጣት ፤ በ ኀላፊ፡ የሆነለት፡ ሰው፡ ወይም፡ አደራ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ድርጅት ፡ ለከተው ፡ ጊዜ ፡ ለወጣቱ ፡ ጥቅም ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነው ፡ መሠረት ፡ ትእዛ መለወጥ ፡ ወይም ፡ ማሻሻል ፡ ይችላል ።

BACK



# አምስተኛ ፡ መጽሐፍ ።

## ስለ ፡ ይግባኝና ፡ ተከሳሹ ፡ በሌለበት ፡ የተሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ ለማሻር ፡ ስለሚቀርበው ፡ ማመልከቻ ።

### ፩ኛ ፡ አንቀጽ ።

### ይግባኝ ።

ቍ ፡ ፻፹፩ ። መሠረቱ ።

(፩) የወንጀል ፡ ፍርድ፡ ቤት ፡ በተከሳሹ ፡ ላይ ፡ ጥፋተኛ ፡ መሆኑን ፡ በመፍረዱ ፤ ለጊዜው ፡ የመልቀቅ ፡ ወይም ፡ ነጻ ፡ የመለቀቁ ፡ ፍርድ ፡ በመሰጠቱ ፡ የሚቀርቡ ፡ ይግባኞች ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማሉ ።

(፪) ሁለተኛ፡ ይግባኝ ፡ በቍ ፡ ፻፹፪ ፡ መሠረት ፡ ይቀርባል ።

ቍ ፡ ፻፹፪ ። ይግባኝ ፡ ለማየት ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ።

(፩) በሚሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ይግባኙ ፡ ከዚህ ፡ በሚቀጥለው ፡ ደረጃ ፡ ይቀርባል ።

(ሀ) ከወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወረዳው ፡ በሚገኝበት ፡ አውራጃ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ሥልጣኑ ፡ ለሆነው ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤

(ለ) ከአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤

(ሐ) ከከፍተኛው፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤

(፪) በሚሰጠው ፡ ፍርድ ፡ የሚቀርበው ፡ ሁለተኛው ፡ ይግባኝ፡ ከዚህ ፡ በሚቀጥለው ፡ ደረጃ ፡ ይቀርባል ።

(ሀ) አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በይግባኝ ፡ ሰሚነት ፡ ያየው ፡ ይግባኝ ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤

(ለ) ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በይግባኝ ፡ ሰሚነት ፡ ያየው ፡ ይግባኝ ፡ ለጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ።

ቍ ፡ ፻፹፫ ። ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ችሎት ፡ ስለሚቀርቡ ፡ ማመልከቻዎችን ።

(፩) በቍ፡ ፻፹፪፡ መሠረት፡ የይግባኝ ፡ መብቱን፡ የፈጸመ ፡ ባለጕዳይ ፡ ነገሩ ፡ እ ፡ ደገና ፡ እንዲታይለት ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ለማመልከት ፡ በቍጥር ፻፹፪ ፡ የተመለከተው ፡ አይከለክለውም ።

BACK



(፪) ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ከሚቀርበው፡ ማመልከቻ ፡ ጋራ ፤

(ሀ) አመልካቹ ፡ ያልተስማማበትን ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ ፍርዶችና ፤

(ለ) አመልካች፡ ነገሩ፡ እንደ፡ ገና ፡ እንዲታይለት፡ የሚጠይቅበትን ፡ ምክንያት ፡ ባጭሩ ፡ የሚገልጽ፡ የይግባኝ ፡ ማመልከቻ ፡ አያይዞ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪፻፬ ። የትእዛዝ ፡ ይግባኝ ፡ ስላለመኖሩ ።

ከዚህ ፡ በታች ፡ ባሉት ፡ ሁኔታዎች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሚሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ይግባኝ ፡ ለማለት ፡ አይቻልም ።

(ሀ) በቍ ፡ ፺፬ ፡ መሠረት ፡ ቀጠሮ ፡ መስጠት ፡ ወይም ፡ አለመስጠት ፤ ወይም ፡

(ለ) በቍ ፡ ፪፴፩ ፡ መሠረት ፡ ስለሚቀርብ፡ መቃወሚያ ፤ ወይም ፡

(መ) በቍ ፡ ፪፶፯ ፡ መሠረት ፡ ማስረጃን ፡ ስለ፡መቀበል ፡ ወይም ፡ ስላለመቀበል ። ነገር፡ ግን፡ የጥፋተኛነት፡ ውሳኔ፡ በተሰጠበት፤ ለጊዜው ፡ በመልቀቅ ፡ ወይም፡ ነጻ፡ በመልቀቅ፡ ፍርድ፡ ተሰጥቶ፡ ይግባኝ ፡ በተባለበት ፡ ጊዜ ፡ እነዚህ ፡ የተሰጡት ፡ ትእዛዞች ፡ ይግባኝ ፡ ለማለት ፡ ምክንያቶች ፡ ለመሆን ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፪፻፭ ። የጥፋተኛነት፡ ውሳኔ፡ በተሰጠበት፡ ወይም፡ በቅጣቱ፡ ይግባኝ፡ ስለ፡ ማለት።

(፩) የተፈረደበት፡ ሰው ፡ የጥፋተኛነት፡ ውሳኔ፡ በተሰጠበትና፡ በቅጣቱ ፡ ይግባኝ ፡ ማለት ፡ ይችላል ።

ነገር፡ ግን፡ ተከሳሹ፡ የተከሰሰበትን ፡ ወንጀል፡ ያመነ ፡ ሆኖ ፡ በእምነቱ ፡ መሠረት ፡ ጥፋተኛነቱ ፡ ከተወሰነ ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ ቅጣቱ ፡ ልክ ፡ ወይም ፡ ቅጣቱ ፡ ሕጋዊ ፡ ላለመሆኑ ፡ ይግባኝ ፡ ማለት ፡ ይችላል ፡ እንጂ ፤ የጥፋተኛነት ፡ ውሳኔ ፡ በተሰጠበት ፡ ላይ ፡ ይግባኝ፡ ማለት ፡ አይችልም ።

(፪) ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ወይም፡ የግል ፡ ከሳሹ ፤ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሚሰጠው ፡ ለጊዜው፡ በመልቀቅ ፡ ወይም ፡ ነጻ ፡ በመልቀቅ ፡ ፍርድ ፡ ላይ ፤ ወይም ፡ ቅጣቱ ፡ በቂ ፡ አይደለም ፡ በማለት ፡ ይግባኝ ፡ ማለት ፡ ይችላል ።

(፫) አካለመጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ወጣት ፡ ወይም ፡ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡ ይግባኝ ፡ ሲል ፡ ይግባኙን ፡ የሚያቀርብለት ፡ እንደራሴው ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪፻፮። የተበደለው ፡ ሰው ፡ ካሣ ፡ በሚጠይቅበት ፡ ነገር ፡ ይግባኝ ፡ ስለ ፡ ማለት ።

(፩) በወንጀለኛው ፡ መቅጫ፡ ሕግ፡ ቍ ፡ ፻ ፡ መሠረት፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ካሣ ፡ ማግኘት ፡ አይገባውም፡ ብሎ ፡ የፈረደ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ የተበደለው ፡ ወገን ፡ በውሳኔው ፡ ይግባኝ ፡ ለማለት ፡ ይችላል ።

(፪) ፍርድ፡ ቤቱ፡ የተበደለው፡ ሰው ፡ ካሣ ፡ መቀበል ፡ ይገባዋል ፡ ብሎ ፡ በፈረደ ፡ ጊዜ ፡ ተከሳሹ ፡ በውሳኔው ፡ ይግባኝ ፡ ማለት ፡ ይችላል ።

(፫) በተፈረደው ፡ የካሣ ፡ ልክ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍ ፡ ፻፹፩፻፺፫ ፡ መሠረት ፡ ይግባኝ ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ።

(፬) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፡ ይግባኝ ፡ ሲባል ፡ የጥፋተኛነት ፡ ውሳኔ ፡ በተሰጠበት ፡ ወይም ፡ በቅጣቱ ፡ ውሳኔ ፡ ይግባኝ ፡ ሲቀርብ ፡ ይግባኙን ፡ የሚሰማው ፡ የወንጀል ፡ ይግባኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የጥፋተኛነት ፡ ውሳኔ ፡ በተሰጠበት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ቅጣቱ ፡ ይግባኝ ፡ ባልተባለ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ይግባኙ ፡ በተተወ፡ ጊዜ ፡ የካሣውን ፡ ፍርድ ፡ ይግባኝ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ችሎት ፡ ይሰማል ።

<u>ቍ ፡ ፻፹፯ ። ይግባኝ ፡ ማለትን ፡ ስለ ፡ ማስታወቅና ፡ የይግባኝ ፡ ማመልከቻ ።</u>

(፩) ይግባኝ ፡ ማለቱን፡ ለማስታወቅ፡ የሚጽፈውን ፡ ማመልከቻ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ወይም ፡ ጠበቃው ፡ ይግባኝ ፡ የሚልበት ፡ ፍርድ፡ በተሰጠ ፡ በዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ። ይግባኝ ፡ ማለቱን ፡ ለማስታወቅ ፡ የጻፈው ፡ ማመልከቻ ፡ ለፍርድ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ (ለሬጂስትራሩ) ፡ ሲደርሰው፡ ይግባኝ ፡ የተባለበትን ፡ ፍርድ ፡ አስገልብጦ ፡ ለይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ወይም ፡ ለጠበቃው ፡ ይሰጣል ። ይግባኝ፡ ባዩ ፡ በእስር፡ ቤት፡ ያለ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ይግባኝ ፡ የተባለበትን፡ ፍርድ፡ ግልባጭ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ለይግባኝ፡ ባይ ፡ እንዲሰጥ፡ ለወህኒ፡ ቤቱ ፡ ሹም ፡ ይልካል ። ፍርዱ፡ ተገልብጦ፡ ያለቀበት ፡ ቀንና ፡ ኋላም፡ ለይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ወይም ፡ ለጠበቃው ፡ ወይም ፡ ለወህኒ ፡ ቤቱ ፡ ሹም ፡ የደረሰበትን፡ ቀን፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ በፊርማው ፡ ያረጋግጣል ።

(፪) በቍ ፡ ፻፹፯ ፡ መሠረት፡ የሚቀርበው፡ የይግባኝ፡ ማመልከቻ ፡ የፍርድ ፡ ግልባጭ ፡ በደረሰው ፡ በሠላሳ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ፍርዱን ፡ ለሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ መቅረብ ፡ አለበት ።

(፫) ተከሳሹ ፡ በእስር፡ ቤት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ፡ የወህኒ ፡ ቤቱ ፡ ሹም ፡ ሳይዘገይ ፡ የይግባኙን ፡ ማመልከቻ ፡ ይግባኝ ፡ የተባለበትን ፡ ፍርድ ፡ ለሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መላክ ፡ አለበት ።

(፬) የይግባኙ ፡ ማመልከቻ ፡ ግልባጭ ፡ ለመልስ ፡ ሰጪው ፡ እንዲደርሰው ፡ መደረግ ፡ አለበት ።

<u>ቍ ፡ ፻፹፰ ። ፍርድ ፡ እንዳይፈጸም ፡ ስለ ፡ ማገድ ።</u>

(፩) ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ የተፈረደበት ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ የይግባኝ ፡ ማስታወቂያ ፡ የሰጠ፡ እንደ፡ሆነ፤ ይግባኙ፡ ሳይሰማ፡ ወይም ፡ ይግባኙን፡ ይግባኝ፡ ባዩ፡ ካልተወ ፡ በቀር ፤ የግርፋቱ ፡ ቅጣት ፡ አይፈጸምም ።

(፪) ተከሳሹ ፡ ይግባኙ ፡ እስኪወሰን ፡ ድረስ ፡ በዋስትና ፡ ወረቀት ፡ የተለቀቀ ፡

BACK



እንደ፡ ሆነ ፤ የእስራቱ ፡ ቅጣት ፡ የይግባኙ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ እስኪሰጥ ፡ ድረስ ፡ አይጀመርም ።

(፫) ይግባኝ ፡ የተባለበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲፈጸሙ ፡ ለጥንቃቄ ፡ የሰጣቸው ፡ ትእዛዞች ፡ ይግባኝ ፡ የተባለባቸው ፡ ቢሆኑም ፡ መፈጸም ፡ አለባቸው ።

(፬) ስለ ፡ ካሣ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ኪሣራ ፡ ወጪ ፡ የተሰጠ ፡ ፍርድ ፡ ከመፈጸም ፡ አይታገድም ።

(፭) ይግባኙ፡ ከመሰማቱ፡ በፊት ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ይግባኙ ፡ በሚሰማበት ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ፍርዱ ፡ እንዲታገድ ፡ ለይግባኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማመልከት ፡ ይቻላል ።

<u>ቍ ፡ ፫፻፶፱ ። በይግባኝ ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ ስለሚጻፈው ።</u>

(፩) ይግባኝ ፡ ማመልከቻ ፡ ይግባኝ ፡ በተባለበት ፡ ፍርድ ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ የመቃወሚያ ፡ ምክንያቶች ፡ ባጭሩ ፡ ለይቶ ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹን ፡ ነገሮች ፡ በክርክር ፡ መልክ ፡ ሳይተቹ፡ በተራ ፡ ቍጥር ፡ በዝርዝር ፡ መጻፍ ፡ አለባቸው ። ከይግባኝ ፡ ማመልከቻው ፡ ጋራ ፡ ይግባኝ ፡ የተባለበት ፡ ፍርድ ፡ ግልባጭ ፡ መቅረብ ፡ አለበት ። የይግባኙ፡ ማመልከቻ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ እንዲወገድለት ፡ የሚጠይቀውን ፡ የፍርድ ፡ ልመናውን ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።

(፪) የይግባኙን፡ ማመልከቻ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ራሱና ፡ ጠበቃ ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ጠበቃው ፡ ይፈርማሉ ።

<u>ቍ ፡ ፫፻፷ ። ለይግባኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለሚላኩ ፡ የይግባኝ ፡ ማመልከቻዎች ፡ መረጃዎችና ፡ (ኤግዚቢቶች ፡ ) እና፡ መዝገብ ።</u>

(፩) ይግባኝ ፡ የተባለበትን ፡ ፍርድ ፡ የሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የይግባኝ ፡ ማመልከቻ ፡ እንደ ፡ ደረሰው ፡ ካ፲፭ ፡ ቀን ፡ ባልበለጠ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የመዝገቡን ፡ ግልባጭና ፡ የይግባኝ ፡ መዝገብ ፡ ( ያለ ፡ እንደሆን ) ፡ ይግባኝ ፡ እላለሁ ፡ ሲል ፡ ያስታወቀበትንም ፡ ከይግባኙ ፡ ማመልከቻ ፡ ጋራ ፡ መረጃዎችን ፡ ጭምር ፡ ለይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይልካል ።

፪) መዝገቡን፡ መገልበጥ፡ የነገሩን፡ በይግባኝ፡ መታየት ፡ የሚያዘገየው ፡ ሲሆን፡ ይግባኝ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ፡ ቤት ፡ የመዝገቡ ፡ መገልበጥ ፡ እንዲቀርና ፡ ዋናው ፡ መዝገብ ፡ ባትውስት ፡ እንዲቀርብለት ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

<u>ቍ ፡ ፫፻፷፩ ፡ የይግባኝ ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ይግባኝ ፡ ለማቅረብ ፡ ፈቃድ ፡ ለማግኘት፡ የሚቀርብ ፡ ማመልከቻ ።</u>

(፩) ይግባኝ፡ የተባለበትን፡ፍርድ፡ የሰጠው፡ ፍርድ፡ ቤት፡ የይግባኙ፡ ማስታወቂያ፡ ወይም፡ ማመልከቻ፡ ጊዜው፡ ካለፈ፡ በኋላ፡ የቀረበለት፡ እንደ፡ሆነ፡ አልቀበልም፡ ለማለት ፡ ይችላል ። በዚህ፡ ጊዜ ፡ የይግባኙን ፡ ማስታወቂያ ፡ ወይም ፡ ማመል

BACK



ከቻ ፡ የሚያቀርበው ፡ ሰው ፡ የይግባኙ ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ይግባኙን ፡ ለማ ቅረብ ፡ እንዲፈቀድለት ፡ ማመልከቻውን ፡ በጽሑፍ ፡ ለይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲያቀርብ ፡ ያደርጋል ።

(፪) ማመልከቻውም ፡ የይግባኙ ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ነገሩ ፡ ሊሰማ ፡ ይገባል ፡ የሚባልበትን፡ ምክንያትና፡ የዘገየበትን፡ ምክንያት፡ ገልጾ ፡ ማስረዳት ፡ አለበት።

(፫) የይግባኝ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የይግባኙ ፡ ጊዜ ፡ ያለፈው ፡ በአመልካቹ ፡ ጥፋት፡ ባልሆነ ፡ ምክንያት ፡ ለመሆኑ ፡ ካልተረዳ ፡ በቀር ፡ ጊዜው ፡ ያለፈ ፡ ይግባኝ ፡ እንዲሰማ ፡ አይፈቀድም ።

(፬) ጊዜው ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ይግባኙ ፡ እንዲሰማ ፡ የይግባኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የወ ሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የይግባኙ ፡ ማመልከቻ ፡ የሚቀርብበትን ፡ ቀን ፡ ይወስናል።

## ቍ ፡ ፻፺፪ ። የነገሩ ፡ መሰማት ።

የይግባኙ፡ ፍርድ ፡ ቤት፡ ሰብሳቢ፡ ዳኛ ፡ ይግባኙ ፡ የሚሰማበትን ፡ ቀን ፡ ወስኖ፡ ለነገረተኞቹ ፡ ይነገራቸዋል ። ይግባኝ፡ ባዩ ፡ ይግባኙን ፡ ማስረዳት ፡ ይጀም ራል ፤ መልስ ፡ ሰጪውም ፡ መልስ ፡ ይሰጣል ፤ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ የመልስ ፡ መልስ ፡ የመስጠት ፡ መብት ፡ አለው ።

## ቍ ፡ ፻፺፫ ። ከነገረተኞቹ ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ ይግባኙ ፡ በሚሰማበት ፡ ቀን፡ስላለመቅረቡ ።

(፩) ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ወይም ፡ ጠበቃው ፡ የይግባኙ ፡ ቀን ፡ ተነግሯቸው ፡ በተወሰ ነው ፡ ቀን ፡ ያልቀረቡ ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ ይግባኙ ፡ ይሰረዛል ።

ነገር፡ ግን፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ወይም ፡ ጠበቃው ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ምክ ንያት ፡ ሳይቀርብ ፡ መቅረቱን ፡ ያረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይግባኙ ፡ እንዲሰማ ፡ ማድረግ ፡ ይቻላል ።

(፪) መልስ ፡ ሰጪው ፡ ወይም ፡ ጠበቃው ፡ ያልቀረቡ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ በሌሉበት ፡ ነገሩ ፡ ይቀጥላል ።

## ቍ ፡ ፻፺፬ ። ተጨማሪ ፡ ማስረጃ ።

(፩) የይግባኝ፡ ሰሚ ፡ ፍርድ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ በሚያይበት ፡ ጊዜ፡ ተጨማሪ ፡ ማስ ረጃ ፡ የሚያስፈልግ ፡ መስሎ ፡ ከታየው ፤ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ ሊታየው ፡ የቻ ለበትን ፡ ምክንያት ፡ በመዝገብ ፡ ጽፎ ፡ ማስረጃውን ፡ መቀበል ፡ ይችላል ።

(፪) በንኡስ ፡ ቍጥር፡ (፩) መሠረት ፡ የሚቀርብ ፡ ማስረጃ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ፡ ፍርድ፡ ቤት፡ ነገሩ፡ በተሰማበት፡ ጊዜ፡ እንደ፡ ቀረበ፡ ዐይነት ፡ ሆኖ፡ ይቈጠራል።

## ቍ ፡ ፻፺፭ ። የይግባኝ ፡ ሰሚ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ።

(፩) ይግባኙ ፡ በሚሰማበት ፡ ጊዜ ፡ በነገሩ፡ ውስጥ ፡ ለመግባት ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ የሌለ፡ መስሎ ፡ ከታየው ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኙን ፡ ማሰና በት ፡ አለበት ።

BACK



(፪) በነገሩ ፡ ለመግባት፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ያለ ፡ በመሰለው ፡ ጊዜ ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከዚህ ፡ የሚቀጥሉትን ፡ ይፈጽማል ።

(ሀ) ተከሳሹን ፡ ነጻ ፡ በመልቀቅ ፡ ወይም ፡ ለጊዜው ፡ በመልቀቅ ፡ በተሰጠ ፡ ትእዛዝ ፡ ይግባኝ ፡ የተባለ ፡ ሲሆን ፤ ትእዛዙን ፡ ሰርዞ ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ሌላ ፡ ፍርድ፡ ቤት ፡ ነገሩን ፡ እንደ፡ገና ፡ እንዲያይ ፡ ማዘዝ ፡ ወይም ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊፈርድበት ፡ ይችላል ፤ ወይም ፡

(ለ) ጥፋተኛ፡ ነው፡ በተባለበት፡ ውሳኔ፡ እና፡ በቅጣቱ፡ ይግባኝ፡ በተባለ፡ ጊዜ ፤

(፩) ጥፋተኛ ፡ ነው ፡ የተባለበትን ፡ ውሳኔና ፡ ቅጣቱን ፡ ሰርዞ ፡ ተከሳሹን ፡ በነጻ ፡ ለመልቀቅ ፡ ይችላል ፤ ወይም ፡

(፪) ፍርዱን ፡ ለውጦ ፡ ወይም ፡ ሳይለውጥ ፡ ቅጣቱን ፡ ያጸናል ፤ ይጨምራል ፤ ወይም ፡ ይቀንሳል ።

(ሐ) ጥፋተኛ ፡ ነው ፡ በተባለበት ፡ ውሳኔ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ይግባኝ ፡ በተባለ ፡ ጊዜ፡ ፍርዱንና ፡ ቅጣቱን ፡ ሰርዞ ፡ ተከሳሹን ፡ በነጻ ፡ ለመልቀቅ ፡ ይችላል ።

(መ) በቅጣቱ ፡ ላይ፡ ብቻ ፡ ይግባኝ ፡ በተባለ ፡ ጊዜ ፡ ቅጣቱን ፡ ያጸናል ፤ ይጨምራል ፤ ወይም ፡ ይቀንሳል ።

(፫) <u>የይግባኝ ፡ ሰሚ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው</u> ፡ የተባለበትን ፡ ውሳኔ ፡ አጽንቶ ፡ ቅጣቱን ፡ የለወጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ቅጣቱን ፡ አጽንቶ ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው ፡ የተባለበትን ፡ ውሳኔ ፡ የለወጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው ፡ በተባለበት ፡ ወይም ፡ ቅጣቱ፡ እንዲለወጥ ፡ በተወሰነው ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ሁለተኛ ፡ ጊዜ፡ ይግባኝ ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ።

<u>ቍ ፡ ፻፺፯ ። የተፈረደባቸው ፡ ብዙ ፡ ሰዎች፡ ሆነው፡ አንዱ፡ ብቻ ፡ ይግባኝ ፡ ሲያቀርብ ።</u>

(፩) ለይግባኝ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ፡ ቤት ፡ የቀረበው፡ ይግባኝ ፡ ስለ፡ ተፈረደባቸው ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ የሚመለከት ፡ ሆኖ፡ ይግባኝ፡ ያለው፡ ግን ፡ የተፈረደበት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ብቻ፡ በሆነ፡ ጊዜ ፤ ከዚህ፡ በታች፡ እንደተመለከተው ፡ ሲሆን፤ የይግባኙ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ይግባኝ ፡ ላላሉትም ፡ ሰዎች ፡ ይግባኝ ፡ እንዳሉ ፡ ተቈጥሮ ፡ ይፈጸምላቸዋል ፡ ለማለት ፡ የሚችለው ፤

(ሀ) በይግባኝ፡ የተሰጠው፡ ፍርድ፡ ለይግባኝ፡ ባዩ፡ የሚጠቅም፡ በሆነ፡ ጊዜና ፡

(ለ) ተከሳሾቹ ፡ ይግባኝ፡ ቢሉ ፡ ኖሮ ፡ በፍርዱ ፡ እነሱም ፡ ሊጠቀሙ ፡ ይችሉ ፡ ነበር ፡ የሚያሰኝ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

(፪) ፍርዱ፡ በይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ላይ ፡ ጉዳት፡ የሚያመጣበት ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ይግባኝ፡ ባላሉ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ አይፈጸምም ።

## አንቀጽ ፡ ፰ ።

## ተከሳሹ ፡ በሌለበት ፡ የተፈረደውን፡ ፍርድ ፡ ውድቅ ፡ ለማድረግ ፡ ስለሚቀርብ ፡ ማመልከቻ ።

ቍ ፡ ፻፺፯ ። ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ።

እንድ ፡ ሰው ፡ በሌለበት ፡ ሲፈረድበት ፡ የፈረደበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፍርዱን ፡ ውድቅ ፡ እንዲያደርግለት ፡ ማመልከቻ ፡ ማቅረብ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፻፺፰ ። ማመልከቻው ፡ የሚቀርብበት ፡ ጊዜና ፡ ዐይነት ።

በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ መሠረት ፡ የሚቀርብ ፡ ማመልከቻ ፡ በሌለበት ፡ የተፈረደበት ፡ ሰው ፡ ፍርዱን ፡ ካወቀበት ፡ ቀን፡ አንሥቶ ፡ በሠላሳ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ መቅረብ ፡ አለበት ። እንዲሁም ፡ ማመልከቻውን ፡ ለማቅረብ ፡ ምክንያት ፡ የሆነውን ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፻፺፱ ። ማመልከቻውን፡ ለመቀበል ፡ የሚፈቀድባቸው ፡ ምክንያቶች ።

ከዚህ ፡ በታች ፡ የተመለከቱትን ፡ ማስረዳት ፡ የተቻለ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ መሠረት ፡ የሚቀርብ ፡ ማመልከቻ ፡ ሊፈቀድ ፡ ይችላል ።

(ሀ) እንዲቀርብ ፡ መጥሪያ ፡ ያልደረሰው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡

(ለ) ራሱ ፡ ወይም ፡ ጠበቃው ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ኀይል ፡ ምክንያት ፡ መቅረብ ፡ አለመቻሉን ፡ ያስረዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪፻ ። ማመልከቻው ፡ ሲቀርብ ፡ ስለሚፈጸመው ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ።

(፩) ማመልከቻው ፡ ሲቀርብ ፡ ግልባጩ ፡ ለዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ይላካል ፤ ለአመልካቹና ፡ ለዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ የቀጠሮው ፡ ቀን ፡ ይነገራቸዋል ።

(፪) አመልካቹ ፡ በተወሰነው ፡ ቀጠሮ ፡ ሳይቀርብ ፡ የቀረ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ማመልከቻው ፡ ውድቅ ፡ እንዲሆን ፡ ይወሰናል ።

ቍ ፡ ፪፻፩ ። የነገሩ ፡ መሰማት ።

(፩) አመልካቹ ፡ ወይም ፡ ጠበቃው ፡ ማመልከቻውን ፡ በመደገፍ ፡ ይናገራል ፤ ዐቃቤ ፡ ሕጉም ፡ መልስ ፡ ይሰጣል ፤ አመልካቹ ፡ የመልስ ፡ መልስ ፡ የመስጠት ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በማመልከቻው ፡ ላይ ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጣል ።

ቍ ፡ ፪፻፪ ። ፍርድ ።

(፩) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማመልከቻውን ፡ በቍ ፡ ፻፺፱ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት፡ ፡ ፈቅዶ ፡ የተቀበለው ፡ ሲሆን ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነገሩን ፡ እንደገና ፡ እንዲያይ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ። ዓቃቢ ፡ ሕጉም ፡ ክሱን ፡ ሥልጣን ፡ ላለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያቀርባል ።

BACK



(፪) ፍርድ ፡ ቤቱ፡ ማመልከቻውን፡ ሳይቀበል ፡ የቀረ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ አስፈላጊውን ፡ ተጨማሪ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

(፫) ማመልከቻውን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ፡ ሳይቀበል፡ ቀርቶ ፡ ውድቅ ፡ እንዲሆን ፡ በመወሰኑ ፡ ይግባኝ ፡ ማለት ፡ አይቻልም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ተፈረደበት ፡ ቅጣት ፡ ብቻ ፡ ማመልከቻው ፡ ውድቅ ፡ እንዲሆን ፡ ከተወሰነበት፡ ቀን ፡ እንሥቶ ፡ በዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ይግባኝ ፡ ቢል ፡ አይከለከልም ።

# ስድስተኛ ፡ መጽሐፍ ።

## የቅጣት ፡ አፈጻጸም ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

**ቍ ፡ ፪፻፫ ። መሠረቱ ።**

(፩) ማንኛውም፡ ፍርድ ፡ ቤት፡ በወንጀል፡ ነገር፡ የቅጣት ፡ ፍርድ ፡ ከሰጠ ፡ በኋላ ፡ በዚህ፡ መጽሐፍ ፡ መሠረት፡ የቅጣቱ ፡ ፍርድ ፡ እንዲፈጸም ፡ ወይም ፡ ቍጥጥር ፡ እንዲደረግ ፡ ለአስፈላጊው፡ ባለሥልጣን ፡ አስፈላጊውን ፡ ማዘዣ ፡ ወይም ፡ ማንኛውንም ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

(፪) በቍ ፡ ፪፻፰ ፡ የተጻፈውን፡ የዚህ፡ ቍጥር ፡ ድንጋጌ ፡ አይለውጠውም ።

**ቍ ፡ ፪፻፬ ። የሞት ፡ ፍርድ ፡ ስለ ፡ ተፈረደበት ፡ ሰው ፡ የሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ።**

(፩) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ሞት ፡ ሲፈረድበት ፡ ሰብሳቢው ፡ ዳኛ ፡ በፈረመበት ፡ ትእዛዝ ፡ በሦስተኛው ፡ ሠንጠረዥ ፡ በ፲፫ኛው ፡ ፎርም ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ ዐይነት ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርዱን ፡ እስኪያጸኑ ፡ በእስራት ፡ እንዲቈይ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

(፪) ቅጣቱ ፡ የጸና ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እንዲጸና ፡ በተደረገው ፡ ትእዛዝ ፡ ላይ ፡ በተጻፉት ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማል ።

(፫) ቅጣቱ ፡ የተቀነሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱን ፡ በመቀነስ ፡ የተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ በትእዛዙ ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማል ።

**ቍ ፡ ፪፻፭ ። የግል ፡ ነጻነቱን ፡ እንዲያጣ ፡ ስለ ፡ ተፈረደበት ፡ ሰው ፡ የሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ።**

(፩) ማንኛውም ፡ ሰው፡ እንዲያዝ ፡ እንዲታሰር፡ ወይም ፡ በአንድ ፡ ቦታ ፡ እንዲወሰን ፡ ትእዛዝ ፡ ሲሰጥ ፡ ሰብሳቢው ፡ ዳኛ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ፡ በሦስተኛው ፡ ሠንጠረዥ ፡ ዐይነት ፡ በሚፈርምበት ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ ቅጣቱ ፡ እንዲፈጸም ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

BACK



(፪) ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ የወህኒ ፡ ቤቱ ፡ ሹምና፡ ሌሎችም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በትእዛዙ ፡ ላይ ፡ የተነገረውን ፡ ቅጣት ፡ የመፈጸም ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ።

ቊ ፡ ፪፻፮ ። በአንዳንድ ፡ ነገሮች ፡ የቅጣቱ ፡ ጊዜ ፡ እንዲተላለፍ ፡ ለማድረግ ፡ የሚቻል፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

እንዲያዝ ፡ ወይም፡ ከአንድ ፡ ዓመት፡ ባልበለጠ፡ ጊዜ፡ በእስራት ፡ እንዲቀጣ፡ የተፈረደበት ፡ ሰው ፤

(ሀ) ነፍሰ ፡ ጡር ፡ የሆነች ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡

(ለ) የቤተ፡ ሰቡ፡ ደጋፊ፡ ሰውዬው፡ ብቻ፡ የሆነ ፡ እንደ፡ ሆነና ፡ ይኸውም፡ ሰው፡ ለሕዝብ ፡ ጸጥታ ፡ አሥጊ ፡ ያልሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለመልካም፡ ጠባዩ፡ ዋስ፡ አስጠርቶ፡ ከስድስት፡ ወር፡ ላልበለጠ፡ ጊዜ፡ ቅጣቱ ፡ ከመፈጸሙ፡ እንዲቈይ ፡ ሊያስተላልፍለት ፡ ይችላል ።

ቊ ፡ ፪፻፯ ። ግርፋት ፡ ስለ ፡ ተፈረደበት ፡ ሰው ፡ የሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ።

በወንጀለኛው ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቊ ፡ ፺፻፴፭ ፡ ንኡስ ፡ ቊጥር ፡ ፫ ፡ ወይም፡ ፺፪፴፯ ፡ ንኡስ ፡ ቊጥር ፡ ፩ ፡ መሠረት ፡ ግርፋት ፡ ስለ ፡ ተፈረደበት ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ሰብሳቢው ፡ ዳኛ ፡ በሚፈርምበት ፡ ትእዛዝ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በሦስተኛው ፡ ሠንጠረዥ ፡ በ፲፯ኛው ፡ ፎርም ፡ በተጻፈው ፡ ዐይነት ፡ በወንጀለኛው ፡ መቅጫ ፡ በቊ ፪፰ ፡ (ሀ) መሠረት ፡ የግርፋቱን ፡ ቅጣት ፡ የሚፈጽመውንና ፡ የሚፈጸምበትን ። ስፍራ ፡ ለይቶ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

ቊ ፡ ፪፻፰ ። ለወንጀሉ ፡ አላፊ ፡ ስላልሆኑ ፡ ሰዎች ፡ የሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ።

ለተግባሩ ፡ ሙሉ ፡ አላፊ ፡ ያልሆነ ፡ ሰው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቊ ፡ ፪፴፬ ፡ ወይም ፡ ፪፴፭ ፡ መሠረት ፡ ሕክምና ፡ እንዲደረግለት ፡ ወይም ፡ በአንድ ፡ ቦታ ፡ በጥንቃቄ ፡ ግዞት ፡ ተወስኖ ፡ እንዲጠበቅ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ሰብሳቢው፡ ዳኛ ፡ በሚፈርምበት ፡ የትእዛዝ ፡ ወረቀት ፡ በዚህ፡ ሕግ ፡ በሦስተኛው ፡ ሠንጠረዥ ፡ በአሥራ ፡ አምስተኛው ፡ ፎርም ፡ በተመለከተው ፡ ዐይነት ፡ ተከሳሹ ፡ ተስማሚ ፡ በሆነ ፡ ድርጅት ፡ ውስጥ ፡ በግዞት ፡ ተወስኖ ፡ እንዲጠበቅ ፡ ወይም ፡ የአእምሮ ፡ ሕክምና ፡ እንዲደረግለት ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

ቊ ፡ ፪፻፱ ። የቅጣት ፡ ገንዘብን ፡ ስለ ፡ ማስገባት ።

(፩) በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ አስፈጻሚው ፡ በወንጀለኛው ፡ መቅጫ፡ ሕግ፡ ቊ ፡ ፺፩ ፤ ፻፸፩ ፡ ንኡስ፡ ቊጥር ፡ ፩ ፤ ፺፪፰ ፡ እና ፡ ፺፻፲ ፡ መሠረት ፡ የመቀጫውን ፡ ገንዘብ ፡ ገቢ ፡ ያደርጋል ።

(፪) የመቀጫውን ፡ ገንዘብ፡ በሙሉ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ፍርድ ፡ አስፈጻሚው ፡ ማስገባት ፡ ያልቻለ ፡ እንደሆን ፡ ጉዳዩን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያስታውቃል ፤ ፍርድ፡ ቤቱም፡ ለአፈጻጸሙ፡ ወይም፡ በወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቊ ፡ ፺፪ ፤ ፺፬፤

BACK



፺፮ ፤ ፪፻፷፩ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፪ ፡ እና ፡ ፺፻፱ ፡ መሠረት ፡ የመቀጫውን ፡ ገንዘብ ፡ በግዴታ ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በአነስተኛ ፡ እስራት ፡ እንዲለወጥ ፡ አስፈላጊውን ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

(፫) ሰውዬው ፡ በሌለበት ፡ መቀጫ ፡ እንዲከፍል ፡ ሲፈረድበት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በተፈረደበት ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ትእዛዙ ፡ እንዲፈጸም ፡ ያደርጋል ፡ እንጂ፤ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።

ቍ ፡ ፪፻፲ ። ስለ፡ ኪሣራ ፡ ወጪ ፡ እና ፡ ስለ ፡ ካሣ ፡ አከፋፈል ።

የወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሰጠው ፡ ፍርድ ፡ የኪሣራ ፡ ወጪና ፡ ካሣ፡ እንዲከ ፈል ፡ የሚያዝ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለኪሣራ፡ ወጪና ፡ ለካሣ ፡ የተሰጠው ፡ የፍ ርዱ ፡ ክፍል ፡ ትእዛዝ ፡ እንደ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ነገር ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፪፻፲፩ ። ንብረት ፡ ስለ ፡ መውረስ ።

(፩) በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቍ ፡ ፪፻፳፪ ፡ መሠረት ፡ ንብረቱ ፡ እንዲወረስ ፡ ትእዛዝ ፡ የተሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በወንጀለኛው ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር፡ ፺፯ ፡ መሠረት ፡ የሚያዘውን ፡ ንብረት ፡ ለይቶ ፡ በመግለጽ ፡ ፍርድ ፡ አስ ፈጻሚ ፡ ይህንኑ ፡ ንብረት ፡ እንዲይዝ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

(፪) ፍርድ፡ አስፈጻሚው፡ ንብረቱን፡ ከያዘ፡ በኋላ ፡ ለዚሁ ፡ ነገር ፡ መብት ፡ ያለው፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣን ፡ ፍርድ ፡ አስፈጻሚው ፡ የያዘውን ፡ ንብረት ፡ ለሚያ ስረክበው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ሰዎች ፡ በትእዛዝ ፡ እስኪገልጽለት፡ ድረስ ፡ ይዞ ፡ ይቈያል ። ፍርድ፡ አስፈጻሚው፡ ንብረቱን ፡ ሲያስረክብ ፡ ንብረቱን ፡ በዝርዝር፡ የሚያስረዳ ፡ ደረሰኝ ፡ ካስረከበው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ሰዎች ፡ ይቀበላል ።

(፫) የተፈረደበት ፡ ሰው ፤ ቤተ፡ ሰቦች ፡ በስሕተት ፡ የተወረሰባቸውን ፡ ንብረት ፡ እንዲለቀቅላቸው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ መጠየቅ ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፪፻፲፪ ። ንብረትን ፡ ስለ ፡ ማስያዝ ።

(፩) አንድ፡ ሰው፡ በሌለበት ፡ በወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቍ ፡ ፪፻፳፪ ፡ መሠረት፡ ለተመለከተው ፡ ወንጀል ፡ ንብረቱ ፡ እንዲያዝ ፡ ሲፈረድበት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከዚህ ፡ በሚቀጥለው ፡ ዐይነት ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

(ሀ) ፍርድ፡ አስፈጻሚው፡ በወንጀለኛው፡ መቅጫ፡ ሕግ ፡ ቍ ፡ ፺፰፡ መሠረት፡ መያዝ ፡ የሚገባውን ፡ ንብረት ፡ እንዲይዝና ፡ ትእዛዙም ፡ የሚያዘውን ፡ ንብ ረት ፡ ለይቶ ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።

(ለ) ንብረቱን ፡ የሚያስተዳድር ፡ (ጠባቂ) ፡ መሾምና ፡ አስተዳዳሪውም ፡ በተ ሾመ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ አስፈጻሚው፡ የንብረቱን ፡ ዝርዝር ፡ ደረሰኝ ፡ ተቀብሎ፡ ንብረቱን ፡ ለአስተዳዳሪው ፡ ያስረክባል ።

(፪) ቤወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቍ ፡ ፺፯ ፤ ንኡስ፡ ቍ ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰው ፡ ማን ኛውም ፡ ንብረት ፡ እንዳይያዝ ፡ ማድረግ ፡ ኀላፊነቱ ፡ የፍርድ ፡ አስፈጻሚው ፡

ነው ፤ የተፈረደበት ፡ ሰው ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ በስሕተት ፡ የተያዘ ፡ ማንኛውም ፡ ንብረት ፡ እንዲለቀቅላቸው ፡ ለንብረቱ ፡ አስተዳዳሪ ፡ ማመልከት ፡ ይችላሉ ።

(፫) በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ መሠረት ፡ የተሰጠው ፡ የማስያዙ ፡ ትእዛዝ ፡ ለዚህ ፡ ነገር ሥልጣን ፡ ያለው ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣን ፡ እንዲነሣለት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ እስኪጠይቅ ፡ ድረስ ፡ ትእዛዙ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ይኸው ፡ ባለ ሥልጣን ፡ ትእዛዙ ፡ እንዲነሣለት ፡ ባመለከተ ፡ ጊዜ ፡ ንብረቱ ፡ እንዲያዝ ፡ የተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ተነሥቶ ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪው ፡ ትክክለኛ ፡ ሒሳብ ፡ አቅርቦ ፡ ከግዴታው ፡ ነጻ ፡ እንዲሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

<u>ቍ ፡ ፻፲፫ ። አካለመጠን ፡ ስላላደረሱ ፡ ወጣቶች ፡ የሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ።</u>

(፩) ፍርድ ፡ ቤቱ ፤ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ ፡ ፻፷፪ ፤ ፻፷፫ ፤ ፻፷፬ ፤ ፻፸፫ ፡ ወይም ፡ ፪፻፫ ፡ መሠረት ፡ አካለመጠን ፡ ስላላደረሰ ፡ ወጣት ፡ ትእዛዝ ፡ በሰጠ ፡ ጊዜ ፤ ሰብሳቢው ፡ ዳኛ ፡ ፊርሞ ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ ለክፍሉ ፡ ኀላፊ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፤ ለትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ዲሬክተር ፤ ለዲሬክተሩ ፡ ወይም ፡ ኀላፊ ፡ ለሆነው ፡ መኰንን ፡ ትእዛዙን ፡ ይልካል ፤ በትእዛዙ ፡ ላይ ፡ በተገለጸው ፡ መሠረት ፡ አካለመጠን ፡ ባላደረሰው ፡ ወጣት ፡ ላይ ፡ አስፈላጊውን ፡ ለመፈጸም ፡ በቂ ፡ ሥልጣን ፡ ነው ።

(፪) አካለመጠን ፡ ስላላደረሰ ፡ ወጣት ፡ በወንጀለኛው ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቍ ፡ ፻፷፫ ፡ መሠረት ፡ ትእዛዝ ፡ ሲሰጥ ፤ ሰብሳቢው ፡ ዳኛ ፡ በወንጀለኛው ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፻፷፫ ፡ ከተጠቀሱት ፡ ሰዎች ፡ ለአንዱ ፡ ፈርሞ ፡ ትእዛዙን ፡ ይልካል ። በትእዛዙ ፡ ላይ ፡ በተገለጸው ፡ መሠረት ፡ አካለመጠን ፡ ለላደረሰው ፡ ወጣት ፡ ላይ ፡ አስፈላጊውን ፡ ለመፈጸም ፡ በቂ ፡ ሥልጣን ፡ ነው ።

(፫) አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ወጣት ፡ የአርጩሜ ፡ ቅጣት ፡ በወንጀለኛው ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቍ ፡ ፻፸፪ ፡ መሠረት ፡ ሲፈረድበት ፡ የአርጩሜ ፡ ቅጣት ፡ ሰውነቱ ፡ የሚችል ፡ እንደሆን ፡ በሐኪም ፡ ተመርምሮ ፡ እንዲረጋገጥ ፡ ሰብሳቢው ፡ ዳኛ ፡ ያዛል ። ሰውነቱ ፡ የሚችል ፡ መሆኑ ፡ ከተረጋገጠ ፡ በኋላ ፡ የአርጩሜውን ፡ ቅጣት ፡ በገለልተኛ ፡ ስፍራ ፡ ከቤተ ፡ ሰቡ ፡ በዕድሜ ፡ የላቀው ፡ ወይም ፡ ሰሳቢው ፡ ዳኛ ፡ የመረጠው ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ የመረመረው ፡ ሐኪምና ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ወጣት ፡ ወላጆች ፤ ቤተ ፡ ዘመዶቹ ፡ ያሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ሞግዚቱ ፡ ባሉበት ፡ ይፈጸማል ።

<u>ቍ ፡ ፻፲፬ ። ስለ ፡ ግዴታ ፡ ሥራ ፤ ስለ ፡ ተጨማሪ ፡ ቅጣትና ፡ ስለሚወሰደው ፡ ጥንቃቄ ፤</u>

በወንጀለኛው ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቍ ፡ ፻፪ ፤ ፻፫ ፤ ፻፷፪ ፤ ፻፶፩ ፤ ፻፶፯ ፤ ፻፶፰ ፤ ከ፻፶፱ ፡ እስከ ፡ ፻፶፩ ፤ ከ፻፶፭ ፡ እስከ ፡ ፻፷፱ ፣ ፻፷፭ ፤ ፻፷፱ ፤ ፪፻፲፭ ፤ ፪፻፲፯ ፡ ወይም ፡ ከ፪፻፲፰ ፡ እስከ ፡ ፪፻፳ ፡ መሠረት ፡ ትእዛዝ ፡ የተሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የፍርዱ ፡ ፍሬው ፡ ነገር ፡

ግልባጭ ፡ አግባብ ፡ ላላቸው ፡ ባለሥልጣኖች ፡ እንዲደርስና ፡ አስፈላጊውን ፡ እን ዲያደርጉ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

**ቍ ፡ ፫፻፲፭ ። የፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ትእዛዝን ፡ በመዝገብ ፡ ስለ ፡ መጻፍ ።**

ስለ ፡ ቅጣቱ ፡ አፈጻጸም ፡ የሚሰጠውን ፡ ማንኛውንም ፡ ትእዛዝ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በመዝገብ ፡ ይጽፋል ። ትእዛዙ ፡ የተፈጸመበትን ፡ ቀን ፡ የሚገልጽ ፡ በመዝገቡ ፡ ላይ ፡ ይጽፋል ፤ አስፈላጊ ፡ ሲሆንም ፡ ትእዛዙ ፡ ሊፈጸም ፡ ያልተቻለበት ፡ ምክን ያት ፡ በመዝገብ ፡ ይጻፋል ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ቅጣት ፡ የሚሰጡትን ፡ትእዛዞች ፡ ስለ፡መለወጥ ።

**ቍ ፡ ፫፻፲፮ ። መሠረቱ ።**

(፩) በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፪ ፡ በተወሰነው ፡ መሠረት፡ ትእዛዝ ፡ መስጠት ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የቅጣቱን ፡ ፍርድ ፡ የሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ራሱ ፡ ትእዛዙን ፡ ይሰጣል ።

(፪) ከዚህ ፡ በታች ፡ የተዘረዘሩት ፡ ሁኔታዎች ፡ ሲያጋጥሙ ፤

(ሀ) በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፪፴፪ ፡ መሠረት ፡ ጽኑ ፡ ግዞትን ፡ ለማስገደድ ።

(ለ) በወንጀለኛ፡መቅጫ፡ ሕግ በቍጥር ፡ ፪፴፮ ፡ መሠረት ፡ ሙሉ፡ አላፊ ፡ ስላል ሆኑ ፡ ጥፋተኞች ፡ የተሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ ለመለወጥ ።

(ሐ) በወንጀለኛ፡ መቅጫ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፪፵ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፪ ፡ መሠረት ፡ የእስራትን ፡ ጊዜ ፡ ለማርዘም ።

(መ) በወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፪፺፰ ፤ ፫፻፪ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፫፡ እና ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፬ ፡ መሠረት ፡ ለመፈተኛ ፡ የተሰጠውን ፡ ጊዜ ፡ ለማስቀረት ፡ ወይም ፡ በአጥፊው ፡ ላይ ፡ የሚወሰን ፡ የአኗኗር ፡ ደንብን ፡ ለመለወጥ ።

(ሠ) በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ፡ በቍጥር፡ ፪፴፩፤ ፫፻፯ ፤ ከ፫፻፱ ፡ እስከ ፡ ፫፻፲፪ ፡ መሠረት ፡ በአመክሮ ፡ ገደብ ፡ ለመልቀቅ ።

(ረ) በወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፪፹፬ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፪፡ እና ፡ ፪፶፯፡ መሠረት ፤ ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ ንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

(፫) አካለመጠን ፡ ስላላደረሱ ፡ ወጣቶች ፡ የሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ፡ በዚህ፡ ሕግ ፡ በቍ፡ ፪፹ ፡ መሠረት ፡ ሊለወጥ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፫፻፲፯ ። ሥነ ፡ ሥርዐትና ፡ ውሳኔ ።**

(፩) የተፈረደበት ፡ ሰው ፡ ራሱ ፡ ወይም ፡ ሕጋዊ ፡ እንደራሴው ፤ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ወይም ፡ የቅጣቱን ፡ ፍርድ ፡ እንዲያስፈጽም ፡ ወይም ፡ አፈጻጸሙን ፡ እንዲቈጣ ጠር ፡ የተፈቀደለት ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ባለሥልጣን ፡ በማመልከቻ፡

ካላመለከተው ፡ በቀር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ መሠረት ፡ ትእዛዝ ፡ አይሰጥም ።

(፪) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ከመስጠቱ ፡ በፊት ፡ ትእዛዙ ፡ የሚመለከተውን ፡ ሰውና ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማወቅ ፡ የሚፈልገውን ፡ ነገር ፡ ለመግለጽ ፡ የሚችለውን ሰው ፡ እንዲቀርብ ፡ መጥሪያ ፡ ይልክለታል ። ይኸውም ፡ በምርመራ ፡ እንዲጣራ ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

(፫) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተጠሩትን ፡ ሰዎች ፡ ቃል ፡ ከሰማና ፡ አስፈላጊው ፡ ነገር ፡ ከተገለጸለት ፡ በኋላ ፤ ውሳኔ ፡ ይሰጣል ። ውሳኔ ፡ የሚሰጠው ፡ ሰው ፡ ሳይቀርብ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በሌለበት ፡ ውሳኔውን ፡ ይሰጣል ።

(፬) በፍርድ ፡ ቤት ፡ የተሰጠው ፡ ማንኛውም ፡ ቃል ፡ እና ፡ ውሳኔ ፡ በመዝገብ ፡ ይጻፋል ።

(፭) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፡ በሚሰጥ ፡ ውሳኔ ፡ ይግባኝ ፡ ማለት ፡ አይቻልም ፤ ውሳኔውም ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ምዕራፍ ፡ ፩ ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማል ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ መሰየም ።

### ቍ ፡ ፻፲፰ ። ስለ ፡ መሰየም ፡ የሚቀርብ ፡ ማመልከቻ ።

(፩) የተፈረደበት ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ሕጋዊ ፡ እንደራሴው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቍ ፡ ፻፶፫ ፡ እና ፡ ፻፶፬ ፡ የተገለጸው ፡ የተፈጸመ ፡ መሆኑን ፡ ሲረዳው ፡ ቀድሞ ፡ የተሰጠው ፡ ቅጣት ፡ ተሰርዞለት ፡ እንዲሰየም ፡ የቅጣቱን ፡ ፍርድ ፡ ለሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማመልከት ፡ ይችላል ።

(፪) ማመልከቻው ፡ በጽሑፍ ፡ ሆኖ ፡ ምክንያቱን ፡ መግለጽ ፡ አለበት ። በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቍ ፡ ፻፶፫ ፡ እና ፡ ፻፶፬ ፡ የተገለጸው ፡ የተፈጸመ ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዲገነዘብ ፡ የሚያስፈልጉት ፡ መረጃዎች ፡ አብረው ፡ ይቀርባሉ ።

### ቁ ፡ ፻፲፱ ። ሥነ ፡ ሥርዐትና ፡ ውሳኔ ።

(፩) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በዝግ ፡ ችሎት ፡ ስለ ፡ ማመልከቻው ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጣል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውሳኔ ፡ ከመስጠቱ ፡ በፊት ፡ አስፈላጊ ፡ ከመሰለው ፡ ነገሩ ፡ እንዲጣራ ፡ ወይም ፡ ተጨማሪ ፡ ማስረጃ ፡ እንዲቀርብ ፡ ማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፪) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማመልከቻውን ፡ ፈቅዶ ፡ የተቀበለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቍ ፡ ፻፶፰ ፡ መሠረት ፡ እንዲፈጸምና ፡ የሰረዘው ፡ የቅጣት ፡ ፍርድ ፡ የተሰያሚው ፡ ስም ፡ በጥፋት ፡ ተመዝግቦበት ፡ ከነበረው ፡ ከፖሊስ ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ እንዲሰረዝ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

(፫) ፍርድ፡ ቤቱ፡ ማመልከቻውን፡ ፈቅዶ ፡ ያልተቀበለው፡ እንደ፡ ሆነ፡ በወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቍ ፡ ፪፻፵፯ ፡ የተመለከተው ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

(፬) በንዑስ ፡ ቍ ፡ ፪ ፡ መሠረት ፡ የተሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ በጽሑፍ ፡ ሆኖ ፡ ምክንያቱም ፡ ጭምር ፡ መገለጽ ፡ አለበት ። ውሳኔውም፡ በግልጽ ፡ ችሎት ፡ በዐደባባይ፡ መነበብና ፡ በጋዜጣም ፡ መውጣት ፡ አለበት ።

(፭) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ መሠረት፡ በማናቸውም፡ ፍርድ፡ ቤት ፡ የሚሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ይግባኝ ፡ የለውም ።

# ሰባተኛ ፡ መጽሐፍ ።

## በወንጀል ፡ ነገር ፡ የሚከፈል ፡ የኪሣራ፡ ወጪ ።

### ቍ ፡ ፪፻፳ ። ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ለሚያቀርበው ፡ ክስ ፡ የኪሣራ ፡ ወጪ ።

(፩) በዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ በኩል ፡ ለሚቀርበው ፡ ክስ ፡ የኪሣራ ፡ ወጪ ፡ በሙሉ ፡ ከይግባኙ ፡ ጭምር ፡ መንግሥት ፡ ኀላፊ ፡ ነው ።

(፪) በተፈረደበት፡ ሰው ፡ ምክንያት ፡ በዐቃቢ ፡ ሕጉ ፡ በኩል ፡ የቀረበው ፡ ክስ ፡ የተለየ፡ የኪሣራ፡ ወጪ ፡ የሚደረግ፡ እንደ፡ሆነና ፡ የተፈረደበት ፡ ሰው ፡ ንብረት፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በሕግ ፡ ከሚወሰንበት ፡ ቅጣት ፡ በላይ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የመዝገብ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ የሚወስነውን ፡ የኪሣራ ፡ ወጪ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ እንዲከፍል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊያዝ ፡ ይችላል ።

(፫) በአቤቱታ ፡ በሚቀርብ፡ ክስ፡ በዐቃቢ፡ ሕግ ፡ በኩል ፡ ክሱ ፡ ከቀረበ ፡ በኋላ ፡ የተበደለው ፡ ሰው ፡ አቤቱታውን ፡ የተወ ፡ እንደሆነ ፡ (በወንጀለኛ ፡ መቅጫ፡ ሕግ ፡ ቍ ፡ ፪፻፳፩) ፡ መሠረት ፡ ለወንጀሉ ፡ ክስ ፡ ለተደረገው ፡ የኪሣራ ፡ ወጪ ፡ ሁሉ ፡ ኀላፊ ፡ ይሆናል ።

### ቍ ፡ ፪፻፳፩ ። የግል ፡ ክስ ፡ የኪሣራ ፡ ወጪ ።

(፩) በግል፡ ክስ ፡ በሚቀርቡ ፡ ነገሮች፡ ላለው፡ የኪሣራ ፡ ወጪ ፡ ሁሉ ፡ በቍ፡ ፶፮፡ መሠረት ፡ የግል ፡ ከሳሹ ፡ ኀላፊ ፡ ነው ።

(፪) በግል፡ ክስ ፡ ቀርቦ ፡ ተከሳሹ ፡ ነጻ ፡ የተለቀቀ፡ እንደ፡ ሆነና ፡ ክሱ ፡ የቀረበው፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ አለመሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተገነዘበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተከሳሹ ፡ ያወጣውን ፡ የኪሣራ ፡ ወጪ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ የግል ፡ ከሳሹ ፡ እንዲከፍል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፫) የግል ፡ ክሱ፡ በቍ ፡ ፶፰ ፡ መሠረት ፡ የታገደ ፡ እንደሆነ ፤ ለግል ፤ ክሱ ፤ የኪሣራ ፡ ወጪ ፡ ሁሉ ፡ መንግሥት ፡ ኀላፊ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪፻፳፪ ። የተበደለው ፡ ወገን ።

(፩) የተበደለው፡ ወገን፡ በወንጀል ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ ካሣ ፡ እንዲከፈለው ፡ የጠየቀ፡ እንደሆን ? ከዚህ ፡ የሚከተሉትን ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

(ለ) ምስክሮችና ፡ በምስክርነት ፡ ቃላቸውን ፡ የሚሰጡትን ፡ ልዩ ፡ ዐዋቂዎች ፡ ለመጥራት ፡ አስፈላጊውን ፡ ወጪ ፡ ይከፍላል ።

(፪) የተበደለው፡ወገን፡ካሣ፡እንዲያገኝ፡የተፈረደለት፡እንደሆነ፡በንኡስ፡ቍጥር፡፩፡የተ ጠቀሰውን፡የኪሣራ፡ወጪና፡የዳኝነት፡ተከሳሹ፡ እንዲከፍል፡ ፍርድ ፡ ቤቱ፡ ያዛል።

# ስምንተኛ ፡ መጽሐፍ ።

የአጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ በአጭር ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ የሚያዩት ፡ ዳኝነት ።

ቍ ፡ ፪፻፳፫ ። ዳኝነቱ ።

(፩) የአጥቢያ፡ ዳኛ፡ በሥልጣኑ፡ ውስጥ፡ በሚገኘው፡ ስፍራ ፡ ንኡሳን፡ ወንጀሎች ፡ የሆኑትን ፡ የስድብን ፤ የእጅ፡ እልፊትን፤ በሰው፡ ንብረት፡ ላይ ፡ የሚደረግ ፡ ጉዳ ትን ፡ ወይም ፡ የንብረቱ ፡ ዋጋ ፡ ከአምስት ፡ ብር ፡ በላይ ፡ የማይሆን ፡ ስርቆ ትን ፡ ነገሩ ፡ በዕርቅ ፡ እንዲያልቅ ፡ የተቻለውን ፡ ያደርጋል ።

(፪) የአጥቢያው፡ ዳኛ፡ ነገሩን፡ በዕርቅ፡ ለመጨረስ፡ ያልቻለ፡ እንደ፡ሆነ፤ ከሁለት፡ እማኞች፡ ጋር፡ ተቀምጦ፡ እነዚህን፡ ንኡሳን ፡ ወንጀሎችን ፡ አከራክሮ ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት፡ ይችላል ። ከዐሥራ ፡ አምስት፡ ብር ፡ በላይ፡ ቅጣት ፡ መወሰን፡ አይች ልም ። እማኞቹና ፡ የአጥቢያ ፡ ዳኛው ፡ በሚሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ባንድ ፡ ቃል ፡ ካልተስማሙ ፡ የአጥቢያ ፡ ዳኛው ፡ ውሳኔ ፡ የጸና ፡ ይሆናል ።

(፫) የአጥቢያው፡ ዳኛ ፡ በፍርድ ፡ መዝገብ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የተመለከቱት ፡ እን ዲጻፉ ፡ ያደርጋል ።

(ሀ) የከሳሹ ፡ ስም ፤

(ለ) ክስ ፡ የቀረበበት ፡ ወንጀል ፤

(ሐ) ማስረጃው ፡ ባጭሩ ፤

(መ) እማኞች ፡ የሰጡት ፡ አስተያየት ፤

(ሠ) ተከሳሹ ፡ የተፈረደበት ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ የተወሰነበት ፡ ቅጣት ፡ እንዲባል ።

ቍ ፡ ፪፻፳፬ ። ይግባኝ ።

የአጥቢያው፡ ዳኛ ፡ በቍ ፡ ፪፻፳፬ ፡ ንኡስ ፡ ቍ፡ (፪) መሠረት ፡ በሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ይግባኙ ፡ በዚያው ፡ ስፍራ ፡ ላለው ፡ የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይቀርባል ።

# አንደኛ ፡ ሠንጠረዥ ።

| የወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ፡ ቍጥር | ወንጀሉ ። | ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
|---|---|---|
| ፯፻፹፰ | በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በንጉሣውያን ፡ ቤተ ፡ ሰቦቹ ላይ ፡ አደጋ፡ በመጣል፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች። | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፯፻፹፱ | በዙፋኑ፡ አወራረስ፡ ላይ፡ አደጋን፡ በመጣል፡ ስለ ሚደረጉ ፡ ወንጀሎች ። ..................... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፯፻፺ | በሕገ፡ መንግሥቱና ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ በተ ቋቋሙ፡ ባለሥልጣኖች፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ በመጣል፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ። .................. | ከፍተኛው ፡ ፍርድ፡ ቤት ። |
| ፯፻፺፩ | በሕገ፡ መንግሥቱ፡ የሥልጣን፡ ሥራ፡ መልካም፡ እርምጃ፡ መሰናከል ፡ በመሆን ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ። .............................. | ከፍተኛው፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፯፻፺፪ | የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ይዞ ፡ ሽብር ፡ በማድረግና ፡ ባገር፡ ውስጥ፡ ጦርነት፡ በማንሣት፡ ስለ ፡ ሚሠራ፡ ወንጀል ። .............................. | ከፍተኛው፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፯፻፺፫ | የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ መንግሥት ፡ የፖለቲካ ፡ ሥልጣን፡ ወይም ፡ የግዛቱን ፡ ሙሉነት ፡ በመ ንካት ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ። .............. | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፯፻፺፬ | የማነሣሣት፡ ተግባሮችን፡ ግዙፍ፡በሆነ፡ ዐይነት፡ ማሰናዳት ። .............................. | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፯፻፺፭ | የአገርን፡ ወሰንና፡ የፖለቲካን፡ ሙሉ፡ ሥልጣን፡ በመጣስ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ። ............ | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፯፻፺፮ | ንጉሠ፡ ነገሥቱን፡ ወይም፡ የሕገ፡ መንግሥቱን ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በመድፈር ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ። .............................. | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፯፻፺፯ | ያገር ፡ ምልክቶች ፡ የሆኑ ፡ ዓላማዎችን ፡ በመድ ፈር ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ። ............. | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፯፻፺፰ | ግልጽ ፡ በሆኑ ፡ ምልክቶች ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ ስለ ፡ መገልገል ። ................................ | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፯፻፺፱ | የመንግሥቱን፡ ነጻነት፡ በመንካት፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ፡ .............................. | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |

| የወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ፡ ቍጥር | ወንጀሉ ፤ | ስሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
|---|---|---|
| ፪፻፶ | ያገሩን ፡ መከላከያ ፡ ኀይል ፡ በመንካት፡ ስለሚ ሠራ ፡ ወንጀል ። | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፪፻፶፩ | ከፍ ፡ ያለ ፡ ክዳት ። | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፪፻፶፪ | የዲፕሎማቲክ ፡ ክዳት ። | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፪፻፶፫ | የኤኮኖሚክ ፡ (የሀብት) ፡ ክዳት ። | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፪፻፶፬ | ከጠላት ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ ስለ ፡ መሥራት፡ (ጠላ ትን ፡ ስለ ፡ መርዳት) ። | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፪፻፶፭ | ስለላ ። | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፪፻፶፮ | — | — |
| ፪፻፶፯ | በዘወርዋራ ፡ እንደ፡ ተደረገ፡ ስለሚቈጠር ፡ ማገ ዝና ፡ መርዳት ። | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፪፻፶፰ | በወንጀል ፡ ተካፋይነት ፡ ጊዜ ፡ ስለሚደረግ ፡ ሙከራ ። | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፪፻፶፱ | ስለ ፡ ማነሣሣትና፡ ስለ፡ ማዘጋጀት ። | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፪፻፷ | ከባድ ፡ ሁኔታ ። | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፪፻፷፩ | — | — |
| ፪፻፷፪ | — | — |
| ፪፻፷፫ | በውጭ፡ አገር፡ መንግሥት፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ የተቃዋሚነት ፡ ሥራ ። | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፪፻፷፬ | በውጭ፡ አገር፡ መንግሥታት ፡ መሪዎች ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ በመጣል ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ። | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፪፻፷፭ | የውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥትን ፡ ግዛት ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ስለ ፡ መጣስ ። | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፪፻፷፮ | የውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥትን ፡ ስለ ፡ ማዋረድ ። | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፪፻፷፯ | ግልጽ፡ የሆኑ፡ የውጭ ፡ አገር፡ መንግሥት ፡ ምል ክቶችን፡ ስለ፡ ማዋረድ ። | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፪፻፷፰ | በመንግሥታት፡ መካከል፡ የተቋቋሙትን፡ ሥራ ዎች ፡ እንስቲቱሲዮኖች፡ ስለ ፡ ማዋረድ ። | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፪፻፷፱ | — | — |
| ፪፻፸ | — | — |
| ፪፻፸፩ | ዘርን ፡ ስለ፡ማጥፋት፤ በሰብአዊ ፡ ፍጥረት ፡ ላይ፡ ስለሚደረግ ፡ ወንጀል ። | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |

| የወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ፡ቍጥር | ወ ን ጀ ሉ ። | ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| --- | --- | --- |
| ፪፻፹፪ | በብሔራዊ፡ በሰላማዊ፡ ሕዝብ፡ ላይ ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ስለሚፈጸም ፡ የጦርነት ፡ ወንጀል ። | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፪፻፹፫ | በቍስለኞች፤ በበሽተኞችና፡ በስጥመት ፡ አደጋ፡ ላይ፡ ባሉ፡ ሰዎች፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ የጦርነት ፡ ወንጀል ። ............................ | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፪፻፹፬ | በታሰሩና ፡ በተጋዙ ፡ የጦር ፡ ምርኮኞች ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸሙ ፡ የጦርነት ፡ ወንጀሎች ። ... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፪፻፹፭ | በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ስለሚደረግ ፡ የዘረፋ ፡ የየብስና፡ የባሕር ፡ ወንበዴነት ። .................. | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፪፻፹፮ | ስለ ፡ ማነሣሣትና ፡ ስለ፡ ማዘጋጀት ። . . . | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፪፻፹፯ | ለጠላት፡ ሊደረግ ፡ የሚገባውን ፡ ተግባር፡ ስለ ፡ መጣስ ። ............................ | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፪፻፹፰ | ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆኑ ፡ የጦር ፡ መሣሪያዎች ፡ ስለ ፡ መታገዝ ። ............................ | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፪፻፹፱ | የጦር፡ ማቆም ፡ ውልን ፡ ወይም ፡ የሰላም ፡ ስምምነትን ፡ ስለ፡ማፍረስ ። .................... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፪፻፺ | የፋኖ ፡ አለቃ ፡ በመሆን ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ። ...................... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፪፻፺፩ | በቍስለኞች፤በበሽተኞችና፡ በእስረኞች፡ላይ፡ ስለ፡ መጫንና ፡ የሚገባቸውን ፡ ስለ ፡ ማጓደል ። . . | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፪፻፺፪ | ፍትሕ ፡ ስለ ፡ መከልከል ። ................ | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፪፻፺፫ | በኢንተርናሲዮናል፡ የበጎ፡ አድራጎት ፡ ሰብአዊ ፡ ማኅበሮች፡ ላይ፡ ስለሚደረግ፡ ተቃዋሚ ፡ ሥራ ። | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፪፻፺፬ | በኢንተርናሲዮናል ፡ አርማዎችና ፡ ምልክቶች ፡ ያላገባብ ፡ ስለ ፡ መገልገል ። ............. | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፪፻፺፭ | በዕርቅ፡ መልክተኛ፡ ላይ ፡ ተቀዋሚ ፡ ተግባር ፡ ስለ፡ መፈጸም፡ ......................... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፪፻፺፮ እስከ፡ ፫፻፴፩ | በጦር ፡ ኀይል፡ ባልደረባዎች፡ ስለሚሠሩት ፡ ወንጀሎች ። ........................ የፖሊስ፡ ሠራዊት፡ ባልደረባዎች፡ ስለሚፈጽሟቸው፡ ወታደራዊ፡ ጠባይ ፡ ያላቸው፡ወንጀሎች። | የጦር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻ | የጦር ፡ ክፍሉን ፡ ትቶ ፡ ስለ ፡ መሄድ ፤ ተራ፡ ክስ፡ (ንኡስ፡ቍ ፩)። ............... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |

| የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር | ወንጀሉ ። | ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
|---|---|---|
| | ከባድ ፡ ሁኔታ ፡ (ንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፪) ።.... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፩ | ያለ ፡ ፈቃድ ፡ ስለ ፡ መቅረት ። ............. | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፪ | ስለሚፈጽመው ፡ የሥልጣን ፡ መተላለፍ ። | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፫ | በበታች ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸም ፡ ዛቻና ፡ የእጅ ፡ እልፊት ። ........................... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፬ | የፖሊስ ፡ ደንቦችን ፡ ስለ ፡ መጣስ ። ....... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፭ | ዐውቆ ፡ ያልተካከለ ፡ መረጃ ፡ ስለ ፡ መስጠት ። | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፮ | በሥራ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ መስከር ። ............ | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፱ | ከሥነ ፡ ሥርዐት ፡ (ዲስፕሊን) ፡ ውጭ ፡ ስለ ፡ መሆን ። ........................... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፲ | በበላይ ፡ አለቃ ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ የስድብ ፡ ዛቻና ፡ የእጅ ፡ እልፊት ፡ ወንጀል ። ...... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፲፩ | ለበላይ ፡ ባለሥልጣን ፡ ስለ ፡ አለመታዘዝ ፤ | |
| | ተራ ፡ ክስ ፡ (ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩) ። ........... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| | ከባድ ፡ ሁኔታ ፡ (ንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፪ ) ። | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፲፪ | አድማ ። ........................... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፲፫ | ግርግር ፡ ለማንሣት ፡ ስለሚደረግ ፡ አድማ ፡ ወይም ፡ ስምምነት ።.................... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፲፬ | በተካፋይነት ፡ ስለሚደረግ ፡ ሙከራ ። .... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፲፭ | የዘብ ፡ ወንጀል ፤ | |
| | ተራ ፡ ክስ ፡ (ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩) ።............ | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| | ከባድ ፡ ሁኔታ ፡ (ንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፪) ፡ (መጀ መሪያው ፡ ኀይለ ፡ ቃል) ።.............. | አውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፲፮ | ምስጢራዊ ፡ ትእዛዝ ፡ ስለ ፡ መግለጽና ፡ ስለ ፡ መለዋወጥ ፤ | |
| | ተራ ፡ ክስ ፡ ( ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩) ።.......... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| | ከባድ ፡ ሁኔታ ፤ ( ንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፫) ። | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፲፱ | በዕቃዎች ፡ ያላገባብ ፡ ስለ ፡ መጠቀምና ፡ ዕቃ ዎችን ፡ ስለ ፡ ማባከን ፤ | |
| | ተራ ፡ ክስ ፡ (ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩) ።......... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| | ከባድ ፡ ሁኔታ ፡ (ንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፪) ። | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |

| የወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ፡ቍጥር | ወንጀሉ ። | ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
|---|---|---|
| ፫፻፷ | የማይገባውን ፡ ጥቅም ፡ ስለ ፡ መቀበልና ፡ ያላ ገባብ ፡ ስለ ፡ ማጥፋት ፤ | |
| | ተራ፡ ክስ ፡ (ንኡስ፡ ቍ ፡ ፩)። .......... | አውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| | ከባድ፡ ሁኔታ፡ (ንኡስ፡ ቍጥር፡ ፪) ። . . . | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፷፩ | በአደጋ ፡ ጊዜ ፡ የማስጠንቀቅን ፡ ተግባር ፡ ስላለመፈጸም ። ........................ | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፷፪ | አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ የጸጥታ ፡ ጥንቃቄ ፡ ስላ ለማድረግ ። ........................ | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፸፪ | የአገልግሎቱን ፡ ተግባር ፡ በማይገባ ፡ እንዲፈ ጽም ፡ ወይም ፡ እንዲጥስ ፡ ስለ ፡ ማስገደድ ። | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፸፫ | በሥራ ፡ ላይ ፡ ከሚገኝ ፡ ወታደር ፡ ጋራ ፡ የጸብ ፡ ግጭት ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። ................ | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፸፬ | ከባድ ፡ ሁኔታ ። ........................ | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፸፭ | የሕግ ፡ ወይም ፡ የውል ፡ ግዴታዎችን ፡ ስለ ፡ መጣስ ። .............................. | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፫፻፸፮ | ስለ ፡ ማሰናከል ። ..................... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ፡ ቤት። |
| ፫፻፸፯ | በጦር ፡ ሠራዊት ፡ ዕቃ ፡ ስለ ፡ መነገድ ። . . . | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፸፰ | የጦር ፡ ሠራዊትን ፡ መለዮ ፡ ልብስ ፡ ምልክትና፡ ሽልማት፡ሕገ፡ወጥ፡በሆነ ፡ አኳኋን ፡ በፋብሪካ ፡ ስለ ፡ መሥራትና ፡ በንግድ ፡ ስለ ፡ ማዛወር ። | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፸፱ | የወታደር ፡ መለዮ፡ልብስ ፡ ወይም ፡ የወታደርን፡ ምልክትና ፡ ሽልማት ፡ በማይገባ ፡ ስለ ፡ መልበስ፡ | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፹ | ወታደራዊ ፡ ጠባይ ፡ የያዙ ፡ የጥንቃቄ ፡ ትግባ ሮችን ፡ ትእዛዝ ፡ ስላለመቀበል ። .......... | ወረዳ፡ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፹፩ | የወታደር ፡ ትእዛዞች ፡ እንዳይፈጸሙ ፡ ወይም ፡ እንዲጣሱ ፡ ለማድረግ ፡ ሌሎችን ፡ ሰዎች ፡ ስለ፡ ማደፋፈር ። ............................ | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፹፪ | አንዳንድ፡የወታደር፡ስፍራዎችን ፡ ወይም ፡ ዕቃ ዎችን ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ፡ የተደረገውን ፡ ክልከላ፡ ስላለመከተል ። ............................ | ወረዳ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፹፫ | ጠቅላላ ፡ ትእዛዞችና፡ አመራሮችን ፡ ወደ፡ ሐሰት ፡ ስለ ፡ መለወጥ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ማጥፋት ። .... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |

| የወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ፡ቍጥር | ወንጀሉ ። | ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
|---|---|---|
| ፫፻፵፩ | በጦር፡ሠራዊትና፡በወታደር፡ግዴታዎች፡ላይ፡ የሚሠሩትን ፡ ወንጀሎች ፡ ስላለመግለጽ ።... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፵፪ | የወታደርነትን ፡ ምስጢር ፡ ስለ ፡ መግለጽ ። .. | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፫፻፵፫ | የሐሰት ፡ ወይም ፡ የማደናገር ፡ ወሬ ፡ ስለ ፡ መስጠት ። ............................ | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፵፬ | በአደጋ ፡ ወይም ፡ በጦር ፡ ጊዜ ፡ ቅጣትን ፡ ስለ ፡ ማክበድ ። ............................ | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፵፭ | እስከ ፡ ፫፻፶ ። — | — |
| ፫፻፶፩ | በልዩ ፡ ደንብ ፡ ወንጀለኛ ፡ ስለ ፡ መባል ። ..... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፶፪ | የወንጀል ፡ ቅጣቶች ፤ ዐይነታቸውና ፡ መጠናቸው ። .. ............................ | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፶፫ | — | — |
| ፫፻፶፬ | በወርቅ ፡ በጥሬ ፡ ገንዘብ፡በውጭ፡አገር፡ገንዘብ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ስለ ፡ መነገድ ። | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፶፭ | ባለዋጋ ፡ ማዕድኖችንና ፡ ዕንቍችን ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ በንግድ ፡ ስለ ፡ ማዛወር ። | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፶፱ | ታማኝነት ፡ ባለው ፡ በመንግሥት ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ የተንኰል ፡ አሠራር ። | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፷ | ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ የመንግሥትን ፡ ቀረጥና ፡ ግብር ፡ የመክፈልን ፡ እንቢተኛነት ። | አውራጃ ፡ ፍርፍ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፷፩ | ግብር ፡ እንዳይከፈል ፡ ስለ ፡ ማነሣሣት ። | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፷፪ | በግብርና፡በሌሎቹ ፡ የመንግሥት፡ቀረጥ ፡ ገቢ ፡ ምንጮች ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ እንዲደርስ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። ............................ | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፷፫ | ኬላ ፡ ስለ ፡ መስበር ፡ (ኮንትራባንድ) ። ... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፷፬ | በመንግሥት ፡ የገንዘብ ፡ ኤኮኖሚ ፡ ጉዳይና ፡ በሞኖፖል ፡ ረገድ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ። | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፷፭ | ቅጣትን ፡ የሚያከብዱ ፡ ምክንያቶች ። .... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፷፮ | ገንዘብ ፡ ስለ ፡ መሥራት ። .................. | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፷፯ | ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ ስለ፡ መለወጥ ። ....... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፷፰ | የገንዘቡን ፡ ዋጋ ፡ ስለ ፡ ማዋረድ ። ......... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፷፱ | ገንዘቡ ፡ እንዲዛወር ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። ...... | ከፍተኛውፍርድ ፡ ቤት ። |

| የወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ፡ቍጥር | ወንጀሉ ። | ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
|---|---|---|
| ፫፻፷ | የሐሰት ፡ ገንዘብን ፡ ባገር ፡ ስለ ፡ ማስገባት ፡ ስለ፡ መግዛት ፡ በአደራ ፡ አስቀማጭነት ፡ ስለ ፡ መያዝና ፡ ለስጦታ ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ። ...... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፫፻፷፩ | የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ወይም ፡ የመንግሥቱን ፡ ማኅተሞች ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ ስለ ፡ መለወጥ። | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፷፪ | ሌሎችን ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ያላቸውን ፡ ማኅተሞች ፡ ስለ ፡ መለወጥ ። .............. | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፷፫ | ግልጽ ፡ የሆኑ ፡ ምልክቶችን ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ ስለ ፡ መለወጥ ። ...................... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፷፬ | ዋጋ ፡ ያላቸውን ፡ ግልጽ ፡ የሆኑ ፡ ቴምብሮችን፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ ስለ ፡ መለወጥ ። | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፷፭ | መመዘኛዎችንና ፡ መለኪያዎችን ፡ ወደ ፡ ሐሰት፡ ስለ ፡ መለወጥ ። ...................... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፷፮ | ወደ፡ አገር፡ ውስጥ፡ ስለ ፡ ማግባትና ፡ ስለ፡ መግዛት ፡ በአደራ፡ ስለ፡ ማስቀመጥና፡ ስለ፡ማቅረብ፡ | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፷፯ | የማሳሳት ፡ ዐቅድ ፡ በሌለው ፡ አሳብ ፡ አስመስሎ ፡ ስለ ፡ መሥራት ። .............. | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፷፰ | ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ገንዘብ ፡ በባለዋጋ ፡ ነገሮች ፡ ወይም ፡ ሰነዶች ፡ ወይም ፡ ማኅተሞች ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ስለ ፡ ማድረስ ። .................... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፷፱ | የሐሰት ፡ ነገር ፡ መሥሪያዎችና ፡ መሣሪያዎች ። | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፸ | — | — |
| ፫፻፸፩ | — | — |
| ፫፻፸፪ | — | — |
| ፫፻፸፫ | በግዙፍ ፡ ስለሚሠራ ፡ ሐሰት ። .............. | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፸፬ | በርቀት ፡ ስለሚሠራ ፡ ሐሰት ። ........... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፸፭ | ስለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታዎች ። ............ | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፸፮ | በሐሰት ፡ ማስረጃ ፡ ስለ ፡ መገልገል። ......... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፸፯ | የመንግሥትና ፡ የወታደራዊን ፡ ሰነዶች ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ በመለወጥ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ። | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፫፻፸፰ | ሰነዶችን ፡ ስለ ፡ ማጥፋት ። .............. | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |

| የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ፡ቍጥር | ወንጀሉ ። | ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
|---|---|---|
| ፫፻፹፱ | (፩) የመንግሥት ፡ ወይም ፡ የወታደር ፡ ሰነዶችን ፡ ስለ ፡ ማጥፋት ። ........ | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| | (፪) የመንግሥት ፡ ወይም ፡ የወታደር ፡ ሰነዶችን ፡ ያጠፋው ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ ሲሆን ። ........ | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፫፻፺ | የንግድ ፡ ሰነዶችንና ፡ የባንክ ፡ ማስረጃዎችን ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ ስለ ፡ መለወጥና ፡ ስለ ፡ ማጥፋት። | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፺፩ | — | — |
| ፫፻፺፪ | የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ መመላለሻ ፡ ወረቀቶችን፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ ስለ ፡ መለወጥና ፡ በነዚሁ ፡ ስለ፡ መገልገል ። ........ | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፺፫ | ስለ ፡ ሐሰተኛ ፡ ምስክር ፡ ወረቀት ። ........ | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፺፬ | ሐሰተኛ ፡ የሆኑትን ፡ ግልጽ ፡ ምስክርነቶችን ፡ በማጭበርበር ፡ ስለ ፡ ማግኘት ። ........ | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፺፭ | ሐሰተኛ ፡ የሐኪም ፡ ምስክር ፡ ወረቀት ። ........ | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፺፮ | — | — |
| ፫፻፺፯ | ሥራ ፡ ሰጪዎችና ፡ የማደሪያ ፡ ቤት ፡ ሥራ፡ አስኪያጆች ፡ ስለሚያደርጉት ፡ ሐሰተኛ ፡ ቃል ፡ አሰጣጥና ፡ አመዘጋገብ ። ........ | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፺፰ | ወደ ፡ ሐሰት ፡ ለመለወጫ ፡ የሚያገለግሉ ፡ መሣሪያዎችና ፡ ጥበቦች ። ........ | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፫፻፺፱ | የንግድ ፡ ዕቃዎችን ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ ስለ ፡ መለወጥና ፡ ዋጋቸውን ፡ ስለ ፡ ማርከስ ። .... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፬፻ | የንግድ ፡ ዕቃዎችን ፡ እንዲዘዋወሩ ፡ ስለ፡ማድረግ። | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፬፻፩ | የንግድ ፡ ዕቃዎችን ፡ ስለ ፡ ማስመጣት ፡ ስለ ፡ መግዛትና ፡ በአደራ ፡ አስቀማጭነት ፡ ስለ ፡ መቀበል ። | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፬፻፪ | የማክበድ ፡ ቅጣቶችና ፡ ተጨማሪ ፡ ቅጣቶች ። | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፬፻፫ | — | — |
| ፬፻፬ | የወታደርን ፡ ምስጢር ፡ ስለ ፡ መግለጽ ። .... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፬፻፭ | የሥራን ፡ ምስጢር ፡ ስለ ፡ መግለጽ ። ...... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፬፻፮ | — | — |
| ፬፻፯ | የግል ፡ ሞያን ፡ ሥራ ፡ ምስጢር ፡ ስለ ፡መግለጽ ። | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፬፻፰ | | |

| የወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ፡ቍጥር | ወንጀሉ ። | ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
|---|---|---|
| ፬፻፱ | የሳይንስ ፤ የኢንዱስትሪን ፡ ወይም ፡ የንግዱን ፡ ምስጢር ፡ ስለ ፡ መግለጽ ። ................ | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፬፻፲ | — | — |
| ፬፻፲፩ | — | — |
| ፬፻፲፪ | የሥራ ፡ ግዴታን ፡ ተግባር ፡ ስለ ፡ መጣስ ። .. | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፬፻፲፫ | የሥራ ፡ ማቆም ፡ አድማ ፡ በማድረግ ፡ የአገልግሎትን ፡ ሥራ ፡ መከናወን ፡ ስለ ፡ ማወክ ። ... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፬፻፲፬ | በሥልጣን ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ ስለ ፡ መሥራት ። | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፬፻፲፭ | የሰውን ፡ ንብረት ፡ ለመፈተሽ ፡ ለመበርበር ፡ ወይም ፡ ዕቃውን ፡ ለመያዝ ፡ የተሰጠውን ፡ ሥልጣን ፡ ( መብት ) ፡ ከመጠኑ ፡ ስለ ፡ ማሳለፍ ። | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፬፻፲፮ | ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ሰውን ፡ ስለ ፡ መያዝና ፡ ስለ ፡ ማሰር ። ................ | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፬፻፲፯ | የማይገባ ፡ አሠራር ፡ ስለ ፡ መሥራት ። .... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፬፻፲፰ | እስረኛን ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ስለ ፡ መፍታትና ፡ እንዲያመልጥ ፡ ስለ ፡ መርዳት ። .. | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፬፻፲፱ | የጦር ፡ ምርኮኞችንና ፡ የወታደር ፡ ግዞተኞችን ፡ ስለ ፡ መፍታትና ፡ እንዲያመልጡ ፡ ስለ፡መርዳት፡ | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፬፻፳ | ለሕዝብ ፡ አገልግሎትና ፡ ጥቅም ፡ የሚከናወኑትን፡ ሥራዎች ፡ በተንኰል ፡ ዘዴ ፡ ስለ ፡ መምራት ። | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፬፻፳፩ | በአደራ ፡ በተሰጠው ፡ ዕቃ ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ ስለ ፡ ማዘዝ ። .............................. | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፬፻፳፪ | በሥራ ፡ ተግባር ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸም ፡ የመውሰድና ፡ የመስረቅ ፡ ወንጀል ። ............... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፬፻፳፫ | የማይገባውን ፡ ጥቅም ፡ ስለ ፡ መቀበል ። ....... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፬፻፳፬ | በግልጽ ፡ በተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ ስለ ፡ መነገድ። | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፬፻፳፭ | መደለያ ፡ ስለ ፡ መቀበል ። ................ | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፬፻፳፮ | በመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ በማስገደድ ፡ ስለ ፡ መጠቀም ። ...................... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፬፻፳፯ | ግልጽ ፡ የሆኑ ፡ ማስታወቂያዎችንና ፡ ዐዋጆችን፡ ስለ ፡ መናቅ ። ......................... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |

| የወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ፡ቍጥር | ወንጀሉ ። | ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| --- | --- | --- |
| ፬፻፹፰ | የማስመዝገብን ፡ ትእዛዝ ፡ ግዴታ ፡ የሚመለከቱትን ፡ ደንቦች ፡ ስለ ፡ መጣስ ። ........... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፬፻፹፱ | ክርክሮች ፡ ወይም ፡ የመንግሥት ፡ ጕዳዮች፡እንዳይገለጽ ፡ የሚከለክለውን ፡ ደንብ ፡ ስለ ፡ መጣስ። | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፬፻፺ | በራሱ ፡ ሥልጣን ፡ ፍርድን ፡ የመፈጸም ፡ ተግባር። | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፬፻፺፩ | ሥልጣንን ፡ በማይገባ ፡ ስለ ፡ መያዝ ። ..... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፬፻፺፪ | እሽጎችን ፡ ስለ ፡ መቅደድና ፡ ስለ ፡ መስበር ፤ በጥበቃ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ዕቃ ፡ ስለ ፡ መውሰዱ ። | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፬፻፺፫ | መቃወምና ፡ አለመታዘዝ ። ................. | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፬፻፺፬ | የኀይልና ፡ የማስገደድ ፡ ሥራ ። ........... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፬፻፺፭ | — | |
| ፬፻፺፮ | በግል ፡ ወዳጅነት ፡ ስለ ፡ መነገድ ።............ | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፬፻፺፯ | ጉቦ ፡ መስጠት ። ....................... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፬፻፺፰ | ለፍርድ ፡ ባለሥልጣን ፡ ስለ ፡ አለመግለጽ ። | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፬፻፺፱ | አንድ ፡ ተከሳሽ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ እንዳይቀርብ ፡ ስለ ፡ መደበቅ ። ...................... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻ | የፍርድን ፡ ሥራ ፡ እንዲሳሳት ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፩ | በሐሰት ፡ ስለ ፡ መወንጀል ፡ ወይም፡ስለ ፡ መክሰስ። | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፪ | ለፍርድ፡ ርዳታ ፡ መስጠትን ፡ እንቢ ፡ ስለ፡ ማለት። | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፫ | ፍርድ ፡ ቤትን ፡ ስለ ፡ መድፈር ።............. | በማናቸውም፡ፍርድ፡ቤት። |
| ፭፻፬ | የፍርድ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ምስጢርን ፡ ስለ ፡ መግለጽ ። ............................. | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፭ | ትክክለኛ ፡ ያልሆኑትን ፡ ወይም ፡ የተከለከሉትን፡ የሥራ ፡ ማስታወሻዎች ፡ በአደባባይ ፡ ስለ ፡ መግለጽ ። ......................... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፮ | አንዱ ፡ ወገን ፡ ስለሚሰጠው ፡ ሐሰተኛ ፡ ቃል ። | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፯ | ሐሰተኛ ፡ ምስክርነት ። ................. | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፭፻፰ | — | — |
| ፭፻፱ | ስለ ፡ ማነሣሣትና ፡ ስለ ፡ ማግባባት ። ....... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፭፻፲ | በሙግት ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ማጭበርበር ። ....... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፲፩ | የፍርድን ፡ ውሳኔ ፡ ለማሳሳት ፡ በተንኰል ፡ ስለሚደረግ ፡ የወሬ ፡ መግለጽ ፡ ሥራ ።......... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |

| የወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ፡ቍጥር | ወንጀሉ ። | ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
|---|---|---|
| ፩፻፸፪ | ባንዱ ፡ ወገን ፡ ተከራካሪ ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ የክሕደት ፡ ሥራ ፡ ስለመፈጸም ። ...... . . . . | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፻፸፫ | ተጨማሪ ፡ ቅጣቶችንና ፡ ጠቅላላውንም ፡ የጸጥታ ፡ ጥንቃቄ ፡ ስላለመጠበቅ ። ...... ...... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፩፻፸፬ | የተወሰነው፡ቅጣት፡እንዳይፈጸም፡ስለ፡ማሰናከል ። | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፩፻፸፭ | የእስረኛ ፡ ማምለጥ ። .................. | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፩፻፸፮ | እስረኛ ፡ እንዲያመልጥ ፡ ስለ ፡ ማደራጀትና ፡ ርዳታ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። ............ | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፩፻፸፯ | — | — |
| ፩፻፸፰ | የእስረኞች ፡ ግርግር ። .................. | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፩፻፸፱ | ከግዞት ፡ ቦታ ፡ ስለ ፡ ማምለጥ ። ........... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፩፻፹ | ለምርጫ ፡ ጉዳይ ፡ የሚደረገውን ፡ ስብሰባና ፡ የሥራ ፡ መከናወን ፡ ስለ፡ማወክና ፡ ስለ፡ማሰናከል። | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፩፻፹፩ | የምርጫ ፡ ድምፅ ፡ የመስጠትን ፡ ወይም ፡ የመምረጥን ፡ መብት ፡ ስለ ፡ መንካት ። ........ | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፩፻፹፪ | በምርጫ ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ የመደለያ ፡ ስጦታ ። .......................... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፩፻፹፫ | የማይገባ ፡ አሠራር ። .................. | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፩፻፹፬ | ባመዘጋገብ ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ ስለሚሠራ ፡ የማጭበርበር ፡ ወንጀል ።................ | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፩፻፹፭ | በድምፅ ፡ መስጠት ፡ ጊዜ ፡ የሚደረግ ፡ የማጭበርበር ፡ ሥራ ። ...................... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፩፻፹፮ | | |
| ፩፻፹፯ | የድምፅ ፡ መስጠትን ፡ ምስጢር ፡ ስለ ፡ መግለጽ። | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፩፻፹፰ | የድምፅ ፡ መስጫ ፡ ወረቀቶችንና ፡ የመሰብሰቢያቸውን ፡ ሣጥን ፡ ስለ ፡ መውሰድ ፡ ወይም፡ ስለ ፡ ማጥፋት ።......................... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፩፻፹፱ | — | — |
| ፩፻፺ | — | — |
| ፩፻፺፩ | አደገኛ ፡ የሆነ ፡ ሥራ ፡ ፈትነት ። .......... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፩፻፺፪ | የክፉ ፡ አድራጊዎች ፡ ማኅበረተኛነት ። ...... | ማናቸውም ፡ ፍርድ፡ቤት። |
| ፩፻፺፫ | — | — |

| የወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ፡ቍጥር | ወንጀሉ ። | ሰሚው፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
|---|---|---|
| ፩፻፷፭ | ለወንጀል ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ የወንጀልን ፡ ሥራ ፡ በጅቷል ፡ በማለት ፡ ስለሚደረግ ፡ መቀስቀስ ። | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፩፻፷፮ | በተከለከሉ ፡ መሣሪያዎች ፡ መነገድ ። ...... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፩፻፷፯ | የተከለከሉ ፡ ማኅበሮችና ፡ ስብሰባዎች ። .... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፩፻፷፰ | ድብቅ ፡ የሆኑ ፡ ማኅበሮች ፤ መሣሪያ ፡ የያዙ ፡ ክፍሎች ። ........................ | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፩፻፷፱ | የተከለከሉ ፡ ስብሰባዎች ። ............. | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፩፻፸ | በወሬ ፡ ሕዝብን ፡ ስለ ፡ ማሸበር ። ........ | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፩፻፸ | የሐሰት፡ ወሬዎችን፡ ስለ፡ ማውራትና፡ ሕዝብን፡ ስለማነሣሣት ። .................... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፩፻፸፩ | የማነሣሣት ፡ ጠባይ ፡ ያላቸው ፡ ሐሳብ ፡ መግለጫዎች ፡ (ማኒፌስታሲዮን) ። .......... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፩፻፸፪ | ሽብር ። ......................... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፩፻፸፫ | — | — |
| ፩፻፸፬ | ስብሰባንና ፡ ጉባኤን ፡ ስለ ፡ መበጥበጥ ። ...... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፩፻፸፭ | በጥፋተኛነት ፡ ከኀላፊነት ፡ ውጭ ፡ በመሆን ፡ ስለሚሠሩ ፡ ተግባሮች ። ............ | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፩፻፸፮ | የሃይማኖትን ፡ ስሜትና ፡ ሰላም ፡ ስለ ፡ መንካት። | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፩፻፸፯ | የሙታንን ፡ ሰላምና ፡ ክብር ፡ መንካት ። ... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፩፻፸፰ | የእሳት ፡ ቃጠሎ ። .................... | ከፍተኛው፡ ፍርድ፡ ቤት። |
| ፩፻፸፱ | ፍጥረታውያን፡ መቅሠፍቶችን፡ ስለ፡ መቀስቀስ። | ከፍተኛው፡ ፍርድ፡ ቤት። |
| ፩፻፹ | የሥራ ፡ ቦታዎችንና ፡ የመጠባበቂያ ፡ ሥራዎችን ፡ ስለ ፡ መጉዳት ። ................ | ከፍተኛው፡ ፍርድ፡ ቤት። |
| ፩፻፹፩ | ስለ ፡ ማፈንዳት ። ..................... | ከፍተኛው፡ ፍርድ፡ ቤት። |
| ፩፻፹፪ | በቸልተኝነት ፡ የሚደረግ ፡ ወንጀል ።........ | ከፍተኛው፡ ፍርድ፡ ቤት። |
| ፩፻፹፫ | በሚፈነዱ ፡ ነገሮች ፡ ወይም ፡ በሚመርዙ ፡ ጋዞች ፡ አደጋ ፡ ስለ ፡ ማድረስ ። .......... | ከፍተኛው፡ ፍርድ፡ ቤት። |
| ፩፻፹፬ | በሕግ ፡ የተከለከሉ ፡ ዕቃዎችን ፡ መሥራት ፡ መግዛት ፡ መሰወርና ፡ ማመላለስ ። ....... | ከፍተኛው፡ ፍርድ፡ ቤት። |
| ፩፻፹፭ | የሕንጻ፡ ሥራ ፡ ኪነ ፡ ጥበብ ፡ ደንቦችን ፡ ስለ ፡ መጣስ ። ........................ | ከፍተኛው፡ ፍርድ፡ ቤት። |

| የወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ፡ቍጥር | ወንጀሉ ። | ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
|---|---|---|
| ፬፻፺፮ | መጠባበቂያ ፡ የሚሆኑትን ፡ መሣሪያዎች ፡ ወይም ፡ የሚያገለግሉትን ፡ ዕቃዎች ፡ ማጥፋት፡ ወይም ፡ አለማደራጀት ። ............. | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፬፻፺፯ | በሕዝብ ፡ ላይ ፡ ከባድ ፡ አደጋ ፡ ሲደርስ ፡ ባለማስታወቅ ፡ የሚደረግ ፡ ጥፋት ።............ | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፬፻፺፰ | — | — |
| ፬፻፺፱ | ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ በተቋቋሙ ፡ ሥራዎችና ፡ አገልግሎቶች ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። . . . | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻ | በመገናኛዎችና ፡ በሕዝብ ፡ መመላለሻ ፡ ላይ ፡ ስለሚደርስ ፡ ከባድ ፡ ጉዳትና ፡ መበላሸት ። | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፩ | ምልክቶችንና ፡ የርዳታ ፡ ጥሪዎችን ፡ አላገባብ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። ...................... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፪ | ለሕዝብ ፡ ማመላለሻ ፡ ለሆኑት ፡ አደገኛ ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ ከደንብ ፡ ውጭ ፡ ስለ ፡ መስጠት። | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፫ | የሰውን ፡ በሽታ ፡ ስለ ፡ ማባዛት ። .......... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፬ | የከብት ፡ በሽታን ፡ ስለ ፡ ማባዛት ። ........ | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፭ | የሰብልን ፡ ወይም ፡ የደንን ፡ ትል ፡ ስለ፡መንዛት። | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፮ | ውሃን ፡ ስለ ፡ ማበላሸት ። .............. | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፭፻፯ | ግጦሽን ፡ ስለ ፡ ማበላሸት ። .............. | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፰ | የጤና ፡ አጠባበቅ ፡ ድንጋጌዎችን ፡ ስለ ፡ መጣስ። | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፱ | ችግር፡ ወይም ፡ ረኃብ ፡ እንዲመጣ ፡ ስለ፡ማድረግ። | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፭፻፲ | መርዛም ፡ ወይም ፡ የሚያፈዙ ፡ ነገሮችን ፡ ማውጣት ፡ ወይም ፡ መሥራት ፡ እንዲዘዋወሩ ፡ ማድረግ ። ........................ | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፲፩ | የሚጎዱ ፡ ወይም ፡ የተበላሹ ፡ ምግቦችንና ፡ ዕቃዎችን ፡ መሥራትና ፡ መሸጥ ።............ | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፲፪ | ለከብት ፡ ጉዳት ፡ የሚያመጣ ፡ ድርቆሽና ፡ ሌላም፡ ምግብ ፡ ስለ ፡ መሥራት ፡ ስለ ፡ ማበላሸትና ፡ ስለ ፡ መሸጥ ። ...................... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፲፫ | — | — |
| ፭፻፲፬ | አልኮል ፡ ወይም ፡ እስፒርቶ ፡ ያለባቸውን ፡ መጠጦች ፡ በማይገባ ፡ ስለ ፡ መስጠት ። ..... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |

| የወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ፡ቍጥር | ወንጀሉ ። | ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
|---|---|---|
| ፭፻፲፭ | አእምሮን ፡ በሚነኩ ፡ ሥራዎች ፡ አደጋ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። .. ........................ | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፲፮ | ሥራይ ፡ በሚሆኑ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ በመሳሰሉ ፡ ነገሮች ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፲፯ | ከባዶች ፡ ሁኔታዎች ። ................. | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፲፰ | የሕክምናንና፡ የጤና፡ አጠባበቅን ፡ ሥራ ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ ስለ ፡ መሥራት ። .............. | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፲፱ | መርዛምና ፡ አደገኛ ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ ስለ ፡ መስጠት ። ............... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፳ | የሕክምና፡ርዳታን፡ያለምክንያት፡ስለ፡መከልከል። | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፳፩ | — | — |
| ፭፻፳፪ | ከባድ ፡ (የግፍ) ፡ አገዳደል ። .............. | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፭፻፳፫ | ተራ ፡ የሆነ ፡ አገዳደል ፡ (ግዳይ) ። .......... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፭፻፳፬ | የመግደልን ፡ ቅጣት ፡ ስለ ፡ ማቅለል ። ..... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፭፻፳፭ | ራሱን ፡ እንዲገድል ፡ ስለ፡ ማነሣሣትና ፡ ስለ ፡ ማገዝ ።........................... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፭፻፳፮ | በቸልተኝነት ፡ ስለ ፡ መግደል ። ........... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፭፻፳፯ | ሕፃንን ፡ ስለ ፡ መግደል ። ............... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፳፰ | — | — |
| ፭፻፳፱ | እናት ፡ የፈጸመችው ፡ የማስወረድ ፡ ተግባር ። | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፴ | ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ የፈጸመው ፡ የማስወረድ ፡ ተግባር ። ........................... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፴፩ | እስከ ፡ ፭፻፴፯ — | — |
| ፭፻፴፰ | ታስቦ ፡ ስለ ፡ ተደረገ ፡ ከባድ ፡ የአካል ፡ ጉዳት ። | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፴፱ | አስቦ ፡ ስለ ፡ ተደረገ ፡ ቀላል ፡ የአካል ፡ ጉዳት ። | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፵ | ከአድራጊው ፡ አሳብ ፡ በላይ ፡ ሆኖ ፡ የሚገኝ ፡ የጥፋት ፡ ውጤት ። .................. | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፵፩ | — | — |
| ፭፻፵፪ | — | — |
| ፭፻፵፫ | — | — |
| ፭፻፵፬ | የእጅ ፡ እልፊት ። ...................... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፵፭ | የሰውን ፡ ሕይወት ፡ ለአደጋ ፡ ማጋለጥ ። ..... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |

| የወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ፡ቁጥር | ወንጀሉ ። | ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
|---|---|---|
| ፭፻፵፮ | ሰውን ፡ በአደገኛ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ማጋለጥና ፡ ስለ ፡ መተው ። ................. | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፵፯ | አንድ ፡ ሰው ፡ በአደጋ ፡ ላይ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ስላለመርዳት ። ........................ | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፵፰ | ልጆችን ፡ ስለ ፡ መጉዳት ። ................ | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፵፱ | ስለ ፡ አምባጓሮ ። ......................... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፶ | የይዋጣልን ፡ ፉክክር ። ................ | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፶፩ | የይዋጣልን ፡ ፉክክርን ፡ ስለ ፡ ማነሣሣት ፡ ስለ ፡ ማደፋፈር ፡ በክርክር ፡ ቦታ ፡ ስለ ፡ መገኘት ። | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፶፪ | ስለ ፡ ዛቻ ። ............................. | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፶፫ | የመክሰስ ፡ ወይም ፡ የማዋረድ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ዛቻ። | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፶፬ | ስለ ፡ ማስገደድ ። ...................... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፶፭ | የማሰብን ፡ ችሎታ ፡ ስለ ፡ ማሳጣት ። ...... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፶፮ | — | — |
| ፭፻፶፯ | ሰውን ፡ በግድ ፡ ይዞ ፡ ስለ ፡ ማስቀመጥ ።..... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፶፰ | ስለ ፡ መጥለፍ ። ...................... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፶፱ | ክፉና ፡ በጎ ፡ ለይታ ፡ ለማወቅ ፡ የማትችልና ፡ የመከላከል ፡ ዐቅም ፡ የሌላትን ፡ ሴት ፡ ስለ ፡ መጥለፍ ። ......................... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፷ | ሕፃንን ፡ ስለ ፡ መዝረፍ ፡ (ስለ ፡ መንጠቅ) ። | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፷፩ | ቅጣቱን ፡ የሚያከብዱ ፡ ሁኔታዎች ፤ | |
| | ፭፻፶፪ ፡ እስከ ፡ ፭፻፶፬ | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| | ፭፻፶፭ ፡ እስከ ፡ ፭፻፶፯ | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| | ፭፻፶፰ ፡ እስከ ፡ ፭፻፷ | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፭፻፷፪ | ሕፃኑን ፡ ስላለማቅረብ ። ................ | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፷፫ | ስለ ፡ ወላጆች ፡ የሚደረግ ፡ ልዩ ፡ አስተያየት ። | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፷፬ | በፖለቲካ ፡ ምክንያት ፡ ሰውን ፡ ስለ ፡ መስረቅ ። | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፭፻፷፭ | ሰውን ፡ በማይገባ ፡ አገልጋይ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፭፻፷፮ | የጥበቃ ፡ ወይም ፡ የመቈጣጠር ፡ ጉድለት ። | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፷፯ | በሰዎች ፡ ለመነገድ ፡ የተቋቋሙ ፡ ክፍሎች ፡ ወይም ፡ ማኅበሮች ። ................... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ፡ቤት ። |

| የወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ፡ቍጥር | ወንጀሉ ። | ስሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
|---|---|---|
| ፭፻፳፰ | የብሔራዊ ፡ መብቶችን ፡ ነጻ ፡ ተግባር ፡ ስለ ፡ መድፈር ። ........................ | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፳፱ | የነጻ ፡ መዘዋወርን ፡ መብት ፡ ስለ ፡ መድፈር ። | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፴ | የሥራ ፡ ነጻነትን ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ መድፈር ። ... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፴፩ | መኖሪያ ፡ ቤትን ፡ ስለ ፡ መድፈር ።.......... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፴፪ | ቅጣትን ፡ የሚያከብዱ ፡ ሁኔታዎች ።........ | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፴፫ | ደብዳቤዎችንና ፡ የሚላኩ ፡ ዕቃዎችን ፡ ስለ ፡ ማቋረጥና ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ ስለ ፡ ማዛወር ። | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፴፬ | እስከ ፡ ፭፻፴፱ — | — |
| ፭፻፵ | ስምን ፡ ስለ ፡ ማጥፋትና ፡ በሐሰት ፡ ስለ ፡ መወ ንጀል ።............................ | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፵፩ | — | — |
| ፭፻፵፪ | — | — |
| ፭፻፵፫ | ስድብና ፡ ማዋረድ ። .................. | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፵፬ | — | — |
| ፭፻፵፭ | — | — |
| ፭፻፵፮ | ቅጣትን ፡ የሚያከብዱና ፡ ልዩ ፡ ሁኔታዎች ። .. | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፵፯ | — | — |
| ፭፻፵፰ | — | — |
| ፭፻፵፱ | የመድፈር ፡ ሥራ ። .................... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፭፻፶ | በንጽሕና ፡ ክብር ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ የኀ ይል ፡ ተግባር ። .................... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ፡ቤት። |
| ፭፻፶፩ | ለመቃወም ፡ በማይችሉ ፡ አእምሮዋቸው ፡ በተበ ላሸ ፡ ወይም ፡ የአእምሮ ፡ ደካማ ፡ በሆኑ ፡ ሰዎች፡ ክብረ ፡ ንጽሕና ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ የድፍ ረት ፡ በደል ። ......................... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፭፻፶፪ | በሆስፒታል ፡ ውስጥ ፡ በተገኙ ፡ ሰዎች ፡ በተ ጋዙ ፡ ወይም ፡ በታሰሩ ፡ ሰዎች ፡ ክብረ ፡ ንጽሕና፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ በደል ። ........... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፭፻፶፫ | ከፍ ፡ ያለውን ፡ የሴት ፡ ችግር ፡ ወይም ፡ ተገዥ ነትዋን ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ስለሚደረ ገው ፡ የማታለል ፡ ሥራ ።................ | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |

| የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር | ወንጀሉ ። | ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
|---|---|---|
| ፭፻፺፬ | በሕፃኖች ፡ ክብረ ፡ ንጽሕና ፡ ላይ ፡ ስለሚደረገው ፡ በደል ። ...................... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፺፭ | ከዐሥራ ፡ አምስት ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ ባላቸው ፡ አካለመጠን ፡ ባላደረሱ ፡ ልጆች ፡ ክብረ ፡ ንጽሕና ፡ ላይ ፡ ስለሚደረገው ፡ በደል ። .................... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፺፮ | ማሳት ። ............................ | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፺፯ | — | — |
| ፭፻፺፰ | ከባዶች ፡ ሁኔታዎች ። .................... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፭፻፺፱ | — | — |
| ፮፻ | ለተፈጥሮ ፡ ግብር ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ የአመንዝራነት ፡ ሥራ ። ...................... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፩ | ቅጣቱን ፡ የሚያከብዱ ፡ ሁኔታዎች ።......... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፪ | ለተፈጥሮ ፡ ተግባር ፡ ተቃራኒ ፡ የሆኑ ፡ ሌሎች ፡ ሥራዎች ። ........................ | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፫ | — | — |
| ፮፻፬ | የሌላውን ፡ ሰው ፡ የአመንዝራነት ፡ ሥራ ፡ የዘወትር ፡ መጠቀሚያ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። ....... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፭ | ሴቶችንና ፡ አካለመጠን ፡ ያልደረሱትን ፡ በማቃጠር ፡ በማከራየት ፡ ስለ ፡ መነገድ ። ...... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፮ | ስለ ፡ ከባድ ፡ ሁኔታዎች ። ................ | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፯ | ሴቶችን ፡ ወይም ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሱትን ፡ ለዝሙት ፡ ለማቅረብ ፡ ስለሚደረጉት ፡ ዝግጅቶች ። ........................ | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፰ | ክብረ ፡ ንጽሕናንና ፡ መልካም ፡ ጠባይን ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ የሚያሳፍር ፡ ሥራን ፡ በአደባባይ ፡ ስለ ፡ መግለጽ ። .................... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፱ | ኀፍረተ ፡ ነገርን ፡ የሚያሳዩ ፡ ወይም ፡ ለመልካም ፡ ጠባይ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ አሳትሞ ፡ ስለ ፡ ማውጣት ። ...................... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፲ | አሳፋሪ ፡ ወይም ፡ ለመልካም ፡ ጠባይ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆኑትን ፡ ስለ ፡ ማሳየት ። .............. | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |

| የወንጀለኛ፣ መቅጫ ፣ ሕግ፡ቍጥር | ወንጀሉ ። | ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
|---|---|---|
| ፮፻፲፩ | — | — |
| ፮፻፲፪ | መልካም፡ጠባይን ፡ የሚነኩ ፡ ነገሮችን ፡ ለሕዝብ፡ ስለ ፡ መግለጽ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ማስታወቅ ። | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፲፫ | አካለመጠን ፡ ያላደረሱትን ፡ ልጆች ፡ በሕሊና ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ ከሚጥሉ ፡ ዕቃዎች ፡ ሥዕሎች ፡ ጽሑፎች ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ። ........ | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፲፬ | ጋብቻን፡ በተንኰል ፡ በማታለል ፡ ስለ፡መፈጸም ። | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፲፭ | በሕግ ፡ የተከለከለ ፡ የጋብቻን ፡ ሥርዐት ፡ ስለ ፡ መፈጸም ። ........................... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፲፮ | በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። . . . | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፲፯ | — | — |
| ፮፻፲፰ | ስለ ፡ ሴሰኝነት ። ......................... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፲፱ | — | — |
| ፮፻፳ | — | — |
| ፮፻፳፩ | በዘመድ ፡ መካከል ፡ ስለሚፈጸመው ፡ የዝሙት ፡ ተግባር ። ...................... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፮፻፳፪ | በሥጋ ፡ ዘመዶች ፡ መካከል ፡ ክብረ ፡ ንጽሕናን፡ በሚያበላሽ ፡ ተግባር ፡ ስለ ፡ መደፋፈር ።...... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፮፻፳፫ | የሕፃኑን ፡ መወለድ ፡ ስለ ፡ አለማስታወቅ ። . . | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፳፬ | የሕዝብን ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ በሐሰት ፡ ስለ ፡ መለወጥ ፡ ሕፃኑን ፡ አስመስሎ ፡ ስለ ፡ ማቅረብና ፡ ከተባለው ፡ መዝገብ ፡ ስለ ፡ መሰረዝ ። | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፳፭ | ቀለብ ፡ የመስጠት ፡ ተግባርን ፡ ስላለመፈጸም ። | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፳፮ | ልጅን ፡ የማሳደግ ፡ ተግባርን ፡ ስለ ፡ መጣስ ። | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፳፯ | እስከ ፡ ፮፻፳፱ — | — |
| ፮፻፴ | ስለ ፡ ስርቆት ። ......................... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፴፩ | የሥራ ፡ ኀይልን ፡ ስለ ፡ መስረቅ ። ......... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፴፪ | የጋራ ፡ የሆኑትን ፡ ዕቃዎች ፡ ስለ ፡ መስረቅ ። | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፴፫ | በሙታን፡ ላይ፡ ስለሚሠራ ፡ የስርቆት ፡ ወንጀል። | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፴፬ | ቀላል ፡ የሆነ ፡ ስርቆት ።................. | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፴፭ | ከባድ ፡ ስርቆት ።..................... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፮፻፴፮ | ስለ ፡ ወንበዴነት ። .................... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |

| የወንጀለኛ፡ መቅጫ፡ ሕግ፡ቍጥር | ወንጀሉ ። | ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
|---|---|---|
| ፮፻፴፯ | ከባድ ፡ የሆነ ፡ የወንበዴነት ፡ ሥራ ። ........ | ከፍተኛው፡ ፍርድ፡ ቤት። |
| ፮፻፴፰ | ስለ ፡ ዘረፋ ። ........................ | ከፍተኛው፡ ፍርድ፡ ቤት። |
| ፮፻፴፱ | የባሕር ፡ ወንበዴነት ። .................... | ከፍተኛው፡ ፍርድ፡ ቤት። |
| ፮፻፵ | የተጠበቁ ፡ ሁኔታዎች ። ................ | ከፍተኛው፡ ፍርድ፡ ቤት። |
| ፮፻፵፩ | እመነትን ፡ ስለ ፡ ማጕደል ። ............... | ከፍተኛው፡ ፍርድ፡ ቤት። |
| ፮፻፵፪ | ከባድ ፡ የሆነ ፡ የእምነት ፡ ማጕደል ። ........ | ከፍተኛው፡ ፍርድ፡ ቤት። |
| ፮፻፵፫ | አግኝቶ ፡ ስለ ፡ መደበቅ ። ................ | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፵፬ | የሌላ ፡ ሰው ፡ በሆነ ፡ ሀብት ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ ስለ ፡ መገልገል ። ........................ | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፵፭ | ወድቆ ፡ የተገኘውን ፡ ዕቃ ፡ ለራስ ፡ ስለ ፡ ማድረግ። | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፵፮ | ባለቤት ፡ የሌለውን ፡ ዕቃ ፡ ወይም ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብቶችን ፡ ስለ ፡ መውሰድ ። .............. | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፵፯ | የመሸሸግ ፡ ወንጀል ። .................... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፵፰ | ከባድ ፡ የሆነ ፡ የመሸሸግ ፡ ወንጀል ። ........ | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፵፱ | በሰው ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ የከብት ፡ መንጋ ፡ ሰዶ ፡ ስለ ፡ ማበላሸት ። .................... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፶ | በሰው ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ ሁከት ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፶፩ | በሰው ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ስለ ፡ ማድረስ ። | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፶፪ | የወሰን ፡ ምልክቶችን ፡ ከስፍራቸው ፡ ስለ ፡ ማዘዋወርና ፡ ስለ ፡ ማጥፋት ። ............... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፶፫ | መደበኛ ፡ ሁኔታ ። ...................... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፶፬ | ከባድ ፡ ሁኔታ ። ...................... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፶፭ | — | — |
| ፮፻፶፮ | ስለ ፡ አታላይነት ። .................... | ከፍተኛው፡ ፍርድ፡ ቤት። |
| ፮፻፶፯ | ልዩ፡ ሁናቴ ፤ ሥንቅ ፡ ሳይኖር ፡ ቼክ ፡ ስለ ፡ መስጠት ። ......................... | ከፍተኛው፡ ፍርድ፡ ቤት። |
| ፮፻፶፰ | ስለ ፡ ከባድ ፡ አታላይነት ። ............. | ከፍተኛው፡ ፍርድ፡ ቤት። |
| ፮፻፶፱ | የኢንሹራንሱን ፡ ኩባንያ ፡ ስለ ፡ ማታለል ። | ከፍተኛው፡ ፍርድ፡ ቤት። |
| ፮፻፷ | — | — |
| ፮፻፷፩ | በሕዝብ ፡ እምነት ፡ ስለ ፡ መጠቀም ። ....... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፷፪ | አነስተኛ ፡ የሆኑ ፡ የማታለል ፡ ሥራዎች ። ... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |

| የወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ፡ቍጥር | ወንጀሉ ። | ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
|---|---|---|
| ፮፻፷፫ | በግል ፡ ሰው ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ ተደረገ ፡ የተንኰል ፡ ሥራ ፡ አመራር ። ................... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፮፻፷፬ | ከባድ ፡ የሆነ ፡ ተንኰል ፡ ያለበት ፡ የሥራ ፡ አመራር ። ........................... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፮፻፷፭ | ጥቅም ፡ ታገኛለህ ፡ በማለት ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ በመደለል ፡ ስለ ፡ ማነሣሣት ። .......... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፷፮ | አካለመጠን ፡ ያላደረሱትን ፡ ወይም ፡ ችሎታ ፡ የሌላቸውን ፡ ሰዎች ፡ ንብረታቸውን ፡ የሚጎዳ ፡ ሥራ ፡ እንዲሠሩ ፡ ስለ ፡ ማነሣሣት ። ....... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| ፮፻፷፯ | አራጣ ። ................................ | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፮፻፷፰ | ስለ ፡ መንጠቅ ። ..................... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፮፻፷፱ | ስለ ፡ ማስፈራራት ። ................... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፮፻፸ | ከባድ ፡ ሁኔታ ። ....................... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፮፻፸፩ | በሌላ ፡ ሰው ፡ ታማኝነት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። ......................... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፮፻፸፪ | ጉዳትን ፡ የሚያደርሱ ፡ ሐሰተኛ ፡ መግለጫዎች። | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፮፻፸፫ | የማይገባ ፡ ውድድር ። ................... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፮፻፸፬ | የፋብሪካ ፡ ምልክቶችን ፡ (ማርኮችን)፡ የመጡበትን ፡ ስፍራ ፡ ማመልከቻ ፡ ጽሑፎችን ፡ ሥዕሎችንና ፡ ዐይነቶችን ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ ስለ ፡ መለወጥ ። ........................... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፮፻፸፭ | የድርሰት ፡ መጻሕፍትን ፡ ወይም ፡ የጥበብ ፡ ሥራዎችን ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ ስለ ፡ መለወጥ ። ...... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፮፻፸፮ | የተከለከሉትን ፡ ድርሰቶች ፡ ስለ ፡ ማሳየት ፡ ወይም ፡ ማሠራት ። .................... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፮፻፸፯ | እስከ ፡ ፮፻፸፱ — | — |
| ፮፻፹ | በአጭበርባሪነት ፡ ዕዳ ፡ ለመክፈል፡ስላለመቻል። | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፮፻፹፩ | ስለ ፡ መክሠር ። ...................... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፮፻፹፪ | በአጭበርባሪነት ፡ ኪሣራ ፡ እንዲደርስ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። ......................... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |

| የወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ፡ቍጥር | ወንጀሉ ። | ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
|---|---|---|
| ፯፻፹፫ | በተያዘ ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ የአጭበርባሪነት ፡ ወን ጀል ፡ ስለ ፡ መሥራት ።................. | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፯፻፹፬ | በመያገዣ ፡ ስም ፡ የተቀመጡትን ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ አግባብ ፡ የትያዙትን ፡ ዕቃዎች ፡ ለሌላ ፡ ስለ ፡ ማዋል ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ማጥፋት ። ..... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፯፻፹፭ | በፍርድ ፡ የተያዘውን ፡ ዕቃ ፡ ለሌላ ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ ማዋል ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ማጥፋት ። ........ | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፯፻፹፮ | የማይገባ ፡ ጥቅም ፡ ስለ ፡ ማስገኘት ። ....... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፯፻፹፯ | የድምፅ ፡ ብልጫን ፡ ለማግኘት ፡ መደለያ ፡ ስለ ፡ መስጠት ። ..................... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፯፻፹፰ | የስምምነት ፡ ድምፅ ፡ አጭበርብሮ ፡ ስለ ፡ ማግ ኘት ። ........................... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |
| ፯፻፹፱ | — | — |
| ፯፻፺፫ | እስከ ፡ ፰፻፳ ፤ ከቍ ፡ ፯፻፵፰ ፡ በቀር ፡ በወንጀ ለኛ ፡ መቅጫ ፡ ስምንተኛ ፡ መጽሐፍ ፤ ልዩ ፡ ክፍል ፤ በሕዝባዊና፡ በማኅበራዊ፡ ጥቅሞች፡ላይ፡ ስለሚፈጸም ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ። ......... | ወረዳ ፡ ፍርድ ፤ ቤት ። |

## በሌላ፡ ሕጎች ፡ ስለ ፡ ተወሰኑ፡ ቅጣቶች ።

| | | |
|---|---|---|
| | ቅጣቱ ፡ ከሦስት፡ ዓመት፡የማይበልጥ ፡ እስራት ፡ መቀጫ ፡ ሳይኖረውም ፡ ወይም ፡ ከነመቀጫው ፡ ሲሆን ። ........................... | ወረዳ ፤ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| | ቅጣቱ ፡ ከአምስት ፡ ዓመት ፡ የማይበልጥ ፡ እስራት ፡ መቀጫ ፡ ሳይኖረው ፡ ወይም ፡ ከነ መቀጫው ፡ ሲሆን ።.................... | አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። |
| | ቅጣቱ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከተሰጠው ፡ የሚበ ልጥ ፡ ከሆነ ። ......................... | ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት። |

# ሁለተኛ ፡ ሠንጠረዥ ።

(በቍጥር ፡ ፭፲፩ ፡ መሠረት) ።

የክሶች ፡ ዐይነት ።

ከባድ ፡ ( የግፍ ፡ ) አገዳደል ።

<u>የክሱ ፡ ማመልከቻ ።</u>

በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር፡ ፭፻፳፪ ፡ የተመለከተውን ፡ በመተላለፍ ፡ ከባድ ፡ የግፍ ፡ አገዳደል ፡ በመፈጸም ።

<u>የወንጀሉ ፡ ዝርዝር ።</u>

እገሌና ፡ እገሌ ፡ (የተከሳሽን ፡ ስም ፡ ሙላ)፡ በ............ቀን ፡ ................. በ.................. አስበ ፡ እገሌና ፡ እገሌን ፡ (የሟቹን ፡ ስም ፡ ጥቀስ)፡ ገድሎአል።

*(ሀ) በወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፳፩፡ ወይም ፡ ፳፪ ፡ በተመለከቱት ፡ ቅጣትን ፡ በሚያከብዱ ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፤

*(ለ) ነፍስ ፡ ለመግደል ፡ ወይም ፡ በጦር ፡ መሣሪያ ፡ ለመዝረፍ ፡ ዶልቶ ፡ የወንበዴ ፡ ማኅበረተኛ ፡ በመሆን ፡ ወይም ፡ የሴራ ፡ አባል ፡ ጋራ ፡ በማበር ፤

*(ሐ) በወንጀል ፡ ላይ ፡ ወንጀል ፡ በመጨመር ፡ ወይም ፡ ሌላውን ፡ ወንጀል ፡ በመሸፈን ፡ ተከሷል ።

*ተገቢ ፡ ያልሆነውን ፡ ለይቶ ፡ መሰረዝና ፡ ዝርዝር ፡ መስጠት ።

---

ነፍስ ፡ ለመግደል ፡ በመሞከር ።

<u>የክሱ ፡ ማመልከቻ ።</u>

በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፳፯ ፡ እና ፡ ፭፻፳፪ ፡ የተመለከተውን ፡ በመተላለፍ ፡ ነፍስ ፡ ለመግደል ፡ በመሞከር ።

<u>የወንጀሉ ፡ ዝርዝር ።</u>

እገሌና ፡ እገሌ ፡ (የተከሳሽን ፡ ስም ፡ ሙላ)፡ በ............ቀን፡.................. በ............ እገሌና ፡ እገሌ ፡ ( ጉዳት ፡ የደረሰበትን ፡ ሰው ፡ ስም ፡ ሙላ ) ፡ የተባለውን ፡ ለመግደል ፡ በመሞከር ፤

*(ሀ) በወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፳፩ ፡ እና ፡ ፳፪፡ በተመለከቱት ፡ ቅጣትን ፡ በሚያከብዱ ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፤

*(ለ) ነፍስ ፡ ለመግደል ፡ ወይም ፡ በጦር ፡ መሣሪያ ፡ ለመዝረፍ ፡ ዶልቶ ፡ የወንበዴ ፡ ማኅበረተኛ ፡ በመሆን ፡ የሴራ ፡ አባል ፡ ጋራ ፡ በማበር ፤

*(ሐ) በወንጀል ፡ ላይ፡ወንጀል ፡ በመጨመር ፡ ወይም ፡ ሌላን ፡ወንጀል ፡ በመሸፈን፤

*ተገቢ ፡ ያልሆነውን ፡ ለይቶ ፡ መሰረዝና ፡ ዝርዝር ፡ መስጠት ፡ ተከሷል ።

---

በቸልተኝነት ፡ ነፍስ ፡ ስለ፡መግደል ።

የክሱ ፡ ማመልከቻ ።

በወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፳፮ ፡ የተመለከተውን፡ በመተላለፍ በቸልተኝነት ፡ ነፍስ ፡ በመግደል ።

የወንጀሉ ፡ ዝርዝር ።

እገሌና ፡ እገሌ ፡ (የተከሳሽን ፡ ስም ፡ ሙላ) ፡ በ......... ቀን፡............በ..........

እገሌና ፡ እገሌ ፡ (የሟቹን ፡ ስም ፡ ሙላ) ፡ የተባለውን ፡ በቸልተኝነት ፡ በመግደል* ።

*በወንጀለኛ፡ ሕግ፡ በቍጥር፡ ፶፱፡ እንደ፡ ተደነገገው፡ የቸልተኝነትን ፡ ሁኔታ ፡ በዝርዝር ፡ መግለጽ ።

---

በጽሑፍ ፡ ላይ ፡ የሐሰት ፡ ሥራ ፡ ስለ፡ መሥራት ።

የክሱ ፡ ማመልከቻ ።

በወንጀለኛ፡ መቅጫው ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፹፫ ፡ የተመለከተውን ፡ በመተላለፍ ፡ በጽሑፍ ፡ ላይ ፡ የሐሰት ፡ ሥራ ፡ በመሥራት ።

የወንጀሉ ፡ ዝርዝር ።

እገሌና ፡ እገሌ ፡ (የተከሳሽን ፡ ስም ፡ ሙላ)፡ በ........... ቀን ፡ ...... ......... በ................ የእገሌና ፡ የእገሌ ፤ ................ ነው ፡ የተባለውን ፡ ንዛዜ፡ የሐሰት ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ ሠራበት ፡ ተከሷል ።

---

በሐሰት ፡ ሥራ ፡ በተሠራበት ፡ ሰነድ ፡ ስለ ፡ መጠቀም ።

የክሱ ፡ ማመልከቻ ።

በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቍ. ፫፻፺፯ ፡ የተመለከተውን ፡ በመተላለፍ ፡ የሐሰት ፡ ሥራ ፡ በተሠራበት ፡ ሰነድ ፡ ስለ፡ መጠቀም ።

የወንጀሉ ፡ ዝርዝር ።

እገሌና ፡ እገሌ ፡ (የተከሳሽን ፡ ስም ፡ ሙላ) ፡ በ........... ቀን ፡ ................ በ............. እገሌና ፡ እገሌ ፡ (የሐሰት ፡ ሥራ ፡ የሠራውን ፡ ስም ፡ ሙላ) ፡ የተባለው ፡ የሐሰት ፡ ሥራ ፡ የተሠራበትን ፡ ቼክ ፤ የሐሰት፡ ሥራ ፡ የተሠራበት ፡ መሆኑን ፡ እያወቀ ፡ እንዲጠቀምበት ፡ በማድረጉ ፡ ተከሷል ።

---

### የሐሰተኛ ፡ ምስክርነት ።

**የክሱ ፡ ማመልከቻ ።**

በወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፵፯ ፡ የተመለከተውን ፡ በመተላለፍ ፡ በሐሰት ፡ በመመስከር ።

**የወንጀሉ ፡ ዝርዝር ።**

እገሌና ፡ እገሌ ፡ (የተከሳሽን ፡ ስም ፡ ሙሉ ) ፡ በ············ቀን ፡ ················ በ ················ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በነበረው ፡ ክርክር ፡ ዘንድ ፡ በምስክርነት ፡ ቀርቦ ፡ በነገሩ ፡ እገሌና ፡ እገሌ ፡ ከሳሽ ፡ እገሌና ፡ እገሌ ፡ ተከሳሽ ፡ በነበሩበት ፡ ጉዳይ ፡ ዐውቆ ፡ በመዋሸት ፡ ምሎ ፡ በመመስከሩ ፡ ····················(የሐሰት ፡ ምስክርነቱን ፡ ቃል ፡ ግለጽ ) ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ በምስክርነት ፡ የተሰጠው ፡ ማስረጃ ፡ በተባለው ፡ ክርክር ፡ ውስጥ ፡ ቀዋሚ ፡ ማስረጃ ፡ በመሆኑ ፡ ተከሷል ።

---

### የእስረኛ ፡ ማምለጥ ።

**የክሱ ፡ ማመልከቻ ።**

በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር፡ ፬፻፶፭ ፡ የተመለከተውን ፡ ተላልፎ ፡ ከእ ስር ፡ ቤት ፡ በማምለጥ ።

**የወንጀሉ ፡ ዝርዝር ።**

እገሌና ፡ እገሌ ፡ (የተከሳሽን፡ ስም ፡ ሙሉ) ፡ በ··········· ቀን ፡············ በ······· ከ··············· እገሌ ፡ ( ሕጋዊ ፡ በሆነ ፡ ስፍራ ፡ የታሰረበትን ፡ ግለጽ ) ፡ አም ልጦ ፡ በሰዎች ፡ ወይም ፡ በንብረቶች ፡ ላይ ፡ ( ዝርዝሩን ፡ አብራርተህ ፡ ግለጽ ፡ ) የማስ ፈራራት ፡ ወይም ፡ የአጥቂነት ፡ ተግባር ፡ በመፈጸም ፡ ተከሷል ።

---

### የእሳት ፡ ቃጠሎ ።

**የክሱ ፡ ማመልከቻ ።**

በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፹፰ ፡ የተመለከተውን ፡ ተላልፎ፡ ቤት ፡ በማቃጠል ።

**የወንጀሉ ፡ ዝርዝር ።**

እገሌና፡ እገሌ፡ (የተከሳሽን፡ ስም ፡ ጥቀስ)፡ በ············ቀን፡··········በ········· በተንኰል* ፡ (አደጋ* ፡ ለመጣል፡ አስቦ፡ በመነሣት ፡ ) (በራሱ* ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ እሳት ፡ በመለኰሱ ፡ ( በእገሌና ፡ በእገሌ ፡ ንብረት* ፡ ላይ ፡ እሳት ፡ በመለኰሱ ፡ ) (የተቃጠለ ውን ፡ ንብረት ፡ ግለጽ ፡ ) ተከሷል ።

* ተገቢ ፡ ያልሆነው ፡ ይሰረዝ ።

አስበ ፡ ስለ ፡ ተደረገ ፡ ከባድ ፡ የአካል ፡ ጉዳት ።

<u>የክሱ ፡ ማመልከቻ ።</u>

በወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፴፰ ፡ የተመለከተውን ፡ ተላልፎ ፡ አስበ ፡ ስለ፡ ተደረገ ፡ ከባድ ፡ የአካል ፡ ጉዳት ።

<u>የወንጀሉ ፡ ዝርዝር ።</u>

እገሌና ፡ እገሌ ፡ (የተከሳሽ ፡ ስም ፡ ሙሉ) ፡ በ............ቀን ፡............በ..........

*(ሀ) እገሌና ፡ እገሌን ፡ (የተጎጂውን ፡ ስም ፡ ሙሉ)፡ አስበ ፡ ለተጎጂው ፡ ሕይወት ፡* በሚያሠጋ ፡ ሁኔታ ፡ በሰውነትም ፡ ሆነ ፡ በአእምሮው ፡ ላይ ፡ ለዘወትር ፡ ጠንቅ ፡ በሚያተርፍ ፡ ዐይነት ፡ ያቈሰለ ።

*(ለ) አስበ ፡ የእገሌንና ፡ የእገሌን ፡ አካል* ፡ ያጎደለ ፡ (የእገሌንና ፡ የእገሌን ፡ ቀዋሚ ፡ ከሆኑት ፡ ክፍለ ፡ አካላቱ ፡ ወይም ፡ አስፈላጊ ፡ ከሆኑት ፡ ብልቶቹ* ፡ አንዱን ፡ ያጎደለ) ፡ በእገሌና ፡ በእገሌ ፡ አካል ፡ ላይ ፡ በጠነከረና ፡ በሚያሰቅቅ ፡ ዐይነት ፡ መልክ ፡ ያበላሸ ።

*(ሐ) አስበ ፡ በእገሌና ፡ በእገሌ ፡ ላይ ፡ የጠነከረ ፡ መቍሰል ፡ ወይም ፡ ሕመም ፡ እንዲደርስበት ፡ በማድረጉ ፡ ተከሷል ።

*ተገቢነት ፡ የሌላቸውን ፡ ለይቶ ፡ መሰረዝና ፡ ዝርዝር ፡ መስጠት ።

---

የመድፈር ፡ ሥራ ።

<u>የክሱ ፡ ማመልከቻ ።</u>

በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፹፱ ፡ የተመለከተውን ፡ ተላልፎ ፡ የመድፈር ፡ ሥራ ፡ በመሥራቱ ።

<u>የወንጀሉ ፡ ዝርዝር ።</u>

እገሌና ፡ እገሌ ፡ (የተከሳሽን ፡ ስም ፡ ሙሉ)፡ በ............ቀን ፡..........በ.......
እገሌንና ፡ እገሌን ፡ (የተጎጂን ፡ ስም ፡ ጥቀስ) ፤

*(ሀ) በኀይል ፤

*(ለ) በብርቱ ፡ ዛቻ ፤

*(ሐ) አእምሮዋ ፡ እንዳያውቅ ፡ በማድረግ ፤

*(መ) ለመቃወም ፡ እንዳትችል ፡ በማድረግ ፤ አስገድዶ ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ተግባርን ፡ በመፈጸሙ ፡ ተከሷል ።

*ተገቢ ፡ ያልሆነውን ፡ ለይቶ ፡ መሰረዝና ፡ ዝርዝር ፡ መስጠት ።

ስርቆት ።

የክሱ ፡ ማመልከቻ ።

በወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቊጥር ፡ ፮፻፴ ፡ የተመለከተውን ፡ ተላልፎ ፡ በመ ስረቅ ።

የወንጀሉ ፡ ዝርዝር ።

እገሌና ፡ እገሌ፡ (የተከሳሽን፡ ስም ፡ ሙላ) ፡ የተባለው ፡ በ······· ቀን ፡ ········በ······· የእገሌንና ፡ የእገሌን ፡ (የባለንብረቱን ፡ ስም ፡ ግለጽ) ፡ ሀብት ፡ የሆነውን ፡ ዕቃ ፡ (የተሰረቀውን፡ዕቃ፡ዝርዝር ) ፡ የማይገባውን፡ብልጽግና፡ለማግኘት፡ሲል ፡ ስለ ፡ ወሰደ ፡ ተከሷል ።

---

ወንበዴነት ።

የክሱ ፡ ማመልከቻ ።

በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቊጥር ፡ ፮፻፴፮ ፡ የተመለከተውን ፡ ተላልፎ ፡ የወንበዴነት ፡ ሥራ ፡ በመሥራቱ ።

የወንጀሉ ፡ ዝርዝር ።

እገሌና ፡ እገሌ፡ (የተከሳሽን ፡ ስም ፡ ሙላ) ፡ የተባለው ፡ በ········· ቀን ፡ ··········· በ················ የስርቆት ፡ ወንጀል ፡ ለመሥራት ፡ አስቦ * ፤ የስርቆት ፡ ወንጀል ፡ ሲሠራ ፡ ተይዞ* ፤

*(ሀ) በእገሌና ፡ በእገሌ ፡ (የተጎጂን ፡ ስም ፡ ጥቀስ) ፡ ላይ ፡ የኀይል ፡ ሥራ ፡ በመፈጸሙ ፤

*(ለ) በእገሌና ፡ በእገሌ ፡ ላይ ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ የማንገላታት ፡ ( የማስፈራራት ) ፡ ተግባር ፡ በመፈጸሙ ።

*(ሐ) እገሌና ፡ እገሌ ፡ ለመከላከል ፡ እንዳይችሉ ፡ በማድረጉ ፤ ተከሷል ።

* ተገቢ ፡ ያልሆነውን ፡ ለይቶ ፡ መሰረዝና ፡ ዝርዝር ፡ መስጠት ።

---

መሸሸግ ።

የክሱ ፡ ማመልከቻ ።

በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቊጥር ፡ ፮፻፵፯ ፡ የተመለከተውን ፡ ተላልፎ ፡ በመሸሸግ ።

የወንጀሉ ፡ ዝርዝር ።

እገሌና ፡ እገሌ ፡ (የተከሳሹን ፡ ስም ፡ ሙላ) ፡ በ········ ቀን ፡ ············በ········· ········ዕቃው ፡ (የተቀበለውን ፡ ዕቃና ፡ ዝርዝሩን፡ ግለጽ) ፡ የተገኘው፡ ባንድ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ በተፈጸመ ፡ ወንጀል ፡ ምክንያት ፡ መሆኑን ፡ እያወቀ ፡ ወይም ፡ ለማወቅ ፡ የሚገባው ፡ ሆኖ ፡ የሸሸገ ፡ ( የተቀበለ ) ስለሆነ ፡ ተከሷል ።

የሚያዝዝበት ፡ ገንዘብ ፡ ሳይኖር ፡ ቼክ ፡ መስጠት ።

የክሱ ፡ ማመልከቻ ።

በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፮፻፶፯ ፡ የተመለከተውን ፡ ተላልፎ ፡ የሚያዝዝበት ፡ ገንዘብ ፡ ሳይኖር ፡ ቼክ ፡ በመስጠት ።

የወንጀሉ ፡ ዝርዝር ።

እገሌና፡ እገሌ፡ (የተከሳሹን ፡ ስም ፡ ሙሉ) ፡ በ.........ቀን ፡..........የሚያዝዝበት ፡ ገንዘብ ፡ አለመኖሩን ፡ እያወቀ ፡ ወይም ፡ ቼኩ ፡ በሚቀርብበት ፡ ጊዜ ፡ የሚያዝዝበት ፡ የሚበቃ፡ ገንዘብ፡ አለመኖሩን ፡ እያወቀ ፡ የኢ.ት/............ብር ፡ በተጻፈበት ፡ ቼክ ፡ ፈርሞ ፡ በመስጠቱ ፡ ተከሷል ።

---

በተጨማሪ ፡ የሚተኩ ፡ ክሶች ።

እምነት ፡ ስለ ፡ ማጉደል ።

የክሱ ፡ ማመልከቻ ።

በወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፮፻፴፭ ፡ የተመለከተውን ፡ ተላልፎ ፡ እምነትን ፡ በማጉደል ።

የወንጀሉ ፡ ዝርዝር ።

እገሌና ፡ እገሌ ፡ (የተከሳሹን ፡ ስም ፡ ሙሉ) ፡ በ............ቀን ፡ ......... በ....... ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ ብልጽግና ፡ ለራሱ ፡ ለማግኘት ፡ ዐቅዶ ፡ እገሌንና ፡ እገሌን ፡ (የባለቤቱን ፡ ስም ፡ ጥቀስ ፡) ለ.............አገልግሎት ፡ በአደራ ፡ እንዲቀመጥለት ፡ የሰጠውን ፡ የኢ.ት /...... ብር ፡ ለራሱ ፡ ጥቅም ፡ በማዋሉ ፡ ተከሷል ።

በተጨማሪ ፡ የሚተካ ፡
ስርቆት ።

የክሱ ፡ ማመልከቻ ።

በወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፮፻፴ ፡ የተመለከተውን ፡ ተላልፎ ፡ በመስረቅ ።

የወንጀሉ ፡ ዝርዝር ።

እገሌና ፡ እገሌ ፡ (የተከሳሹን ፡ ስም ፡ ሙሉ) በ.... ....ቀን ፡.... ....በ... .. .. የእገሌና፡ የእገሌን፡ (የባለቤቱን ፡ ስም ፡ ጥቀስ) ፡ የሆነውን ፡ ገንዘብ ፡ የኢ.ት/ ..... ብር ፡ የማይገባውን ፡ ብልጽግና ፡ ለማግኘት ፡ ሲል ፡ ዐቅዶ ፡ በመውሰዱ ፡ ተከሷል ።

## ተጨማሪ ፡ ክሶች ።

### አንደኛ ፡ ክስ ።

ስርቆት ።

**የክሱ ፡ ማመልከቻ ።**

በወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፮፻፴ ፡ የተመለከተውን ፡ ተላልፎ ፡ በመ ስረቅ ።

**የወንጀሉ ፡ ዝርዝር ።**

የእገሌና ፡ እገሌ ፡(የተከሳሹን ፡ ስም ፡ ሙላ ፡)በ . . . . . . . ቀን ፡. . . . . . . . በ. . . . . . .
የእገሌንና፡ የእገሌን፡(የባለቤቱን፡ ስም፡ ጥቀስ)፡ የሆነውን፡ መኪና፡ ሰሌዳ፡ቍጥር፡ አ. አ. ፩ሺ፩፻፲፩ ፡ የማይገባውን ፡ ብልጽግና፡ ለማግኘት ፡ ሲል ፡ ዐቅዶ ፡ በመውሰዱ ፡ ተከሷል ።

### ሁለተኛ ፡ ክስ ።

በቸልተኝነት ፡ ነፍስ ፡ በመግደል ።

**የክሱ ፡ ማመልከቻ ።**

በወንጀለኛ፡ መቅጫ፡ ሕግ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፳፮ ፡ የተመለከተውን ፡ ተላልፎ ፡ በቸ ልተኝነት ፡ ነፍስ ፡ በመግደል ።

**የወንጀሉ ፡ ዝርዝር ።**

እገሌና ፡ እገሌ ፡ (የተከሳሹን ፡ ስም ፡ ሙላ ፡) በ. . . . . . ቀን ፡. . . . . . . . . በ. . . . . . . . .
የሰሌዳ፡ ቍጥር፡ አ.አ.፩ሺ፩፻፲፩፡የሆነውን፡መኪና፡ ሲነዳ፡ እገሌ ፡ (የሟቹን፡ ስም፡ጥቀስ)፡ የተባለውን ፡ ሰው ፡ እመንገዱ ፡ ላይ ፡ አይቶት ፡ የመኪናዋን ፡ ፍጥነት ፡ ባለመቀነሱ ፡ የተነሣ ፡ በቸልተኝነት ፡ ድጠ ፡ ስለ፡ ገደለው ፡ ተከሷል ።

# ሦስተኛ ፡ ሠንጠረዥ ።

ፎርሞች ።      ፩ኛ ፡ ፎርም ። የዋስትና ፡ ወረቀት ።
(በቍጥር ፡ ፳፰ ፡ መሠረት ) ።

እኔ ፡................................የ........................................

በ...............ፖሊስ ፡ ጣቢያ ፡ በእስር ፡ ቀርቤ ፡ ስለ፡ቀረበብኝ ፡ የ.......

.........................................ክስ ፡ ቃሌን ፡ ለመስጠት ፡ ቀርቤ ፤

በ...................ፖሊስ፡ ጣቢያ*/በ......................................

ፍርድ ፡ ቤት* ፡ በ.........ሰዓት..........ቀን..........ለመገኘት፡ ግዴታ፡ ገብቻለሁ።
ፖሊሱ*/ፍርድ፡ቤቱ* ፡እስኪያሰናብተኝ፡ድረስ፡በየጊዜው፡ ሳላቋርጥ ፡ እንድቀርብ፡ ግዴታ፡
የገባሁ፡ በመሆኔና፡ ይህንኑ ፡ ግዴታ ፡ ሳልፈጽም ፡ ብገኝ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት፡
መንግሥት ፡ የኢት /...................ብር ፡ ገቢ ፡ ላደርግ ፡ ግዴታ ፡ ገብቻለሁ ።

ዛሬ ፡ ............. ቀን ፡ ............. ፲፱ ..........ዓ. ም.

ፊርማ ፡

* ተገቢ ፡ ያልሆነው ፡ ይሰረዝ ።

---

ፖሊሱ ፤ በተጨማሪ ፡ ዋስ ፡ መጥራት ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ባገኘው ፡ ጊዜ ፡ የሚሞላ ።
እኔ* / ወይም ፡ እኛ*/ ከዚህ፡ በላይ፡ በስም ፡ ለተጠቀሰው ፡ ..............................
የ.................በ..................ፖሊስ ፡ ጣቢያ* ፡ በ.......እንዲቀርብ /
.............ፍርድ ፡ ቤት* ፡ በ...............ሰዓት ፡ .......ቀን........ ፡ በተያዘ
በት ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ ቃሉን ፡ ለመስጠት ፡ እንዲቀርብ ፡ ዋስ* / ወይም ፡ ዋሶች*/
መሆኔን / ፡ መሆናችን ፡ ሳረጋግጥ ፡ / ስናረጋግጥ ፤ ፖሊሱ* / ፍርድ ፡ ቤቱ* ፡ እስኪ
ያሰናብተው ፡ ድረስ ፡ በየጊዜው ፡ ሳያቋርጥ ፡ እንዲቀርብ ፡ ለማድረግ ፡ ግዴታ ፡
የገባሁ/፡የገባን ፡ በመሆኔ/፡በመሆናችን ፡ ይህን ፡ ሳያደርግ ፡ ቢቀር ፡ ግን ፡ እኔ*/ ወይም ፡
እኛ* ፡ ለኢትዮጵያ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የኢት.................ብር ፡ ገቢ ፡
ለማድረግ፡ በአንድነት*፡ /ሳይከፋፈል* ፡ ግዴታ ፡ መግባቴን* ፡ (ወይም፡ መግባታችንን*)፡
አረጋግጣለሁ / ፡ እናረጋግጣለን ።-

ዛሬ ፡ .......... ቀን ፡ ....................፲፱.............ዓ. ም.

*ተገቢ ፡ ያልሆነው ፡ ይሰረዝ ።

፪ኛ ፡ ፎርም ። የብርበራ ፡ ትእዛዝ ።

( በቍጥር ፡ ፴፪ ፡ መሠረት ) ።

ለ····················ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ፖሊስ ፡ አዛዥና ፡

ለሌሎቹም ፡ ፖሊሶች ፡ ( ስም ፡ በመጥቀስ ) ፡

የግል ፡ ከሳሹ፡ እኔ ፡ ፊት ፡ ቀርበው፡ ስለ፡ ተሠራው፡ ወይም፡ (ተሠርቷል ፡ ስለ ፡ ተባለው) ፡ . . . ወንጀል ፡ ያመለከቱኝ፡ በመሆናቸውና፡ ከዚህ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ በተገለጠው፡ ሠንጠረዥ ፡ ውስጥ ፡ የተጠቀሱት ፡ ዕቃዎች ፡ በምርመራ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፤ (ወይም፡ ለሚጀመረው ፡ ምርመራ ፡ ) አስፈላጊ ፡ በመሆናቸው ፡ የተባለው ፡ ወንጀል ፡ ወይም ፡ ተሠራ ፡ የተባለው ፡ ወንጀል ፡ እንዲጣራ ፡ ለማድረግ ፤

ከዚህ ፡ በታች ፡ በተገለጸው ፡ ሠንጠረዥ ፡ ውስጥ ፡ በዝርዝር ፡ የተመለከቱትን ፡ ዕቃዎች ፡ በ··················ቀኖች ፡ ውስጥ ፡ እንዲፈትሹና ፡ . . . (በቤቱ፡ ወይም ፡ በስፍራው ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ቦታ ፡ በከፊል ፡ ብርበራው ፡ የሚደረግ በትን ፡ መግለጽ ) ፡ ያገኙዋቸውን ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ወዲያውኑ ፡ እንዲያቀርቡ ፤ በዚሁ፡ ማዘዣ ፡ መሠረት ፡ የፈጸሙትን ፡ ተግባር ፡ የብርበራው ፡ ሥራው ፡ እንዳለቀለት ፡ በማዘዣው ፡ ጀርባ ፡ ላይ ፡ ገልጸው ፡ እንዲጽፉልን ፡ ታዝዘዋል ።

እኔው ፡ ፊርሜበት ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ ዐውቆት ፤

ዛሬ ፡ ···············ቀን ፡ ··············፲፱ ···············ዓ. ም. ተጻፈ ።

ዳኛ ።

<u>ሠንጠረዥ</u> ።

( የሚያዙት ፡ ዕቃዎች ፡ ዐይነት ፡ ትክክለኛ ፡ መግለጫ ) ።

፫ኛ ፡ ፎርም ። የፖሊስ ፡ ምርመራ ፡ ራፖር ።

(በቍጥር ፡ ፴፯ ፡ መሠረት ) ።

ለዐቃቤ ፡ ሕጉ ።

፩ በ............ሰዓት ፡ ...............ቀን ፡ ፲፱...........ዓ.ም ፡ ከ.........
የተላለፈው ፡ በ................ አማካኝነት ፡ የደረሰኝ ፡ መግለጫ ፡ የ.........
............ወንጀል ፡ በ...........ፈጽመዋል ፡ ተብለው፡ ............ሰዎች ፡ የተጠረጠሩ ፡ ወይም ፡ ወንጀሉ ፡ የሚመለከታቸው ፡ ሲሆኑ ፤ በራፖሩም ፡ ውስጥ ፡ ተወስድዋል ፡ ተብሎ ፡ የተገለጸው ፡ ንብረት ፡ ግምት ፡ የኢ.ት /...........ብር ፡ ይሆናል ።

፪ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ በዕለት ፡ ምርመራው ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ በዝርዝር ፡ እንደ፡ ተገለጸው ፡ የሚገባውን ፡ ተግባር ፡ ፈጽሜያለሁ ።

፫ የሚከተሉትን ፡ ፍሬ ፡ ነገሮች ፡ አረጋግጫለሁ ።

..............................................................

፬ ከዚህ ፡ የሚከተሉትን ፡ ምስክሮች፡ ከመረመርኩ፡ በኋላ፡ የሰጡት ፡ ቃል ፡ ከዚሁ ፡ ራፖር ፡ ጋራ ፡ ተያይዟል ።

..............................................................

፭ ምስክሮች ፡ ከሰጡት ፡ ቃል ፡ በላይ፡ በተጨማሪ ፡ ከዚህ፡ የሚከተሉት ፡ ሰነዶች፡ ከዚሁ ፡ ራፖርት ፡ ጋራ ፡ አባሪ ፡ ሆነዋል ።

የዕለት ፡ የምርመራ ፡ መዝገብ ፡ ቍጥር፡ ............ ።

..............................................................

፮ በእኔ ፡ አስተያየት ፡ ስለ፡.................. የተፈጸመው ፡ ወንጀል ፡ የተገለጸ፡ መሆኑንና፡ የሚከተሉት ፡ ሰዎች ፡ ወንጀሉ፡ የሚመለከታቸው፡ መሆናቸው ፡ ተገልጿል ።

፯ ተከሳሾች ፡ ሆነው ፡ ካልተያዙት ፡ ሰዎች ፡ በስተቀር ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በስም ፡ የተገለጹት ፡ ሰዎች ፡ በነገሩ ፡ አግባብ ፡ ያላቸውና ፡ አስረጅነታቸው ፡ ነገሩን ፡ ለማብራራት፡ የሚችሉ ፡ (የሚጠቅሙ) መሆናቸውን ፡ በበኩሌ ፡ በሚገባ ፡ የተረዳሁ ፡ ቢሆንም፡ ከዚህ ፡ በሚከተለው ፡ ምክንያት ፡ የተነሣ ፡ ልመረምራቸው ፡ አልቻልኩም ።

፰ ከዚህ ፡ በታች ፡ የተጻፉት ፡ ዕቃዎች ፡ በጥንቃቄ ፡ የተቀመጡ ፡ ወይም ፡ የተገኙ ፡ ስለ፡ ሆነ ፡ መረጃዎች ፡ (ኤግዚቢቶች ) ፡ ሆነው ፡ የሚቀርቡ ፡ ናቸው ።

..............................................................

ፊርማ ፡

፬ኛ ፡ ፎርም ። የፖሊስ ፡ የምርመራ፡

መዝገብ ፡ እንዲዘጋ ፡ ስለ፡ ማድረግ።

( በቊጥር ፡ ፴፱ ፡ መሠረት ) ።

ለ... ...... ....ፖሊስ ፡ ጣቢያ ፡ የምርመራ ፡ ክፍል ፡ ሹም ።

የተከሳሹ ፡ ስም.. ...... .......... ....

የፖሊስ ፡ የዕለት ፡ ምርመራ ፡ መዝገብ ፡ ቊጥር ፡. ...... ....

ከዚህ ፡ በሚከተሉት ፡ ምክንያቶች ፡ ይህ ፡ የፖሊስ ፡ ምርመራ ፡ መዝገብ ፡ እን ዲዘጋ ፡ የታዘዙ፡ መሆንዎን ፡ አስታውቃለሁ ።

* (ሀ) ተከሳሹ ፡ ስለ፡ ሞተ ።
* (ለ) የተከሳሹ ፡ ዕድሜ ፡ ከ፱ ፡ ዓመት ፡ በታች ፡ በመሆኑ ።
* (ሐ) በኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ተከሳሹ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ክስ ፡ ሊቀርብበት ፡ ስለማይችል ።

ፊርማ ፡
ዐቃቤ ፡ ሕጉ ።

* ተገቢ ፡ ያልሆነው ፡ ይሰረዝ ።

ግልባጭ ፤ ፩ኛ/ ፡ ለጠቅላይ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ።

፪ኛ/ ፡ ለግል ፡ ከሳሹ ።

፳፫ ፡ ፎርም ። ክስ ፡ አይቀርብም ፡

የማለት ፡ ውሳኔ ፡ የሚጻፍበት ፡ ፎርም ።

( በቍጥር ፡ ፵፪ ፡ መሠረት ) ።

እኔ ፡ እገሌ ፤ (የዐቃቤ ፡ ሕጉን ፡ ስም ፡ ጥቀስ ) ፡ በ ···· (ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ሕግ ፡ እንዲያስከብር ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠውን ፡ ስፍራ ፡ ሙላ ) ፡ በእገሌ ፡ ( የከሳሹን ፡ ስም ፡ ጥቀስ) ፡ ላይ ፡ ከዚሁ ፡ በሚከተሉት ፡ ምክንያቶች ፡ የተነሣ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ አልችልም ።

* (ሀ) ተከሳሹን ፡ ለማስቀጣት ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ማስረጃ ፡ የሌለ ፡ መሆኑን ፡ ተረድቻለሁ ። (አጥጋቢ ፡ ማስረጃ ፡ ያልቀረበበትን ፡ ምክንያት ፡ አብራርቶ ፡ በግልጽ ፡ ማስረዳት ፡ ነው ) ።

* (ለ) ተከሳሹን ፡ ለማግኘት ፡ የማይቻልና ፡ ተከሳሹም ፡ በሌለበት ፡ ክሱ ፡ ሊሰማ ፡ የማይችል ፡ በመሆኑ ፡ (ተከሳሹን ፡ ለማግኘት ፡ የማይቻልበትን ፡ ምክንያት ፡ መግለጽና ፡ እርሱ ፡ በሌለበት ፡ ነገሩ ፡ እንዳይሰማ ፡ የሚከለክለውን ፡ የወንጀል ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ጥቀስ) ።

* (ሐ) ክሱን ፡ ለማቅረብ ፡ በይርጋ ፡ የታገደ ፡ ወይም ፡ ለተፈጸመው ፡ ወንጀል ፡ ምሕረት ፡ ወይም ፡ የዐዋጅ ፡ ምሕረት ፡ (ይቅርታ ) ፡ በመደረጉ ። ( ወንጀሉ ፡ የተፈጸመበትን ፡ ቀንና ፡ ዓመት ፡ ምሕረት ፡ ወንጀሉ ፡ በይርጋ ፡ የታገደ ፡ ለመሆኑ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ መጥቀስ ፡ ወይም ፡ ተከሳሹን ፡ በምሕረት ፡ ወይም ፡ በዐዋጅ ፡ ምሕረት ፡ የሚያድነውን ፡ መጥቀስ ) ።

* (መ) ሚኒስትሩ ፡ ፈረሙበት ፡ ማዘዣ ፡ ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ ሲሉ ፡ ክስ ፡ እንዳይቀርብ ፡ በወንጀል ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፵፪ ፡ መሠረት ፡ ያዘዙኝ ፡ በመሆኑ ፡ (የፍርድ ፡ ሚኒስትሩ ፡ በፊርማቸው ፡ ያዘዙበትን ፡ ደብዳቤ ፡ ቍጥርና ፡ ቀን ፡ መጥቀስ ) ።

ፊ ር ማ ፡

ዐቃቤ ፡ ሕጉ ።

* ተገቢ ፡ ያልሆነው ፡ ይሰረዝ ።

ግልባጭ ፡ ፩ኛ/ ፡ ለጠቅላይ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ።

፪ኛ/ ፡ ለፖሊስ ፡ ምርመራ ፡ ክፍል ፡ ሹም ።

፫ኛ/ ፡ በወንጀል ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፵፯ ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ በግል ፡ ከሳሽነት ፡ ለቀረበው ፡ ሰው ።

፯ኛ ፡ ፎርም ። የመያዝ ፡ ትእዛዝ ።

( በቍጥር ፡ ፷፯ ፡ መሠረት ).።

ለ............ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ፖሊስ ፡ አዛዥ ፡
እና ፡ ለሌሎቹም ፡ ፖሊሶች ፡ ሁሉ ።

ስሙ ፡ ......................የተባለውና ፡ መኖሪያው ፡.........................
የሆነው ፡ ሰው ፡ በ..............ወንጀል፡ ስለ፡ተከሰሰ፡ ይህነኑ ፡ ሰው ፡ ይዘው ፡......
......................በዚሁ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በእስር ፡ እንዲያቀርቡ ፡ ታዝዘዋል ።

ዛሬ ፡..........ቀን ፡ ..............፲፱.............ዓ. ም.

ዳኛው ።

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መስሎ ፡ ከታየው ፡ ይህ ፡ የመያዝ ፡ ትእዛዝ ፡ በሚከተለው ፡ ዐይነት ፡ ለመጻፍ ፡ ይችላል ።

ስሙ ፡ ......... የተባለው ፡ ተከሳሽ ፡ ለኢ.ት/ ........ ብር ፡ የዋስትና ፡ ወረቀት ፡ የሚፈርም ፡ ከሆነና ፡ ለኢ.ት/......ብር፡ አንድ፡ ዋስ፡ በማቅረብ ፡ በ............ ......ቀን፡ ......እፍርድ፡ቤቱ፡ድረስ፡የሚቀርብ፡መሆኑንና፡ፍርድ፡ቤቱ፡ እስታሰናበተው፡ ድረስ ፡ በየጊዜው ፡ ሳያቋርጥ ፡ የሚቀርብ ፡ መሆኑን ፡ ካረጋገጠ ፡ ሊለቀቅ ፡ ይችላል ።

ዛሬ ፡ ........................ቀን ፡ .............፲፱..................ዓ. ም.

ዳኛው ።

፯ኛ ፡ ፎርም ። የዋስትና ፡ ወረቀት ።

(በቍጥር ፡ ፸፩ ፡ መሠረት) ።

እኔ ፡ ……………የ…………በ………ፍርድ ፡ ቤት ፡ በ………………… በተከሰስኩበት ፡ ነገር ፡ ቃሌን ፡ እንድሰጥ ፡ በአስራት ፡ ቀርቤ ፡ በነበረው ፡ መሠረት ፡ አሁንም ፡ በ………ፍርድ ፡ ቤት ፡ በ…………………ቀን ፡ ……በየጊዜው ፡ ሳላቋርጥ ፡ እየቀረብኩ ፡ ለዚሁ ፡ ለቀረበብኝ ፡ ክስ ፡ የሚገባውን ፡ መልስ ፡ ለመስጠትና ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እስኪያሰናብተኝ ፡ ድረስ ፡ ለመገኘት ፡ ግዴታ ፡ የገባሁ ፡ ስሆን ፤ ይህነኑ ፡ ግዴታ ፡ ተላልፌ፡ ብገኝ፡ ግን፡የኢ.ት/…………ብር፡ የሆነውን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ገቢ ፡ ለማድረግ ፡ ግዴታ ፡ ገብቻለሁ ።

ዛሬ ፡ …………………ቀን፡ …………………፲፱…………ዓ. ም.

ፊርማ ፡

---

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ዋስ ፡ መጥራት ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ሲያገኝ ፡ የሚሞላ ።

እኔ* ፡ (ወይም ፡ እኛ* ፡ ) ከላይ ፡ ስሙ፡ ለተጠቀሰው ፡ ………የተባለው ፡ ሰው፡ የ………………ነዋሪ ፡ ………ፍርድ ፡ ቤት ፡ በ…………………

ቀን ፡ ……………………… ተገኝቶ ፡ ለታሰረበት ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ መልስ ፡ እንዲሰጥ ፤ እንዲሁም ፡ በየጊዜው ፡ ሳያቋርጥ ፡ እንዲቀርብና ፡ ፍርድ፡ ቤቱ ፡ እስኪያሰናብተው ፡ ድረስ ፡ እንዲገኝ፤ እንዲሁም ፡ ይህነኑ ፡ ግዴታ ፡ ተላልፎ፡ ሳይቀርብ፡ ቢቀር፡ እኔ*/ወይም፡ እኛ*፡ ሳይከፋፈልና*፡ በአንድነት*፡ ኀላፊ*/ኀላፊዎች*፡በመሆን፡ለኢትዮጵያ፡ንጉሠ፡ነገሥት፡መንግሥት፡የኢ.ት/………ብር፡ ገቢ፡ ለማድረግ ፡ እኔ*/ወይም፡ እኛ*/ራሴን*/ራሳችንን*/ዋስ*/ ዋሶች* ፡ አድርጌያለሁ/፡ አድርገናል ።

ዛሬ ፡ …………ቀን ፡ ………፲፱…………ዓ. ም.

ፊርማ ፡ (ፊርማዎች) ፡

* ተገቢ ፡ ያልሆነው ፡ ይሰረዝ ።

፳ኛ ፡ ፎርም ። የምስክር ፡ የዋስትና፡ ወረቀት ።

(በቍጥር ፡ ፺ ፡ መሠረት) ።

እኔ ፡ ..................የ..................በ.......................ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተገኝቼ ፡ በ..................ዕለት ፡ በመጥሪያው ፡ መሠረት ፡ ቀርቤ ፡ በእገሌና ፡ በእገሌ ፡ ላይ ፡ ስለ፡ ቀረበው ፡ የ....................ክስ ፡ በምስክርነት ፡ ቃሌን ፡ ለመስጠት ፡ ግዴታ ፡ ገብቻለሁ ።

ይህንኑ ፡ ግዴታ ፡ ሳልፈጽም ፡ ብቀር ፡ ግን ፡ የኢ.ት/ ..............ብር ፡ ለኢ. ትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ገቢ ፡ እንዲሆን ፡ ግዴታ ፡ ገብቻለሁ ።

ዛሬ ፡ .....................ቀን ፡ ..................፲፱..................ዓ. ም.

ፊርማ ፡

፱ኛ ፡ ፎርም ። ችሎት ፡ እንዲቀርብ ፡

የሚሰጥ ፡ መጥሪያ ።

(በቍጥር ፡ ፩፻፳፫ ፡ መሠረት) ።

ለ ፡ ........................ዐቃቤ ፡ ሕ

ለተከሳሹ ፡ ........................የ..................
(ስሙን ፡ ጥቀስ) (አድራሻውን ፡ ጥቀስ)

ተከሳሹ ፡ ..........(የተከሳሹን ፡ ስም፡ ጥቀስ) ። በ..................
.............. በተከሰሰበት ፡ ወንጀል ፡ ነገሩ ፡ እንዲሰማ ፡ የተወሰነው ፡
በ..............ቀን፡................በ................ፍርድ ፡
ቤት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እዚሁ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በ..........ሰዓት ፡ እላይ ፡ በተጠቀ
ሰው ፡ ቀን ፡ እንዲቀርቡ ፡ ታዝዘዋል ።

(ተከሳሹ ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ ያለ ፡ ሲሆን ፡ የሚከተለውን ፡ ጥቀስ) -
*እንዲሁም፡ የ.........(የወህኒ፡ ቤቱን፡ ስም፡ ጥቀስ) ፡ የወህኒ ፡ ቤት ፡ አዛዥ ፡
የሆኑት ፡ ከላይ ፡ በስም ፡ የተጠቀሰውን ፡ ተከሳሽ ፡ ከላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ስፍራ ፡
ቀንና ፡ ሰዓት ፡ እንዲያቀርቡ ፡ ታዝዘዋል ።

የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ (ሬጂስትራር) ።

* ተከሳሹ ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ የተያዘ ፡ ካልሆነ ፡ ይሰረዝ ።

፲ኛ ፡ ፎርም ። የምስክር ፡ መጥሪያ ።

(በቍጥር ፡ ፩፱፻፷፩ ፡ መሠረት) ።

የወንጀል፡ ነገር ፡ ቍጥር ፡...............

በዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ — በተከሳሽ ፡ ...............................:

(የተከሳሹን ፡ ስም ፡ ጥቀስ) ፡

ለ.....................................................

ከዚህ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ነገር ፡.............ቀን ፡ ፲፱.......ዓ. ም.
በ..............ሰዓት ፡ ወደዚሁ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርበው ፡ ስለ ፡ ....
ከሳሹ* / ተከሳሹ* ፡ እንዲመሰክሩ ፡ ታዝዘዋል ።
ሳይመጡ ፡ የቀሩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የስራት ፡ ቅጣት ፡ ያገኝዎታል ።

ዛሬ..............ቀን ፡............፲፱..............ዓ. ም.

የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ (ሬጂስትራር) ።

* ተገቢ ፡ ያልሆነው ፡ ይሰረዝ ።

፲፩ኛ ፡ ፎርም ።  ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ራሱ ፡

የሚሰጠው ፡ የመያዝ ፡ ትእዛዝ ።

(በቍጥር ፡ ፩፻፷፭ ፡ መሠረት) ።

*ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ .......... የተባለው ፡ ተከሳሽ ፡ መጥሪያ ፡ ደርሶትና ፡ ተቀብሎ ፡ በተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ ባለመቅረቡ ፤

* ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ ............................................................ የተባለው ፡ ምስክር፡ መጥሪያ ፡ ደርሶትና ፡ ተቀብሎ ፡ በተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ ባለመቅረቡ ፤ ............................................................

(የፖሊስ ፡ መኰንኑን ፡ ስም ፡ ጥቀስ) ፡

የተባሉት ፡ በስም ፡ የተጠቀሰውን ፡ ይዘው ፡ ያለመዘግየት ፡ እዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ድረስ ፡ እንዲያቀርቡ ፡ ታዝዘዋል ።

ዳኛ ።

* ተገቢ ፡ ያልሆነው ፡ ይሰረዝ ።

፲፪ኛ ፡ ፎርም ። ይግባኙ ፡ የሚሰማበትን ፡ ቀን፡
ማስታወቂያ ።

(በቍጥር ፡ ፩፻፺፪ ፡ መሠረት ) ።

የወንጀል ፡ ነገር ፡ ቍጥር ፡ ................

.................................................................ይግባኝ ፡ ባይ ።

(ስም ፡ ጥቀስ) ፡

.................................................................መልስ ፡ ሰጭ ።

(ስም ፡ ጥቀስ) ፡

ከላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ የይግባኝ ፡ ነገር ፡ በ..................... ፍርድ፡ ቤት ፡ በ.................ቀን ፡ ............... ፲፱......... ............ ዓ. ም. በ........... ሰዓት፡ ሊሰማ፡ ስለ፡ ተቀጠረ ፡ ................. (ስም ፡ ጥቀስ)፡ ይግባኝ ፡ ባይ */ መልስ ፡ ሰጭ* ፡ እንዲቀርቡ ፡ ታዝዞዋል ።

* ይግባኝ፡ ባዩ ፡ ወይም ፡ ጠበቃው ፡ ያልቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይግባኙ ፡ ይሰረዛል።

* መልስ ፡ ሰጪው ፡ ወይም ፡ ጠበቃው ፡ ያልቀረቡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የይግባኙ ፡ መሰማት ፡ ወዲያውኑ ፡ ለመቀጠል ፡ ይቻላል ።

የይግባኙ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የመዝገብ ፡ ሹም ፡ (ሬጂስትራር) ።

* ተገቢ ፡ ያልሆነው ፡ ይሰረዝ ።

፲፫ኛ ፡ ፎርም ። የሞት ፡ ፍርድ፡ ስለተፈረደበት፡

ሰው ፡ የሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ።

(በአንቀጽ ፡ ፪፻፩ ፡ መሠረት) ።

ለ.....................የ.........................ወህኒ፡ ቤት ፡ ሹም ።

..................................................................................

(የተከሳሹን ፡ ስም ፡ ጥቀስ) ።

የተባለው ፡ ተከሳሽ ፡ በተከሰሰበት ፡ የ..........................ወንጀል ፡ (ጥፋተኛ፡ ሆኖ፡ የተፈረደበትን፡ ወንጀል ፡ ግለጽ ) ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ስለ፡ተፈረደበት ፤ ይህንኑ፡ ......................................ተፈረደበትን ፡ ሰው ፡ ስም ፡ ጥቀስ) ፡ በወህኒ ፡ ቤት ፡ ተቀብለው ፡ የግርማዊ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ትእዛዝ ፡ እስኪደርስዎ ፡ ድረስ ፡ ታስሮ ፡ እንዲቆይ ፡ እንዲያደርጉ ፡ ታዝዘዋል ።

ዛሬ ፡...................ቀን ፡....................፲፱.....................ዓ. ም.

ሰብሳቢው ፡ ዳኛ ።

፲፬ኛ ፡ ፎርም ። በፖሊስ ፡ ተይዞ ፡ እንዲቈይ * / በአነስተኛ ፡ እስራት */ በከባድ ፡ እስራት * / በአንድ ፡ ቦታ ፡ እንዲወሰን * / ስለሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ።

(በቍጥር ፡ ፪፻፭ ፡ መሠረት) ።

የወንጀል ፡ ነገር ፡ ቍጥር ፡ ................................

የእስረኛው ፡ ስም ፡ ................................

ለ.............. ለወህኒ፡ ቤቶች ፡ ሹም*/ ለ.............. ፖሊስ፡ አዛዥ * ።
..........................................................................

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ስሙ ፡ የተጻፈው ፡ እስረኛ ፡ በዚህ ፡ ............. ፍርድ ፡ ቤት ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ .............................. ተፈርዶበታል ።

የተፈረደበትን ፡ በፖሊስ ፡ ተይዞ ፡ የመቈየት * / አነስተኛ ፡ የእስራት * / ከባድ ፡ የእስራት * / በአንድ ፡ ቦታ ፡ የመወሰን * / ፍርድ ፤ እንደ ፡ ሕጉ ፡ እንዲፈጸም ፡ እንዲ ያደርጉ ፡ ታዝዘዋል ።

ዛሬ ፡ .................. ቀን ፡ ................. ፲፱............ዓ. ም.

ሰብሳቢው ፡ ዳኛ ።

* ተገቢ ፡ ያልሆነው ፡ ይሰረዝ ።

፲፭ኛው ፡ ፎርም ፡ ስለ ፡ ግርፋት ፡ አፈጻጸም ፡ የሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ፤
በቍጥር ፡ ፪፻፺ ፡ መሠረት ፡

የወንጀል ፡ ነገር ፡ ቍጥር ፡ .......... የእሥረኛው ፡ ስም ፡ .......... ............ ለ .......... ለወህኒ ፡ ቤቶች ፡ ሹም ፡ ለ ............ ፖሊስ ፡ አዛዥ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ስሙ ፡ የተጻፈው ፡ እሥረኛ ፡ .......... ፍርድ ፡ ቤት ጥፋተኛ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ......... ስለ ፡ ተፈረደበት ፡ ........... የግርፋቱ ፡ ልክ ፡ ይጻፋል ፡ ........... የመገረፊያው ፡ ዓይነት ፡ ይጻፋል ፤ ግርፋቱን ፡ የሚፈጽመው ፡ ሰው ፡ ይጻፋል ፤ .......... ግርፋቱ ፡ መቼ ፡ እንደሚፈጸም ፡ ይጻፋል ፡ ...........እንደሕጉ ፡ እንዲፈጸም ፡ እንዲያደርጉ ፡ ታዘዋል ።

ዛሬ ________ ቀን ፡ ፲፱ ______ ዓ. ም.

ሰብሳቢው ፡ ዳኛ ፤

---

፲፯ኛ ፡ ፎርም ። ለወንጀሉ ፡ አላፊ ፡ ስላል
ሆኑ ፡ ሰዎች ፡ የሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ።
(በቍጥር ፡ ፪፻፳ ፡ መሠረት) ።

............................................................ .....
(እንዲታሰር ፡ የተደረገውን ፡ ሰው ፡ ስም ፡ ጥቀስ ) ፡
በፈጸማቸው ፡ ተግባሮች ፡ ሁሉ ፡ ሙሉ ፡ ኀላፊነት ፡ ሊጣልበት ፡ ባለመቻሉ ፡
እርስዎ ፡ የ .................................................
(ተወስኖ ፡ የሚጠበቅበትን ፡ ድርጅት ፡ ስም ፡ ጥቀስ) ፡
ሹም፡ይህነኑ፡የተፈረደበትን፡ ሰው፡ በጥበቃው፡ ቦታ፡ ተቀብለው፡ የሚያስፈልገውን፡ ..............................ሕክምና፡እንዲያገኝ፡እንዲያደርጉ፡ታዝዘዋል።
(የሕክምናውን ፡ ዐይነት ፡ ግለጽ) ፡

ሰብሳቢው ፡ ዳኛ ።